# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ ረቂቅ

# <u>የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀልሥነ ሥርዐት ሕግ</u>

የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግን ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፣ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው አቀፍዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ስምምነቶችና መርሆች ጋር በማጣጣም የሰዎችን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በወንጀል ፍትሕ ሥርዐቱ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የሕግ ሥርዐት መቅረጽ በማስፈለጉ፤

በ1954 ዓ.ም የወጣው ሥነ ሥርዐት የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ የወንጀል ፍትሕ ሥርዐቱን በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ፣ ፍትሐዊ፣ ተደራሽና ቀልጣፋ ለማድረግ፣ በየጊዜው የሚከሰቱ ውስብስብ ወንጀሎችን በበቂ ሁኔታ ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማምከን የሚያስችል ባለመሆኑ እና ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል ጠንካራ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግን ጨምሮ በወንጀል የፍትሕ ሥርዐቱ የተደረጉ ለውጦችን ለማስፈጸም የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕጉን የተሟላ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በተለያዩ ጊዜያት የወጡ የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕጎችን በማጠቃለል የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ማደራጀት በማስፈለጉ፤

ሀገሪቱ በወንጀል የፍትሕ ሥርዐት ከዓለም አቀፍ ሕግጋት እና የአሠራር ሥርዐት አንፃር ያሏትን መብቶች ለማስከበርና የተጣሉባትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል ዘመናዊ የሕግ ማዕቀፍ መቅረጽ በማስፈለጉ፤

በአጠቃላይ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዐትን ለመገንባት እና ለማስፈን የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕጉን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) እና አንቀጽ 55(5) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ አዋጅ ቁጥር ________/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>**የተሻሩ ሕጎች**</u>

   1. የ1954 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት አዋጅ ቁጥር <u>፭/፲፱፻፶፬</u> ከጸናበትበዚህ ሕግ ተሽሯል፡፡

2. ከዚህ ሕግ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ ሕግ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የለውም፡፡

3. <u>የልዩ ሕጎች ተፈጻሚነት</u>

ለተለዩ ወንጀሎች የወጡ ልዩ የሥነ ሥርዐትና የማስረጃ ሕጎች በተለየ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

4. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያሉ የወንጀል ጉዳዮች በነበሩ የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ ውሳኔ ያገኛሉ፡፡
2. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት የተፈጸመ ወይም ፍርድ ቤት ያልቀረበ የወንጀል ጉዳይ የተከሳሽን መብት የማያጣብብ እስካልሆነ ድረስ በዚህ ሕግ መሠረት ውሳኔ ያገኛል፡፡
3. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በነባሩ ሕግ መሠረት የተሰጡ ውሳኔዎች ወይም ትእዛዞች የጸኑ ናቸው፡፡

5. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ከዘጠና ቀናት በኋላ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ________ ቀን 2ሺ5 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

## **የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ**
## **አንደኛ መጽሐፍ**
## **የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች እና መርሆዎች**
## **ምዕራፍ አንድ**
## **ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

### **አንቀጽ 1 የሕጉ ተፈጻሚነት ወሰን**

ግልጽ የሆነ ሌላ ልዩ ሕግ ወይም ስምምነት ከሌለ በስተቀር ይህ ሕግ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### **አንቀጽ 2 ትርጓሜ**

በዚህ ሕግ፡-

(1) **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ዕውቅና የተሰጠው ክልል ነው፡፡

(2) **"መርማሪ"** ማለት በሕግ መሠረት የወንጀል ምርመራ ለማድረግ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ወይም አካል ነው፡፡

(3) **"ፖሊስ"** ማለት የፌዴራል ወይም የክልል ፖሊስ ማለት ነው፡፡

(4) **"የዐቃቤ ሕግ ተቋም"** ማለት በሕግ የዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው ሆኖ የፌዴራል ወይም የክልል ተቋምን ያጠቃልላል፡፡

(5) **"ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ"** ማለት የዐቃቤ ሕግ ተቋም ኃላፊ ነው፡፡

(6) **"ዐቃቤ ሕግ"** ማለት በሕግ የዐቃቤ ሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሲሆን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉን እና ምክትሉን ያጠቃልላል፡፡

(7) **"ፍርድ ቤት"** ማለት በሕግ የተቋቋመ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ሆኖ፣ ወታደራዊ ፍርድ ቤትን እና ሌላ የወንጀል ጉዳይ ለመዳኘት በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን ፍርድ ቤት ያጠቃልላል፡፡

(8) **"ጠቅላይ ፍርድ ቤት"** ማለት በዚህ ሕግ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር የፌዴራል ወይም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማለት ነው፡፡

(9) **"ፕሬዘዳንት"** ማለት በማንኛውም ደረጃ ያለ ፍርድ ቤት ኃላፊ ነው፡፡

(10) **"ሬጂስትራር"** ማለት በዚህ ሕግ አንቀጽ ---- ሥር የተመለከቱት እና በሌላ ሕግ የተለዩ ተግባራትን የሚያከናውን የፍርድ ቤት ባለሙያ ነው፡፡

(11) **“ማቆያ ቤት”** ማለት በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የወንጀል ምርመራው እስከሚጠናቀቅ የሚቆይበት በፖሊስ ተቋም ያለ ክፍል ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ያቋቋመው የታወቀ ቦታ ነው፤

(12) **“ማረፊያ ቤት”** ማለት የወንጀል ምርመራ ተጠናቆ ክስ እስኪመሠረት ወይም ክስ ተመሥርቶ ውሳኔ እስከሚሰጥ በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚቆይበት በማረሚያ ቤት የሚገኝ ክፍል ነው፤

(13) **“ማረሚያ ቤት”** ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ ፍርደኛ የተወሰነበትን የእሥራት ቅጣት የሚፈጽምበትና የሚታረምበት በሕግ የተቋቋመ ተቋም ነው፡፡

(14) **“ተጎጂ”** ማለት በወንጀል ድርጊት ጉዳት የደረሰበት ሰው ነው ፡፡

(15) **“ጉዳት”** ማለት የደረሰና ይደርሳል ተብሎ የተረጋገጠ የአካል፣ የገንዘብ፣ የንብረት ወይመ የሞራል ጉዳትን ያጠቃልላል፡፡

(16) **“ከባድ ወንጀል”** ማለት ለዚህ ሕግ አፈጻጸም ሲባል በዚህ ሕግ አንደኛ ሠንጠረዥ **“ሀ”** ላይ የተጠቀሰ ወንጀል ነው፤

(17) **“መካከለኛ ወንጀል”** ማለት ለዚህ ሕግ አፈጻጸም ሲባል በዚህ ሕግ አንደኛ ሠንጠረዥ “**ለ**” ላይ የተጠቀሰ ወንጀል ነው፤

(18) **“ቀላል ወንጀል”** ማለት ለዚህ ሕግ አፈጻጸም ሲባል በዚህ ሕግ አንደኛ ሠንጠረዥ “**ሐ**” ላይ የተጠቀሰ ወንጀል ነው፤**“ኤግዚቢት” ማ**ለት አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ማንኛውም ነገር **ሆኖ ድምፅ**ን፣ ምስልን፣ ዳታን የያዘ ዕቃን ወይም የወንጀል ምልክት ሆኖ አሻራን፣ የጫማ ኮቴን እና ሌሎች መሰል ነገሮችን ይጨምራል፡፡**“ማስረጃ”** ማለት አግባብነት ያለውን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል የሚያስችል ማንኛውም ነገር ወይም ሒደት ሆኖ በምስክር ወይም በተከሳሽ የሚሰጥ ቃልን፣ ሰነድን፣ የኤሌክትሮኒክ መረጃን፣ በሕግ የተወሰደ የሕሊና ግምትን፣ ፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወስድበትን ፍሬ ነገር፣ የአንድ ነገርን ሒደት ማሳያ እንዲሁም ፍርድ ቤት በዐይነት የሚመለከተውን ነገር ያጠቃልላል፡፡

(19) **“አግባብነት ያለው ማስረጃ”** ማለት የአንድን ድርጊት ውጤት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለመወሰን የሚያስችል፣ ሊረጋገጥ የተፈለገ ፍሬ ነገርን የሚያሳይ ወይም አጠራጣሪ የሚያደርግ ማንኛውም ማስረጃ ሲሆን፣ በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገርን የሚገልጽ ወይም የሚያረጋግጥ ወይም ፍሬ ነገሩ ያመለከተውን ሁኔታ የሚያፈርስ ወይም የሚደግፍ፣ የተደረገበትን ቦታ ወይም ጊዜ ወይም የፈፀሙ ወገኖች ግንኙነትን የሚያሳይ ወይም የሚያረጋግጥ ማስረጃን ይጨምራል፡፡

(20) **"ትእዛዝ"** ማለት ከውሳኔ የተለየ ሆኖ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ማናቸውም ዐይነት ተፈጻሚ ትእዛዝ ነው፡፡

(21) **"ፍርድ"** የውሳኔ ወይም ትእዛዝ መሠረት ሆኖ ነጻ መሆን ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔን የያዘ ነው፡፡

(22) **"ውሳኔ"** ማለት የቀረበን ክስ፣ መልስ፣ እና ማስረጃን በመመርመር ስለተከራካሪ ወገኖች መብትና ግዴታ በሚመለከት  የሚሰጥ ተፈጻሚ የሚሆነው የፍርድ አካል ነው፡፡

(23) **"የመጨረሻ ውሳኔ"** ማለት በሕግ የመጨረሻ የተባለ ወይም ይግባኝ የማይባልበት ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ነው፤

(24) **"ሕግ"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ሆኖ ሕግ ለማውጣት ሥልጣን ባለው አካል ወይም ሕግ ለማውጣት በተወከለ አካል የወጣ ሕግ ነው፡፡

(25) **"ወጣት"** ማለት ክስ በቀረበበት ጊዜ ዕድሜው ከዘጠኝ እስከ አሥራ አምስት ዓመት የሆነ ማለት ነው፡፡

(26) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ማንኛውም ሰው ነው፡፡

(27) በዚህ ሕግ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ያካትታል፡፡

**<u>አንቀጽ 3 ዓላማ</u>**

የዚህ ሕግ ዓላማ፡-

(1) በወንጀል ምርመራ፣ ክስና ፍርድ ሒደት በሕገመንግሥቱ የተረጋገጡ መብቶችን በማስከበር እና በማስጠበቅ የወንጀል ሕጉን ዓላማዎች ማሳካት፣

(2) የወንጀል ፍትሕ ሥርዐቱ እውነትን በማውጣት ውጤታማ፣ ፍትሐዊ፣ ሚዛናዊ፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማች ወጥነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት፣ እንዲኖረው ማስቻል፤

(3) የመንግሥትን፣ የሕዝብን፣ የግለሰብንና የወንጀል ተጎጂን መብትና ጥቅም ማስከበር እና

(4) በወንጀል ፍትሕ ሥርዐቱ ውስጥ አሳታፊነትን በተለይም የሕዝብ ተሳትፎን ማጎልበትና ማረጋገጥ፣

ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## መሠረታዊ መርሆዎች

**አንቀጽ 4 ጠቅላላ**

በሕገ መንግሥቱ፣ በዚህ ሕግና በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ ሕግ አፈጻጸም በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት መርሆዎች ይመራል፡፡

**አንቀጽ 5 ጥፋተኛ ሆኖ አለመቆጠር**

1. በወንጀል የተከሰሰ ሰው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ታይቶ በመጨረሻ ውሳኔ ጥፋተኝነቱ እስካልተረጋገጠ ድረስ በተከሰሰበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት አለው፤ በራሱ ላይም እንዲመሰክር አይገደድም፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ የመሠረተውን ክስ የማስረዳትና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ ተከሳሽ ራሱን የመከላከል መብት አለው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ተከሳሹ የተከሰሰበት የወንጀል ጉዳይ በሕገ መንግሥቱ እና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዐቱ ላይ አደጋ የሚፈጸም ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ሙስና ወይም በተደራጁ ቡድኖች ወይም በሕግ በተደነገገ ጊዜ ዐቃቤ ሕግ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮችን ካስረዳ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ ሊዛወር ይችላል፡፡

**አንቀጽ 6 በአንድ ወንጀል ድጋሚ ክስ ወይም ቅጣት መከልከሉ**

ማንኛውም ሰው በዚህ እና በወንጀል ሕግ መሠረት የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ በተቀጣበት ወይም ሌላ ሕጋዊ ርምጃ በተወሰደበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም፡፡

**አንቀጽ 7 ሕጋዊነት**

1. ማንኛውም በዚህ ሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ተቋም በሕግ የበላይነት መርህ ይመራል፡፡
2. በወንጀል ጉዳይ የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ በዚህ ሕግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም የተከሰሰ ሰው ጉዳይ የሚታየው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ብቻ ይሆናል፡፡

4. በሌላ ሕግ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር የወንጀል ምርመራና የክስ ሒደት የሚከናወነው በዚህ ሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 8 በሕግ ፊት እኩል መሆን

1. ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዐይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በሕግ እኩል ተጠያቂነት ይኖረዋል፡፡
3. ይህ ሕግ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፣ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር የተጣጣመና በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በኃብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም በሕገ መንግሥቱ በዓለም አቀፍ ሕግ ወይም ስምምነት፣ በዚህ ወይም በተለየ ሕግ መሠረት የወንጀሉን ከባድነት፣ የጥፋቱ ደረጃ፣ ወይም የአድራጊው ዕድሜ፣ ሁኔታዎች ወይም ልዩ ግላዊ ጠባዩ ወይም ወንጀሉ በኅብረተሰቡ ላይ ያስከተለውን አድጋ ግምት ውስጥ በማስገባት ልዩነት ማድረግ የእኩልነት መርህን እንደመሻር አይቆጠርም፡፡

## አንቀጽ 9 የተከራካሪዎች እኩልነት

ማንኛውም የፍርድ ሒደት የዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽን እና የተከሳሽን እኩልነት በሚያረጋግጥ መልኩ ይካሔዳል፡፡

## አንቀጽ 10 ፍትሐዊና ቀልጣፋ ውሳኔ ማግኘት

ማንኛውም በወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው በዚህ ሕግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ፍትሐዊ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 11 እውነትን ማውጣት

1. ማንኛውም የምርመራ ሂዳት መረጃን መሠረት ባደረገ የምርመራ መርህ መመራት አለበት፡፡
2. ማንኛውም የምርመራና የክስ ሒደት እውነትን በማውጣት መርህ ላይ መመሥረት አለበት፡፡
3. በወንጀል ክስ ላይ ፍትህዊ ውሳኔ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ፍርድ ቤት በሕጉ መሠረት እውነትን የማውጣት ኃላፊነት አለበት፡፡

4. እውነትን የማውጣት ሒደት ወንጀል ፈጻሚ ከሕግ ተጠያቂነት እንዳያመልጥ ወንጀል ያልፈጸመ ንጹህ ሰው አላግባብ እንዳይያዝ እና ተጠያቂ እንዳይሆን በሚያደርግ መርህ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡
5. በዚህ ሕግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም አካል እውነትን በማውጣት ሒደት የተጠርጣሪ፣ የተከሳሽ፣ የምስክር እና የሌሎች ሰዎች መብት እንዳይጣስ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 12 መያዝ</u>**

ማንኛውም ሰው ወንጀል ስለመፈጸሙ በቂ ጥርጣሬ ሳይኖር ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 13 በግልጽ ችሎት መዳኘት</u>**

1. ማንኛውም ክስ በግልጽ ችሎት መሰማት አለበት፡፡ ሆኖም በተከሳሹና በተጎጅው የግል ህይወት፣ በሕዝብ የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱ ደኅንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፡፡
2. በሕግ ወይም በፍርድ ቤት ካልተከለከለ በስተቀር ማንኛውም በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ለሕዝብ ግልጽ መደረግ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 14 የትርጉምና የቋንቋ አጠቃቀም መርህ</u>**

1. የወንጀል ፍትሕ ሒደቱ በፌዴራል መንግሥት በአማርኛ፣ በክልል ደግሞ በክልሉ ወይም በአስተዳደሩ ወሰን የሥራ ቋንቋ የሚመራ ይሆናል፡፡
2. በወንጀል ጉዳይ የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው የተጠረጠረበት ወይም የተከሰሰበት ወይም ክስና ምክንያቱ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባው ቋንቋ ይነገረዋል፤ የፍርድ ሒደቱ በማይገባው ወይም በማይረዳው ቋንቋ በሚካሔድበት ወቅት በሚገባው ቋንቋ ወይም በሚረዳው ምልክት እንዲተረጎምለት አስፈላጊነቱ ሲታመን ወይም ከጠየቀ በመንግሥት ወጪ አስተርጓሚ ይመደባል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው የክስና የሰነድ ማስረጃ ትርጉምን ያጠቃልላል፡፡

**<u>አንቀጽ 15 የሕዝብን ጥቅም ማስጠበቅ</u>**

በዚህ ሕግ መሠረት የሚካሔድ ማንኛውም የምርመራ፣ የክስና የፍርድ ሒደት የሕዝብን ጥቅም ቅድሚያ መስጠትና ማስከበር አለበት፡፡ ሒደቱም የተጠረጠሩ፣ የተያዙና የተከሰሱ ሰዎችን እንዲሁም የተጎጂውን መብት ማስከበር አለበት፡፡

**አንቀጽ 16 ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ መከልከሉ**

በወንጀል የተጠረጠረ፣ የተከሰሰ ወይም በፍርድ ሒደቱ ተሳታፊ በሆነ ሰው ላይ ጭካኔ የተሞላበት ኢ-ሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብሩን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

**አንቀጽ 17 በጠበቃ መወከል**

1. የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው ከተያዘበት ወይም ከተከሰሰበት ጊዜ ጀምሮ በመረጠው የሕግ ጠበቃ ምክርና ድጋፍ የማግኘት ወይም የመወከል መብት አለው፡፡ በመረጠው የሕግ ጠበቃ ለመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም የገንዘብ አቅም የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ እና በዚህም ምክንያት ፍትሕ ሊጓደል የሚችል ሁኔታ ሲያጋጥም በመንግሥት ወጪ ጠበቃ ይመደብለታል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘው ወይም የተከሰሰው ሰው
   (ሀ) በወንጀል ድርጊት ገብቶ የተገኘ ወጣት፣
   (ለ) በዕድሜ መጃጀት ወይም በማይድን በሽታ በመያዙ ጉዳዩን መከታተል ያልቻለ፣
   (ሐ) የወንጀል ጉዳይ በጥፋተኝነት ድርድር የሚታይ፣ ወይም
   (መ) በዚህ ሕግ ጠበቃ መወከል ግዴታ መሆኑ በግልጽ የተደነገገ፣
   እንደሆነ በመንግሥት ወጭ በጠበቃ ይወከላል፡፡

**አንቀጽ 18 ጥፋተኛው ባቀረበው ይግባኝ ላይ ቅጣትን ስላለመጨመር**

1. ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተሰኘ ተከሳሽ ባቀረበው ይግባኝ ቅጣት መጨመር የለበትም፡፡
2. 
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ይግባኝ ሰሚው ፍር ቤት በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ፍትሕን ያዛባል ብሎ ሲያምን፡-
   (ሀ) በሥር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተሰኘ ተከሳሽ በቅጣት መጠን ላይ ይግባኝ ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን አክብዶ፣ ወይም
   (ለ) በሥር ፍርድ ቤት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት በመቃወም ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ ባቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን አቅልሎ
   ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 19 የወንጀል ክስ የመንግሥት መሆኑ**

1. በምርመራ መዝገብ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የመንግሥት ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎችን በተመለከተ ዐቃቤ ሕግ ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖሩን ባመነ ጊዜ ተበዳዩ በራሱ ወጭ የግል ክስ እንዲያቀርብ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡
3. ወንጀሉ የተፈጸመው በሕገ መንግሥቱ በተቋቋሙ የሕግ አውጭ፣ የሕግ አስፈፃሚ ወይም የዳኝነት ተቋማት ባለሥልጣናት ላይ የተፈጸመ የስም ማጥፋትና የሐሰት የወንጀል ድርጊት እንደሆነ አቤቱታ ባይቀርብም ክሱ የሚቀርበው በዐቃቤ ሕግ ነው፡፡

**አንቀጽ 20 የዐቃቤ በአማራጭ የመወሰን ሥልጣን**

ምርመራ እንዲካሔድ፣ የተጀመረ ምርመራ እንዲቋረጥ፣ የተቋረጠ ምርመራ እንዲቀጥል፣ መዝገብ እንዲዘጋ፣ ክስ እንዳይመሠረት፣ በዚህ ሕግ መሠረት በአማራጭ ዘዴዎች እንዲታይ፣ ክስ እንዲመሠረት፣ እንዲቋረጥ ወይም እንዲነሳ በአማራጭ የመወሰን ሥልጣን የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ሲሰጥ በዚህና በሌላ ሕግ በተመለከቱ መርሆዎችና ድንጋጌዎች ይመራል፡፡

**አንቀጽ 21 የፍትሕ አካላት ትብብር**

በፌዴራልና በክልል የሚገኙ ፍትሕ አካላት የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲን፣ የወንጀል ሕግን ይህንን ሕግ ለመፈጸም እና የሌሎች የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ተግባራትን ለማስፈጸም የመተባበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## ስለተግባርና ኃላፊነት

**አንቀጽ 22 መርህ**

በሕገ መንግሥቱና በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ፍትሕ ሒደት ተሳታፊ የሚሆኑ አካላት በዚህ ምዕራፍ የተመለከቱትን ተግባራት የማከናወን ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ክፍል አንድ
## ስለፍትሕ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

### አንቀጽ 23 የወል ተግባርና ኃላፊነት

1. የፍትሕ ተቋማት በተናጥል የሚኖራቸው ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የወንጀል ፍትሕ ሥርዐቱን ውጤታማነት፣ ፍትሐዊነት፣ ሚዛናዊነት፣ ተደራሽነት፣ ቀልጣፋነት፣ ተገማችነት ወጥነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት፣ ለማረጋገጥና ሥርዐት ለመዘርጋት የወል ኃላፊነት አለባቸው፡፡
2. የፍትሕ ተቋማት የሚከተሉትን የወል ተግባራት የማከናወን ኃላፊነት አለባቸው፡፡
   (ሀ) በወንጀል ጉዳይ፣ በወንጀለኞች ሁኔታ፣ ወንጀል ስለሚቀንስበት ሁኔታ፣ በወንጀል ጉዳዮችና ተከሳሾች አያያዝና በመሳሰሉት ጥናትና ምርምር ያደርጋሉ፡፡
   ((ለ) የወንጀል መረጃንና ስታስቲክስን በጋራና በተናጠል ይሰበስባሉ፣ ያደራጃሉ፣ ይተነትናሉ፣ ያሳራጫሉ፡፡ የመረጃ ሥርዐቱ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ያደርጋሉ፡፡
   (ሐ) ለተገልጋዮች መስተንግዶ አስፈላጊ የሆኑ የአገልግሎት መስጫ መሣሪያዎችን ያሟላሉ፣ የመስተንግዶ መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃሉ፡፡
   (መ) የጋራ እና የተናጠል የቅሬታና የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዐትን ይዘረጋሉ፡፡
   (ሠ) የተጠርጣሪ፣ ተከሳሽ፣ ተጎጂና ምስክር አያያዝ ሥርዐት የሕገ መንግሥቱና የሌሎች ሕጎችን ድንጋጌ የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡
   (ረ) በወንጀል የፍትሕ አስተዳደር የጋራ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች የፍትሕና ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራና በትብብር ይሠራሉ፡፡

### አንቀጽ 24 የፖሊስ ተግባር እና ኃላፊነት

1. የፖሊስ ተቋም የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለበት፡፡
   (ሀ) ወንጀልን ይከላከላል፤ የወንጀል ድርጊትን እና አደጋን ለመከላከል በሕግ መሠረት ርምጃ ይወስዳል፤
   (ለ) በዚህ ሕግና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ክትትል ያደርጋል፣ ምርመራ ያካሔዳል፣ ማስረጃ ይሰበስባል፤
   (ሐ) በሕግ መሠረት የፍርድ ቤት መጥሪያ ለተከሳሽና ምስክር ያደርሳል፣ ተጠርጣሪን ወይም ተከሳሽን ይይዛል፣ ይፈትሻል፣ ተከሳሽንና ምስክርን

ያቀርባል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ፍተሻ ወይም ብርበራን ያካሔዳል፣ እንዲሁም የሚፈለግ ማስረጃን በይዞታው ሥር ያደረገ ሰው ማስረጃውን እንዲያስረክብ ትእዛዝ ይሰጣል፣

(መ) ተፈጸመ የተባለው የወንጀል ክስ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ አግባብነት ያላቸውን ኤግዚቢቶች ያስተዳድራል፤

(ሠ) ከዐቃቤ ሕግ ተቋም ጋር የወንጀል ምርመራ አመራር ሥርዐትን ያደራጃል፣

(ረ) በሌለበት የተቀጣን ሰው ተከታትሎ በመያዝ ፍርዱ እንዲፈጸም ያደርጋል፣

((ሰ)) የወንጀል ሪከርድን፣ አሻራን፣ እንዲሁም ሌሎች ተጠርጣሪን ወይም ወንጀለኛን ለመለየትና ያለፈ ታሪክን ለመረዳት የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ያደራጃል፡፡

((ሸ)) ለወንጀል ምርመራ እና ከምርመራ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊ የሆኑ የምርመራና የምርምር ተቋማትን እንዲሁም መሣሪያዎችን ያደራጃል፤

((ቀ)) በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ያሉ የምርምር፣ የምርመራ እና ሌሎች ተቋማት ጋር በትብብር የሚሰራበትን ሥርዐት ይዘረጋል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደየአግባብነቱ ምርመራ ለማከናወን በሕግ ሥልጣን ለተሰጣቸው ሌሎች አካላት ተፈጻሚነት አለው፡፡

## አንቀጽ 25 የዐቃቤ ሕግ ተቋም ተግባርና ኃላፊነት

የዐቃቤ ሕግ ተቋም የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለበት፡፡

(1) የወንጀል ምርመራን ይመራል፣ ምርመራ ያካሔዳል፣ እንዲቋረጥ ያደርጋል፣ በተጣራ የምርመራ መዝገብ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን በመለየት ክስ ይመሰርታል፣ በፍርድ ቤት ክርክር ያደርጋል፣ እንዳስፈላጊነቱም ክስ ያነሳል፣ የይግባኝና የሰበር አቤቱታ ያቀርባል፣ በኤግዚቢትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

(2) በዚህ ሕግ መሠረት እንዳግባብነቱ ለግል ከሳሽ ፈቃድ ይሰጣል፤ በፈቃዱ መሠረት የክስ ሒደቱ እየተካሔደ መሆኑን ይከታተላል፤

(3) ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ የፈጸመየፈጸመው የወንጀል ድርጊት ከመደበኛው የወንጀል የፍርድ ሒደት ውጪ ባለ አማራጭ ሥርዐት እንዲታይ እና ተስማሚ ርምጃ እንዲወሰድ ይወስናል ወይም ሌላ ማንኛውንም ተስማሚ ርምጃ

ለመውሰድ የሚያስችል ፕሮግራምና ሥርዐት ያደራጃል፣ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

(4) በተከሳሽ ላይ የሚቀርብ ማስረጃን በዚህ መሠረት ለፍርድ ቤት እና ለተከሳሽ እንዲደርስ ያደርጋል፣ በማንኛውም ሁኔታ ያገኘውንና ለተከሳሽ በመከላከያ ማስረጃነት ሊጠቅም የሚችል ማስረጃን ለፍርድ ቤት ወይም ለተከሳሹ ይሰጣል፡፡

(5) የጉዳዩ መነሻ ወንጀል የሆነ የመንግሥት የፍትሐብሔር ጉዳይን ከወንጀል ጉዳዩ ጋር በማጣመር እንደነገሩ ሁኔታ በድርድር እንዲቋጭ ያደርጋል፣ ክስ ይመሰርታል፣ ክርክር ያካሔዳል፤ በፍርድ ቤት የሚሰጡ ትእዛዞችንና ውሳኔዎችን ተከታትሎ ያስፈጽማል፡፡

(6) የወንጀል ተጎጂ የሆኑ ሕፃናት እና ሴቶችን በመወከል የፍትሐብሔር የጉዳት ካሣ ክስን ከወንጀል ክሱ ጋር በማጣመር ለፍርድ ቤት ያቀርባል፣ ተከራክሮ ያስወስናል፣ የሚሰጡ ትእዛዞችንና ውሳኔዎችን ያስፈጽማል፡፡

(7) ከተጠርጣሪ ወይም ከተከሳሽ ጋር የጥፋተኝነት ድርድር ያካሔዳል፣ በዚህ ሕግ መሠረት እንደአግባብነቱ አባሪ ተጠርጣሪን ከክስ ነፃ ያደርጋል፡፡

(8) ለምስክር ተገቢውን አያያዝ ያደርጋል፣ የወጭ ማካካሻ ይከፍላል፣ በሕግ መሠረት ለጠቋሚ የወሮታ ክፍያ ይፈጽማል፡፡

(9) በፍርድ ቤት የሚወሰን የገንዘብ መቀጮን፣ የንብረት መውረስን፣ ከሲቪል መብት መታገድን፣ ከእስራት ቅጣት ጋር ተያይዞ የሚወሰን የጥንቃቄ ርምጃን እና ሌሎች ቅጣቶችን ያስፈጽማል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

(10) ማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤትን ይጎበኛል፣ የተጠርጣሪን ወይም የታራሚን አያያዝ ሕገ መንግሥቱን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፣ እንዳስፈላጊነቱም ርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

(11) ከሌሎች የፍትሕ አካላት ጋር በመተባበር የወንጀል ክስ አመራር ሥርዐትን ያደራጃል፡፡

(12) በምርመራና ክስ ሒደት የሚነሳ ቅሬታን መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ባፋጣኝ ይሰጣል፡፡

## <u>አንቀጽ 26 የፍርድ ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

ፍርድ ቤት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለበት፡-

(1) ፍርድ ቤት የቀረበ ተጠርጣሪ፣ ተከሳሽ፣ ምስክር ወይም ሌላ ተሳታፊ የፍርድ ቤቱ የሥራ ቋንቋ የማይገባው ወይም በምልክት ቋንቋ መግለጽ አስፈላጊ እንደሆነ አስተርጓሚ ይመድባል፡፡

(2) የቀረበ የወንጀል ክስን ይመረምራል፣ ያከራክራል፣ እንደአግባብነቱ ትእዛዝ፣ ፍርድ ወይም ወሳኔ ይሰጣል፡፡

(3) በሕመም ምክንያት ችሎት መቅረብ የማይችል ሰው ወይም ለጥቃት የተጋለጠ ሕጻን፣ የጾታ ጥቃት ወንጀል የተፈጸመባት ሴት፣ የወንጀል ተጎጂ ወይም ሌለሰ ምስክር ችሎት ሳይቀርብ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጡበት ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

(4) በዚህ ሕግ መሠረት በንብረት ላይ የዕግድ ትእዛዝ ይሰጣል፣ እንደ አስፈላጊነቱ የታገደ ንብረትን የሚያስተዳድር አካል ይሾማል፣ ወይም ንብረቱ እንዲወረስ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

(5) በጥፋተኛ ላይ የተሰጠን ቅጣት፣ የጥንቃቄ ርምጃ እና ሌላ ማንኛውንም የፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ በራሱ ያስፈጽማል ወይም እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

(6) የጾታ ጥቃት፣ የሕፃናት፣ የሽብርተኝነት፣ የሙስና ወንጀል እና ሌሎች ትኩረት የሚሻ የወንጀል ጉዳይ የሚታይበትን ችሎት ያደራጃል፡፡

(7) የችሎት ክርክርና አጠቃላይ ሒደቱ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ እና በሒደቱ በሚያስፈልጉ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴዎች እንዲደገፍ ያደርጋል፡፡

**<u>አንቀጽ 27 የማረሚያ ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የማረሚያ ቤት አስተዳደር የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለበት፡-

(1) በፍርድ ቤት ትእዛዝ በጥበቃ ሥር ያለ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ የወንጀል ምርመራ ወይም ክርክር እስከሚጠናቀቅ ድረስ በማረፊያ ቤት ያቆያል፡፡

(2) በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትእዛዝ መሠረት ታራሚ እንደነገሩ ሁኔታ ቅጣቱን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ በማረሚያ ቤት ያቆያል፡፡

(3) ታራሚ ወይም በማረፊያ ቤት እንዲይ የተወሰነበት ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ከሕግ አማካሪው፣ ከሐኪሙ ወይም ከኃይማኖት አማካሪው ወይም ከቅርብ ዘመዶቹ ጋር የሚገናኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

(4) ታራሚዎች እና በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ የተወሰነባቸው ተጠርጣሪዎች ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር በግል የሚገናኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

(5) በፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም በሕግ መሠረት በማረፊያ የሚቆይ ተጠርጣሪን ወይም ተከሳሽን እና በማረሚያ ቤት ያለ ታራሚን ለፍርድ ቤት ወይም ሥልጣን ላለው አካል ያቀርባል፡፡

(6) ታራሚዎች የትምህርትና የሙያ ሥልጠና እንዲያገኙ አስፈላጊውን ያደርጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

(7) ታራሚዎችን በማረሚያ ቤት ወይም ከማረሚያ ቤት ውጪ ባሉ ቦታዎች በልማት ሥራዎች ላይ ለማሰማራት የሚያስችል ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ ከልማት ሥራው በሚገኝ ገቢ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሥርዐት ይዘረጋል፡፡

(8) በወንጀል ምክንያት የተፈጠረ አለመግባባት በዘላቂነት እንዲፈታ ታራሚዎች ከኅብረተሰቡ ጋር ከመቀላቀላቸው በፊት በአጥፊው እና በግል ተበዳዩ እንዲሁም በአጥፊውና በግል ተበዳዩ ቤተሰብ መካከል ዕርቅ እንዲፈጸም አስፈላጊውን ያደርጋል፡፡

(9) ታራሚዎች ከወንጀለኝነት ባሕርይ ተላቀው የተረጋጋ ስብዕና እንዲኖራቸው፣ ከኅብረተሰቡ ጋር ሲቀላቀሉ የራሳቸውን መልካም ሕይወት ለመምራት የሚረዳቸው ሥርዐት ይዘረጋል፣ አስፈላጊ የሆነ የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

(10) ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው በሚያሳዩት የባሕርይ ለውጥ፣ የአምራችነት ጥረት፣ መልካም ሥነ ምግባርና በመሳሰሉት ሁኔታዎች የአመክሮ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሥርዐት ይዘረጋል፣ ይፈጽማል፣ እንደአስፈላጊነቱም ያስፈጽማል፡፡

## <u>አንቀጽ 28 የፍትሕ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. ፍትሕ ሚኒስቴር በዚህ ሕግ አንቀጽ 25 በዐቃቤ ሕግ ተቋምነቱ የሚኖረው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለበት፡-

   (ሀ) የወንጀል መነሻዎችን ያጠናል፣ ወንጀል የሚቀንስበትን ሥልት ይቀይሳል፤ በወንጀል መከላከል ረገድ የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ አካላትና ኅብረተሰቡን ያስተባብራል፤ አገራዊ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፡፡

   (ለ) ስለወንጀል ምርመራ፣ ክስ፣ ፍርድ ማስፈጸም የመሳሰሉትን በሚመለከት ሥርዐት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

(ሐ) የጥፋተኛነት ድርድር በሚካሔድበት ወይም የአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ በሚወሰድበት ወቅት ተጠርጣሪው የሕግ ምክር አገልግሎት የሚያገኝበትን ሥርዐት ያመቻቻል፡፡ ነጻ የሕግ ምክር አገልግሎት ሥርዐትን ይዘረጋል፡፡

(መ) የወንጀል ድርጊት ጠቋሚዎችና ምስክሮች በሕግ መሠረት ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

(ሠ) የአመክሮና ይቅርታ አሰጣጥ አፈጻጸምና ክትትል ሥርዐትን ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

(ረ) የግዴታ ሥራ ወይም የማኅበረሰብ አገልግሎት ቅጣት፣ በገደብ፣ በአመክሮ እና በይቅርታ የተለቀቁ ፍርደኞችን የመከታተያ ሥርዐት ይዘረጋል አስፈላጊውን አደረጃጀት ይፈጥራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ አስፈላጊውን ርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

(ሰ) በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሀገር አቀፍ የመረጃ አሰባሰብ ሞዴል ይቀርፃል፣ የወንጀል ፍትሕ መረጃዎችና ስታቲስቲክስን ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል፤ ያሰራጫል እንዲሁም ለሚመለከታቸው የፍትሕ አካላት ድጋፍ ይሰጣል፤

(ሸ) በወንጀል ጉዳዮች የዓለም አቀፍ ትብብርን በሚመለከት የሚፈጸሙ ሥራዎችን ያስተባብራል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደአግባብነቱ በክልል ፍትሕ ቢሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 29 የተከላካይ ጠበቃ ተግባርና ኃላፊነት

ተከላካይ ጠበቃ የሚከተሉት ተግባራት ማከናወን አለበት፡-

(1) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በተጠረጠረበት ወይም በተከሰሰበት ወንጀል የሕግ ምክርና ድጋፍ ያደርጋል፤

(2) በዚህ ሕግ መሠረት የተከሳሹን ፍላጎት መሠረት በማድረግ በፍርድ ቤት ክርክር ያደረጋል፤

(3) የጥፋተኛነት ድርድርን ጨምሮ ማንኛውም የወንጀል የፍርድ ሒደት እና ክርክሩ ያለበትን ደረጃ ለተከሳሹ ያሳውቃል፤

(4) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት በሚገኝበት ጊዜ የማግኘት፣ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መቀበልና መስጠት ይችላል፤

(5) በሕገ መንግሥቱና በሕግ የተደነገገ የተከሳሹ መብት እንዲከበር የሙያ ሥነ ምግባሩንና ሕግን መሠረት በማድረግ አስፈላጊዉን ሁሉ ይፈጽማል፡፡

(6) ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ በመከላከያነት የሚያገለግል እና በግሉ ያወቀውን ማንኛውንም ማስረጃ ያለተከሳሹ ፈቃድ በማስረጃነት እንዳይቀርብ ተገቢውን ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 30 የክልሎች ሥልጣን**

በዚህ ክፍል ስለተግባርና ኃላፊነት የተደነገገው ቢኖርም ክልሎች እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በሕግ በተለየ ሁኔታ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለሌሎች ሰዎች መብትና ኃለፊነት

**አንቀጽ 31 የተያዘ ሰው መብትና ኃላፊነት**

1. በሕገ መንግሥቱና በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው፡-

(ሀ) የተያዘበትን ምክንያት በሚረዳው ቋንቋ ወዲያውኑ በመርማሪው ወይም በዐቃቤ ሕጉ እንዲነገረው፤

(ለ) ከተያዘበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለማምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ ሳይጨምር በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ እና በተጠረጠረበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑን ወዲያውኑ የማወቅ፤

(ሐ) መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕጉ የተያዘበትን ምክንያት ፍርድ ቤት ቀርቦ በጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስረዳ ወይም የቀረበው ምክንያት አሳማኝ ካልሆነ የአካል ነጻነቱ እንዲከበርለት የመጠየቅ፤

(መ) በፈቃደኝነት ካልሆነ በቀር በምርመራ ላይ ለሚቀርብለት ጥያቄ መልስ ያለመስጠት ወይም ያለመናገር፤

(ሠ) በምርመራ ላይ ለሚቀርብለት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ እንደሆነ፣ የሰጠው ቃል በፍርድ ቤት በማስረጃነት እንደሚቀርብበት አስቀድሞ በሚረዳው ቋንቋ እንዲነገረው፤

(ረ) ምርመራውን በተመለከተ መረጃ ወይም ማስረጃ የመስጠት፤

(ሸ) ለምርመራው እንቅፋት ወይም ለጸጥታ አስጊ ካልሆነ በስተቀር በትዳር ጓደኛው፣ በኃይማኖት አማካሪው፣ በሕግ አማካሪው፣ በሀኪሙ፣ በቅርብ ዘመዱ የመገናኘት ወይም የመጎብኘት፤

(ቀ) መርማሪው ወይም ዐቃቤ ሕግ ያለበትን አድራሻና ሁኔታ ለሚማርበት ተቋም፣ ለአሰሪው ወይም ለሚቀርበው ሰው፣ የውጭ ሀገር ዜጋ እንደሆነም ለሀገሩ የቆንጽላ ጽሕፈት ቤት ወይም ለኤምባሲው አመቺ በሆነ መንገድ እንዲነግርለት ሊጠይቅ ይችላል፤

(ሰ) ስለወንጀል የፍርድ ሒደቱ አስፈላጊ ነው ተብሎ በዐቃቤ ሕግ የታመነበት መረጃ በመርማሪው ወይም በዐቃቤ ሕጉ እንዲነገረው የመጠየቅ፣

(ተ) ከምርመራው ጋር በተያያዘ በተወሰነ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ወይም አቤቱታውን ሥልጣን ላለው አካል የማቅረብ፤

(ቸ) ከወንጀል ተጎጂው ወይም ከቤተሰቡ ጋር በመስማማት ለመታረቅ ወይም የጉዳት ካሣ ለመክፈል የመጠየቅ፤

መብት አለው፡፡

2. በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው፡-

(ሀ) በዚህ ሕግ መሠረት እንዲቀርብ መጥሪያ ሲደርሰው በተወሰነው ሰዓትና ቦታ መገኘት፤

(ለ) ምስክርን በማስፈራራት ወይም በመደለል፣ ማስረጃን በመሰወር ወይም ምርመራውን በማደናቀፍ ለወንጀል ፍትሕ ሒደት እክል ያለመፍጠር፤

(ሐ) በሕግ መሠረት የተወሰኑ ውሳኔን፣ ትእዛዝን ወይም ሌላ ክልከላን የማክበር፤

(መ) በሕግ በተደነገገው መሠረት የፈሳሽ፣ የፀጉር፣ የዘር ቅንጣት ወይም ሌሎች ናሙናዎችን የመስጠት፤

(ሠ) በዚህ ሕግ የተደነገጉ መርሆች የማክበርና ሌሎች በሕግ የተደነገጉ ግዴታዎችን የመፈጸም ግዴታ፤

ግዴታ አለበት፡፡

## <u>አንቀጽ 32 የተከሰሰ ሰው መብትና ኃላፊነት</u>

1. በሕገ መንግሥቱና በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የተከሰሰ ሰው፡-

(ሀ) ክስ ከቀረበበት በኋላ በሕግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት የመሰማት፤

(ለ) የተከሳሹንና የተጎጅው የግል ሕይወት፣ የሕዝብ  የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱ ደኅንነት ለመጠበቅ ሲባል ጉዳዩ በዝግ እንዲታይ ፍርድ ቤት ካላዘዘ በስተቀር በቀረበበት ክስ በግልጽ ችሎት የመሰማት መብት አለው፤

(ሐ) የቀረበበት ክስ በዳኛው እንዲነበብለት፣ እንዲረዳው እና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት፤

(መ) በተከሰሰበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር ወይም በምስክርነት እንዲቀርብ ያለመገደድ፤

(ሠ) በፈቃደኝነት  የእምነት  ወይም የምስክርነት ቃል የመስጠት፤

(ረ) የቀረበበትን ማንኛውንም ማስረጃ የመመልከት ወይም እንዲሰጠው የመጠየቅ፤

(ሰ) ማቆያ ወይም ማረፊያ ቤቱ ተጠርጣሪው ያለበትን አድራሻና ሁኔታ ለሚማርበት ተቋም፣ ለአሰሪው ወይም ለሚቀርበው ሰው፣ የውጭ ሀገር ዜጋ እንደሆነም ለሀገሩ ኤምባሲ ወይም የቆንፅላ ጽሕፈት ቤት አመቺ በሆነ መንገድ እንዲነገርለት የመጠየቅ፤

(ሸ) የዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ ምስክርን መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ፣

(ቀ) ለመከላከል የሚያስችለውን ማንኛውንም ማስረጃ ለማቅረብ ወይም በፍርድ ቤት ትእዛዝ ለማስቀረብ፣ የመከላከያ ምስክሮቹን ጥያቄ የመጠየቅ፤

(በ) በመረጠው ጠበቃ እንደሚወከል፤ ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣቱ ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም በመንግሥት ወጪ ጠበቃ እንደሚቆምለት በሚረዳው ቋንቋ አስቀድሞ በፍርድ ቤቱ እንዲነገረው፣

(ተ) የችሎቱን ጊዜ፣ ቦታ እና ሰዓትን ጨምሮ ማንኛውንም በሚስጢር ያልተያዘ መረጃ ከፍርድ ቤት ለመጠየቅ እና ምላሽ የማግኘት፤

(ቸ) ክርክር በሚካሔድበት ወቅት ተከላካይ ጠበቃው እንዲገኝለት የመጥራት ወይም እንዲጠራለት የመጠየቅ፣

(ከ) ክሱ በሚሰማበት ወቅት የመሳተፍ፤ የፍርድ ሒደቱ በማይረዳው ቋንቋ በማይካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምለት ወይም አስተርጓሚ እንዲመደብለት የመጠየቅ፤

(ዘ) በመንግሥት ወጪ የተመደበለት ጠበቃ በሕግ መሠረት ሙያውን፣ እውቀቱን እና ልምዱን በመጠቀም ኃላፊነቱን ሳይወጣ በቀረ ጊዜ በሌላ እንዲተካ ፍርድ ቤቱን የመጠይቅ፣

(ወ) በተሰጠ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ በዚህ ሕግ መሠረት ይግባኝ የማለት ወይም አቤቱታ የማቅረብ፤

(ዠ) የይግባኝ አቤቱታውን አስመልክቶ ማናቸውንም ዐይነት ማብራሪያ መስጠት ወይም ተቃውሞ የማቅረብ፣

(ደ) አቤቱታውን ማቅረብና ማስረዳት ወይም በጠበቃው የቀረቡ አቤቱታዎችን የማንሳት፣

መብት አለው፡፡

2. ማንኛውም የተከሰሰ ሰው በዚህ ሕግ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገጉ ግዴታዎችን የማክበርና በፍርድ ሒደት ላይ በአካል የመገኘት ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 33 የወንጀል ተጎጂ መብትና ኃላፊነት

1. ማንኛውም የወንጀል ተጎጂ፡-

(ሀ) ክብሩን በጠበቀ፤ በእንክብቃቤ፣ በትህትና፣ የመያዝ የመስተናገድና የመጠበቅ፤

(ለ) በወንጀል ምርመራ ክስና ፍርድ ሒደት የመሳተፍ እና መረጃ የማግኘት፤ መረጃ ወይም ማስረጃ የመስጠት፤

(ሐ) በግል አቤቱታና በቀላል ወንጀሎች ላይ የግል ክስ ወይም ይግባኝ የማቅረብ እና ክስን የማንሳት፣ የመዝጊያ ንግግር የማድረግ፣ ክሱን በዕርቅ የመጨረስ፤

(መ) በዚህ ሕግ የተደነገጉ የወንጀል እና የፍትሐብሔር መብቶቹን በውክልና የማስፈጸም፤

(ሠ) በፍርድ ቤት ሲፈቀድለት ተከሳሽን ወይም መከላከያ ምስክርን መጠየቅ፣

(ረ) ክርክሩ የሚካሔድበት ቦታ፣ ችሎትና ሰዓት የማወቅ፣ ሲሞት የፍትሐብሔርን መብቶች እንዲተላለፍላት፤

(ሰ) ፍርድ ቤት ቀርቦ ሲመሰክር ደህንነቱ፣ የግል ሚስጥሩ እና ማንነቱ እንዲጠበቅ ወይም እንዳይገለፅ ለምስክር የሚደረግ ልዩ ጥበቃ የማግኘት፤

(ሸ) ከወንጀል ምርመራ፣ ክስና የፍርድ ሒደቱ ጋር በተያያዘ በተወሰነ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ወይም አቤቱታውን ሥልጣን ላለው አካል የማቅረብ እና ምላሽ የመግኘት፤

(ቀ) በሕግ መሠረት ተመጣጣኝ የጉዳት ካሣ የማግኘት፤

እና ሌሎች በሕግ የተደነገጉ መብቶች ይኖሩታል፡፡

2. ተጎጂው የተፈጸመበት ወንጀል የአስገድዶ መድፈር ወይም በሕፃናት ላይ የተፈጸመ ያታዊ ጥቃት እንደሆነ በተለየ ሁኔታ አስፈላጊው የሕግ ምክርና ድጋፍ የማግኘት መብት አለው፡፡

3. ማንኛውም የወንጀል ተጎጂ ሀሰተኛ ጥቆማ በማድረግ የተሳሳተ መረጃ ወይም ማስረጃ ወይም ሐሰተኛ ምስክርነት መስጠት የለበትም፡፡

## አንቀጽ 34 የምስክር መብትና ኃላፊነት

1. ማንኛውም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ሰው፡-

(ሀ) ክብሩን በጠበቀ፤ በእንክብቃቤ፣ በትህትና፣ የመያዝ የመስተናገድና የመጠበቅ፤

(ለ) ከምርመራ ወይም ከጥያቄ በፊት መርማሪው መብቱን፣ ግዴታውን እና ኃላፊነቱን እንዲሁም የተጠራበት ጉዳይ ምን እንደሆነ እንዲነገረው የመጠየቅ፣ ማስረጃውን ወይም የምስክርነት ቃሉን ለመቀበል የቀረበው ሰው የሥራ ኃላፊነትን የማወቅና መረጃ የማግኘት፤

(ሐ) የምስክርነት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ በሚያውቀው ቋንቋ የመጠቀም፣ መረጃውን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚቀበለው ተቋም የሥራ ቋንቋ የማይረዳ እንደሆነ በሚያውቀው ቋንቋ ወይም ምልክት እንዲተረጎምለት በመንግሥት ወጪ አስተርጓሚ እንዲመደብለት የመጠየቅ፣

(መ) ከወንጀል ምርመራ፣ ክስና የፍርድ ሒደቱ ጋር በተያያዘ በተወሰነ ውሳኔ ወይም ሌሎች ሁኔታዎች ላይ ቅሬታ ወይም አቤቱታውን ሥልጣን ላለው አካል የማቅረብ እና ተገቢውን ምላሽ የመግኘት፤

(ሠ) ለምስክርነት ሲቀርብ የወጪ ማካካሻ ክፍያ የማግኘት፣

(ረ) የወንጀሉ ውስብስብነት ወይም ያለበት የማስታወስ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት መርማሪው ወይም ፍርድ ቤት ሲፈቅድለት ማስታወሻውን እና ተጨማሪ የጽሑፍ ምስክርነቱን ለመስጠት ወይም ምስክርነቱን በጽሑፍ የመስጠት፣

(ሰ) በሚያስከስሰው ወይም በሚያስቀጣው ጉዳይ ወይም በፈቃደኝነት በሚመሰክርባቸው በሕግ ተለይተው በታወቁ ሰዎች ላይ ላለመመስከር፤

(ሸ) ምስክሩ በተለይ የአስገድዶ መድፈር የተፈጸመበት ሴት ወይም የፆታ ጥቃት የተፈጸመበት ህጻን እንደሆነ ክብሩን የሚነካ ጥያቄ ከመጠየቅ የመጠበቅ ፣

(ቀ) ስለ ወንጀል ፍርድ ሒደቱና ውጤቱ አጠቃላይ መረጃ የማግኘት፣

እና ሌሎች በሕግ የተደነገጉ መብቶች ይኖሩታል፡፡

2. ማንኛውም ምስክር፡-

(ሀ) በሕግ መረጃ፣ ማስረጃ ወይም የምስክርነት ቃል ለመስጠት የማይገደድ ወይም የማይፈቀድለት ካልሆነ በቀር የሚቀርብለትን ጥያቄዎች የመመለስ፣

(ለ) እውነተኛ መረጃ ወይም ማስረጃ የመስጠት፣ ከወንጀል ድርጊቱ ጋር በተገናኘ የሚያውቀውን ሁሉ በትክክል የመመስከር፤

(ሐ) ሥልጣን ባለው አካል በተወሰነው ቦታና ሰዓት የመገኘት፤

(መ) በችሎት የሰማውን በሚስጥር እንዲይዝ በዳኛው ከተነገረው፣ መረጃውን በሚስጥር የመያዝ፤

(ሠ) አጠቃላይ በዚህ ሕግ የተደነገጉ መርሆችን የማክበር፤

ግዴታ አለበት፡፡

## <u>አንቀጽ 35 የአስተርጓሚ ኃላፊነት</u>

በወንጀል ፍርድ ሒደት በአስተርጓሚነት የሚሰራ ሰው ቃለ መኃላ የመፈጸም ያለ አድሎ የመተርጎም እና በሚፈለግበት በማንኛውም ቦታና ጊዜ የመገኘትና ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

## <u>አንቀጽ 36 ተጠያቂነት</u>

በዚህ ክፍል የተመለከቱ ግዴታዎችን እና ኃላፊነቶችን የጣሰ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## የፍርድ ቤቶች ሥልጣን
## ክፍል አንድ
## የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን

**አንቀጽ 37 መሠረቱ**

1. የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 11-20 በተደነገገው መሠረት የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡
2. ለክልል ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 መሠረት የተሰጠው የውክልና ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፣ የፌዴራል መንግሥቱን ሕግና ዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት በማድረግ በሚነሳ ጉዳይ፣ በፌዴራል መንግሥቱ ሕግ ተገልፀው በተወሰኑ ሰዎች፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ወይም በሕግ በተገለፁ ቦታዎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ፣ የይግባኝና የሰበር የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡
3. የክልል ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጎች ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ባልተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች፣ ሰዎች እና ቦታዎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ፣ የይግባኝና የሰበር የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

**አንቀጽ 38 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ሥልጣን**

1. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡
   (ሀ) አፈጻጸማቸው የፌዴራል መንግሥት ወይም አንድ የክልል መንግሥት ከሚያስተዳድረው የአስተዳደር ክልል በላይ የሆኑ ወንጀሎች፤
   (ለ) ዓለም አቀፍ ባሕርይ ያላቸው ወይም ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች፤
   (ሐ) ከውጭ ጉዳይ ተያያዥነት ያላቸው ወንጀሎች፤
   (መ) በፌዴራል መንግሥቱ ተቋማትና ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤
   (ሠ) የፌዴራል መንግሥቱ ሕግ እንዲያወጣ በሕገ መንግሥቱ ሥልጣን በተሰጠው ጉዳዮች ጋር ተያያዘው የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤
   (ረ) ከኃላፊነት ጋር በተያያዘ በፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣናትና ሠራተኞች የሚፈጸም ወንጀል፤

(ሰ) የጉምሩክና የፌዴራል መንግሥት ግብርና የገንዘብ ጥቅም ሕጎችን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤

(ሸ) ለፌዴራል መንግሥቱ ተጠሪ የሆኑ ከተሞች ወይም ቦታዎች የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤

(ቀ) በሕግ መንግሥቱና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዐቱ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች፡-

(1) በመንግሥት፣ በሀገርና በዓለም አቀፍ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

(2) ዓለም አቀፍ ሕጎችን በመጣስ በሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

(3) ወታደራዊ ወንጀሎች፣ በመከላከያ ሠራዊትና ተቋማት እንዲሁም በፌዴራል ፖሊስ፣ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ፖሊስ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

(4) በፌዴራል መንግሥቱ የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች፤

(5) በአንድ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ፣ ኃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ወይም ተለይቶ በሚታወቅ አናሳ ማኅበረሰብ ከሚኖር ጥላቻ ጋር ተያይዞ በሚፈጸም ወንጀል በተለይም የብሔሩን፣ የብሔረሰቡን ወይም የሕዝቡን ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ እምነት፣ ወይም ማንኛውም የማንነት መገለጫ የሆነን እሴት ለማጥፋት፣ ለማንቋሸሽ የማይጠቅም ወይም ከሌላ ያነሰ አድርጎ ለማቅረብ፣ እንዲናቅ ወይም እንዲጠላ ለማድረግ በሚፈጸም ወንጀል፣

(6) የሐሰት ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን በሚመለከቱ ወንጀሎች፤

(7) የፌዴራል መንግሥት ሰነዶችን መፍጠር፣ ሰነዶችን ወደሐሰተኛነት መለወጥና ማጥፋትን የሚመለከቱ ወንጀሎች፣

(8) በፌዴራል መንግሥት ሥራ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

(9) ከአንድ ክልል በላይ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ አገልግሎት በሚሰጡ መገናኛዎች ፀጥታና ነጻነት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች፤

(10) የበረራ ደኅንነትን በሚመለከቱ ወንጀሎች፤

(11) ዓለም አቀፍ የዲፕሎማቲክ ሕጎችና ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ልዩ መብትና ጥበቃ ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ ሀገር ሰዎች ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች፣

(12) የውጭ ሀገር ዜጎች ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች፤

(13) የአደገኛና አደንዛዥ እጾች ማምረት፣ መሥራት፣ ማዘዋወር ወይም መጠቀምን በሚመለከቱ ወንጀሎች፤

(14) በተለያዩ ክልሎች ወይም በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልል ሥር በሚወድቁና በተያያዙ ወንጀሎች፤

(15) በተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ በኃይማኖት ተከታዮች ወይም በፖለቲካ ቡድኖች መካከል ከተፈጠረ ግጭት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፤

(16) በፌዴራል መንግሥቱ ንብረቶች ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

(17) በሽብርተኝነት ወንጀሎች፣

(18) በአዲስ አበባና በድሬዳዋ በሚፈጸሙ በወንጀል ሕጉ በተመለከቱ ማናቸውም የወንጀል ጉዳዮች ላይ

የወል የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

## አንቀጽ 39 የክልል ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ሥልጣን

በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ፍርድ ቤቶች፡-

(1) በዚህ ሕግ በአንቀጽ 37 ከተዘረዘሩት ውጪ ባሉ የወንጀል ጉዳዮች፣

(2) በዚህ ሕግ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ (4)፣ (6)፣ (7)፣ (8)፣ (12)፣ (13) እና (16) የተደነገጉ የወንጀሎች ሆነው ከአምስት ዓመት በታች በሚያስቀጡ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች፣ እና

(3) በሕገ መንግሥቱ በውክልና በተሰጡ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ላይ

የወል የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

## አንቀጽ 40 የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ

1. የፌዴራል ፍርድ ቤት የያዘው ጉዳይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ያስነሳል ብሎ ካመነ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ጉዳዩን ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ መላክ አለበት፡፡
2. የክልል ፍርድ ቤት የያዘው ጉዳይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ያስነሳል ብሎ ካመነ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ጉዳዩን ለክልሉ ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ መላክ አለበት፤ ጉዳዩ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ጋር ተያይዞ የትርጉም ጥያቄ ያስነሳል ብሎ ካመነ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ለፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባኤ መላክ አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል አንድ
## የፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ሥልጣን

### አንቀጽ 41 የመጀመሪያ፣ የይግባኝ እና የሰበር የሥረ ነገር ሥልጣን

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በፌዴራል የወንጀል ጉዳይ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር ሥልጣን አላቸው፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዐይቶ በወሰነው ጉዳይ ላይ የይግባኝ ሥልጣን አለው፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል የወንጀል ጉዳይ የይግባኝ እና የሰበር ሥልጣን አለው፡፡
2. የክልል የመጀመሪያ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በክልል የወንጀል ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር ሥልጣን አላቸው፤ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዐይቶ በወሰነው ጉዳይ ላይ የይግባኝ ሥልጣን አለው፤ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልል የወንጀል ጉዳይ የይግባኝና የሰበር ሥልጣን አለው፡፡
3. የክልል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በሠንጠረዥ አራት በተመለከቱ የፌዴራል የወንጀል ጉዳይ ላይ የመጀመሪያ እና የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡
4. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የውክልና ሥልጣኑ ዐይቶ በወሰነው የፌዴራል የወንጀል ጉዳይ ላይ የይግባኝ ሥልጣን አለው፡፡

### አንቀጽ 42 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

(1) አንድ ጉዳይ ከአንድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ አቤቱታ ወይም

(2) በውክልና ለክልል ፍርድ ቤቶች በተሰጡ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮችን በሚመለከት ከአንድ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ አቤቱታ፣

ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን አለው፡፡

## አንቀጽ 43 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን አለው፡-

(1) በዚህ ሕግ በአንቀጽ 43 መሠረት በወሰናቸው የወንጀል ጉዳዮች፣

(2) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠባቸው የወንጀል ጉዳዮች፣

(3) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ በሰጠባቸው የወንጀል ጉዳዮች፤

(4) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውክልና በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠባቸው የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች፤

(5) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል የውክልና ዳኝነት ሥልጣን በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ በሰጠባቸው የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች፡፡

## አንቀጽ 44 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥልጣን

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለባቸው የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የሰበር ሥልጣን አለው፤

(1) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ዐይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች፤

(2) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች፤

(3) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች፡፡

## አንቀጽ 45 የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር ሥልጣን

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን አለው፤

(ሀ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 37 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሠንጠረዥ ሦስት በተመለከቱ በአዲስ አበባ ወይም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የግዛት ወሰን

ውስጥ በተፈጸሙ እንዲሁም በሠንጠረዥ አራት በተመለከቱ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች፣

(ለ) የፌደራል መንግሥቱ ባለሥልጣናት በሥራ ኃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ በሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮች፣

(ሐ) ከአንድ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ አቤቱታ፣

(መ) በውክልና ለክልል ፍርድ ቤቶች በተሰጡ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮችን በሚመለከት ከአንድ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ አቤቱታ፣

(ሠ) በሌሎች ሕጎች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች፣

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) አፈጻጸም "የፌዴራል መንግሥት ባለሥልጣን" ማለት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል፣ ከሚኒስትር ደረጃ በላይ የሆነ የፌዴራል መንግሥት ባለሥልጣን፣ ሚኒስትር፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ወይም በተመሣሣይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የፌዴራሉ መንግሥት ባለሥልጣንን ይመለከታል፡፡

## <u>አንቀጽ 46 የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፡-

(1) የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በሰጠባቸው የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች፣ እና

(2) በሌሎች ሕጎች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲታዩ በተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች፣

ላይ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

## <u>አንቀጽ 47 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 37 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፡-

(ሀ) በሠንጠረዥ ሦስት “ሠ” የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በተመለከቱና በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ የአስተዳደር ወሰን ውስጥ በተፈጸሙ፣ እና

(ለ) በሠንጠረዥ አራት “ሠ” በተመለከቱ

የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር ሥልጣን አለው፡፡

2. በሌሎች ሕጎች ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጡ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣኖች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 48 የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን

የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

(1) አንድ የክልል የወንጀል ጉዳይ ከአንድ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ አቤቱታ፣

(2) በሠንጠረዥ አራት “መ” በተመለከቱ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ላይ፣ እና

(3) በውክልና ለክልል ፍርድ ቤቶች በተሰጡ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮችን በሚመለከት ከአንድ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ አቤቱታ፣

ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

## አንቀጽ 49 የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን

ክልሉ የሚያወጣው ሕግ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

(1) በዚህ ሕግ በአንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (3) መሠረት በወሰናቸው የወንጀል ጉዳዮች፣

(2) የክልል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠባቸው በሠንጠረዥ ሦስት “መ” በተመለከቱ የክልል የወንጀል ጉዳዮች፤

(3) የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሥልጣኑ የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጠው የተለየ ውሳኔ በሰጠባቸው የወንጀል ጉዳዮች፤

(4) በሠንጠረዥ አራት “ሠ” በተመለከቱ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች፤

ላይ የይግባኝ ሥልጣን አለው፡፡

## አንቀጽ 50 የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥልጣን

የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸውን የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ዐይቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጠባቸው የክልል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የሰበር ሥልጣን አለው፡፡

## አንቀጽ 51 የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር ሥልጣን

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 40 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን አለው፤
   (ሀ) በሠንጠረዥ ሦስት “ለ” በተመለከቱ በክልል የግዛት ወሰን ውስጥ በተፈጸሙ የክልል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡
   (ለ) የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት በሥራቸው ወይም በኃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ በሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮች፣
   (ሐ) በሌሎች የክልሉ ሕጎች ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች፣
   (መ) በሠንጠረዥ አራት “ሠ” በተመለከቱ በክልሉ በተፈጸሙ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) የተመለከተው “የክልል መንግሥት ባለሥልጣን” ማለት የክልል መንግሥት ምክር ቤት አባል፣ ከክልል ቢሮ በላይ የሆነ የክልል መንግሥት ባለሥልጣን፣ የክልል ቢሮ ኃላፊ፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ የክልል መንግሥት ባለሥልጣን ነው፡፡

## አንቀጽ 52 የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን

የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፡-

(1) የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በሰጠባቸው የክልል የወንጀል ጉዳዮች፣ እና
(2) በሌሎች ሕጎች ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲታዩ በተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች፣

ላይ የይግባኝ ሥልጣን አለው፡፡

## አንቀጽ 53 የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር ሥልጣን

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 40 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሠንጠረዥ ሦስት "ሠ" በተመለከቱ በክልል የግዛት ወሰን ውስጥ በተፈጸሙ የክልል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡
2. በሌሎች ሕጎች ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጡ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣኖች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 54 ክሶችን ስለማጣመር

1. በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ አመልካችነት በተለያዩ ትይዩ ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች እንዲጣመሩ ጥያቄ ሲቀርብ ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ከሁለቱ በአንደኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተጣምሮ እንዲታይ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡
2. ከክሶቹ በከፊል በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ በከፊል በከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚታዩ እንደሆነ ከክሶቹ ከባዱን ክስ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ሆኖ ክሶቹን በማጣማር ያያል፡፡
3. ከክሶቹ በከፊል፡-
   (ሀ) በፌዴራል ፍርድ ቤት እና በከፊል በተለያዩ የክልል ፍርድ ቤቶች ወይም በክልል ፍርድ ቤቶች ወይም
   (ለ) በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የሚወድቅ እንደሆነ ከባዱን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ክሶቹን አጣምሮ ያያል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት ከባዱን የወንጀል ክስ ለመለየት አጠራጣሪ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ የፌዴራል ወይም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 55 የሥረ ነገር ሥልጣን በሌለ ጊዜ ክሱን ስለማዛወር

1. የወንጀል ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሥረ ነገር ሥልጣን የሌለው መሆኑን ከተረዳ ሥልጣን ወዳለው ፍርድ ቤት ያስተላልፋል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው ሁኔታ ክሱን ወደ ሌላ ፍርድ ቤት የሚያስተላልፈው እንደሆነ ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ ጉዳዩን እንዲከታተሉት ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ 56 በግልጽ ስላልተደነገ የወንጀል የሥረ ነገር ሥልጣን

1. በዚህ ወይም በሌላ ሕግ የፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ለመወሰን ከተዘረዘሩት ወንጀሎች ውጭ ሌሎች ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን አላቸው፡፡

2. በሌሎች ሕጎች ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣኖች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 57 የሥረ ነገር ሥልጣን ድልድልን ስለ ማሻሻል

በዚህ ክፍል ስለፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ሥልጣን የተደነገገው ቢኖርም፡-

(1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የሥረ ነገር ሥልጣን ድልድል በመመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

(2) ክልሎች ስለክልል ፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ሥልጣን በተለየ ሁኔታ በሕግ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

# ንዑስ ክፍል ሁለት
# የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን

## አንቀጽ 58 መደበኛ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን

1. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን በአዲስ አበባና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ወይም በሌሎች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በተፈጸሙ የፌዴራል የወንጀል ጉዳይ ላይ ይሆናል፡፡
2. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ስልጣናቸው ውስጥ በተፈጸመ ወይም ድርጊቱ ውጤት ባገኘበት በሠንጠረዥ ሦስት እና አራት በተጠቀሱ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡
3. የክልል ፍርድ ቤቶች በክልሉ የግዛት ወሰን ውስጥ በተፈጸሙ ወይም ድርጊቱ ውጤት ባገኘበት በሠንጠረዥ ሦስትና አራት በተጠቀሱ የክልል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

**አንቀጽ 59 ተከሳሹን ወንጀሉ በተፈጸመበት ሥፍራ ወይም ውጤት ባገኘበት ቦታ ስለመክሰስ**

ወንጀሉ የተፈጸመው በአንድ ቦታ ሆኖ የወንጀሉ ውጤት የተገኘው በሌላ ቦታ እንደሆነ ወንጀሉ በተፈጸመበት ወይም የወንጀሉ ውጤት በተገኘበት ሥፍራ የሚገኘው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ 60 ከአንድ ወንጀል ጋር ነክነት ስላለው ብቻ እንደአንድ ወንጀል የሚቆጠር ተግባር ክሱ የሚታይበት ፍርድ ቤት**

ከሌላው ወንጀል ጋራ ግንኙነት በመደረጉ እንደአንድ ወንጀል የሚቆጠር ተግባር በክሱ ማመልከቻ የሚጠቀሰው የመጀመሪያው የወንጀል ተግባር ክስ የሚታየው ከሁለቱ አንዱ ተግባር ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ ለማየት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ነው፡፡

**አንቀጽ 61 ወንጀል የተሠራበት ቦታ ያልታወቀ ሲሆን ክሱ የሚታይበት ፍርድ ቤት**

ወንጀሉ የተሠራበት ቦታ በርግጠኝነት ያልታወቀ እንደሆነ ክሱ የሚታየው፡-

(1) ከልዩ ልዩ ሥፍራዎች ውስጥ በየትኛው ሥፍራ ወንጀሉ እንደ ተፈጸመ ያልተረጋገጠ እንደሆነ፣

(2) ወንጀሉ በከፊል አንድ ሥፍራ በከፊል ደግሞ በሌላ ሥፍራ የተፈጸመ እንደሆነ፣

(3) ወንጀሉ ከአንድ በበለጠ ሥፍራ መፈጸሙ ሲቀጥል፣ ወይም

(4) በልዩ ልዩ ሥፍራዎች የተፈጸሙ በርካታ ወንጀሎች የተሠሩ ሲሆን፣

ሥልጣን ባለው በአንድ ሥፍራ በሚገኘው ፍርድ ቤት ሊሆን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 62 በጉዞ ላይ የተፈጸመ ወንጀል**

ተጠርጣሪው በጉዞ ላይ ሳለ ወንጀል የፈጸመ እንደ ሆነ ተጠርጣሪው ወይም ተጎጂው ወይም ወንጀል የተፈጸመበት ነገር በጉዞው በሚያልፍበት ሥፍራ ያለ ፍርድ ቤት የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ 63 በውጭ ሀገር የሚፈጸም ወንጀል**

1. ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ በተፈጸመ ወይም ውጤት ባገኘ በፌዴራል ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር በሚወድቅ ወንጀል ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤት የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

2. ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ የመንግሥት ጥቅም ወይም በኢትዮጵያ መርከብ ወይም አውሮፕላን ላይ በተፈጸመ በፌዴራል ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር በሚወድቅ ወንጀል ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፤ ወንጀሉም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንደተፈጸመ ይቆጠራል፡፡
3. ከኢትዮጵያ ውጪ በተፈጸመ ዓለም አቀፍ ወንጀል ላይ የሥረ ነገር ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

## አንቀጽ 64 ተደራራቢ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን

1. ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ እንደሆነ አስቀድሞ ክስ የተመሠረተበት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የቀዳሚ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡
2. ጉዳዩ በአንድ ክልል ባሉ ከአንድ በላይ በሆኑ የክልል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ እንደሆነ አስቀድሞ ክስ የተመሠረተበት የክልል ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የቀዳሚነት የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡
3. ጉዳዩ በክልል ወይም በፌዴራል ወይም በተለያዩ ክልሎች ባሉ ትይዩ የሥረ ነገር ሥልጣን ባላቸው የአስተዳደር ወሰን ዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ እንደሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ 54 ከባዱን የወንጀል ክስ የሚያይ የክልል ወይም የፌዴራል ፍርድ ቤት ተጣምረው በሚታዩት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡
4. የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመበት ወይም ውጤት ያገኘበት ቦታ አጠራጣሪ እንደሆነ አስቀድሞ ክስ የተመሠረተበት ፍርድ ቤት የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)-(4) የተደነገገው ቢኖርም ለፍርድ ሒደቱ ሊኖረው የሚችለውን ውጤታማነት፣ አመችነትና የበለጠ አስተማሪነት እና ለተከሳሽና ለምስክር አቀራረብ የሚኖረውን አመቺነት ከግምት በማስገባት ዐቃቤ ሕግ ተደራራቢ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን ካላቸው ፍርድ ቤቶች በአንዱ ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ መሠረት የቀዳሚነት የዳኝነት ሥልጣን የሌለው የክልል ወይም የፌዴራል ፍርድ ቤት እያከራከረ ያለውን ጉዳይ የቀዳሚ ሥልጣን ወዳለው ፍርድ ቤት መምራት አለበት፡፡

## አንቀጽ 65 ክስን ማዛወር

1. በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ አመልካችነት አንድ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ከአንድ የዳኝነት ሥልጣን ካለው ፍርድ ቤት ወደ ሌለው ፍርድ ቤት ሊዛወር ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ክስ የሚዛወረው፡-
   (ሀ) ክሱ በቀረበበት ፍርድ ቤት ፍትሐዊና ሚዛናዊ ፍርድ ለማግኘት አያቻልም ተብሎ ሲታመን፣
   (ለ) ለሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ወይም ለምስክሮች ምቹ አለመሆኑን፣
   (ሐ) ጉዳዩ በአጭር ጊዜ ውሳኔ ሊያገኝ የማይችል መሆኑን፣ ወይም
   (መ) በሌላ አሳማኝ ምክንያት በተለመደው ሁኔታ ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የሚያስቸግር መሆኑን፣

   በመግለጽ ክሱ ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ተዛውሮ እንዲታይ ጉዳዩን በመስማት ላይ ላለው ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ ሲያቀርብ እና ፍርድ ቤቱም ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ክሱን ለማየት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲሰማ ያስተላልፋል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ጥያቄ ሳይቀበለው የቀረ እንደሆነ በጉዳዩ ላይ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ ጉዳዩን በይግባኝ ለሚያየው ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡
4. አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ፣
   (ሀ) የአካባቢ ሥልጣን ባይኖረውም የስረነገር ሥልጣን ላለው ማንኛውም ፍርድ ቤት ነገሩ እንዲታይ፣
   (ለ) ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በራሱ እንዲታይ
   ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑሰ አንቀጽ (4) መሠረት የሚሰጠው ትእዛዝ የመጨረሻና ይግባኝ የሌለው ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 66 የመሰየም ሥልጣን

በአንድ ጉዳይ ላይ ፍርድ የሰጠ ፍርድ ቤት በዚያው ጉዳይ ላይ በሚቀርብ የመሰየም ጥያቄ ላይ ሥልጣን አለው፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ከወንጀል የፍርድ ሒደት ስለመነሳት እና የአቤቱታ አቀራረብ

### አንቀጽ 67 ከፍርድ ሒደት ተሳትፎ ወይም ከችሎት ስለሚያስነሱ ምክንያቶች

1. ማንኛውም ዳኛ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ መርማሪ ወይም የፍርድ ቤት ሥራ አከናዋኝ፡-
   (ሀ) በተፈጸመው ወንጀል የግል ተበዳይ ወይም ተከሳሽ እንደሆነ፣

   (ለ) ከተበዳይ ወይም ከተከሳሽ ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፤

   (ሐ) ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የራሱ ወይም የዘመዱ የግል ጥቅም ካለ፣

   (መ) በጉዳዩ ላይ ቀደም ሲል በዐቃቤ ሕግነት፣ በተከላካይ ጠበቃነት ወይም በአማካሪነት ይዞ ሲከራከርበት ወይም ተሳትፎ ሲያደርግበት የነበረ እንደሆነ፤

   (ሠ) በጉዳዩ ላይ በልዩ አዋቂነት፣ በአስተርጓሚነት ወይም በምስክርነት ቀርቦ አስተያየቱን ወይም ምስክርነቱን የሰጠበት እንደሆነ፣

   (ረ) ሥራውን እንዲያከናውን በሕግ መሠረት ያልተሾመ ወይም ያልተመደበ እንደሆነ፣

   (ሰ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ)-(ሰ) ከተዘረዘሩት ውጭ ፍትሐዊ ወይም ገለልተኛ ውሳኔ ከመስጠት የሚያግዱት ሌሎች ምክንያቶች ካሉ፣

   ከፍርድ ሒደት ተነስቶ በሌላ መተካት አለበት፡፡
2. ማንኛውም ተከላካይ ጠበቃ ወይም ተሳሽን በመወከል የቀረበ ጠበቃ፡-
   (ሀ) ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል በዳኝነት፣ በዐቃቤ ሕግነት፣ በመርማሪነት፣ በምስክርነት፣ በልዩ አዋቂነት ወይም በአስተርጓሚነት ይዞ በጉዳዩ ላይ ተሳትፎ ሲያደርግበት የቆየ፣

   (ለ) ከተበዳዩ ጥቅም በተቃራኒ የተበዳዩን ወይም የተከሳሹን ጥቅም በሚነካ ሁኔታ የሕግ ምክር አገልግሎት የሰጠ፣ ወይም

   (ሐ) በጠበቆች የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት የጥቅም ግጭት የሚያስነሳ ተግባር የፈጸመ እንደሆነ፣

   ከፍርድ ሒደት ተነስቶ በሌላ መተካት አለበት፡፡
3. ማንኛውም፡-

(ሀ) ልዩ አዋቂ ወይም አስተርጓሚ በሥራው ወይም በሌላ ምክንያት ከተጎጂው ወይም ከተከሳሽ ጋር የግል የጥቅም ወይም ሌላ ግንኙነት ያለው ወይም የነበረው እንደሆነ፣

(ለ) ልዩ አዋቂ ቀደም ሲል በጉዳዩ ላይ በሰነድ መርማሪነት ወይም በሌላ ሁኔታ ከተበዳዩ ወይም ከተከሳሹ መብትና ጥቅም ጋር በተያያዘ ተግባር ላይ የተሳተፈ እንደሆነ፣ ወይም

(ሐ) ልዩ አዋቂ ወይም አስተርጓሚ በሙያው ብቃት ላይ ጥያቄ የተነሳበት እንደሆነ፣

በፍርድ ሒደት ተነስቶ በሌላ መተካት አለበት፡፡

4. በሌላ ሕግ ስለዳኞች፣ ዐቃቤያን ሕግ፣ መርማሪ፣ ጠበቃ፣ አስተርጓሚና ልዩ አዋቂ የተደነገገው እንደተጠበቀ ነው፡፡

## <u>አንቀጽ 68 አስቀድሞ የታየ ጉዳይ</u>

1. ማንኛውም ዳኛ ክርክር በተነሳበት የወንጀል ጉዳይ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የተካፈለ እንደሆነ ጉዳዩን በድጋሚ ተሰይሞ ማየት አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጉዳዩን በጊዜ ቀጠሮ፣ በይግባኝ ማስፈቀጃ፣ እንደገና በማስከፈት አቤቱታ ላይ እና በሌሎች መሰል ጉዳዮች በሚሰጥ ዳኝነት መሳተፍ ጉዳዩን አስቀድሞ እንደመመልከት አይቆጠርም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ወይም በዲሲፒሊን በሚሰጥ ዳኝነት ጉዳዩን ከማየት አያግድም፡፡

## <u>አንቀጽ 69 አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

1. ማንኛውም ዳኛ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ መርማሪ፣ ተከላካይ ጠበቃ፣ አስተርጓሚ ወይም የፍርድ ሥራ የሚያከናውን ባለሙያ፡-

   (ሀ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 67 እና 68 በተደነገገው መሠረት በፍርድ ሒደት መሳተፍን የሚከለክሉ ምክንያቶች መኖሩን እንዳወቀ በራሱ ተነሳሽነት ከሒደቱ መነሳት አለበት፡፡

   (ለ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከፍርድ ሒደቱ በራሱ ተነሳሽነት ካልተነሳ ከሳሽ ወይም ተከሳሹ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. ማንኛውም ልዩ አዋቂ በዚህ ሕግ አንቀጽ 66 ንዑስ አንቀጽ (3) በተዘረዘሩ ምክንያቶች በፍርድ ቤት አነሳሽነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች አቤቱታ እንዲነሳ ጥያቄ ካልቀረበበት በስተቀር በራሱ ከፍርድ ሒደት ሊነሳ አይችልም፡፡
3. አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታውን ሲያቀርብ አለኝ የሚለውን ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ)

መሠረት እንደሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ 67 እና 68 ከተዘረዘሩ ምክንያቶች አንዱን መጥቀስ በቂ ይሆናል፡፡

4. አቤቱታው የቀረበው በዚህ ሕግ አንቀጽ 67 መሠረት አስቀድሞ በታየ ጉዳይ እንደሆነ አስቀድሞ የታየውን የፍርድ ቤት መዝገብ ማመልከት በቂ ነው፡፡

## አንቀጽ 70 አቤቱታው የሚቀርብበት ጊዜ

1. አቤቱታው የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም አቤቱታውን ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካች እንዳወቀ ወዲያውኑ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. በማንኛውም ሁኔታ አቤቱታው የሚቀርበው በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት መሆን ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 71 የአቤቱታ አቀራረብ ሒደት

1. ከፍርድ ሒደት የመነሳት ጥያቄ የቀረበው በዚህ ሕግ አንቀጽ 68 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) በተደነገገው መሠረት እንደሆነ፡-
   (ሀ) ዳኛ የመነሳት ጥያቄውን ጉዳዩን ለሚመለከተው ችሎት ያቀርባል፤ ጉዳዩ በአንድ ዳኛ እየታየ እንደሆነ በራሱ ውሳኔ ይነሳል፡፡
   (ለ) ዐቃቤ ሕግ የመነሳት ጥያቄውን ለቅርብ ኃላፊው ያቀርባል፡፡
   (ሐ) መርማሪ የመነሳት ጥያቄውን ለቅርብ ኃላፊው ያቀርባል፡፡
   (መ) ተከላካይ ጠበቃ፣ ልዩ አዋቂ፣ አስተርጓሚ እና የፍርድ ቤት ሥራ አከናዋኝ የመነሳት ጥያቄውን ጉዳዩን ለሚመለከተው ዳኛ ያቀርባል፣ ዳኛውም ጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2. ከፍርድ ሒደት የመነሳት ጥያቄ የቀረበው በዚህ ሕግ አንቀጽ 68 ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) በተደነገገው መሠረት
   (ሀ) በዳኛ፣ ጠበቃ፣ አስተርጓሚ፣ ልዩ አዋቂና የፍርድ ቤት ሠራተኛ እንደሆነ አቤቱታው ጉዳዩን ለሚመለከተው ችሎት፣ ወይም
   (ለ) በመርማሪ ላይ እንደሆነ ለቅርብ ኃላፊው
   (ሐ) ዐቃቤ ሕግ ላይ እንደሆነ ለቅርብ ኃላፊው
   ይቀርባል፡፡
3. አቤቱታ የቀረበው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) በተደነገገው መሠረት እንደሆነ ጥያቄው ክርክሩ በሚመራበት የፍርድ ቤት መዝገብ ላይ እንዲመዘገብ ይደረጋል፤ ጥያቄውም በቃል ሊቀርብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 72 ውሳኔ መስጠት

1. በዚህ ሕግ መሠረት ከፍርድ ሒደት እንዲነሳ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ማንኛውም አቤቱታ የቀረበበት ሰው ስለጉዳዩ አስተያየቱን እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
2. ጌቱታው የቀረበው በመርማሪ ወይም በዐቃቤ ሕግ ላይ እንደሆነ አግባብነት ያለው የቅርብ ኃላፊ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. ከችሎት የመነሳት አቤቱታ የቀረበው በዳኛ ላይ ሆነ፡-
   (ሀ) ጉዳዩ አንድ ዳኛ ባለበት ፍርድ ቤት የሚታይ እንደሆነ እና ጉዳዩ ከቀረበበት ዳኛ ውጭ በችሎቱ ሌላ ዳኛ የሌለ ወይም የማይገኝ ሲሆን አቤቱታውን ይኸው ዳኛ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤ እንዳስፈላጊነቱም ክሱ እንዲዛወር ያደርጋል፡፡
   (ለ) ጉዳዩ በአንድ ዳኛ በሚታይበት ችሎት እንደሆነ ጥያቄው በሌላ ዳኛ ተምርምሮ ውሳኔ ይሰጥበታል፤ እንዳስፈላጊነቱም ክሱ በዚሁ ዳኛ እንዲታይ ይደርጋል፡፡
   (ሐ) ጉዳዩ በሦስት ዳኛ የሚታይ ሆኖ አቤቱታው የቀረበው በአንዱ ዳኛ ላይ እንደሆነ ሰብሳቢ ዳኛ፣ አቤቱታ የቀረበው በሰብሳቢ ዳኛ ላይ እንደሆነ ከቀሩት ዳኞች መካከል በሹመት ቅድሚያ ያለው ዳኛ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
   (መ) ጉዳዩ በአምስት ዳኛ የሚታይ ሆኖ አቤቱታው የቀረበው በአንዱ ዳኛ እንደሆነ የተቀሩት ሌሎች ዳኞች አቤቱታውን በመመርመር ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡
   (ሠ) ጉዳዩ በሦስት ወይም በአምስት ዳኛ የሚታይ ጉዳይ ሆኖ አቤቱታው የቀረበው ከአንድ በላይ በሆኑ ዳኞች ላይ እንደሆነ አቤቱታ ያልቀረበባቸው የተቀሩት ሌሎች ዳኞች አቤቱታውን በመመርመር ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡
   (ረ) ጉዳዩ በሦስት ወይም በአምስት ዳኛ የሚታይ ጉዳይ ሆኖ አቤቱታው የቀረበው በሁሉም ዳኞች ላይ እንደሆነ ጉዳዩን በራሳቸው ወይም እንዳስፈላጊነቱ በሌሎች ተመሳሳይ የሹመት ደረጃ ባላቸው የፍርድ ቤቱ ዳኞች ተመርምሮ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡ ክሱ የሚወሰንበትን አግባብ የፍርድ ቤቱ ፕሬዘዳንት ይወስናል፡፡
4. ማንኛውም አስተርጓሚ፣ ልዩ አዋቂ ወይም የችሎት ሥራ አከናዋኝ ከፍድ ሂዳት ተሳትፎ እንዲነሳ አቤቱታ ከቀረበበት ክሱን የሚያየው ችሎት በቀረበው አቤቱታ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ ውሳኔን የመጨረሻ ይሆናል፡፡

5. ከፍርድ ሒደት ይነሳልኝ አቤቱታ ወይም ከችሎት የመነሳት ጥያቄ እንደቀረበ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጥበታል፣ ለሒደቱ ማስረጃ መስማትና መዝገቡን አስቀርቦ ማየት አስፈላጊ መሆኑ ከታመነበት ከሦስት ቀን በማይበልጥ ጊዜ መወሰን አለበት፡፡

**አንቀጽ 73 ይግባኝ ማቅረብ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 71 (3) በተደነገገው መሠረት ከችሎት መነሳት፡-
   (ሀ) በቀረበው አቤቱታ መሠረት የተሰጠ እንደሆነ ውሳኔው ይግባኝ አይባልበትም፡፡
   (ለ) የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም በማስረጃ ካልተረጋገጠ ለፍርድ ቤቱ ፕሬዘዳንት ቅሬታ ሊቀርብበት ይችላል፤ ፕሬዘዳንቱም ጉዳዩን ዐይቶ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) የተደነገገው ቢኖርም በወንጀል ክሱ ላይ ውሳኔ የሰጠው ዳኛ አቤቱታ የቀረበበት ሆኖ አቤቱታው ተቀባይነት ያላገኘ ወይም በማስረጃ ያልተረጋገጠ እንደሆነ ቀድሞ አቤቱታ ያቀረበው ወገን ቅሬታውን በዋናው ጉዳይ ላይ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር በማጣመር ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የሌሎች ፍትሕ አካላት ሥልጣን

**አንቀጽ 74 የፌዴራል የፍትሕ አካላት ሥልጣን**

1. በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል የዐቃቤ ሕግ ተቋም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ላይ ሥልጣን አለው፡፡
2. የፌዴራል ፖሊስ ወይም በሕግ የመመርመር ሥልጣን የተሰጠው የፌዴራል አካል በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ላይ ሥልጣን አለው፡፡
3. በሕግ ወይም በፍርድ ቤት በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎችን የማስፈጸም ሥልጣን አላቸው፡፡

**አንቀጽ 75 የክልል የፍትሕ አካላት ሥልጣን**

1. የክልል የዐቃቤ ሕግ ተቋም በክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የክልል የወንጀል ጉዳዮች ላይ ሥልጣን አለው፡፡

2. የክልል ፖሊስ ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል በክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የክልል የወንጀል ጉዳዮች ላይ ሥልጣን አለው፡፡
3. በሕግ ወይም በፍርድ ቤት በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር የክልል ማረሚያ ቤቶች በክልል ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎችን የማስፈጸም ሥልጣን አላቸው፡፡

**አንቀጽ 76 ውክልና ስለመስጠት**

1. የፌዴራል የፍትሕ አካላት በዚህ ሕግ በፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ላይ ከተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት እንደአግባብነቱ ለክልል የፍትሕ አካላት በውክልና ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
2. ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጠ ውክልና ክልሎች ለሚያከናውኑት ተግባር የፌዴራል ፍትሕ አካላት አስፈላጊውን ወጭ ይሸፍናሉ፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የፍትሕ አካላት ማለት ፖሊስ፣ የዐቃቤ ሕግ ተቋምና ማረሚያ ቤቶች ናቸው፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## ሊፈጸም የተቃረበ ወንጀል ወይም ሊደርስ የተቃረበ አደጋን ስለመከላከል

**አንቀጽ 77 ጠቅላላ**

በሌላ ሕግ ለሌላ አካል የተሰጠው ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ፖሊስ በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርሰ የሚችል፣ ሊፈጸም የተቃረበ ወንጀል ወይም ሊደርስ የተቃረበ አደጋ አለ ብሎ በበቂ ሁኔታ ሲያምን ወንጀሉን ለመከላከል ወይም አደጋውን ለማስወገድ በዚህ ሕግ መሠረት ርምጃ ይወስዳል፡፡

**አንቀጽ 78 አደጋን መከላከል**

ፖሊስ የእሳት አደጋ፣ ርዕደ መሬት፣ የጎርፍ አደጋ፣ የወረርሽኝ በሽታ እና መሰል የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተከስተዋል ወይም ሊከሰቱ ይችላሉ ብሎ በበቂ ሁኔታ ሲያምን አደጋውን ለመቀነስ ወይም ለመከላከል ሲባል የፍርድ ቤት ትእዛዝ ሳያስፈልግ፣

(1) በአደጋው አካባቢ ያሉ ሰዎች ከቦታው እንዲነሱ፣
(2) በአደጋው አካባቢ የሚገኝ ንብረት እንደነገሩ ሁኔታ እንዲነሳ ወይም እንዲወገድ፤

(3) በአካባቢው ያለ ሰው አንድን ድርጊት እንዲያከናውን ወይም ከማከናወን እንዲቆጠብ፣

(4) አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን እንዲሰጥ ወይም እንዲያስወግድ አስገዳጅ ርምጃዎችን ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 79 በፈንጂና ተቀጣጣይ ነገር የሚደርስ አደጋን ስለመከላከል

ፖሊስ ሊፈነዳ የተቃረበ ፈንጂ፣ ቦንብ፣ ተቀጣጣይ ወይም በሰውና በንብረት ላይ ተመሳሳይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ሌላ ነገር መኖሩን በበቂ ሁኔታ ሲያምን አደጋውን ለማስወገድ፡-

(1) መንገድ፣ ቦታ ወይም ቤት ለተወሰነ ጊዜ ይዘጋል፣ ያሽጋል ወይም ከልሎ ያቆያል፤

(2) በአካባቢው የሚገኝ ተሽከርካሪ ወይም ሰው በመፈተሽ ሕገ ወጥ ዕቃዎችን ይይዛል፤

(3) ሌላ ተመጣጣኝ የሆነ ተመመሳሳይ ርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 80 ሌላ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነገር ላይ የሚወሰድ ርምጃ

ፖሊስ አደጋ ሊያስከትል ይችላል የሚል በቂ ምክንያት ሲኖረው፡-

(1) የዘመመ የኤሌትሪክ፣ የስልክ እና የመሳሰለ ምሰሶ እንዲቃና ወይም በሌላ እንዲተካ፤

(2) የተከፈተ ወይም የተቆፈረ ጉድጓድ እንዲዘጋ ወይም ጥንቃቄ ለማድረግ እንዲረዳ ምልክት በቦታው እንዲተከል፤

(3) የተጠራቀመ መርዝ ወይም ኬሚካል ወይም በሰው መኖሪያ አካባቢ የሚገኝ አውሬ እንዲወገድ አስፈላጊውን ርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 81 ሊፈጠር ስለተቃረበ ፀብ ወይም ግጭት

1. ፖሊስ በሁለት እና ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል ሊፈጠር የተቃረበ ፀብ ወይም ግጭት ወይም ሌላ ሁከትን ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ አለ ብሎ በበቂ ሁኔታ ሲያምን እንደነገሩ ሁኔታ፡-

(ሀ) ፀቡን፣ ግጭቱን ወይም ሁከቱን ለማብረድ አስፈላጊውን ተመጣጣኝ ርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፣

(ለ) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለፀቡ፣ ለግጭቱ ወይም ለሁከቱ ምክንያት የሆነውን ሰው ይይዛል፣

(ሐ) በሰው ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መሣሪያ ይይዛል ወይም እንዲያዝ ያደርጋል፣

2. ፖሊስ ሁኔታው በፈቀደ መጠን ፀብ፣ ግጭት ወይም ሁከት ሊያስነሳ የነበረ ወይም ያነሳ ሰው ወይም ቡድን በዕርቅ እንዲስማማ ተገቢውን ሊፈጽም ይችላል፡፡

3. በፀቡ፣ በግጭቱ ወይም በሁከቱ ምክንያት በቁጥጥር ሥር የዋለ ሰው በዚህ ሕግ ስለተያዙ ሰዎች በተደነገገው መሠረት አስፈላጊው ርምጃ ይወሰዳል፡፡

**አንቀጽ 82 <u>የሚወሰደው ርምጃ ሕጋዊነት እና ተመጣጣኝነት</u>**

1. በዚህ ሕግ መሠረት ፖሊስ አደጋን ለማስወገድ የኃይል ርምጃና የጦር መሣሪያ መጠቀም የለበትም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ሌሎች አማራጭ ርምጃዎችን በመውሰድ የወንጀል አደጋን መከላከል ያልተቻለ እንደሆነ ወይም በሌሎች አማራጭ ርምጃ ማስወገድ የማይቻል መሆኑን ባመነ ጊዜ ፖሊስ ኃይልና የጦር መሣሪያ ሊጠቀም ይችላል፡፡
3. በኃይል ወይም በጦር መሣሪያ በመጠቀም የሚወሰደው ርምጃ የሰው ሕይወትን አደጋ ላይ የማይጥል፣ ሊደርስ ከሚችለው አደጋው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እና የሚፈለገውን ዓላማ ለማሳካት ተገቢ መሆን አለበት፡፡
4. የተወሰደው የኃይል ወይም የጦር መሣሪያ ርምጃ የሰው አካል ወይም ሕይወት ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣

   (ሀ) አደጋ የደረሰበት ሰው ወዲያውኑ የህክምና ርዳታ እንዲያገኝ፣ እና

   (ለ) አደጋ የደረሰበት ሰው ቤተሰብ ወይም የቅርብ ዘመድ ስለደረሰው ጉዳት ወዲያውኑ እንዲያውቅ

   መደረግ አለበት፡፡

## <u>ሁለተኛ መጽሐፍ</u>
## <u>ስለምርመራ</u>
## <u>ምዕራፍ አንድ</u>
## <u>ክስ፣ የግል አቤቱታ እና ጥቆማ</u>

**<u>አንቀጽ 83 ጠቅላላ</u>**

በዚህ ሕግ መሠረት፡-

(1) ፖሊስ ወይም ዐቃቤ ሕግ ወንጀል እየተፈጸመ ወይም የተፈጸመ መሆኑን በቂ ጥርጣሬ ያለው እንደሆነ፣

(2) ወንጀል እየተፈጸመ ወይም የተፈጸመ መሆኑ ማንነቱ ተለይቶ በታወቀ ወይም ባልታወቀ ሰው ክስ የቀረበ እንደሆነ፣

(3) የግል አቤቱታ ክስ የቀረበ እንደሆነ፣

(4) ወንጀሉ የእጅ ከፍንጅ እንደሆነ ወይም

(5) ጥቆማ የቀረበ እንደሆነ

የወንጀል ምርመራ ተግባር መጀመር አለበት፡፡

## አንቀጽ 84 የወንጀል ክስ በጠቅላላው

1. የወንጀል ድርጊት የተፈጸመ ወይም ሊፈጸም የተቃረበ መሆኑን ያወቀ ወይም መረጃ ያገኘ ማንኛውም ሰው የወንጀል ምርመራ እንዲካሔድ ወይም ሌላ ሕጋዊ ርምጃ እንዲወሰድ በማንኛውም አመቺ መንገድ በአቅራቢያው ለሚገኝ የፖሊስ ወይም የዐቃቤ ሕግ ተቋም ክስ ማቅረብ ወይም ማሳወቅ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ በታች የተደነገጉትን ወንጀሎች መፈጸማቸውን ወይም ሊፈጸሙ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ያወቀ ሰው ወንጀሉን የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
   (ሀ) በሕገ መንግሥቱና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዐት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (ከአንቀጽ 238-242)፣
   (ለ) በመንግሥት የውጭ ደኅንነትና በመከላከያ ኃይል ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (ከአንቀጽ 246-253)፣
   (ሐ) የሙስና ወንጀል፣ (አንቀጽ 404 ንዑስ አንቀጽ 4)
   (መ) የታክስ እና የጉምሩክ ወንጀሎች፣
   (ሠ) ሽብርተኝነት (አዋጅ ቁጥር 652 አንቀጽ 12)፣
   (ረ) በተደራጁ ቡድኖች የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተለይም ሕገ ወጥ የሰው፣ የጦር መሣሪያ፣ የመድኃኒት እና የገንዘብ ዝውውር ወንጀሎች፣
   (ሰ) በሴቶች ላይ የሚፈጸም የአስገድዶ መድፈርና በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጾታዊ ጥቃቶች፣
   (ሸ) ሌላ በሞት ወይም በዕድሜ ልክ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል፣

## አንቀጽ 85 የግል አቤቱታ ለማቅረብ መብት ያለው ሰው

1. በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል መፈጸሙን ያወቀ የግል ተበዳይ ወይም ወኪሉ አቤቱታን በማንኛውም አመቺ መንገድ በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ወይም የዐቃቤ ሕግ ተቋም ማቅረብ ይችላል፡፡

2. በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል የተፈጸመበት ሰው አቤቱታውን ሳያቀርብ የሞተ እንደሆነ አቤቱታው በወላጆቹና ተወላጆቹ፣ በጎን እስከ ሁለት ትውልድ በሚዛመዱ የሥጋ ዘመዶቹ ወይም በትዳር ጓደኛው ሊቀርብ ይችላል፤ በአቤቱታው አቀራረብ የሚች ልጅ፣ የትዳር ጓደኛ፣ ወላጆች እንደ ቅደም ተከተላቸው ቅድሚያ አላቸው፡፡

3. አካለመጠን ያላደረሰ ወይም በሕግ የተከለከለ የግል ተበዳይ አቤቱታውን በሞግዚቱ ወይም በአሳዳሪው አማካኝነት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (3) የተደነገገው ቢኖርም በሕገ መንግሥቱ በተቋቋሙ የሕግ አውጭ፣ የሕግ አስፈፃሚ ወይም የዳኝነት ተቋም ወይም ባለሥልጣን ላይ የተፈጸመ የስም ማጥፋት ወይም የሐሰት የወንጀል ክስ አቤቱታ የሚቀርበው በተቋሙ ወይም በባለሥልጣኑ ወይም በዐቃቤ ሕግ በኩል ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 86 በግል ተበዳይ ስለሚቀርብ አቤቱታ አቀራረብ</u>**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 86 መሠረት ከአንድ በላይ የሆኑ አቤቱታ አቅራቢዎች አቤቱታቸውን በግል ወይም በጋራ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

2. አቤቱታ አቅራቢ በዚህ ሕግ አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ (1)-(4) መሠረት አቤቱታውን ባቀረበ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን በአካል ቀርቦ ካላስረዳ ወይም በጽሑፍ ካላረጋገጠ እንደገና የማቅረብ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ አቤቱታውን እንዳላቀረበ ይቆጠራል፡፡

**<u>አንቀጽ 87 ክስን ወይም የግል አቤቱታን ስለመመዝገብ</u>**

1. የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ ለፖሊስ ወይም ለዐቃቤ ሕግ ተቋም ቀርቦ ይመዘገባል፡፡ ክሱ ወይም የግል አቤቱታው፡-
   (ሀ) ለፖሊስ ተቋም የቀረበ እንደሆነ መርማሪ በማንኛውም መንገድ ወዲያውኑ ለዐቃቤ ሕግ ያሳውቃል፤
   (ለ) ለዐቃቤ ሕግ ተቋም የቀረበ እንደሆነ ተቋሙ በማንኛውም መንገድ ወዲያውኑ ለፖሊስ ወይም በሕግ የመመርመር ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያሳውቃል፡፡

2. አቤቱታው የቀረበለት አካል የቀረበለትን ማንኛውንም የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ አልቀበልም ማለት አይችልም፡፡

3. ክሱን ወይም የግል አቤቱታውን የተቀበለው አካል የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቀን፣ ቦታ፣ የተጠርጣሪው ሙሉ ስም፣ የምስክሮችን ስምና

አድራሻ እና ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን ወዲያውኑ በመዝገቡ ላይ ማስፈር አለበት፡፡

4. አቤቱታውን የተቀበለው አካል የቀረበለትን የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ በዚህ ሕግ አንቀጽ 83 መሠረት በማድረግ ወዲያውኑ የመጀመሪያ ደረጃ የማጣራት ሥራ ማከናወን አለበት፡፡

## አንቀጽ 88 አቤቱታን ስለማንሳት

በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል የተፈጸመበት የግል ተበዳይ ወይም ወኪሉ ለፖሊስ ወይም ለዐቃቤ ሕግ ተቋም ያቀረበውን አቤቱታ ምክንያት መስጠት ሳያስፈልገው የፍርድ ቤት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በጽሑፍ በሚቀርብ ማመልከቻ ለማንሳት ይችላል፡፡

## አንቀጽ 89 አቤቱታን የማንሳት ውጤት

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 88 መሠረት በተነሳ አቤቱታ ላይ እንደገና አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ከነበረበት ለማስቀጠል አይቻልም፡፡
2. ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች የተፈጸመ በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ የወንጀል ድርጊት ላይ የቀረበ አቤቱታ ለአንደኛው ወንጀል አድራጊ ከተነሳ ለሌሎችም እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡
3. የግል አቤቱታው በዚህ ሕግ መሠረት ከተነሳ መዝገቡ ይዘጋል፣ የተያዘ ዕቃ ወይም ኤግዚቢት ለተጠርጣሪው፣ ለተከሳሹ ወይም ለሕጋዊ ባለ መብቱ ይመለሳል፣ ለተከሳሽ እና ለግል ተበዳይ የክስ መነሳት ማስረጃ ይሰጠዋል፡፡

## አንቀጽ 90 ማንነቱ ባልታወቀ ሰው የሚቀርብ የወንጀል ክስ

1. በማንኛውም ሁኔታ ጥቆማ የጠቋሚውን ማንነት መግለጽ ሳያስፈልግ ሊደረግ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ካልታወቀ ጠቋሚ የቀረበ የወንጀል ጥቆማ ከፍ ያለ የሕግ መጣስን የሚገልጽ ሆኖ ወንጀሉ ለመሠራቱ በአካባቢው ሁኔታ የተደገፈና የሚታመን መስሎ የተገኘ እንደሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ 96፣ 101 እና ከአንቀጽ 103 - 164 ስለምርመራ በተደነገገው መሠረት የቀረበውን የወንጀል ክስ ጥቆማ ለማረጋገጥ ምርመራ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 91 የወንጀል ድርጊትን ስለመጠቆም**

1. ፍትሕ ሚኒስቴር በተመረጡ የወንጀል ዓይነቶች ጠቋሚዎች መረጃ ስለሚሰጡበት ሁኔታ የሚደነግግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም “ጠቋሚ” ማለት ገንዘብ ወይም ሌላ የሚታወቅ ጥቅም ለማግኘት ወይም የነፃ አገልግሎት ለመስጠት ሲል መረጃ የሚሰጥ ወይም የሚጠቁም ሰው ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም በሕግ ወይም በውል የወንጀል ድርጊትን ተከታትሎ የማውጣት ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች በሚከታተሉት ጉዳይ ላይ በጠቋሚነት ሊቀርቡ አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 92 ስለጥቆማ አቀራረብ**

1. ጠቋሚው አመቺ በሆነ በማንኛውም መንገድ አግባብ ላለው አካል ጥቆማውን ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ጥቆማው አግባብ ላለው አካል መድረሱ ከተረጋገጠ እንደተመዘገበ ይቆጠራል፡፡
3. በማናቸውም መንገድ የቀረበ ጥቆማ አግባብ ባለው አካል መመዝገብ አለበት፡፡ መዝገቡም የጠቋሚውን መለያ፣ የወንጀሉን ዐይነት፣ የአፈጻጸሙን ዘዴ፣ የተጠርጣሪውንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 93 የሌሎች ተቋማት ኃላፊነት**

1. ሥልጣኑ ሳይኖረው የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ የቀረበለት የመንግሥት ተቋማት ክሱን ወይም የግል አቤቱታውን ለፖሊስ ወይም የዐቃቤ ሕግ ተቋም ወዲያውኑ ያስተላልፋል፡፡
2. የመንግሥት ተቋማት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በራሳቸው የሚወስዱት የአስተዳደር ወይም የዲሲፕሊን ርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በተቋሙ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች በተቋሙ ግቢ ውስጥ ወንጀል ስለመፈጸማቸው ያወቁ እንደሆነ፣ ወይም በተቋሙ ንብረት፣ ገንዘብ፣ ወይም የተቋሙን ኃላፊነትና ተግባር በሚያደናቅፍ መልኩ በማንኛውም ሰው ወንጀል ስለመፈጸሙ ያወቁ እንደሆነ ወይም ጥርጣሬ ሲኖራቸው ወዲያውኑ አግባብ ላለው አካል የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 94 የወንጀል ክስ ያስታወቀ ወይም የግል አቤቱታ አቅራቢ መብት**

የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ ያቀረበ ሰው የወንጀል ምርመራው ስለደረሰበት ደረጃ እና ስለተወሰደው ርምጃ መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡ ሆኖም የሌሎች ሰዎችን ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የወንጀሉን የምርመራ ሥራ የሚያደናቅፍ እንደሆነ መረጃው መሰጠት የለበትም፡፡

## አንቀጽ 95 የመጀመሪያ ደረጃ ማጣራት

1. የፖሊስ ወይም የዐቃቤ ሕግ ተቋም በተመዘገበው የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ የሚያደርግ ሲሆን በዚህም ድርጊቱ፡-
   (1) የእጅ ከፍንጅ ወንጀል፣
   (2) የወንጀል ድርጊት ያልተፈጸመ፣
   (3) ደንብ መተላለፍ፣
   (4) በሌሎች ሥልጣን ባላቸው አካላት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ፤
   (5) በዕርቅ ሊፈታ የሚችል፣
   (6) ወንጀል ተፈጽሞም ምርመራ ማካሔድ ሳያስፈልገው ከወዲሁ በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ የሚዘጋ፤
   (7) የወንጀል ድርጊት የተፈጸመ ስለመሆኑ ፍንጭ በመገኘቱ ምርመራ ሊጣራበት የሚችል፤የጉዳዩ ምንነት የማይታወቅ በመሆኑ ተጨማሪ የማጣራት ሥራ የሚጠይቅ ወይም ሌላ ያልተጠቀሰ ድርጊት መሆኑን በማጣራት ይወስናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የመጀመሪያ ማጣሪያ ያደረገው ፖሊስ እንደሆነ ጉዳዩን ከመወሰኑ በፊት ለዐቃቤ ሕግ ማሳወቅ አለበት፡፡

## አንቀጽ 96 የእጅ ከፍንጅ የወንጀል ድርጊት

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 95 መሠረት በተደረገ ማጣሪያ ተፈጽሞ የተገኘው የእጅ ከፍንጅ የወንጀል ድርጊት እንደሆነ ምርመራውን የሚያደርገው የሚከተሉትን ያከናውናል፤
   (ሀ) ማስረጃውን በአግባቡ መሰብሰብና ማደራጀት፤
   (ለ) አስፈላጊ እንደሆነ የወንጀል ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ መገኘት፤
   (ሐ) ኤግዚቢት ተመዝግቦ እንዲቀመጥ ማድረግ፣ በኤግዚቢትነት የማይፈለግ ዕቃ ወዲያውኑ ዕቃው ለተወሰደበት ባለይዞታ ወይም ባለቤቱ መመለስ፤
   (መ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ የምርመራ እና የማጣራት ሥራ ማከናወን፤
2. የወንጀል ድርጊቱ በግል ተበዳይ አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ሕግ አንቀጽ 192 መሠረት ዐቃቤ ሕግ የሕዝብ ጥቅምና የማስረጃ መመዘኛዎች መሟላታቸውን አረጋግጦ ወዲያውኑ ክስ መመሥረትን ጨምሮ በዚህ ሕጉ መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ይወስናል፡፡

3. ለዚህ ሕግ አፈጻጸም “የእጅ ከፍንጅ የወንጀል ድርጊት” ማለት ተጠርጣሪው የወንጀል ድርጊቱን በመፈጸም ላይ እያለ፣ ለመፈጸም ሲሞክር ወይም እንደፈጸመ የተያዘበት ወይም ሲሸሽ ሕዝቡ ወይም ምስክሮቹ፣ የፖሊስ አባል እየተከታተለው ጩኸትና እሪታ የተሰማበት እና ወዲያውኑ ምርመራ የተጣራበት የወንጀል ድርጊት ነው፡፡

**አንቀጽ 97 የወንጀል ድርጊት ያልሆኑ ጉዳዮች**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 96 በተደረገ ማጣሪያ ተፈጽሞ የተገኘው ድርጊት በወንጀል ሕግ ያልተከለከለና የማያስቀጣ እንደሆነ የወንጀል ምርመራ መዝገቡ ይዘጋል፤ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ርምጃዎችም ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የመጀመሪያ ማጣሪያ ያደረገው ፖሊስ እንደሆነ ጉዳዩን ለዐቃቤ ሕግ በማሳወቅ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

**አንቀጽ 98 ከሥልጣን ውጭ ስለሆኑ ጉዳዮች**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 96 መሠረት በተደረገ ማጣሪያ ተፈጽሞ የተገኘው ድርጊት በከፊል ወይም በሙሉ ጉዳዩን በተቀበለው አካል ሥልጣን ሥር የማይወድቅ ወይም የደንብ መተላለፍ እንደሆነ ጉዳዩን ሥልጣን ላለው አካል ወዲያውኑ መምራት ወይም ውክልና እንዲሰጠው መጠየቅ አለበት፡፡

**አንቀጽ 99 የአያስከስስም ውሳኔ**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 96 መሠረት በተደረገ ማጣሪያ ተፈጽሞ የተገኘው የወንጀል ድርጊት የማያስከስስ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገቡን በዚህ ሕግ አንቀጽ 193 መሠረት ይዘጋል፡፡

**አንቀጽ 100 ምርመራ እንዲደረግ መወሰን**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 96 መሠረት በተደረገው ማጣሪያ ተፈጽሞ የተገኘው ድርጊት ወንጀል ስለመሆኑ አመላካች ነገር ሲኖር ወይም የጉዳዩ ምንነት የማይታወቅ በመሆኑ ተጨማሪ የማጣራት ሥራ የሚጠይቅ ወይም ሌላ ያልተጠቀሰ ድርጊት እንደሆነ በዚህ ሕግ መሠረት የወንጀል ምርመራ እንዲከናወን ዐቃቤ ሕግ ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 101 ስለሌሎች ርምጃዎች**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 96 መሠረት በተደረገው ማጣሪያ ተፈጸመ ከተባለው ድርጊት ጋር በተያያዘ የዲሲፕሊን ርምጃ ሊወሰድ ይገባል ተብሎ ሲታመን አግባብ ያለው አካል እንዲያውቀው ይደረጋል፤ የመንግሥት ጥቅሞችን የሚጎዱ የፍትሐብሔር

ጥፋቶች ካሉ በሕግ መሠረት ተገቢው ርምጃ ይወሰዳል ወይም ሥልጣን ያለው አካል ጉዳዩን እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለወንጀል ምርመራ
## ክፍል አንድ
## ስለምርመራ አጀማመር፣ ማስረጃን ለማሰባሰብ እና ለማደራጀት ስለሚከናወኑ ተግባራት

### አንቀጽ 102 ጠቅላላ

1. የወንጀል ምርመራ ሥራ በመርማሪ ፖሊስና በዐቃቤ ሕግ በጋራ ይከናወናል፡፡ ምርመራውን የመመምራትና የመከታል ኃላፊነት የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡
2. ዐቃቤ ሕግ በማንኛውም የወንጀል ጉዳይ የወንጀል ምርመራ የመምራትና የመከታተል ኃላፊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የወንጀል ምርመራን አስመልክቶ ለሚመለከተው መርማሪ አካል ምክርና ድጋፍ የመስጠት፣ አግባብ ያለው ትእዛዝ የመስጠትና የምርመራ ሒደትን ሕጋዊነት የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡
3. ክስ ወይም የግል አቤቱታ የተቀበለ መርማሪ አካል ስለተቀበለው የወንጀል ክስ አቤቱታ የወንጀል ምርመራ ለመጀመር በቂ መረጃ መኖሩን ካመነ በዚህ ሕግ መሠረት ምርመራ ይጀምራል፤ ይህንኑ ወዲያውኑ ለዐቃቤ ሕጉ አመቺ በሆነ ማንኛውም መንገድ ያሳውቃል፤ ዐቃቤ ሕጉም ምርመራው ስለሚካሔድበት አግባብ ይወስናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም መርማሪ አካል ከወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ በዐቃቤ ሕግ የሚሰጥ ትእዛዝን የመፈጸም ወይም የማስፈጸም ግዴታ ይኖርበታል፡፡
5. የዚህ አንቀጽ አፈጻጸም እንደ አግባብነቱ ፍትሕ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ወይም ክልሎች በሚያወጡት ሕግ ይወሰናል፡፡

### አንቀጽ 103 ማስረጃን ስለማሰባሰብና ስለማደራጀት

የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ለማረጋገጥ በዚህ ሕግ መሠረት፡-

(1) የምስክሮችን ቃል መቀበልና መመርመር፤
(2) ከተከሳሽ ቃል በመቀበል እና ፈሳሽና ሌሎች ናሙናዎችን በመውሰድ፤
(3) ተጠርጣሪን ጨምሮ ሌሎች ሰዎችን በመፈተሽ፣ በቤትና በቦታ ላይ ብርበራ በማካሔድና ዕቃዎችን በመያዝ፤
(4) በምልክታና ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ተገኝቶ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ፣

(5) በተለያዩ የመንግሥት አካላት ማለትም የመንግሥት ተቋማት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና ሌሎች የመንግሥት የአክሲዮን ድርሻ ካለበት ድርጅቶች የሚገኝን ማንኛውም ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ፤

(6) ከተከሳሹ ውጭ ካሉ ሌላ ሰው ወይም ድርጅት ማስረጃ በመጠየቅና በመቀበል፤

(7) የልዩ አዋቂ ባለሙያዎች አስተያየት በመሰብሰብ፤

(8) በልዩ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ማስረጃን መሰብሰብና በሌሎች ሕጋዊ መንገዶች በመሰብሰብ፤

ይከናወናል፡፡

## አንቀጽ 104 <u>የምስክሮችን ቃል ስለመቀበል እና ስለመመርመር</u>

1. መርማሪና ዐቃቤ ሕግ ተፈጸመ ስለተባለው ወንጀል፣ ስለ ተጠርጣሪው ወይም ስለድርጊቱ አፈጻጸም ወይም ተያያዥነት ስላላቸው ሌሎች ጉዳዮች ማንኛውንም ማስረጃ ሙያዊ ትንተና ወይም ማስረጃ መስጠት የሚችልን ሰው መመርመርና ቃሉን መቀበል ይችላሉ፡፡
2. ዐቃቤ ሕግ ስለምስክሮች ቃል አቀባበል ሒደት ሊመረመሩ ስለሚገባው ምስክሮች፣ የምስክርነት ይዘትና አግባብ አስፈላጊውን ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፤ እንደአግባብነቱ ውሳኔ በሚያስፈልግባቸው ጉዳዮች ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## <u>አንቀጽ 105 ለምስክር ስለሚሰጥ መጥሪያ</u>

1. ለምርመራ የሚፈለግ ምስክር የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ በመጥሪያ ሊጠራ ይችላል፤ ምስክርን የጠራው መርማሪ እንደሆነ ይህንኑ በማንኛውም አመቺ መንገድ ለዐቃቤ ሕግ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ መጥሪያ፡-
   (ሀ) የምስክሩን ሙሉ ስም፤
   (ለ) የምስክርነት ቃል የሚሰጥበት ሰዓት፣ ቀንና ዓመተ ምኅረት እንዲሁም ቦታ፤
   (ሐ) የምስክርነት ቃል እንዲሰጥበት የተፈለገበት የወንጀል ጉዳይ፤
   (መ) በሕግ የተመለከተ የምስክር መብትን እና ሌሎች ዝርዝሮችን ፤
   የሚይዝ ሆኖ እንደአመቺነቱ በአካል፣ በኢሜይል፣ በፋክስ፣ በስልክ፣ በስልክ አጭር መልዕክት ወይም በሌላ ማናቸውም ዘዴ ሊላክ ይችላል፡፡
3. የመጥሪያ አደራረስ፣ ቅድም ተከተልን በተመለከተ በዚህ ሕግ ምዕራፍ ስምንት ንዑስ ክፍል አንድ ስለ መጥራት በአንቀጽ 297 ንዑስ አንቀጽ 3-10 የተደነገገው እንደነገሩ ሁኔታ ተፈጻሚነት ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ መሠረት መጥሪያ የደረሰው ምስክር ደርሶት ያልቀረበ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ተይዞ ቃሉን እንዲሰጥ ወይም ሌላ ሕጋዊ ርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 106 ምርመራ ስለሚደረግበት ሁኔታ

1. ምስክር በምርመራ ክፍል በመሆን የምስክርነት ቃሉን ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በሕመም፣ በዕድሜ ወይም በሌላ አስገዳጅ ምክንያት በምርመራ ክፍል የምስክሩን ቃል መቀበል የማይቻል እንደሆነ ምስክሩ በሚገኝበት ወይም አመቺ በሆነ ቦታ እና ታዛቢ ባለበት የምስክርነት ቃሉን መቀበል ይቻላል፡፡
3. የምስክርነት ቃል አቀባበሉ፡-
   (ሀ) ከመርማሪ ለሚቀርብ ጥያቄ እንደ አግባቡ በቃል ወይም በምልክት ምላሽ በመስጠት፣
   (ለ) ምስክሩ መናገር ወይም መስማት የተሳነው እና በምልክት ምላሽ ለመስጠት የማይችል እንደሆነ በምርመራ ጊዜ ለሚቀርብለት ጥያቄ በጽሑፍ ወይም በሌላ ሁኔታ ምላሽ በመስጠት፣
   (ሐ) እንደ አስፈላጊነቱ ሒደቱን በምስል ወይም በድምፅ በመቅረጽ፣
   (መ) አስፈላጊ እንደሆነ ታዛቢዎች ሒደቱን እንዲከታተሉ በማድረግ፣
   (ሠ) ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የምስክር ምላሽ ብቻ በምስክርነት ቃል በመመዝገብ፣
   (ረ) የተመዘገበን የምስክርነት ቃል በማንበብ በታዛቢዎች እና በምስክሩ በየገፁ እንዲፈረም በማድረግ

   ይከናወናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ሐ) መሠረት ምስክሩ ቃሉን ከሰጠ የምስክርነት ቃል መስጠት ሲጀመርና ሲጠናቀቅ ስለሒደቱ የምስክሩ ማንነት፣ አድራሻና ቃሉን በፈቃደኝነት ስለመስጠቱ ተገልፆ መቀረጽ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ረ) መሠረት ምስክሩ ለመፈረም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ይኸው ይመዘገባል፤ ምስክሩ ያለመፈረሙ በምርመራ መዝገቡ የተመዘገበውን የምስክርነት ቃል አስረጅነት አይቀንሰውም፡፡

## አንቀጽ 107 ስለመርማሪ ግዴታ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 31 የተደነገገው እንደተበቀ ሆኖ፡-

(1) ምስክሩ ምርመራው የሚከናወንበትን የሥራ ቋንቋ መረዳት የማይችል እንደሆነ ወይም መስማት ወይም መናገር የተሳነው እንደሆነ መርማሪ አካል በመንግሥት ወጭ አስተርጓሚ ይመድብለታል፡፡

(2) መርማሪው ምስክሩ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት የሚሰጠው የምስክርነት ቃል በወንጀል የሚያስከስሰው እንደሆነ ሊመሰክር እንደማይገደድ እና በዚህ ሕግ አንቀጽ 34 ስለ ምስክር መብትና ኃላፊነት የተደነገጉትን ለምስክሩ በግልጽ መንገር አለበት፡፡

(3) የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተፈፀመበት ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰ በተለይም በወንጀል ድርጊት ተጎጂ የሆነ ሰው የምስክርነት ቃሉን በተለየ ሥርዐት ሞግዚቱ ወይም አሳዳሪው እና የማኅበራዊና የሥነ ልቦና ምክርና ድጋፍ የሚሰጥ ባለሙያ ባለበት ለመስጠት እንዲችል መርማሪ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት፡፡

(4) መርማሪ ምስክሩ የምስክርነት ቃሉን ተገዶ ወይም በተጽዕኖ ሥር ሆኖ እንዲሰጥ የኃይል ተግባር መፈጸም፣ ማስፈራራት፣ መደለል፣ እንዲደለል ማድረግ ወይም ማንኛውንም በሕግ የተከለከለ ተግባር መፈጸም የለበትም፡፡

(5) ለምስክሮችና ጠቋሚዎች በሕግ በተደነገገው መሠረት የሚሰጠው ጥበቃ እንደተጠበቀ ሆኖ መርማሪ ምስክሩ በሚሰጠው የምስክርነት ቃል ጥቃት ይደርስበታል የሚል በቂ መረጃ ካለው ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

(6) በአንድ ላይ የምስክርነት ቃል መስጠት አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ምስክርነት በተናጠል መሰጠት አለበት፡፡ ምስክሮች ከአንድ በላይ የሆኑ እንደሆነ መርማሪ ምስክሮች የሚሰጡትን የምስክርነት ቃል በተናጠል መመዝገብ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 108 በሐሰተኛ ምስክር ላይ ስለሚወሰድ ርምጃ</u>**

ዐቃቤ ሕግ በዚህ ሕግ የምስክርነት ቃሉን ለመርማሪ የሰጠ ምስክር በወንጀል የፍርድ ሒደት በምርመራ ጊዜ የሰጠውን የምስክርነት ቃሉን በመለወጥ ሐሰተኛ ምስክርነት የሰጠ መሆኑን ሲያረጋግጥ ምሥክሩ ያለፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ እንዲያዝና ፍርድ ቤት በቀጥታ እንዲቀርብ ወይም ሐሰተኛ ምስክርነት በመስጠት ወንጀል ምርመራ እንዲጣራበት ሊወስን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 109 ብርበራና ዕቃን ስለመያዝ</u>**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 111 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ያለፍርድ ቤት የብርበራና የማያዣ ትእዛዝ በሰው አካል፣ ቤት ወይም ቦታ ላይ ብርበራ ወይም ፍተሻ ማድረግ ወይም ዕቃ መያዝ አይቻልም፡፡

2. የብርበራ ማዘዣ በማንኛውም ፍርድ ቤት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ ለፍትሕ ዓዓላማ ወይም ለማናቸውም ምርመራ፣ ለክሱ መሰማት ወይም በሕጉ መሠረት ለሌላ የክስ ሥነ ሥርዐት የማዘዣው መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ካልተረዳው በቀር የብርበራ ማዘዣ መስጠት የለበትም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት  የቀረበው የብርበራ ማዘዣ ጥያቄ ውድቅ ከተደረገ መርማሪ ለፍርድ ቤቱ ፕሬዘዳንት አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፤ ፕሬዘዳንቱም ጥያቄው በቀረበ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፤ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

4. ማናቸውም የብርበራ ማዘዣ የሚበረበረውን ቦታ ወይም የሚያዘውን ዕቃ ማመልከት አለበት፡፡ በዚህ ሕግ አንቀጽ 93 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማዘዣው ውስጥ ከተመለከተው በቀር መርማሪው ሌላውን ዕቃ መያዝ የለበትም፡፡

## አንቀጽ 110   ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ብርበራ ስለሚደረግበት ወይም ዕቃ ስለሚያዝበት ሁኔታ

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 95 የተደነገገው ቢኖርም ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ቤትን ወይም የአንድን ሰው የተከለለ ንብረት ወይም ቦታ መበርበር ወይም መፈተሽ የሚቻለው፣

   (ሀ) በፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ የወጣበትን ለመያዝ፣

   (ለ) ተጠርጣሪውን እጅ ከፍንጅ ለመያዝ ክትትል እየተደረገ እቤት ውስጥ ሲገባ ወይም ወንጀል የሠራበትን ነገር ቤት ውስጥ ያስቀመጠ ሲሆን፣

   (ሐ) ለወንጀል ማስረጃ የሚሆን ኤግዚቢትን ወይም ፈለግን የማጥፋት ወይም የማበላሸት እንቅስቃሴን ለማስወገድ፣

   (መ) እንዲያዝ የሚፈለገው ተጠርጣሪ፣ የወንጀል ድርጊት የተፈጸመበት ወይም በማስረጃነት የሚፈለግ ወይም የሚወረስ ዕቃ በመኖሪያ ቤት ወይም ቦታ ውስጥ የተቀመጠ መሆኑን በበቂ ሁኔታ ሲታመንና ከፍርድ ቤት የብርበራ መያዣ ትእዛዝ እስኪመጣ ድረስ ተጠርጣሪው ወይም ዕቃው ይጠፋል ወይም አደጋ ይከሰታል ተብሎ በበቂ ሁኔታ ሲታመን፣

   (ሠ) ለአደጋ የተጋለጠ ሰውን ወይም ንብረትን ለማዳን፣  ወይም

   (ረ) በጦር መሣሪያ በራሱ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ለማድረስ በዝግጅት ላይ ያለን ሰው ለማስቆም ወይም ለመያዝ፤

   አስፈላጊ ሲሆን ነው፡፡

2. በዚህ ሕግ ለብርበራ፣ ለፍተሻ እንዲሁም ዕቃን መያዝ ለሚመለከቱ ድንጋጌዎች አፈጻጸም "ቦታ" ማለት ቤት፣ ተሽከርካሪ፣ አውሮፕላንን፣ መርከብ፣ እና ሌላ ማንኛውንም ዕቃ ማስቀመጫ ነገርንና ሥፍራን ያካትታል፡፡

**<u>አንቀጽ 111 የተያዘን ሰው ስለመፈተሽ</u>**

የተያዘ ሰው የሚፈተሸው ከተያዘው ሰው ጋር ተመሳሳይ ፆታ ባለው ሰው ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 112 ስለብርበራና የመያዝ ሒደት አፈጻጸም</u>**

1. ብርበራው በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚፈጸም እንደሆነ መርማሪ የብርበራውን ትእዛዝ ለቤቱ ነዋሪ ወይም ለባለመብቱ ማሳየትና ማንበብ ይኖርበታል፡፡
2. መርማሪው ብርበራ የሚያደርግበት ቤት ወይም ቦታ ዝግ እንደሆነና ነዋሪው ወይም ባለመብቱ በአካባቢው ከሌለ ወይም ለመክፈት ፈቃደኛ ካልሆነ እና ብርበራውን ለማድረግ ሌላ አማራጭ ዘዴ ከሌለ ተመጣጣኝ ኃይል በመጠቀም ቤቱን ወይም ቦታውን በኃይል በመክፈት ወይም ሌላ ተገቢ ርምጃ በመውሰድ መግባት ይችላል፡፡
3. በፍርድ ቤት በተለየ ሁኔታ ካልታዘዘ በስተቀር ብርበራ የሚደረገው ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡ ሆኖም ጉዳዩ ከባድ ወንጀል መፈጸሙን የሚመለከት እና መደበኛውን የብርበራ ሰዓት መከተል ማስረጃውን የሚያጠፋ እንደሆነ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ በማንኛውም ሰዓት ብርበራ ማካሔድ ይቻላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው መሠረት ከመደበኛው የብርበራ ሰዓት ውጭ ስለተደረገው ብርበራ፣ በብርበራው ስለተገኘ ማስረጃና ስለተያዘ ዕቃ መርማሪው በሚቀጥለው ቀን አቅራቢያው ላለ ፍርድ ቤት ያሳውቃል፡፡ ፍርድ ቤቱ በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት ተገቢውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
5. የተያዘውን ዕቃ ዝርዝር ለመጻፍ እና ምስክሮች እንዲገኙ ለማድረግ የማይቻል ካልሆነ ወይም ብርበራውን ሊያዘገይ የሚችል አሳማኝ ምክንያት ከሌለ በስተቀር መርማሪው ከሁለት ያላነሱ ምስክሮች የማስረጃው ወይም የዕቃው ዝርዝር ትክክል መሆኑን እንዲያረጋግጡና እንዲፈርሙበት ያደርጋል፡፡ የሚቻል እንደሆነ የብርበራው ሒደት በምስልና በድምፅ ተቀርፆ መቀመጥ አለበት፡፡
6. የተያዘው ዕቃ ዝርዝር ተመዝግቦ ባለመብቱ እንዲፈርምበት እና ደረሰኝ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ ባለመብቱ ለመፈረም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ወይም ከሌለ ይኸው እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

7. መርማሪ በብርበራ ከተገኙ ዕቃዎች ውስጥ የሚፈለጉትን ወይም የማስረጃነት ዋጋ ያላቸውን በመለየት ይይዛል፣ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፡፡ መርማሪው ለማስረጃነት የማያገለግል ዕቃን ዕቃው ለተወሰደበት ሰው በማስፈረም ተመላሽ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 113 በመንግሥት ወይም ሕጋዊ ሰውነት ባለው ተቋም ላይ የሚደረግ ብርበራ

መርማሪ የመንግሥት ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ላይ በሚደረግ ብርበራ የተቋሙ ኃላፊ ወይም ተወካይ እንዲገኝ ማድረግ አለበት፡፡

## አንቀጽ 114 በብርበራ የተያዘ ዕቃን ማሸግና ባለበት መጠበቅ

ብርበራውን የሚያከናውነው መርማሪ፡-

(1) በብርበራ የሚፈለገው ዕቃ ወይም የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ በሌላ ዕቃ ወይም መሣሪያ ውስጥ በቀላሉ ሊገኝ በማይችል ሁኔታ የተቀመጠ መሆኑን ሲያረጋግጥ በተመጣጣኝ ኃይል ዕቃውን በመስበር ወይም ከነመያዣ ዕቃው አሽጎ ሊወስድ ወይም ባለበት ሁኔታ ጥበቃ እንዲደረግለት ሊወስን ይችላል፡፡

(2) የዕቃ መጠን ከፍተኛ እንደሆነ ወይም ብርበራውን ማጠናቀቅ የቤቱን ወይም የቦታውን ነዋሪ ወይም ባለቤት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚያውክ እንደሆነ በፍርድ ቤት ፈቃድ ዕቃውን ወደ ሌላ ቦታ አዛውሮ ብርበራው ማከናወን ይችላል፡፡

(3) የሚያዘው ዕቃ ከሌላ ዕቃ ጋር የተጣበቀ ወይም የተቀላቀለ በመሆኑ መለያየቱ በንብረቱ ወይም በሰው ላይ አደጋ የሚያስከትል እንደሆነ በፍርድ ቤት ፈቃድ ዕቃው ባለበት ሁኔታ በጥበቃ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

(4) በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 349-355 ስለኤሌክትሮኒክስ ማስረጃ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኤሌክትሮኒክ ማስረጃን እንደ አመቺነቱ ወደ ሰነድ በመለወጥ፣ ከነመያዣው በመውሰድ ወይም በሌላ መሣሪያ እንዲዛወር በማድረግ መያዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 115 ሌሎች ዕቃዎች

1. መርማሪ በዚህ ሕግ መሠረት በተደረገ ብርበራ እንዲያዝ ከተፈለገው ዕቃ ውጭ ወንጀሉን ወይም ሌላ ወንጀል መፈጸሙን ወይም ከወንጀል ድርጊት የተገኘን የወንጀል ፍሬ መሆኑን ለማስረዳት የሚችል ሌላ ዕቃ ያገኘ እንደሆነ የዕቃውን ዐይነት በብርበራ በተገኘ ማስረጃ ወይም ዕቃ ዝርዝር ሰነድ ላይ በመመዝገብ እና እንዳስፈላጊነቱ ዕቃውን በመያዝ፣ ጥበቃ እንዲደረግ ወይም ሌላ ተገቢውን

ርምጃ በመውሰድ ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡ ፍርድ ቤቱ በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት ተገቢውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተያዘው ዕቃ ወንጀል ስለመፈጸሙ የማያመለክት እንደሆነ  በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ወዲያውኑ ዕቃው ለተወሰደበት ሰው መመለስ አለበት፡፡

## አንቀጽ 116   የኤግዚቢት አያያዝና አቀማመጥ

1. በወንጀል ምክንያት የተያዘ ኢግዚቢት በወንጀል ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በኢግዚቢትነት የተያዘው ዕቃ ወይም ንብረት ወይም ነገር በመርማሪ እጅ የሚቆይ ይሆናል፡፡ ኤግዚቢቱም በመርማሪው አካል ቁጥርና ምልክት ተደርጎበት በተጠበቀ ቦታ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡
2. ከአቅም በላይ ወይም በቂ በሆነ ምክንያት የደረሰ ውድመት ወይም ጉዳት ወይም መጥፋት ካልሆነ በስተቀር በኤግዚቢቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት መርማሪው ኃላፊነቱን ይወስዳል፡፡
3. ስለ ኤግዚቢት አያያዝ፣ አስተዳደርና አወሳሰን በተመለከተ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መመሪያ ያወጣል፡፡

## አንቀጽ 117   በተያዘ ዕቃ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ

1. ስለ ንብረት አወራረስ በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በብርበራ የተያዘ ኤግዚቢት፤
   (ሀ) በሕግ በግለሰብ እጅ እንዳይያዙ የተከለከሉ እንደ የጦር መሣሪያ፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ ሜርኩሪ፣ የዝሆን ጥርስ የመሳሰሉ መሆኑ ሲረጋገጥ ለማስረጃ የሚሆን ናሙና ወይም የፎቶ ግራፍ ምስል በመውሰድ ይወረሳል፤ ንብረቱም ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ወይም ተቋም ገቢ ይደርጋል፡፡
   (ለ) ልዩ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው  እንደ ወርቅ፣ የወጭ ቡና፣ የውጭ ሃገር ገንዘብ የመሳሰሉ መሆኑ ሲረጋገጥ ለማስረጃ የሚሆን ናሙና ወይም የፎቶ ግራፍ ምስል በመውሰድ እንዲቀመጥ ወይም በመንግሥት የሽያጭ ሥርዐት መሠረት ተሸጦ ገንዘቡ ተቀማጭ ይደረጋል፡፡
2. በኤግዚቢትነት የተያዘው ዕቃ የሚበላሽ፣ አያያዙ አስቸጋሪ ወይም  ከፍተኛ ወጭን የሚያስከትል እንደሆነ ናሙና በመውሰድ ወይም በሌላ ማናቸውም

መንገድ ምትክ ማስረጃ እንዲኖር በማድረግ ዕቃውን በገበያ ዋጋ መሸጥና ገንዘቡ በመንግሥት ባንክ ተቀማጭ እንዲደረግ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

3. በኤግዚቢትነት የተያዘው የቤት እንስሳ እንደሆነ ምስሉን በፎቶግራፍ ወይም በቪዲዬ በመቅረጽ እንደነገሩ ሁኔታ ለባለቤቱ ወዲያውኑ ይመለሳል ወይም ባለቤቱ እንስሳው ከተያዘ እስከ አራተኛው ቀን ድረስ ካልቀረበ በሕግ መሠረት ተሸጦ ገንዘቡ በመንግሥት ባንክ ይቀመጣል፤ ሆኖም ባለቤቱ በማንኛውም ዘዴ እንዲያውቀው ተደርጎ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በራሱ ወይም በወኪሉ በኩል የሽያጭ ገንዘቡን ካልተረከበ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

4. በኤግዚቢትነት የተያዘ ዕቃ ክሱን ለማስረዳት በማስረጃነት የማያገለግል ወይም የማያስፈልግ፣ በሕግ መሠረት ሊወረስ የማይችል ወይም በወንጀል ፍሬነት የተያዘ ሆኖ ለባለቤቱ ሊመለስ የሚችል መሆኑን ዐቃቤ ሕግ ሲረዳ ወዲያውኑ ዕቃው ለተወሰደበት ሰው እንዲመለስ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኤግዚቢትነት በተያዘ ዕቃ ላይ የባለቤትነት ወይም የባለይዞታነት ጥያቄ ከተነሳ ዐቃቤ ሕግ ዕቃው በተያዘበት ጊዜ የዕቃው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ለነበረ ሰው እንዲመለስ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

6. ኤግዚቢቱ በተያዘበት ጊዜ ትክክለኛ ባለቤቱ ወይም ባለይዞታው ማን እንደሆነ ማወቅ የማይቻል እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ የፍትሐብሔር መፍትሔ እንዲያገኝ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ያቀርባል፡

7. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 98 መሠረት በወንጀል ፍሬነት የተያዘና ለባለቤቱ ሊመለስ የሚችል ዕቃ ለባለቤቱ በማንኛውም ዘዴ እንዲያውቀው ተደርጎ በስድስት ወራት ውስጥ የይመለስልኝ ጥያቄ ካልቀረበበት ለመንግሥት ገቢ እንዲደረግ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

8. በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ወንጀሉን ለመፈጸም እንደ መሣሪያ ሆኖ ያገለገለ ተሽከርካሪን በፎቶግራፍና በምስል በመቅረጽ ንብረቱ በሕግ መሠረት ሊወረስ የማይችል እንደሆነ ባለቤቱ በሕግ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲከፍል እና በበቂ ዋስትና እንዲለቀቅ አቃግ ሕግ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

9. ለባለቤቱ እንዲመለስ ውሳኔ በተሰጠበት ኤግዚቢት ላይ ባለቤቱ በማንኛውም ዘዴ እንዲያውቀው ተደርጎ ውሳኔው በተሰጠ በሁለት ወራት ውስጥ በራሱ ወይም በወኪሉ በኩል ንብረቱን ካልተረከበ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ዐቃቤ ሕግ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተያዘው ኤግዚቢት የወንጀል ክሱን የሚያስረዳ እንደሆነ እና ዐቃቤ ሕግ ክስ መሥርቶ ማስረጃውን ለፍርድ ቤት ካቀረበ ፍርድ ቤቱ በተያዘው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ በቀረበው ኤግዚቢት ላይም ውሳኔ ይሰጣል፡፡

11. መርማሪ ከኤግዚቢት ጋር በተያያዘ ለሚቀርብ ጥያቄ የጽሑፍ ማስረጃ ይሰጣል፤ ማስረጃውም ኤግዚቢቱ የተያዘበትን ጊዜ፣ ያለበትን ሁኔታ እና የመሳሰሉ ዝርዝር መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

## አንቀጽ 118 በሌላ ሰው እጅ የሚገኝ ማስረጃ

1. በምርመራ ላይ ባለው የወንጀል ጉዳይ ላይ በማስረጃነት የሚያገለግል ማስረጃ ተጠርጣሪ ባልሆነ ሰው እጅ የሚገኝ መሆኑን መርማሪ ሲያረጋግጥ ባለይዞታው እንዲያስረክብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. መርማሪ ባለይዞታው ማስረጃውን በፈቃደኝነት ካስረከበ ደረሰኝ በመስጠት እንደ ሁኔታው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ተይዞ እንዲቆይ ወይም በማናቸውም መንገድ ተለዋጭ ማስረጃ ማለትም በቅጂ፣ በቪዲዮ፣ በፎቶግራፍ ወይም መሰል ዘዴዎች በመጠቀም እንዲደራጅ በማድረግና ለዐቃቤ ሕግ በማሳወቅ ለባለይዞታው እንዲመለስ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. የማስረጃው ባለይዞታ ማስረጃውን ለማስረከብ ፈቃደኛ ካልሆነ መርማሪ ማስረጃው እንዲሰጠው እንዲታዘዝለት ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ በማስረጃነት የተጠየቀን ዕቃ ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ግምት ውስጥ በማስገባት ለመርማሪ እንዲሰጥ ሊያዝ ይችላል፤ በማስረጃው አያያዝና አመላለስ ላይ ሊወስን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 119 በመንግሥት ተቋም የሚገኝ ማስረጃ

1. በምርመራ ላይ ባለው የወንጀል ጉዳይ በማስረጃነት የሚፈለግ ዕቃ በመንግሥት ተቋም የሚገኝ ወይም የሚመነጭ መሆኑን መርማሪ ሲያረጋግጥ ተቋሙ ዕቃውን እንዲያስረክብ ወይም ማስረጃ እንዲሰጥ በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ የተጠየቀን ማስረጃ ያዘገየ ወይም ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ የተቋሙ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ኃላፊነት አለበት፡፡
3. ከአንድ በላይ በሆኑ የመንግሥት ተቋም ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች የሚሰጥ ማስረጃ የተለያየ እንደሆነ መርማሪው የተቋሙን አቋም የሚገልጽ ማስረጃ እንዲሰጠው በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በሌላ ሕግ የተደነገጉ ክልከላዎች እንደተጠበቀ ናቸው፡፡
5. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የመንግሥት ተቋም" ማለት በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚተዳደር ተቋም ሲሆን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፡፡

**አንቀጽ 120 <u>በፋይናንስ ተቋም የሚገኝ መስረጃ</u>**

1. ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ የባንክ ሂሳብ ወይም የገንዘብ እንቅስቃሴ በማስረጃነት እንዲቀርብ ፍርድ ቤት ሊያዝ ይችላል፡፡
2. በዚህ ሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በሠንጠረዥ ------ በተመለከቱ ወንጀሎች (በመካከለኛ ወይም በከባድ ወንጀል) የተጠረጠረን ሰው የባንክ ሂሳብ ወይም የገንዘብ እንቅስቃሴ፤
    (ሀ) መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ የተጠርጣሪውን የባንክ ሂሳብ ወይም የገንዘብ እንቅስቃሴ እንዲመለከት፣ ወይም
    (ለ) ባንኩ ወይም የገንዘብ ተቋሙ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያለውን ማንኛውንም መረጃ ወይም ማስረጃ እንዲሰጥ

    ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚሰጥ ትእዛዝ፡-
    (ሀ) የተጠርጣሪን ሙሉ ስምና አድራሻ፤
    (ለ) ተጠርጣሪው ፈጸመ የተባለው የወንጀል ድርጊት፤
    (ሐ) ከባንኩ የሚፈለግ ማስረጃ ወይም መረጃ፤
    (መ) ትዕዛዙን ፈጽመውየሚያስፈጽመው መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ ስም፤

መያዝ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 121 የተጠርጣሪነት ቃል</u>**

1. በዚህ ሕግ መሠረት ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ እንዲቀርብ የተጠራ ወይም ተይዞ የቀረበ ሰው ስሙ፣ ፆታው፣ ዕድሜው፣ ዜግነቱ እና አድራሻው ተረጋግጠ ለቀረበበት ክስ ወይም የክስ አቤቱታ ቃሉን እንዲሰጥ ይጠየቃል፡፡
2. ቃሉን የሚቀበለው መርማሪ ተጠርጣሪው ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ምላሽ ለመስጠት ነጻ እንደሆነና ላለመናገር መብት እንዳለው፣ በፈቃደኝነት

የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መንገር አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተጠርጣሪው ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ የተደነገገው ቢኖርም ተጠርጣሪው ስሙን፣ ጾታውን፣ ዕድሜውን፣ ዜግነቱንና አድራሻውን እንዲገልጽ ለሚቀርብለት ጥያቄ ትክክለኛውን ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
4. ተጠርጣሪው ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኛ እንደሆነ ከመርማሪ ለሚቀርብለት ጥያቄ እንደአግባቡ በቃል ወይም በምልክት ምላሽ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪው መናገር ወይም መስማት የተሳነው እንደሆነ እና በምልክት ምላሽ ለመስጠት የማይችል እንደሆነ በምርመራ ጊዜ ለሚቀርብለት ጥያቄ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት ይችላል፡፡
5. ተጠርጣሪው ለሚቀርብለት ጥያቄ ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ እንደ ወንጀሉ ክብደትና የማስረጃው አስፈላጊነት ሒደቱ በምስል ወይም በድምፅ ሊቀረፅ ይችላል፡፡
6. ተጠርጣሪው ምርመራ የሚከናወንበትን ቋንቋ በትክክል የማይረዳው እንደሆነ አስተርጓሚ በመንግሥት ወጭ ይመደብለታል፤ አስተርጓሚውም የተጠየቀውንና የሰጠውን ምላሽ ትክክል መሆኑን ያረጋግጥለታል፡፡
7. መርማሪ ተጠርጣሪው የሰጠውን የተከሳሽነት ቃል ብቻ ይመዘግባል፤ ይህንኑም በእርሱና በተጠርጣሪው እንዲፈረም ያደርጋል፤ ተጠርጣሪው ለመፈረም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ይኸው በመዝገብ ላይ ያሰፍራል፡፡
8. ተጠርጣሪው ቃሉን በማቆያ ቤት የምርመራ ክፍል ወይም በመርማሪው በተወሰነ ቦታ ይሰጣል፡፡ ቃሉን ሲሰጥ ከተጠርጣሪ፣ መርማሪውና ሒደቱን ከሚከታተሉ ሁለት ምስክሮች በስተቀር ሌላ ሰው በቦታው መገኘት የለበትም፡፡

## <u>አንቀጽ 122 ናሙና መውሰድ</u>

1. በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ናሙና መውሰድ ለምርመራ አስፈላጊ እንደሆነ መርማሪው ከተጠርጣሪው ወይም ከተከሳሹ የእጅ ጽሑፍ፣ የጣት አሻራ፣ ፎቶግራፍን፣ የፀጉር፣ የድምፅ፣ የሽንት፣ የደም፣ የምራቅ እና ሌላ በሰውነቱ የሚገኝ ፈሳሽ ናሙና የማከም ፈቃድ ያለው ሐኪም እንዲወስድ፣ ምርመራውን እንዲያደርግና ውጤቱንም በጽሑፍ እንዲያስታውቅ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ምርመራው እንዲደረግ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2. ተጎጂው የወንጀል ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ የህክምና ምርመራ የሚያስፈልገው እንደሆነ መርማሪ በተጎጂው ወይም ተጎጂው በሕግ ችሎታ የሌለው እንደሆነ በሞግዚቱ ወይም በአሳዳሪው ፈቃድ ለማከም ፈቃድ ባለው ሐኪም እንዲመረመር ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤ ሐኪሙም የምርመራውን ውጤት በጽሑፍ ማቅረብ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ተጠርጣሪው ከሰውነቱ በቀጥታ የማይወሰዱ እንደ ፎቶግራፍ፣ አሻራ፣ የእጅ ጽሑፍ ወይም መሰል ናሙናዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ተገዶ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ተጠርጣሪው ከሰውነቱ በቀጥታ የሚወሰድ እንደ ደም፣ ሽንት፣ ፀጉር ወዘተ እንደሆነ ናሙና ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ በመርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ ጠያቂነት ናሙናውን እንዲሰጥ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤ በፍርድ ቤት የተሰጠን ትእዛዝ ተጠርጣሪው ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆነ የተጠረጠረበት ወይም በናሙናው ሊረጋገጥ የተፈለገው ነገር እንዳለበት ወይም የራሱ እንደሆነ ግምት ይወሰዳል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተወሰደ ናሙና፡-
   (ሀ) ክስ ለመመሥረት ወይም ወንጀሉን ለማስረዳት አስፈላጊ ባልሆነ ጊዜ በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ፣ ወይም
   (ለ) ክሱ ፍርድ ቤት ቀርቦ ውሳኔ ካገኘ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ
   እንደነገሩ ሁኔታ እንዲወገድ ወይም እንዲወድም ሊደረግ ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ 123 መርቶ ማሳየት ወይም ማውጣት</u>

1. መርማሪ ተጠርጣሪው በራሱ ፈቃደኝነት የተጠረጠረበትን የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም እንዲያሳይ ወይም ማስረጃንና ፈለግን ወይም የወንጀል ፍሬዎችን መርቶ እንዲያወጣ ወይም እንዲያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ተጠርጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወንጀል ድርጊቱን አፈጻጸም፣ ማስረጃ፣ ፈለግና የወንጀል ፍሬን መርቶ እንዲያወጣ ሲደርግ መርማሪው መርማሪ ያልሆኑ ሁለት ምስክሮች ሒደቱን እንዲከታተሉና እንደሁኔታው በድምፅና በምስል እንዲቀረጽ ማድረግ አለበት፡፡

**አንቀጽ 124 በፍርድ ቤት የሚሰጥ የእምነት ቃል**

1. የቀዳሚ ምርመራ ፍርድ ቤት ሥነ ሥርዐት ወይም የወንጀሉ ክስ መስማት ከመጀመሩ በፊት ማናቸውም ፍርድ ቤት ማንኛውንም የተሰጠውን ቃል ወይም የእምነት ቃል ለመመዝገብ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቃል የሰጠውን ሰው በነፃ ፈቃዱ ቃሉን መስጠቱን መጠየቅ፣ ማረጋገጥና በመዝገብ መመዝገብ አለበት፡፡ ሳይጠይቅና ሳያረጋግጥ መመዝገብ የለበትም፤ ይኸውም በመዝገቡ እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ የተሰጠውን ማንኛውም ቃል ወይም የእምነት ቃል ሳያጓድል በጽሑፍ፣ በመቅረጸ ድምፅ፣ በቪዲዮ ወይም በሌላ ማንኛውም አመቺ በሆነ ዘዴ ይመዘግባል፤ የተመዘገበው ቃል ወይም የእምነት ቃል ቃሉን ለሰጠው ሰው ከተነበበለት ወይም ከተገለጸለት በኋላ እንዲፈርም ወይም ይህንኑ እንዲያረጋግጥ ይደረጋል፡፡ ዳኛውም እንዲፈርምበት ወይም ይህንኑ እንዲያረጋግጥ ይደረጋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተጠርጣሪው ጥፋተኛነቱን ካመነ እና ዐቃቤ ሕግ የጥፋተኛነት ውሳኔ እንዲሰጥበት ከጠየቀ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የተጠርጣሪውን አስተያየት በመጠየቅ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ክሱ ለተጠርጣሪው በጽሑፍ እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡
5. ክሱን ለመስማት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ሌላ እንደሆነ ለዚሁ ፍርድ ቤት እና ለዐቃቤ ሕግ የመዝገቡን ግልባጭ መላክ አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት
## ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ማስረጃን ማሰባሰብ

**አንቀጽ 125 ዓላማ**

ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ የሚደረግ ማስረጃ የማሰባሰብ ሒደት ዋና ዓላማ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ በመገኘት የፎረንሲክ፣ ቴክኒካልና አካላዊ ማስረጃ እንዳይባክን፣ ማስረጃው ተደብቋል ተብሎ ከተገመተ ሥፍራ ለማግኘት ወይም ከወንጀል ጉዳዩ ጋር በተያያዘ ጠቃሚ የሆኑ ሌላ ማስረጃን ለማሰባሰብ ነው፡፡

**አንቀጽ 126 ወንጀል በተፈጸመበት ሥፍራ መገኘት**

1. መርማሪ በዚህ ሕግ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ክስ ወይም ጥቆማ ሲቀርብለት ወይም ምርመራ ለማካሔድ ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ መገኘትና

ማስረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ወንጀሉ በተፈጸመበት ሥፍራ በአፋጣኝ መድረስ አለበት፡፡

2. መርማሪ ወንጀል በተፈጸመበት ሥፍራ እንደደረሰ፡-

(ሀ) በቦታው የወንጀል ተጎጂ ወይም የሞተ ሰው መኖሩን ያረጋግጣል፤ የወንጀል ተጎጂ ወይም የሞተ ሰው ካለ እንዳስፈላጊነቱ ተገቢው የህክምና ርዳት እንዲያገኝ ወይም መርመራ እንዲካሔድበት ወደ ህክምና ተቋም እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

(ለ) ማስረጃ እንዳይባክን ወይም እንዳይጠፋ ሥፍራውን መከለልና ጥበቃ ማድረግ፣

(ሐ) ማስረጃዎችን መለየት፣ ማሰብሰብ፣ መመዝገብ፣ ማቀብ እና

ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ማከናወን ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 127 የወንጀል ሥፍራን መመርመርና ማስረጃ ማሰባሰብ**

1. የወንጀል ሥፍራ ምርመራ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ወይም ማስረጃ በተገኘበት ቦታ ላይ የሚካሔድ ሲሆን የወንጀል ፈለግን፣ የሞተ የሰው አካል ማውጣትን፣ አስፈላጊ የሆነ መረጃ አለበት ተብሎ የሚገመት ቦታን፣ ዕቃን እና ሌላ ሰነድ በመፈተሽን ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

2. ወንጀል የተፈጸመበት ሥፍራ ምርመራው እስኪጠናቀቅ ድረስ ተከልሎ እንዲቆይ ይደረጋል፤ ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ ቦታውን ከልሎ ማቆየት አስፈላጊ መሆኑ ከታመነ ከሰባት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ቦታው እንዲከለል ሊደረግ ይችላል፡፡

3. ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ የተሰበሰበ ማስረጃ በየዐይነቱ እንዲመዘገብ፣ ለየብቻ ተጠብቆ እንዲቆይ፣ ለእያዳንዱ ማስረጃ ዝርዝር መግለጫ እንዲዘጋጅለት እና ታሽጎ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ሒደቱ እንዳስፈላጊነቱ በቪዲዮ እንዲቀረፅ ሊደረግ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ማስረጃዎችን ጠብቆ ያቆየ መርማሪ በእያዳንዱ ማስረጃ ዝርዝር ላይ ፊርማውንና ማስረጃው የተሰበሰበበትን ቀን በአግባቡ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

5. ወንጀሉ በተፈጸመበት ሥፍራ የሚደረገው የማስረጃ ማሰባሰብ ሒደት ወይም በወንጀል ሥፍራው የተገኙ ማስረጃዎች ከከባባዊ ሁኔታ የሚደረገው ትንተና ከአንድ ቀን በላይ የሚፈጅ እንደሆነ ምርመራው ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ይከናወናል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተደነገገው ቢኖርም ወንጀሉ በተፈጸበመት ቦታ ማስረጃውን ማሳባሰብ ወይም መተንተን በማስረጃው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሳድር እንደሆነ ምርመራው ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ይከናወናል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው ቢኖርም ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ማስረጃ ማሰባሰብ ወይም መተንተን በማስረጃው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ ማረጃውን መሰብሰብ ወይም መተንተን የሚቻል መሆኑ ከታመነ ምርመራው ከወንጀል ሥፍራ ውጭ ተገቢ በሆነ ሌላ ቦታ ሊካሔድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 128** __የሞተ ሰው አካልን መመርመር__

1. መርማሪ በተፈጸመ ወንጀል የሞተ ሰው ሲኖር ወይም አካሉ የተደበቀ ወይም የተቀበረ ወይም በሌላ ሁኔታ የተበላሸ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ በጥንቃቄ እንዲነሳ ወይም እንዲወጣ እና አስፈላጊ የሆነ ባለሙያ በምርመራው ሒደት እንዲሳተፉ ማድረግ አለበት፡፡

2. መርማሪ በሞተ ሰው አካል ላይ የሚገኙ የአሻራ ምልክቶችን ወይም ለፎረንሲክና ቴክኒካል ምርመራ የሚደረጉ ሌሎች ናሙናዎችን መውሰድ ወይም እንዲወሰድ ማድረግ አለበት፤ አስፈላጊው ትንተናም ወዲያውኑ ይካሔዳልመካሔድ አለበት፡፡

3. ማንነቱ ያልታወቀ የሞተ ሰው አካልን ዐቃቤ ሕግን በማሳወቅ የቀብር ሥነ ሥርዐቱ እንዲፈጸም ወይም ሌላ ርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፤ የቀብር ሥነ ሥርዐቱም በፍትሐብሔር ሕግ በተደነገገው መሠረት ሊፈጸም ይችላል፡፡

**አንቀጽ 129** __የቤተ ሙከራ ምርመራ ቴክኒክን መጠቀም__

1. በተሰበሰበ ማስረጃና በተካሔደ ትንተና ላይ ተጨማሪ ምርመራ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን መርማሪ እና ሌላ በምርመራ ሒደት የተሳተፈ ባለሙያ ምርመራውን

በቤተ ሙከራ እንዲካሔድ ማድረግ አለበት፤ መርማሪ ይኸውን ለዐቃቤ ሕግ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. በቤተ ሙከራ የሚካሔድ ምርመራ፡-

(ሀ) የወንጀሉ አፈጻጸም እና ከባቢያዊ ሁኔታን ለመለየት፣

(ለ) ወንጀሉ የተፈጸመበት ዕቃ ወይም ማንኛውንም ሌላ ነገር በአግባቡ ለመለየት፣

(ሐ) በወንጀል ሥፍራ የተገኙ ማስረጃዎች ከወንጀሉ አፈጻጸም ጋር ያላቸውን ግንኙነት በአግባቡ ለመተንተን፣

(መ) በወንጀል ሥፍራው ከተሰበሰቡ የቃል ምስክርነቶች አንፃር የተፈጸመውን ወንጀል እንደገና በሚያመላክት ሁኔታ ለመሥራት ወይም ለማነፃፀር፣

(ሠ) ስለወንጀሉ አፈጻጸም በተለያዩ ምስክሮች የተሰጡ የምስክርነት ቃሎችን ተመሳሳይነትና ልዩነት ለማነፃፀር፣

መሆን አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በምርመራ ሒደት የተሳተፉ ባለሙያዎች በምርመራው ውጤት ላይ አስተያየታቸውንና ስምና ፊርማቸውን እንዲያስቀምጡ ይደረጋል፡፡ ፍርድ ቤትም ቀርበው እንዲመሰክሩ ሊደረግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 130 <u>ሰውን ወይም ዕቃን መለየት</u>**

ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ የወንጀል ፈፃሚውን ማንነት ወይም ከወንጀሉ ጋር የተያያዘን ዕቃ መለየት አስፈላጊ እንደሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ ----- (ከ108 ቀጥሎ ያለው) የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 131 <u>በምርመራና በድጋሚ ምልከታ መሳተፍ</u>**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ ---- ንዑስ አንቀጽ (2)(ሐ) መሠረት ምስክርነቱን የሰጠ ሰው፡-

(ሀ) ለምርመራ ሥራው የግድ አስፈላጊ እንደሆነና በዐቃቤ ሕግ ከታመነበት ቃሉን እንዲሰጥና በቤተ ሙከራ በሚካሔድ ምርመራ እንዲሳተፍ ሊደረግ ይችላል፡፡

(ለ) ምርመራው የሚካሄደው በወንጀል ሥፍራው ከተሰበሰበ የቃል ምስክርነት አንፃር የተፈጸመውን ወንጀል አካሔድ በድጋሚ ምልከታ ለመሥራት ወይም ለማነፃፀር እንደሆነ የምስክር ቃሉ ከተረጋገጠው ማስረጃ አንፃር ታይቶ መረጋገጥ አለበት፤ ምስክሩም ያየውን ወይም የተሳተፈበትን ሁኔታ በዝርዝር ማስረዳት አለበት፡፡

2. በምርመራው ሒደት የማስረጃውን ተዓማኒነት ለማረጋገጥ በወንጀል ሥፍራ በመገኘት ሁኔታውን እንደገና ማስረዳት አስፈላጊ እንደሆነ መርማሪ ስለሚከናወኑ እና በድጋሜ ምልከታ ስለሚፈጸመው ተግባር በዝርዝር ለምስክሮች መግለጽ አለበት፤ እንዳስፈላጊነቱ ዐቃቤ ሕግ  በአካል በመገኘት ሒደቱን እንዲከታተልና በቪዲዮ እንዲቀረጽ ሊደረግ ይችላል፡፡

3. ምስክሩ ወይም በምርመራው የተሳፈ ባለሙያ ሒደቱን በመርማሪ በተመለከተው መሠረት ማሳየት  ወይም በቃል የገለጸውን ማረጋገጥ ወይም ግልጽ ማድረግ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተደነገገው መሠረት ምስክሮች ወይም በምርመራ የተሳተፉ ባለሙያዎች ሒደቱን በጋራ ማሳየት የለባቸውም፡፡ እያንዳንዱ ሰው የየራሱን በተናጠል ያሳያል፣ አስፈላጊውን ማብራሪያ ያለሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ወይም ጠያቂነት መስጠት አለበት፡፡

5. በምርመራ ሒደት የተሳተፈ ሌላ አካል ስለወንጀሉ አፈጻጸም ሒደት ምልከታው በድጋሚ እንዲካሔድ፣ ማስረጃ በማውጣት ሒደት ምን እንደሠራ እንዲገልጽ ወይም እንዲያሳይ እና የመሰል ጥያቄዎች ለምስክሩ ወይም በምርመራ ሒደት ለተሳተፉ ሰዎች ሊያቀርብ ይችላል፡፡

6. ስለወንጀል ሥፍራ ማስረጃ አሰባሰብና ምርመራ ሒደት የመመርመር ሥልጣን የተሰጠው አካል ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 132** <u>ሌሎች ሁኔታዎች</u>

በዚህ ክፍል በተመለከተ የማስረጃ ማሰባበሰብ ዘዴ የተሳተፉ ባለሙያ በሌላ ሕግ ልዩ አዋቂ ካለበት ኃላፊነት በተጨማሪ እንደአግባብነቱ በዚህ ሕግ ለመርማሪ የተመለከቱ መብትና ኃላፊነት አለው፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለልዩ የምርመራ ዘዴዎች

**አንቀጽ 133 ዓላማ**

የልዩ ምርመራ ዘዴ ዓላማ ሊፈጸም የታቀደ ወንጀል እንዳይፈጸም አስቀድሞ ለመከላከል እና በመደበኛው የምርመራ ዘዴ ማስረጃ ማሰባሰብ ባልተቻለበት የወንጀል ጉዳይ ላይ አስፈላጊ የሆነ ማስረጃ ለማሰባሰብና ለማደራጀት ነው፡፡

**አንቀጽ 134 በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃን ማሰባሰብ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 135 በተደነገገ ልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃን ማሰባሰብ የሚቻለው በመደበኛው የምርመራ ዘዴ ማስረጃ ማግኘት የማይቻል ወይም ይህን የምርመራ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ሲሆን ነው፡፡

2. በዚህ ወይም በሌላ ሕግ ካልተደነገገ በስተቀር በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃን የመሰብሰብና የማደራጀት ተግባር በፍርድ ቤት ትእዛዝ ብቻ የሚከናወን ይሆናል፡፡

3. በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ ሊሰበሰብ የሚችለው በሕገ መንግሥትና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዐት ላይ የሚፈጸም ወንጀል፣ ሽብርተኝነት፣ ሙስና፣ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ የታክስ እና የጉምሩክ ወንጀሎች፣ የኢኮኖሚ ወንጀሎች፣ ሕገ ወጥ የሰው፣ የጦር መሣሪያ፣ የገንዘብና መድኃኒት ዝውውር እናበኮምፒውተር የሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ ይሆናል፡፡
4. ለዚህ ንዑስ ክፍል አፈጻጸም “መደበኛ የምርመራ ዘዴ” ማለት በዚህ ሕግ ክፍል ----- አንቀጽ ---- እስከ --- የተመለከተው የምርመራ ዘዴ ነው፡፡

**አንቀጽ 135 ልዩ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 134 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተ ወንጀል ፈጽሟልተፈጽሟል ወይም ሊፈጸም ተቃርቧል የሚል በቂ ጥርጣሬ ሲኖር በሚከተሉት ልዩ የምርመራ ዘዴዎች ማስረጃ ሊሰበሰብ ይችላል፤

(1) የተጠርጣሪውን በግል የሚጽፉቸውንና የሚፃፃፉቸውን፣ በፖስታ የሚላላካቸውን ደብዳቤዎች፣ በቴሌፎን በቴሌኮሚኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክ መሣሪያ የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች እና የመሳሰሉትን በመጥለፍ፣

(2) ሥርጎ በመግባትና አብሮ በመሆን የተጠርጣሪውን እንቅስቃሴ መከታተል፣ በምስልና በድምፅ መቅረጽ፤

(3) ሰነዶችየተለያዩ የይምሰል ግንኙነቶችን መፍጠር ወይም ማከናወን፣

**አንቀጽ 136** <u>መሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

1. በልዩ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሌላ አካል የበላይ ኃላፊ ወይም በሕግ መሠረት ተክቶ እንዲሠራ ውክልና የተሰጠው ሰው ሲፈቅድ በልዩ ማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ማስረጃ እንዲሰበስብ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት፤

    (ሀ) ተጠርጣሪው የወንጀል ድርጊቱን ለመፈጸም ዝግጅት ማድረጉን ወይም ዕቅድ መንደፉን፤

    (ለ) የወንጀል ድርጊቱን በማንኛውም ሌላ ሁኔታ መከላከል የማይቻል መሆኑን እና ድርጊቱ ቢፈጸም በሰው ሕይወት ወይም ንብረት ላይ ከባድ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መሆኑን፤

    (ሐ) የወንጀል ድርጊቱ በረቀቀ ሁኔታ በመፈጸሙ በመደበኛው የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ማስረጃ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን፤ ወይም

    (መ) ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ትእዛዝ የወንጀል ድርጊቱን ለመከላከል ወይም ተጠርጣሪውን፣ ማስረጃውን እና የወንጀል ፍሬውን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን፣

    በበቂ ምክንያት ያመነ እንደሆነ ማስረጃው በዚህ ሕግ በተደነገጉት ልዩ የምርመራ ዘዴዎች እንዲሰበሰብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. በፍርድ ቤቱ የሚሰጥ ትእዛዝ፤

    (ሀ) የሚታወቅ እንደሆነ የተጠርጣሪውን ስምና አድራሻ፤
    (ለ) እንደነገሩ ሁኔታ ትዕዛዙ የሚፈጸምበት መኖሪያ ቤት ወይም ቦታ አድራሻና መለያ፤
    (ሐ) ትዕዛዙ ተፈጻሚ የሚሆንበት የጊዜ ገደብ፤

(መ) የሚሰበሰብ ማስረጃን እና መረጃን፣ የሚሰበሰብበትን ዘዴ፤ እና

(ሠ) ሌላ አግባብነት ያለውን ዝርዝር መረጃ መያዝ አለበት፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)-(3) የተደነገገው ቢኖርም ከፍርድ ቤት ፈቃድ እስኪገኝ ማስረጃው የሚጠፋ መሆኑ ሲታመን ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በዚህ ሕግ አንቀጽ 137 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃድ በልዩ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ማስረጃ ማሰባሰብ ይቻላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ እንዲሰባሰብ መነሻ የሆነ ማስረጃንና ምክንያቱን ከሰባ ሁለት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍርድ ቤቱ በጽሑፍ አቅርቦ እንዲቀጥል ካልፈቀደለት በስተቀር ያቋርጣል፡፡

## አንቀጽ 137 <u>የጊዜ ገደብ</u>

1. በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ እንዲሰበሰብ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ፈቃድ ከአራት ወር ሊበልጥ አይችልም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጥ ሲያመለክት ፍርድ ቤት አሳማኝ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ የማሰባሰብ ጊዜ ከሃያ ስምንት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 138 <u>የመረጃ ወይም ማስረጃ ሪፖርትን ለፍርድ ቤት ማቅረብ</u>

1. በልዩ ማስረጃ የማሰባሰቢያ ዘዴ የተሰበሰበው መረጃ ወይም ማስረጃ ሪፖርት በትዕዛዙ ላይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ትዕዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መቅረብ አለበት፡፡

2. ፕሬዚዳንቱ የቀረበው የመረጃ ወይም ማስረጃ ሪፖርት በዚህ ሕግ አንቀጽ 136(3) በተፈቀደው መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤ ከተሰጠው ትእዛዝ ውጭ የተከናወነ ተግባር ባጋጠመ ጊዜ ተገቢ መስሎ የታየውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

3. ማስረጃው ወይም መረጃው ለክሱ፣ ለምርመራው ወይም ወንጀል ለመከላከል ጠቃሚ ካልሆነ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃው እንዲወገድ ወይም ማስረጃውን ማስወገድ ተገቢ ባልሆነ ጊዜ አግባብ ባለው አካል ተጠብቆ እንዲቆይ ትእዛዝ ይሰጣል፤ በአግባቡ መጠበቁንም ያረጋግጣል፡፡

4. ከልዩ ማስረጃ ማሰባሰብ ዘዴ ጋር በተያያዘ “ፍርድ ቤት” ማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡

**አንቀጽ 139** <u>የማያስጠይቅ ተግባር</u>

1. በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ እንዲሰበስብ ከፍርድ ቤት፣ ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም የተፈቀደለት ሰው ሊፈጸም የታቀደውን ወንጀል ለመከላከል ወይም በተፈጸመ ወንጀል ማስረጃ ለማሰባሰብ በወንጀል ድርጊት መፈጸም ወይም መሳተፍ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ ማንኛውንም ርምጃ ሊወስድ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት የሚወሰድ ማንኛውም ርምጃ

   (ሀ) የግድ አስፈላጊ፣
   (ለ) ሌላ አማራጭ መንገድ የሌለ መሆኑን የተረጋገጠ እና
   (ሐ) ለማሳካት ከታሰበው ዓላማ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡
3. በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ እንዲሰበስብ ከፍርድ ቤት፣ ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው ሌላ አካል የበላይ ኃላፊ የተፈቀደለት ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ በወንጀል ሕግ መሠረት ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 140** <u>ማስረጃ ተቀባይነት የማያገኝበት ሁኔታ</u>

1. በዚህ ሕግ ወይም ልዩ ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴን በመጠቀም የሚሰበሰብን ማስረጃ ወይም መረጃ በዚህ ሕግ የተደነገገውን በመተላለፍ ከተፈቀደው በተለየ ዘዴ የተሰበሰበ ማስረጃ በፍርድ ቤት ተቀባይነት የለውም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የሽብርተኝነት ወንጀልን በተመለከተ በማንኛውም መንገድ የተገኘ የመረጃ ሪፖርት በማስረጃነት ተቀባይነት አለው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>የተጠርጣሪ ቃል አቀባበል፣ አያያዝ እና አቆያየት</u>

**አንቀጽ 141** <u>ተጠርጣሪን መጥራት</u>

1. መርማሪ ወንጀል ስለመፈጸሙ በበቂ ሁኔታ የተጠረጠረን ሰው በዚህ ሕግ አንቀጽ 143 እና 147 መሠረት ያልተያዘ እንደሆነና በመጥሪያ ቢጠራ

ይቀርባል የሚል እምነት ሲኖረው በፖሊስ ጣቢያ እንዲቀርብ አመቺ በሆነ ማንኛውም መንገድ ሊሰጠው ይችላል፡፡ መርማሪ ተጠርጣሪን ከመጥራቱ በፊት ይኸውን ለዐቃቤ ሕግ ማሳወቅ አለበት፤ ዐቃቤ ሕግም ወዲያውኑ ተገቢውን መመሪያ መስጠት አለበት፡፡

2. በመርማሪ የሚላክ መጥሪያው ተጠርጣሪው ስለሚፈለግበት ጉዳይ፣ ቦታ፣ ጊዜ እና ስላለበት ግዴታ የሚገልጽ ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

3. መጥሪያ የደረሰው ተጠርጣሪ ለምርመራ ካልቀረበ መርማሪው በድጋሚ መጥሪያ ይልክለታል፤ ተጠርጣሪው ካልቀረበ መርማሪው ሊጠራው ወይም የፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ በማውጣት ሊይዘው ይችላል፡፡

## አንቀጽ 142 ተጠርጣሪን መያዝ

1. ወንጀል ስለመፈጸሙ የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ ወይም ጥቆማ ሲቀርብ ተጠርጣሪን በማሰር የምርመራ ሥራ መከናወን የለበትም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ወንጀሉ ከባድ ሆኖ ስለወንጀሉ መፈጸም መርማሪው በቂ ማስረጃ ካለው ወይም ሌላ ወንጀል እንደሚፈጽም የሚያመላክት መረጃ ከተገኘ ወይም ወንጀሉ ለመሠራቱ በአካባቢው ሁኔታ የተደገፈና የሚታመን መስሎ የተገኘ እንደሆነ ተጠርጣሪን ተይዞ ምርመራው ሊካሔድ ይችላል፡፡

3. በዚህ ሕግ አንቀጽ 473 በተመለከቱ ሰዎች ላይ የሚካሔድ ምርመራ ሳይያዙ መከናወን አለበት፡፡

4. በዚህ ሕግ ወይም በሌላ ሕግ በልዩ ሁኔታ ካተደነገገ በስተቀር በወንጀል የተጠረጠረ ማንኛውም ሰው ሊያዝ ወይም በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት ሊቆይ የሚችለው በዚህ ክፍል በተደነገጉ ድንጋጌዎች መሠረት መሆን አለበት፡፡

## አንቀጽ 143 የፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ

1. በዚህ ሕግ ወይም በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ሊያዝ ወይም በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት ሊቆይ የሚችለው በፍርድ ቤት ትእዛዝ ብቻ ነው ፡፡

2. መርማሪ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት የመያዣ ትእዛዝ በማንኛውም ፍርድ ቤት ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 144 __አስፈላጊ ሁኔታዎች__**

ተጠርጣሪን ለመርማሪ ለማቅረብ በሌላ መንገድ የማይቻል እንደሆነ እና መቅረቡ የግድ አስፈላጊ ሲሆን ፍርድ ቤት የመያዝ ትእዛዝ ይሰጣል፤ የመያዝ ትዕዛዙም በማንኛውም ቀንና ሰዓት የሚቀርብ ሆኖ ትዕዛዙ ጥያቄው እንደቀረበ ወዲያውኑ መሰጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 145 __የመያዝ ትእዛዝ__**

1. በፍርድ ቤት የሚሰጥ የመያዣ ትእዛዝ የተጠርጣሪውን ስም እና የታወቀ አድራሻ፣ የተጠረጠረበትን ወንጀል፣ ማዘዣውን የሰጠው ፍርድ ቤት፣ ማዘዣው የተሰጠበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምኅረት፣ ማዘዣው የሚጸናበት ጊዜ እና ሌሎች አግባብ የሆኑ ዝርዝሮችን መያዝ አለበት፡፡

2. በማንኛውም የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት የተሰጠ የመያዣ ትእዛዝ በሀገሪቱ የግዛት ወሰን ውስጥ ተፈጻሚነት አለው፤ ማንኛውም ተቋም ወይም ሥልጣን ያለው ሰው የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 146 __አስቸኳይ ሁኔታ__**

1. መርማሪ ፍርድ ቤት ቀርቦ የመያዣ ትእዛዝ  እስኪያወጣ ድረስ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም በስልክ፣ በፋክስ፣ በኢሜይል፣ ወይም በመሰል በሌላ መንገድ የመያዣ ትእዛዝ እንዲሰጠው ማንኛውንም ፍርድ ቤት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. መርማሪው በዚህ አንቀጽ መሠረት ያቀረበውን አስቸኳይ የመያዣ ጥያቄ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ በጽሑፍ ለፍርድ ቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. መርማሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ጥያቄውን በጽሑፍ ካላረጋገጠ የተሰጠው የመያዝ ትእዛዝ በፍርድ ቤት እንዳልተሰጠ ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 147__ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ተጠርጣሪን መያዝ__**

1. በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠርጣሪው መካከለኛ ወይም ከባድ ወንጀል ፈጽሟል ወይም ሊፈጽም ተዘጋጅቷል ተብሎ በበቂ ሁኔታ ሲታመን

እና ምርመራውን ለማከናወን የተጠርጣሪው መያዝ የግድ አስፈላጊ ሲሆን ተጠርጣሪውን ያለ ፍርድ ቤት መያዣ ትእዛዝ መያዝ ይቻላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መርማሪ፡-

(ሀ) የሕዝብን ፀጥታ ያደፈረሰን፤

(ለ) የፖሊስ ወይም የመርማሪን ሥራ ያደናቀፈ ወይም የተከላከለን፤

(ሐ) ወታደርነት ወይም ከፖሊስ ሠራዊት የኩብለላ ተግባር የፈጸመ ስለመሆኑ የተጠረጠረን፤

(መ) ወንጀል የተፈጸመበትን ወይም ለወንጀል መፈፀሚያ የሚሆን መሣሪያ የያዘ ስለመሆኑ የተጠረጠረን፣ ወይም

(ሠ) አደገኛ ቦዘኔ መሆኑ የተጠረጠረን፤

ሰው ያለፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ መያዝ ይችላል፡፡

ትእዛዝአንቀጽ 148 በ<u>እጅ ከፍንጅ ወንጀል ተጠርጣሪን መያዝ</u>

1. ማንኛውም ሰው ወይም ፖሊስ ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት የሚያስቀጣ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲፈፅም የተገኘን ተጠርጣሪ ያለ ፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ መያዝ ይችላል፤

2. በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ወንጀል እጅ ከፍንጅ ሲፈጽም የተገኘ ተጠርጣሪ ሊያዝ የሚችለው የግል ተበዳይ አቤቱታ ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

3. ተጠርጣሪን የተያዘ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ አቅራቢያው ላለው ፖሊስ ተቋም ማስረከብ አለበት፡፡

አንቀጽ 149 <u>የመተባበር ግዴታ</u>

1. በፍርድ ቤት ወይም ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰው ሲያዝ ትብብር እንዲያደርግ በፖሊስ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው በራሱ ወይም በንብረቱ ላይ አደጋ የማያደርስ እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 808 መሠረት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2. ተጠርጣሪን የያዘ ሰው ወንጀል ስለመፈጸሙ የሚመሰክር እንደሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 97 (ምስክረነት) በተደነገገው መሠረት ቃሉን መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 150 <u>ተጠርጣሪ ሲያዝ የሚፈጸም ሥርዐት</u>**

1. ፖሊስ የሚይዘውን ተጠርጣሪ ማንነቱን አስቀድሞ ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. ፖሊስ በፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ ሰው ሲይዝ ትዕዛዙን ለተጠርጣሪው ማሳየትና ማንበብ አለበት፡፡ ትእዛዙ የተሰጠው በቃል እንደሆነ ይኸው ለተጠርጣሪው መገለፅ አለበት፡፡

3. ተጠርጣሪ በቃል ወይም እጁን በመስጠት እንዲያዝ ያልተስማማ እንደሆነ ፖለስ ሰውነቱን በመንካት ወይም በመጨበጥ ለመያዝ ይችላል፡፡

4. ተጠርጣሪ ላለመያዝ በሀይል የተከላከለ ወይም ለማምለጥ የሞከረ እንደሆነ ፖሊስ ሁኔታው የሚፈቅደውን ተመጣጣኝ ርምጃ በመውሰድ ተጠርጣሪውን ለመያዝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 151 <u>በማቆያ ቤት ቃል መስጠት</u>**

1. በዚህ ሕግ መሠረት በማንኛውም ሁኔታ የተያዘ ሰው በፖሊስ ጣቢያ ቀርቦ የተከሳሽነት ቃሉን እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

2. የተከሳሽ ቃል አሰጣጥን በተመለከተ የዚህ ሕግ አንቀጽ 114 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 152 <u>በመርማሪ ወይም በዐቃቤ ሕግ የሚሰጥ ዋስትና</u>**

1. የተያዘው ሰው የተጠረጠረበት ድርጊት ቀላል ወንጀል ሆኖ መፈጸሙ አጠራጣሪ ሲሆን መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ እንደ ነገሩሁኔታ ተጠርጣሪውን በራስዋስትና ወይም ያለዋስትና ሊለቅ ይችላል፡፡

2. መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተጠርጣሪው የተጠረጠረበት ድርጊት መካከለኛ ወንጀል እንደሆነና አጠራጣሪ ሲሆን እንደነገሩ ሁኔታ ተጠርጣሪውን በዋስትና ሊለቅ ይችላል፡፡

3. የተያዘው ሰው የተጠረጠረበት ድርጊት መካከለኛ ወንጀል ሆኖ አጠራጣሪ ሲሆን መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ እንደነገሩ ሁኔታ ተጠርጣሪውን በማስፈረም በዋስተና ሊለቅ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የተያዘው ሰው በዋስትና በሚለቀቅበት ጊዜ፤

(ሀ) በተወሰነ ጊዜና ቦታ መርማሪ ጋር ወይም ሌላ አመቺ በሆነ አካል ጋር ቀርቦ ሪፖርት እንዲያደርግ፣

(ለ) የተወሰነ ቦታ እንዳይደርስ፣

(ሐ) ከምስክሮች ወይም ከግል ተበዳዮች ጋር እንዳይገናኝ፣

(መ) ከተወሰነ ክልል ወይም ቦታ ውጭ እንዳይሔድ ግዴታ በማስገባት ወይም

(መ) የመሳሰሉትን ቅድመ ሁኔታዎች

ግዴታ በማስገባትና በማስፈረም ሊለቀቅ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከዋስትና ጋር የሚቀመጥ ቅድመ ሁኔታ እንደአግባብነቱ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ወይም ሁሉንም ቅድመ ሆኔታዎች ሊያካትት ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ለተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎች አፈጻጸም መርማሪ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል ወይም እንዲደረግ ተገቢውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰጠ ዋስትና በፍርድ ቤት እንደተሰጠ ዋስትና ይቆጠራል፡፡ የዋስትና ግዴታን አለመፈጸም የሚኖረውን ውጤት በተመለከተ የዚህ ሕግ አንቀጽ ...... ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 153 ተጠርጣሪን ፍርድ ቤት ማቅረብ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 155 መሠረት የተያዘ ሰው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡ ይህም ጊዜ ተጠርጣሪው ከተያዘበት ቦታ ፍርድ ቤት ለማድረስ አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም፡፡

## አንቀጽ 154 በማቆያ ቤት ማቆየት

1. መርማሪው በዚህ ሕግ አንቀጽ 138 መሠረት ፍርድ ቤት የቀረበ ተጠርጣሪ የተያዘው በበቂ ጥርጣሬ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት አለበት፡፡

2. ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው ታስሮ እንዲቆይ የሚያበቃ በቂ ጥርጣሬ የለም ብሎ ካመነ በዋስትና ወይም ያለ ዋስት ሊለቀው ይችላል፡፡

3. ፍርድ ቤቱ ምርመራው ያልተፈጸመ መሆኑንና ምርመራውን ለማድረግ ተጠርጣሪው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ አስፈላጊ መሆኑን ካመነ፣

    (ሀ) ለሽብርተኝነት ወንጀል ሃያ ስምንት ቀናት፤

    (ለ) ለሌላ ወንጀል እስከ አሥራ አራት ቀናት

የምርመራ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 155** <u>ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ</u>

1. ፍርድ ቤቱ መርማሪ ምርመራውን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልገው መሆኑን ሲያምን ለከባድና ለመካከለኛ ወንጀል እስከ አሥራ አራት ቀናት የሚደርስ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ለሽብርተኝነት ወንጀል የሚሰጥ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ እስከ ሃያ ስምንት ቀናት ሊሆን ይችላል፡፡

3. ለመካከለኛ ወንጀሎች በፍርድ ቤቱ የሚፈቀድ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ድምር በጠቅላላው ከሃያ ስምንት ቀናት ሊበልጥ አይችልም፡፡

4. ሽብርተኝነትን ጨምሮ ለከባድ ወንጀሎች የሚሰጥ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ከአራት ወራት መብለጥ የለበትም፤ ተጨማሪ ጊዜ መስጠት የግድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤት ሌላ ተጨማሪ ከአራት ወራት ያልበለጠ የምርመራ ጊዜ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

5. ምርመራው ተጠናቆ ተጨማሪ ጊዜ የማያስፈልገው እንደሆነ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪው በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት በዋስትና እንዲወጣ ወይም ዐቃቤ ሕግ ክስ እስኪመሠርት በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 156 _ያልተጠናቀቀ ምርመራ ስለሚኖረው ውጤት_**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 190 ስለዋስትና የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሕግ አንቀጽ 156 ከንዑስ አንቀጽ (1)-(4) በተደነገገው ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የወንጀል ምርመራው ካልተጠናቀቀ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪውን የተጠረጠረበት ወንጀል ዋስትና የማያስከለክለው እንደሆነ በዋስትና ይለቃል፡፡

2. የወንጀል ምርመራው በተሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ካልተጠናቀቀ በዚህ ሕግ ስለንብረት ዕግድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከወንጀል ድርጊት መፈጸም ጋር በተያያዘ የታገደ ወይም የተያዘ ንብረት ሲኖር እንዲለቀቅ ፍርድ ቤት ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

3. በተጨማሪ ምርመራ ጊዜ ውስጥ ምርመራ ባለመጠናቀቁ መርማሪው በሕግ ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደነገሩ ሁኔታ ምርመራው ሊቀጥል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 157 _በማረፊያ ቤት የሚቆይ ሰው ስላለው መብት_**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 27 የተያዘ ሰው ስለሚኖረው መብትና ግዴታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

(1) በዚህ ሕግ መሠረት ተይዞ በማረፊያ ቤት የሚቆይ ሰው የትዳር ጓደኛውን፣ የቅርብ ዘመዱን፣ ጓደኛውን፣ የኃይማኖት አማካሪውን፣ ሐኪሙንና የሕግ አማካሪውን ጠርቶ ለማነጋገር ይፈቀድለታል፡፡

(2) ማረፊያ ቤቱ ተጠርጣሪው ዋስ እንዲያገኝ ወይም በተጠረጠረበት የወንጀል ጉዳይ ላይ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እንዲችል ድጋፍና ትብብር ማድረግ አለበት፡፡

(3) የማረፊያ ቤቱ ተጠርጣሪው በማረፊያ ቤት ቆይታው ከታራሚዎች ጋር እንዳይገናኝ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እና በማረፊያ ቤቱ ደንብ መሠረት መያዙን ማረጋገጥ አለበት፡፡

**አንቀጽ 158 <u>የወንጀል ምርመራ የሚጠናቀቅበት ጊዜ</u>**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 154፣ 155 እና 156 የተደነገገው የምርመራ ጊዜ እንደተጠበቀ ሆኖ ወይም በሕግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ክስ፣ የግል አቤቱታ ወይም ጥቆማ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ወንጀሉ፡-

    (ሀ) የእጅ ከፍንድ ወንጀል እንደሆነ ከሰባት ቀናት፣

    (ለ) ቀላል ወንጀል እንደሆነ ከሁለት ወራት፣ እና

    (ሐ) መካከለኛና ከባድ ወንጀል እንደሆነ ከአራት ወራት

    ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አጠቃላይ የምርመራው መጠናቀቅ አለበት፡፡

2. ለዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም የመመርመር ሥልጣን የተሰጠው ሌላ አካል ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለንብረት ዕግድ፣ መውረስ፣ ማስተዳደር

**አንቀጽ 159 <u>መርህ</u>**

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ማንኛውም ንብረት ወይም ገንዘብ በዚህ ሕግና አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሠረት መሠረት ሊታገድ፣ ሊያዝ፣ ሊወረስ እና አግባብነት ባለው አካል ሊተዳደር ይችላል፡፡

2. በዚህ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት፡-

    (ሀ) የወንጀል ፍሬ፣

    (ለ) ለወንጀል ሥራ እንዲነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመሥራት እንዲረዳው ወይም ወንጀሉን ለፈጸመበት ዋጋ እንዲሆነው ለተከሳሽ የተሰጠው ወይም ሊሰጠው የታቀደ ንብረትን፣

    (ሐ) በሀገሪቱ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዐት ወይም በውስጥና በውጭ ደኅንነት ላይ አድማ በማድረግ ወይም ጉዳት በማድረስ ወንጀል የተጠረጠረ ሰው የግል ንብረትን፣

(መ) በሕግ በግልጽ መደንገጉ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠርጣሪው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት ያገኘው የግል ንብረትን፣ ወይም

(ሠ) በተጠረጠረበት ወንጀል ሊቀጣ ከሚችለው የገንዘብ ቅጣት ወይም ካገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የግል ንብረትን፣

በዚህ ሕግ መሠረት ሊያግድ ይችላል፡፡

4. ንብረቱ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 119 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ሆኖ በተለያየ ምክንያት በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ያልተሰጠበት እንደሆነ ፍርድ ቤት ንብረቱ እንዲታገድ፣ እንዲወረስ ወይም ሌላ ተገቢ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በሌላ አግባብነት ባለው ሕግ ለተከሳሹና ለቤተሰቡ የእለት ኑሮ አስፈላጊ የሆነ እና እንዳይታገድ የተመለከተ ንብረት ላይ የዕግድ ትእዛዝ መስጠት የለበትም፡፡

## አንቀጽ 160 የዕግድ ማመልከቻ ስለማቅረብ

1. ዐቃቤ ሕግ በዚህ ሕግ አንቀጽ 160 የተጠቀሰው ንብረት እንዲታገድ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. ማመልከቻው የወንጀል ክስ ከመመሥረቱ በፊት ወይም ከተመሠረተ በኋላ ሊቀርብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 161 የማመልከቻው ይዘት

በዚህ ሕግ መሠረት የዕግድ ትእዛዝ እንዲሰጥ የሚቀርብ ማመልከቻ፤

(1) የወንጀሉን ፍሬ ነገር እና በየደረጃው የተወሰዱትን ርምጃዎች ክስ ያልተመሠረተ እንደሆነ ጉዳዩ የሚገኝበት ደረጃ የሚያሳይ መረጃ፣

(2) የሚታገደው ንብረት በዚህ ሕግ አንቀጽ 160 በተዘረዘሩት ሁኔታ የተገኘ መሆኑን የሚያይ ምክንያት፣

(3) የንብረቱ ዝርዝር እና አድራሻ፣ እና

(4) የንብረት ዕግድ የቀረበበት ምክንያትንና እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 162** <u>የዕግድ ትእዛዝ መስጠት</u>

1. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ የዕግዱን አስፈላጊነት ካመነበት ንብረቱ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ወይም ለሌላ ማንኛውም መንገድ ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የዕግድ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ትዕዛዙን የሚመለከተው አካልና የሚቻል እንደሆነ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ትዕዛዙን እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በሌለበት የዕግድ ትእዛዝ ከተሰጠ መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ ትዕዛዙን ለተጠርጣሪው፣ ለተከሳሹ፣ ለወኪሉ ወይም በትዕዛዙ ላይ ስሙ ለተጠቀሰ ሰው ያደርሳል፤ ትዕዛዙንም ለሚመለከተው ሰው ያስታውቃል፡፡

3. ፍርድ ቤቱ የተለየ ትእዛዝ ካልሰጠ በስተቀር ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ የጸና ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 163** <u>ተጨማሪ የዕግድ ትእዛዝ</u>

የዕግድ ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ ተጨማሪ የዕግድ ትእዛዝ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ሁኔታ የተፈጠረ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ የዕግድ ትእዛዝ እንዲሰጥ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 164** <u>የዕግድ ትእዛዝ ቀሪ መሆን</u>

1. ክሱ የተነሳ፣ የተዘጋ፣ የተሻሻለ ወይም የተለወጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝን ቀሪ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ቀሪ የሚሆነው ክሱ

   (ሀ) ክሱ ከተነሳ ወይም ከተዘጋ፣ ወይም

   (ለ) ተከሳሹ በነጻ የተለቀቀ እንደሆነ፣

   ሲሆን ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት ወይም በተከሳሹ ወይም በወኪሉ አመልካችነት ወይም በሕግ በተመለከተው መሠረት ፍርድ ቤት ዕግድ እንዲነሳ ወይም ጸንቶ እንዲቆይ፣ የታገደው ንብረቱ እንዲወረስ ወይም እንዲወድም ወይም ሌላ ተገቢ የሆነ ማንኛውም ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የዕግድ ትዕዛዙ እንዲነሳ ወይም ጸንቶ እንዲቆይ፣ የታገደው ንብረት እንዲወረስ ወይም እንዲወገድ ሲወስን የዐቃቤ ሕግን አስተያየት መስማት አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታውን ለፍርድ ቤቱ ፕሬዘዳንት ማቅረብ ይችላል፡፡ ፕሬዘዳንቱ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፤ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 165** <u>**የዕግድ ትእዛዝን ማንሳት ወይም ማሻሻል**</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 163 መሠረት የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ የደረሰው ወይም እንዲያውቅ የተደረገ ሰው ወይም በትእዛዙ ምክንያት መብቱ ተነካ የሚል ሶስተኛ ወገን ትዕዛዙ እንዲነሳለት ወይም እንዲሻሻል ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

2. የዕግድ ትዕዛዙ እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ሕግ መሠረት በተዘጋጀ ቅፅ ሆኖ በእግዱ ምክንያት መብትና ጥቅሙ የተነካበትን ሰው፣ የታገደውን ንብረት ዐይነትና ዝርዝር አድራሻ፣ እግዱ የሚነሳበትን ምክንያት እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

3. ፍርድ ቤት የቀረበውን ማመልከቻ እና ሌሎች ማስረጃዎችን ተቀብሎ ዐቃቤ ሕግ ምላሽ የሚሰጥበትን ቀን በመግለጽ ለዐቃቤ ሕግ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ አስተያየት እንደደረሰው እንደጉዳዩ ሁኔታ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

4. የዕግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል የቀረበው አቤቱታ በቂ ምክንያት ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሰጥቶ የነበረውን የዕግድ ትእዛዝ እንዲሻሻል ወይም እንዲነሳ ሊያደርግ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ወይም ንዑስ አንቀጽ (4) በተመለከተው መሠረት ፍርድ ቤት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት እንዳስፈላጊነቱ ጉዳዩ በባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል አንድ
## ስለንብረት አስተዳዳሪ

**አንቀጽ 166** ስለንብረት አስተዳዳሪን

1. ፍርድ ቤቱ የዕግድ ትእዛዝ የተሰጠበትን ንብረት በተመለከተ እንደነገሩ ሁኔታ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤

   (ሀ) ንብረቱን የሚያስተዳድር ሰው መሾም፤

   (ለ) ንብረቱን በይዞታ ወይም በአደራ አስቀማጭነት ወይም በአስተዳዳሪነት ለሌላ ሰው ሆኖ የያዘን ሰው ንብረቱን እንዲለቅ፤

   (ሐ) የተለቀቀው ንብረት አስተዳዳሪው ተረክቦ በይዞታው ሥር እንዲያደርግ፣ እንዲጠብቅና እንዲያስተዳድር፤

   (መ) ተቀባዩ የተረከበውን ንብረት ለመጠበቅ፣ ለማስተዳደር፣ ለማሻሻል የሚያስችል ሥልጣን መስጠት፤

   (ሠ) ንብረቱ እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ለሚመለከተው አካል ትእዛዝ መስጠት፤

2. ፍርድ ቤቱ ንብረት አስተዳዳሪው ስለሚያስተዳድረው ንብረት የመከሰስ ኃላፊነት እንዲኖረው፣ ከንብረቱ የሚገኝ ኪራይ፣ ትርፍ ወይም ሌላ ማንኛውንም ገቢ ለመሰብሰብና የሰበሰበውንም ገንዘብ ንብረቱን ለማስተዳደር ጠቃሚ ለሆነ ጉዳይ ለማዋል እንዲችል ወይም ተገቢ መስሎ የታየውን ሌላ ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) መሠረት በንብረት አስተዳዳሪነት የሚሾመው የተፈጥሮ ሰው እንደሆነ አስተዳዳሪው መልካም ሥነ-ምግባርና ችሎታ ያለው፣ ከተከሳሹ ጋር ዝምድና ወይም የጥቅም ግንኙነት የሌለው እና ንብረት ለማስተዳደር ፈቃድ ያለው መሆኑን ፍርድ ቤት ማረጋገጥ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) መሠረት በንብረት አስተዳዳሪነት የሚሾመው የሕግ ሰውነት ያለው እንደሆነ ንብረት ለማስተዳደር ፈቃድና መልካም ስም ያለው፣ የጥቅም ግጭት እና ባለፉት ሦስት ዓመታት የሂሳብ አያያዙ ጉድለት የሌለበት መሆኑን ፍርድ ቤት ማረጋገጥ አለበት፡፡

## አንቀጽ 167 ስለንብረት አስተዳደር ወጪ

1. በዚህ ሕግ መሠረት የታገደ ንብረትን ለማረካከብ፣ ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን ወጪ ወይም ለንብረት አስተዳዳሪው ሊከፈለው የሚገባውን የአበል ክፍያ ከንብረቱ ላይ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ፍርድ ቤት ጠቅላላ ወይም ልዩ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚያስፈልገውን ወጪ ወይም አበል ለመወሰን ፍርድ ቤቱ ንብረት አስተዳዳሪ ከመሾሙ በፊት አስፈላጊው ማጣራት እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል፡፡

3. ጠቅላይ ፍርድ ቤት በንብረት አስተዳዳሪነት ስለሚሾም ሰው፣ የአሿሿም ሒደት፣ ሊኖር የሚገባ ሥነ ምግባር፣ የንብረቱ አስተዳደር ሁኔታ፣ ስለሚከፈል ወጪና የአከፋፈሉ ሁኔታ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 168 የንብረት አስተዳዳሪ ግዴታ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 167 መሠረት የሚሾም ንብረት አስተዳዳሪ፡-

(1) እንዲያስተዳድር የተሾመበትን ንብረት በተመለከተ ተመጣጣኝ የሆነ ዋስ ወይም መያዣ የመስጠት፣

(2) ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ጊዜና ሥርዐት መሠረት ዝርዝር ሪፖርትና የሂሣብ መግለጫ እየሠራ የማቅረብ፣

(3) ፍርድ ቤቱ በሚወስነው መሠረት ከንብረቱ ላይ የሚፈለግበትን ገንዘብ የመክፈል፣

(4) እንደራሱ ንብረት እና ሙያው በሚጠይቀው ደረጃና አሠራር መሠረት ንብረቱን የማስተዳደር፣

(5) ሥነ ምግባርበተረከበው ንብረት በራሱ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ ባደረሰው ጉዳት ወይም ጉድለት ኃላፊ የመሆን፣

ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 169 የንብረት አስተዳዳሪው ኃላፊነት

1. ንብረት አስተዳዳሪው በራሱ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ በንብረቱ ላይ ጉዳት ወይም ጉድለት ያደረሰ እንደሆነ የደረሰውን ጉዳት ወይም ጉድለት ልክ ወጭ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ማዘዝ አለበት፡፡ በዚህ ምክንያት መብቱ የተነካ ሶስተኛ

ወገን በቀረበ ጊዜ በፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ጉዳዩ እንዲታይ ፍርድ ቤት ሊያዝ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ትእዛዝ ንብረት አስተዳዳሪው ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ የግል ንብረቱ ተሸጦ ከሽያጩ ላይ የተገኘው ገንዘብ ለደረሰው ጉዳት ወይም ጉድለት እንዲተካ ወይም ንብረቱን ለመጠገን የሚያስፈልገውን ወጭ እንዲሸፍን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

3. ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን ውሳኔ ለመስጠት እንዳስፈላጊነቱ አጣሪ ሊሾምና የሚቀርብለትን ሪፖርት መሠረት በማድረግ ሊወስን ይችላል፤ እንደነገሩ ሁኔታ ጉዳዩ በሌላ ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን ሊመራው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 170** <u>ንብረት አስተዳዳሪ መሻር</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 167 መሠረት በፍርድ ቤት የተሾመ ንብረት አስተዳዳሪ በፍርድ ቤቱ አነሳሽነት፣ በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ ወይም በማንኛውም መብቱ በተነካ ሶስተኛ ወገን አመልካችነት እንደነገሩ ሁኔታ ሊሻር ይችላል፡፡

2. በአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ንብረት አስተዳዳሪው የሚሻረው፡-

(ሀ) በንብረቱን አስተዳደር ሒደት በንብረቱ ላይ ብክነት ያስከተለ እንደሆነ፣
(ለ) ንብረቱን የማስተዳደር ሥልጣኑን ያለአግባብ የተጠቀመ እንደሆነ ወይም
(ሐ) ሥራው በሚጠይቀው ጥራትና ሥነ ምግባር ንብረቱን ሳያስተዳድር የቀረ መሆኑ፣
(መ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 169 የተመለከቱ ግዴታዎችን ያልተወጣ መሆኑ፣

ከተረጋገጠ ነው፡፡

**አንቀጽ 171** <u>ንብረትን ማሸግ</u>

1. የታገደን ንብረት አሽጎ መጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በዐቃቤ ሕግ አመልካችነት ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ንብረቱ እንዲታሸግ ትእዛዝ ለመስጠት ይችላል፡፡ ተከሳሽ ወይም ማንኛውም መብቱ የተነካ ሶስተኛ ወገን ንብረቱ ታሽጎ እንዲቆይ ጥያቄ ካቀረበ ፍርድ ቤት ተገቢውን ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. ፍርድ ቤት የማሸግ ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ይህን ሥራ ለመፈጸም ተገቢ የሆነ ሰው መርጦ መሾም አለበት፡፡

3. እሸግ የተደረገበትን ንብረት በፍርድ ቤት አነሳሽነት ወይም በሌላ ወገን ጠያቂነት እሸጉ እንዲነሳ ፍርድ ቤት ካላዘዘ በስተቀር እሸጉን መቀደድ ወይም መከፈት የለበትም፡፡

**አንቀጽ 172** <u>መዝገብ ማዘጋጀት</u>

1. ንብረት እንዲያሽግ የተሾመ ሰው የማሸጉን ተግባር በትዕዛዙ መሠረት ከተፈጸመ በኋላ፡-
   (ሀ) የፍርድ ቤቱ ትእዛዝና ትዕዛዙ የተሰጠበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምኅረት፤
   (ለ) የታሸገ ንብረት ዝርዝርና የሚገኝበት ሥፍራ፤
   (ሐ) እንዲታሸግ ከታዘዘ ንብረት የተገኘና መታሸግ የሚገባው ሆኖ ሳይገኝ የቀረን ወይም የጎደለን ንብረት ዝርዝር፤ እና ፤
   (መ) የታሸገው ንብረት ያለበትን ቤት ወይም የሚገኝበትን ቦታ፣ የሚጠብቀውን ወይም ለዚሁ ቤትና ቦታ ኃላፊ የሆነ ሰው ካለ ስሙንና አድራሻውን፤
   የሚያመለክት መዝገብ ማዘጋጀት አለበት፡፡
2. መዝገብ በአሻጊው ሊፈረምበትና እሸጉ የተደረገበትን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምኅረት ማመልከት አለበት፡፡
3. የታሸገ ንብረት የሚገኝበት ቦታ ቁልፍ ያለው እንደሆነ አሻጊው መክፈቻውን ለፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር ማስረከብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 173** <u>ስለማይታሸግ ንብረት</u>

1. የታገደው ንብረት በተፈጥሮው ወይም በመታሸጉ ምክንያት የሚበላሽ ወይም ቶሎ የሚሻግትና የሚበሰብስ እንደሆነ በንብረቱ ላይ የእሸግ ትእዛዝ መሰጠት የለበትም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የማይታሸግ ንብረትን ዝርዝር አሻጊው እንዲያቀርብና በጨረታ ተሽጦ ገንዘቡ ተቀማጭ እንዲሆን ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 174** <u>ኑዛዜና ሌላ የጽሑፍ ሰነድ</u>

1. ንብረት አሻጊ በሚታሸገው ንብረት ውስጥ የኑዛዜ ጽሑፍ ወይም ቀድሞ የታሸገ ንብረት ወይም ሌላ ሰነድ ያገኘ እንደሆነ የዚህን ንብረት ወይም ጽሑፍ ዝርዝር በእሸጉ ውስጥ በማስቀመጥ በኑዛዜው፣ ቀድሞ በታሸገው ንብረት ወይም ሌላ ሰነድ ላይ ትእዛዝ እንዲሰጥበት ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ፍርድ ቤት ኑዛዜው፣ ንብረቱ ወይም የተገኘው ሌላ ሰነድ ስለሚቀመጥበት ሁኔታና ስለ አያያዙ ተገቢው ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 175** __የንብረትን ዝርዝር ማዘጋጀት__

1. የእሽግ ትእዛዝ የተሰጠበት ወይም የሚሰጥበት ንብረት ዝርዝር እንዲዘጋጅና እንዲታወቅ አስፈላጊ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካመነ ለዚሁ ተግባር ችሎታ ያለውን ሰው በመሾም የንብረቱ ዝርዝር ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ትዕዘዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) መሠረት የንብረቱን ዝርዝር የሚያዘጋጅ ሰው እንደአግባብነቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 172 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ንብረት እንዲያሽግ የተሾመ ሰው ሊሆን ይችላል፡፡

3. የንብረቱን ዝርዝር እንዲያዘጋጅ የተሾመው ሰው ከሁለት የማያንሱ ምስክሮች ባሉበት በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ተለይቶ የተገለፀውን የንብረት ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡ ዝርዝሩም ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ እና የንብረቱን የዋጋ ግምት መያዝ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የንብረቱ ዋጋ እንዲገመት ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ የሰጠ እንደሆነ ግምቱ በልዩ አዋቂ አማካይነት ይከናወናል፡፡

5. የተዘጋጀ የዋጋ ግምት ዝርዝር መግለጫ በልዩ አዋቂው ተፈርሞ እና የዋጋ ግምት ዝርዝሩ የተዘጋጀበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምኅረት ተፅፎበት የንብረት ዝርዝር እንዲያዘጋጅ ከተሾመው ሰው ሪፖርት ጋር ይያያዛል፡፡

6. የንብረት ዝርዝር እንዲያዘጋጅ የተሾመው ሰው ሪፖርት የተጻፈበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምኅረት ተፅፎበት እና ተፈርሞበት ለፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡ ፍርድ ቤቱም ለዚሁ ጉዳይ በተለይ በተዘጋጀው መዝገብ ውስጥ በሬጂስትራር እንዲመዘገብ በማድረግ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 176** __እሽግን ማንሳት__

1. ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም በሌላ ወገን አመልካችነት የተሰጠውን የእሽግ ትእዛዝ ማንሳት ተገቢ መሆኑን ሲያምን ፍርድ ቤቱ እሽጉ እንዲነሳ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እሽግ እንዲነሳ ሲወስን መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ እና እንደአስፈላጊነቱ ሌላ አግባብነት ያለው ሰው እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፣ አስተያየታቸውን ይቀበላል፡፡

3. እሽጉ እንዲነሳ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ከሰጠ እሽጉ የተነሳበት ቀን፣ ወርና ዓመት ምኅረት እንዲሁም የተገኙ ንብረቶች ዝርዝር እንዲቀርብበለት ሊያዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ስለ ቀዳሚ ምርመራ

**አንቀጽ 177 ዓላማ**

የቀዳሚ ምርመራ ዓላማ አግባብነት ያለው የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ እንዲሁም ተከሳሹ እንዲመዘገብለት ሲጠይቅ የሚያቀርብ ማስረጃን መያዝና መጠበቅ ነው፡፡

**አንቀጽ 178 መርህ**

1. በዚህ ሕግ በሠንጠረዥ ስድስት በተመለከተ ወንጀል የተጠረጠረን ሰው ዐቃቤ ሕግ በቀጥታ ክስ ለመመሥረት ካልወሰነ በስተቀር በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀዳሚ ምርመራ ሊካሔድ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀዳሚ ምርመራ የሚያስፈልገው በሰንጠረዝ ስድስት የተመለከተ ወንጀልና ሌላ ተደራራቢ ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ የቀዳሚ ምርመራው በሁሉም የወንጀሎች ዓይነቶች ላይ ይካሔዳል፡፡

3. ቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ማስረጃዎች ይመዘግባል፤ ያደራጃል፤ እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 179 የተጠርጣሪው ማስረጃ**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 179 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጉዳዩ በቀዳሚ ምርመራ እንዲጣራ ዐቃቤ ሕግ ሲያመለክት ተጠርጣሪው ያለውን ማስረጃ እንዲመዘገብለት ማመልከት ይችላል፤ የቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት ማስረጃውን ይመዘግባል፤ ያደራጃል፤ ይጠብቃል፡፡

**አንቀጽ 180** **<u>ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት</u>**

1. ቀዳሚ ምርመራ ለማካሔድ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ የአካባቢ ሥልጣን ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡

2. በዘህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የደነገገው ቢኖርም ለማስረጃው ደኅነንትና ለምስክሮች አቀራረብ ሲባል ዐቃቤ ሕግ የቀዳሚ ምርመራ እንዲካሔድ ለማንኛውም የመጀመሪያ ፍረድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡

3. ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሲወስን ለተጠርጣሪው ያለውን አመቺነት ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

**አንቀጽ 181** **<u>ለቀዳሚ ምርመራ ስለማመልከት</u>**

1. ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገቡን መርምሮ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 192 መሠረት ጉዳዩ በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት እንዲጣራ ሲወስን ለቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት ውሳኔውን ከማመልከቻ ጋር ያቀርባል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት ማመልከቻው በቀረበለት ዕለት ቀዳሚ ምርመራ የሚጀመርበትን ቀን በመወሰን ተጠርጣሪ ፣ ዐቃቤ ሕግ እና ምስክሮች በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ዓቃቤ ሕግ በቀጠሮው ቀን ተጠርጣሪው መቅረብ የማይችል፣ማስረጃው የሚበላሽ፣ የሚጠፋ ወይም የማስረጃነት ዋጋው የሚቀንስ እንደሆነመሆኑን ለፍርድ ቤቱ በበቂ ሁኔታ ካስረዳ ፈርድ ቤቱ ተጠርጣሪው በሌለበት በዐቃቤ ሕግ የቀረበውን ማስረጃ ወዲያውኑ መመዝገብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 182** **<u>የማስረጃ አመዘጋገብ</u>**

1. ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው እንደቀረበ ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 182ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ማስረጃውን መመዝገብ አስፈላጊ ሲሆን ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩን አስረድቶ ማስረጃውን እንዲያሰማ ያደርጋል፡፡

2. የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተመዘገበ በኋላ ቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት፣

(ሀ) ፈቃደኛ እንደሆነ ለክሱ መልስ ቃሉን ለመስጠት የሚችል እንዲሁም እንዲመዘገብለት የሚፈልገው ማስረጃ ካለ የሚመዘገብለት፣

(ለ) ቃሉን ለመስጠት የማይገደድ መሆኑን እና የሚሰጠው ቃል በጽሑፍ ሆኖ ነገሩ ሲሰማ በማስረጃነት የሚቀርብ፣

(ሐ) ክሱ የሚያከራክር ያለመሆኑንና የተጠርጣሪውን ጥፋተኝነት ወይም ነጻ መሆን ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የሚወሰን፣

መሆኑን ለተጠርጣሪው ይነግረዋል፡፡

3. በቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት የተመዘገበ ማስረጃ ግልባጭ በማንኛውም ሁኔታ ለዐቃቤ ሕግ መሰጠት አለበት፡፡

4. በሕግ ወይም በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት በሌላ ሁኔታ ካልተከለከለ በስተቀር የተመዘገበ ማስረጃ ግልባጭ ለተጠርጣሪ መሰጠት አለበት፡፡

### አንቀጽ 183 <u>ተጨማሪ ማስረጃ</u>

የቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት ለዚህ ንዑስ ክፍል አፈጻጸም ምስክርነቱ ወይም የማስረጃ ምንጭነቱ አስፈላጊ የሆነ ተጨማሪ ሰው ወይም አግባብነት ያለው አካል እንዲቀርብና የሚሰጠው የምስክርነት ቃል ወይም ሌላ ማስረጃ እንዲመዘገብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 184 <u>ምስክሮች እንዲቀርቡ ስለማሳወቅ</u>

በቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል ወይም ሌላ ማስረጃ የሰጠ ምስክር ወይም አግባብነት ያለው አካል ክሱ በሚሰማበት ፍርድ ቤት የመቅረብ ግዴታ እንዳለበት ፍርድ ቤቱ ማሳወቅ አለበት፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የራስ ዋስትና እንዲፈርም ያደርጋል፡፡

### አንቀጽ 185 <u>የመዝገብና ማስረጃ አላላክ</u>

በዚህ ንዑስ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ቀዳሚ ምርመራ ያደረገው ፍርድ ቤት መዝገቡን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት መላክ አለበት፡፡

**አንቀጽ 186 የመዝገብ ዝርዝር**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 183 ንዑስ አንቀጽ (2) ለዐቃቤ ሕግና ለተጠርጣሪ የሚሰጥ ግልባጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

2. መዝገቡ፡-

(ሀ) የመዝገቡ ቁጥር፣

(ለ) የወንጀሉ ዐይነት፣ የተፈጸመበትን ቀን እና እንደአግባብነቱ ወንጀሉ የተፈጸመበት ንብረት ዋጋ ወይም ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ልዩ ሁኔታ፤

(ሐ) ክስ ወይም የግል አቤቱታ ቀርቦ እንደሆነ የቀረበበትን ቀን፣

(መ) የክስ አቅራቢው ስምና አድራሻ፣

(ሠ) የሚታወቅ እንደሆነ የተጠርጣሪው ስም፣ አድራሻ፣ ሥራ፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ዜግነቱ፣ የቤተሰቡ ሁኔታ እና ሌላ አስፈላጊ መረጃ፣

(ረ) ተጠርጣሪው የተያዘበት ቀን ወይም እንዲያዝ የፍርድ ቤት ትእዛዝ የተሰጠበት ቀን፤

(ሰ)ተጠርጣሪው ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርድ ቤት የቀረበበት ቀን፤

(ሸ) የዐቃቤ ሕጉ ስምና አስፈላጊ ሲሆን የተጠርጣሪው ጠበቃ ስም፤

(ቀ) የተሰጠ ማንኛውም ቃል፤

(በ) የዐቃቤ ሕግና ሌላ የተመዘገበ ማስረጃ፤ እና

(ተ) ቀዳሚው ምርመራ የተካሔደበት ቀን፤

ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 187 የተጠርጣሪ አቆያየት**

1. በዋስትና መልቀቅን የሚመለከት የዚህ ሕግ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት ጉዳዩ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት እስኪሰማ ተጠርጣሪው ማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 181 ንዑስ አንቀጽ (1) ወንጀሎች የተጠረጠረ ሰው ቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ክስ ለመመሥረት የሚያስችል በቂ ምክንያት የለውም ብሎ ሲያምን ተጠርጣሪውን ለጊዜው በነፃ ሊያሰናብት ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪው የሚቆይበትን ሁኔታ የሚሰጠው ትእዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀደም ሲል የተሰጠ ሌላ ትእዛዝ ተፈጻሚነት ጸንቶ ይቆያል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## ስለ ዋስትና
## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 188 መርህ**

1. በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው በዋስ የመፈታት መብት አለው፡፡

2. በዚህ ሕግ ወይም በሌላ ሕግ ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በቅድመ ሁኔታ መፍታትን ጨምሮ የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. ዋስትና እንደነገሩ ሁኔታ በመርማሪ አካል ወይም በዐቃቤ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት ሊሠጥ ይችላል፡፡

4. የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደነገሩ ሁኔታ ሰነድን ለማቅረብ፣ ፍርድን ለማስፈጸም ወይም ከሌላ ተመሳሳይ ግዴታ ጋር በተያያዘ በሚፈረም የዋስትና ግዴታ ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተገባ የዋስትና ግዴታ በተለየ ውሳኔ ካልተሻረ ወይም ካልተሻሻለ በስተቀር በማንኛውም የምርመራ፣ ክስና የፍርድ ሒደትሒደት ተፈጻሚነት አለው፡፡

**አንቀጽ 189 ዋስትና የሚያስከለክል ወንጀል**

ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ የተጠረጠረበት ወይም የተከሰሰበት ወንጀል፡-

(ሀ) የወንጀሉ ቅጣት ጣሪያ አሥራ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ የሚያስቀጣ ሆኖ በሕገ መንግሥትና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዐት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 240 እና 241)፣ በተደራጀ ቡድን የተፈጸመ ወንጀል፣ ከባድ የሰው ግድያ፣ የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በሰው ዘር ላይ የተፈጸመ ወንጀል፣ የአስገድዶ መድፈር፣ በሕፃናት ላይ የተፈጸመ የወሲብ ጥቃት

ወንጀል፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወንጀል፣ ያለ ፍርድ የሞት ቅጣት ርምጃ መውሰድ፣ በሰባዓዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል፣

(ለ) የሽብርተኝነት ወንጀል፣ ወይም

(ሐ) የሙስና ወንጀል ሆኖ ቅጣቱ አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ የሚያስቀጣ፣

(መ) በዕድሜ ልክ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ፣

እንደሆነ የዋስትና መብት አይከበርለትም፡፡

## አንቀጽ 190 ዋስትና በፍርድ ቤት ስለሚከለከልበት ሁኔታ

ፍርድ ቤቱ፡-

(1) ተጠርጣሪው ወይም ተከሣሽ በዋስትና ቢለቀቅ፤

(ሀ) ከወንጀሉ አፈጻጸም፣ ከክሱ ብዛት፣ ክብደት እና የክስ ባህርያት፣

(ለ) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ቀደም ሲል በወንጀል ተከሶ የተቀጣ፣ የዋስትና ግዴታውን ያልተወጣ ወይምቀደም ሲል ክስ ቀርቦበት እንደሆነ የቀረበበት ክስ ብዛት የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ ባህሪያት፣

(ሐ) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ከሕግ ለመራቅ እና ከተጠያቂነት ለማምለጥ ያለው ዕድል እና ፣

በተፈለገ ጊዜና ቦታ ሊቀርብ የማይችል መሆኑን ሲያምን፣

(2) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በዋስትና ቢለቀቅ ሌላ ወንጀል ሊፈጽም ይችላል ተብሎ ሲገመት፣

(3) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ምስክርን በማስፈራራትና ማስረጃን በማጥፋት በፍትሕ አሰጣጥ ላይ እክል ይፈጥራል ተብሎ ሲታመን፤

(4) የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት ተጎጂውን ለሞት የሚያበቃ እንደሆነ፣

እንደሆነዋስትና ሊከለክል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 191** <u>ስለተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ</u>

1. ፍርድ ቤት ዋስትና ሲፈቅድ በዋስትና የተለቀቀው ሰው የዋስትና ግዴታው ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ፡-

(ሀ) ለአንድ  አካል በቋሚነት ሪፖርት እንዲያደርግ፣

(ለ) ፍርድ ቤቱበሚያዘው ጊዜና ቦታ እንዲቀርብ፣

(ሐ) ከተወሰነ አካባቢ እንዳይደርስ ወይም እንዳይርቅ፣

(መ) ከተጎጂ ወይም ከሌላ ተጠርጣሪ ጋር እንዳይገናኝ ወይም በማንኛውም ሁኔታ በማስረጃ ማሰባሰብ ላይ እንቅፋት እንዳይፈጥር፣

(ሠ) በምሥክር፣ በተጎጂ፣ በተጎጂ ቤተሰብ ላይ ዛቻ እንዳይፈፅም፣ እንዳያስፈራራ፤ በንብረት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ፣ ምስክር እንዳያባብል፣ ወይም ሌሎች የወንጀል ድርጊቶችን እንዳይፈፅም፣ ወይም

(ረ) ከፍርድ ቤቱ ፈቃድ ሳያገኝ ከሃገር እንዳይወጣ፣

(ሰ)በተመለከተ ተጨማሪ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. በዚህ ሕግ መሠረት መርማሪ  ወይም ዐቃቤ ሕግ ዋስትና ሲፈቅድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ)፣ (ለ)፣ (መ)፣ (ሠ) የተመለከቱ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ተጨማሪ ትእዛዝ  ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 192** <u>በመያዣ ትእዛዝ ላይ ዋስትናን ማመልከት</u>

1. ፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ ሲሰጥ በዚህ ሕግ መሠረት ተጠርጣሪው ዋስትና የማያስከለክለው መሆኑን ካመነ የሚሰጠውን የዋስትና ግዴታ በትዕዛዙ ላይ ሊያመላክት ይችላል፤ ተጠርጣሪው የዋስትና ግዴታውን ከፈጸመ  ወዲያውኑ መልቀቅ አለበት፡፡

2. የመያዣ ትዕዛዙ እንደአስፈላጊነቱ የዋስትናውን ዐይነትና መጠን፣ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎችን እና ሌሎች ግዴታዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡

3. የመያዣ ትዕዛዙን እንዲያስፈፅም የታዘዘ መርማሪ የተያዘው ሰው መለቀቁን ማሳወቅና  ስለዋስትና የተሰጠውን ትእዛዝ ለፍርድ ቤቱ መመለስ አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለዋስትና ግዴታ

**አንቀጽ 193** <u>**በዋስትና ለመለቀቅ የሚቀርብ ማመልከቻ**</u>

1. በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ በቃል ወይም በጽሑፍ ወይም በሌላ ማንኛውም አመች መንገድ ማመልከት ይችላል፤ በራሱ ማቅረብ የማይችል እንደሆነ ቤተሰቡ ወይም ወኪሉ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. ማመልከቻው በጽሑፍ የቀረበ እንደሆነ መፈረም አለበት፡፡ በጽሑፍ የሚቀርበው ማመልከቻ አቤቱታው የቀረበበትን ምክንያት በአጭሩ መግለጽና ማቅረብ የሚችለውን የዋስትና ዐይነት ማመልከት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ ለማንኛውም ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም የዋስትና ጥያቄ፡-

   (ሀ) ጉዳዩ በጊዜ ቀጠሮ በፍርድ ቤት እየታየ እንደሆነ የጊዜ ቀጠሮው ለቀረበለት ፍርድ ቤት፣

   (ለ) ክሱ ፍርድ ቤት ቀርቦ በመታየት ላይ እንደሆነ ክሱን ማየት ለጀመረው ፍርድ ቤት፣

መቅረብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 194** <u>**በማመልከቻ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ**</u>

1. ፍርድ ቤቱ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻ ሲቀርብለት ሳይዘገይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ውሳኔ ሲሰጥ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ወይም የሚቻል እንደሆነ ተጎጂ ፍርድ ቤቱ በቂ ነው ብሎ በሚሰጠው ጊዜ ውስጥ አስተያየቱን እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ፍርድ ቤቱም አስተያየቱን በተቀበለ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ውሳኔውን መስጠት አለበት፡፡

3. ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ  በጽሑፍ ሆኖ ምክንያቱንም መግለጽ አለበት፡፡

## አንቀጽ 195 <u>ዋስትናን መፍቀድ፣ ዐይነትና መጠንን መወሰን</u>

1. ፍርድ ቤት በዋስትና ግዴታ የመለቀቅ ጥያቄውን የተቀበለው እንደሆነ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የሚለቀቅበትን የዋስትና ግዴታ መወሰን አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፍርድ ቤቱ የሚወስነው የዋስትና ግዴታ የራስ ዋስትና፣ የገንዘብ፣ የሰው ወይም የንብረት የዋስትና ግዴታ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደሆነበዋስትና የተያዘ ስለመሆኑ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

3. ፍርድ ቤቱ ስለዋትና ግዴታው ዐይነትና መጠን ሲወስን፡-

    (ሀ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 193 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገጉ ሁኔታዎችን ፣

    (ለ) የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ ወይም ኃብትና የገቢ መጠን ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን በተፈለገበት ጊዜ እንዲቀርብ የሚያደርገው መሆኑን፤

    (ሐ) የዋሱ ኃብትና የገቢ መጠን፣ ባሕርይ እና ማኅበራዊ ሁኔታ፤

    በማመዛዘን መሆን አለበት፡፡

4. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በማንኛውም የዋስትና ግዴታ ሲለቀቅ መፈረም አለበት፡፡

5. የዋስትና ግዴታ ሲፈቀድ ከዚህ ሕግ ጋር በተያያዘው ቅፅ መሠረት ይሆናል፡፡

6. ፍርድ ቤት የሚወስነውን የዋስትና ግዴታ ወጥነት፤ ተገማችነት እና ትክክለኛነት በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 196 <u>ዋስትና ለማቅረብ ያልቻለ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ</u>

1. አመልካቹ የተጠረጠረው ወይም የተከሰሰው በቀላል ወንጀል እንደሆነ እና የተወሰነው የዋስትና ግዴታ የገንዘብ፣ የሰው፣ ወይም የንብረት ዋስትና ሆኖ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ይህንን ግዴታ ለመፈጸም አቅም የሌለው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን በማሻሻል ወይም በመለወጥ በራስ ዋስትና ከተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ ጋር እንዲለቀቅ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት  ዋስትና እንዲለቀቅ የተፈቀደለት ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የተወሰነውን የዋስትና ግዴታ መፈጸም የማይችል መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያረጋግጥ ግዴታውን ለመፈጸም አቅም እንደሌለው ይገመታል፡፡

3. ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሲወስን የዐቃቤ ሕግን ወይም የሚቻል እንደሆነ የተጎጂን አስተያየት መጠየቅ አለበት፡፡ ዐቃቤ ሕግ ወይም ተጎጂ ፍርድ ቤቱ በቂ ነው ብሎ በሚሰጠው ጊዜ ውስጥ አስተያየቱን መስጠት አለበት፤ ፍርድ ቤቱም እንደነገሩ ሁኔታ አስተያየቱን በተቀበለ ከአምስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ** 197 <u>ስለመልቀቅ</u>

1. ፍርድ ቤት ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በዋስትና ግዴታ እንዲለቀቅ ከወሰነ ተገቢውን ሥርዐት እንዲፈጽምና ከእሥር እንዲለቀቅ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

2. የመልቀቅ ትዕዛዙ የደረሰው ማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት ትዕዛዙ እንደደረሰው ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን ወዲያውኑ መልቀቅ አለበት፡፡

**አንቀጽ** 198 <u>በስህተት ወይም በማታለል የተሰጠ ዋስትና</u>

1. የዋስትና ግዴታው ሆን ብሎ በተፈጸመ የማሳሳት፣ የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት የተሠጠ መሆኑ ከታመነ  ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ሕግ ወይም በተጎጂ አመልካችነት በዋስትና  የተለቀቀው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ እንዲያዝ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

2. ፍርድ ቤት ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ወይም የሚቻል እንደሆነ ተጎጂው ሲቀርብ አስተያየቱን ከጠየቀ በኋላ  ዋስትናው የተሰጠው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተቱት ምክንያቶች መሆኑ ከተረጋገጠ የተፈቀደው ዋስትና በመከልከል ማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተደነገገው ውጭ በሆነ ሌላ ምክንያት የዋስትና ግዴታው የተሰጠ እንደሆነና ይኸው በፍርድ ቤቱ ከታመነ

የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ፣ የዐቃቤ ሕግ እና የሚቻል እንደሆነ የተጎጂን አስተያየት በመጠየቅ ፍርድ ቤት ተጨማሪ የዋስትና ግዴታ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤ የታዘዘውን የዋስትና ግዴታ ያልፈፀመ ወይም ለመፈጸም ያልቻለ እንደሆነ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ተጠርጣሪው ማረፊያ ቤት እንዲቆይ የተደረገ እንደሆነ በተጠረጠረበት ወንጀል ጥፋተኛ ከሆና የእሥራት ቅጣት ቢፈረድበት በዚህ ምክንያት በማረፊያ ቤት የቆየበት ጊዜ አይቆጠርለትም፡፡

**አንቀጽ 199** <u>**የዋስትና ግዴታ ቀሪ መሆን**</u>

1. በዋስትና የተለቀቀው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በነፃ የተለቀቀ ወይም የተፈረደበት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የዋስትናው ግዴታ ገቢ የማይሆንበት ምክንያት አለመኖሩን አረጋግጦ የዋስትና ግዴታው ቀሪ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል፡፡
2. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ለጊዜው የተለቀቀ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ የዋስትና ግዴታውን ሊያሻሽል ወይም እንዲቀጥል ወይም የዋስትናው ግዴታ ገቢ የማይሆንበት ምክንያት አለመኖሩን አረጋግጦ ቀሪ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል፡፡
3. የዋስትና ግዴታ የፈረመው ዋስ የሞተ እንደሆነ ዋስትናው ዋሱ ከሞተበት ቀን ጀምሮ ቀሪ ይሆናል፡፡ ሟች ከመሞቱ በፊት የዋስትና ግዴታውን በአግባቡ መወጣቱ ወይም ግዴታውን ያልተወጣው በበቂ ምክንያት መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ የተያዘው ንብረት ከዋስትናው ግዴታ ነጻ ይሆናል፡፡ በዋስትና ግዴታ የተለቀቀውም ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ሌላ አዲስ ዋስ እንዲጠራ ፍርድ ቤቱ ያዛል፡፡
4. ዋሱ በሕግ ችሎታ ካጣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ተፈጻሚነት አለው፡፡

**አንቀጽ 200** <u>**አዲስ ፍሬ ነገር**</u>

1. የዋስት ጥያቄው በተፈቀደ ወይም በተከለከለ ጊዜ ያልታወቀ ወይም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የተፈጠረ አዲስ ፍሬ ነገር ያለ እንደሆነ በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ሕግ ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት የዋስትና ውሳኔውን መርምሮ እንደነገሩ ሁኔታ ተጠርጣሪው

ወይም ተከሳሹ የዋስትና መብቱ ተከልክሎ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ወይም በዋስ እንዲለቀቅ ወይም አዲስ የዋስትና ግዴታ እንዲገባ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ ትእዛዙን ከመስጠቱ በፊት የዐቃቤ ሕግን፣ የተጠርጣሪውን ወይም የተከሳሽን እና የሚቻል እንደሆነ የተጎጂውን ሀሳብ መጠየቅ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለዋስትና ግዴታ፣ ግዴታን አለመፈጸምና ማውረድ

### አንቀጽ 201 የዋስትና ግዴታ

1. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በራስ ዋስትና ወይም በሌላ የዋስትና ግዴታ የተለቀቀ እንደሆነ ፍርድ ቤት በሚወስነው ማንኛውም ጊዜና ቦታ ወይም ጉዳዩ ለመስማት በሚሰጠው ቀጠሮ የመቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 205 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋሱ ወይም ዋሶቹ በዋስትና ግዴታ የተለቀቀውን ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ፍርድ ቤት በሚወስነው በማንናቸውም ጊዜና ቦታ ወይም ጉዳዩ ለመስማት በሚሰጠው ቀጠሮ እንዲቀርብ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3. የተጠርጣሪ ወይም የተከሳሽ ዋሶች ከአንድ በላይ የሆኑ እንደሆነ የጋራና የተናጠል የዋስትና ግዴታ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

### አንቀጽ 202 የዋስትና ግዴታን አለመፈጸም

1. በዋስትና ግዴታ የተለቀቀ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ፡-

   (ሀ) በቀጠሮው ቀን የዋስትና ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነና ወይም ከወዲሁ በፈቃዱ እንደማይቀርብ ከታወቀ ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ተይዞ እንዲቀርብና ዋሱም ቀርቦ እንዲያስረዳ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

   (ለ) በቀጠሮ ቀን የዋስትና ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ እና ዋሱ በራሱ የቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ያልቀረበበትን ምክንያት ዋሱ እንዲያስረዳ ያደርጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እና (ለ) በተደነገገው መሠረት ዋሱ የዋስትና ግዴታውን ያልተወጣበት ምክንያት በበቂ ሁኔታ ካላስረዳ በዋስትና ግዴታ የተያዘውን ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ ትእዛዝ

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እና (ለ) በተደነገገው መሠረት ዋሱ የዋስትና ግዴታውን ያልተወጣበት ምክንያት በበቂ ሁኔታ ካላስረዳ እና በዋስትና ግዴታ የተያዘው ንብረት እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ በዋስትና ግዴታው ልክ ገንዘቡ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ፍርድ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡ ንብረቱ ከመሸጡ በፊት የዋስትና ገንዘቡን ገቢ ካደረገ የሽያጭ ሒደቱ ሊቋረጥ ይችላል፡፡

4. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት ላይ የተገለጸውን ግዴታ የጣሰ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣ 3) በተደነገገው መሠረት ዋሱ እንዲያስረዳ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ዋሱ ያለቀረበ እንደሆነ ወይም ዋሱ ቀርቦ በቂ ምክንያት ያላቀረበ እንደሆነ በዋስትና ግዴታ የተያዘውን ገንዘብ ወይም ንብረት እንደሆነ ተሸጦ በዋስትና ግዴታው ልክ ገንዘቡ ለመንግሥት ገቢ ማድረግን ጨምሮ እንደሁኔታው ዋስትናው እንዲቀር ወይም እንዲሻሻል ወይም ሌላ ተገቢ መስሎ የታየውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3) እና (4) መሠረት የተሰጠው ትእዛዝ እንደነገሩ ሁኔታ ፍርድ ቤቱ በራሱ ወይም ዐቃቤ ሕግ ወይም ሌላ አስፈጻሚ አካል እንዲያስፈጽም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተ ቅድመ ሁኔታን መጣሱን የሚመለከተው አካል ጥያቄ ካቀረበ እና ፍርድ ቤቱ ካመነበት የተሰጠው ዋስትና እንዲነሳ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

7. በዚህ ሕግ አንቀጽ 192 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በተሠጠ ዋስትና የተጣሉ ቅድመ ሁኔታዎች የተጣሱ እንደሆነ መርማሪው ወይም ዐቃቤ ሕጉ እንደሁኔታው ዋስትናው እንዲሻሻል ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ ሕግ አንቀጽ 192 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ፣ ረ፣ ሰ) የተደነገጉ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ በፍርድ ቤት እንዲጣል ሊያቀርብ ይችላል፤ ፍርድ ቤቱም በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት ተገቢውን ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 203** <u>የዋስትና ግዴታ የሚወርድበት ሁኔታ</u>

1. ዋሱ በማንኛውም ሁኔታ ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን በማቅረብ የዋስትና ግዴታው እንዲወርድለት ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡
2. ዋሱ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ይጠፋል ብሎ ከጠረጠረ ተይዞ እንዲቀርብና ዋስትናው እንዲወርድለት ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ተይዞ እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
3. ዋሶቹ ከአንድ በላይ ሲሆኑ የዋስትና ግዴታ እንዲወርድላቸው በጋራ ወይም በተናጠል ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ፡፡
4. ዋስትና ተፈቅዶለት የነበረው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ እንደቀረበ ፍርድ ቤቱ የዋሱን የዋስትና ግዴታ ወዲያውኑ ያወርዳል፡፡
5. ፍርድ ቤቱ የዋስትና ግዴታውን ካወረደ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ሌላ የዋስትና ግዴታ እንዲያቀርብ ወይም ይህንንም መፈጸም ያልቻለ እንደሆነ በማቆያ ቤት ወይም ማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 204** <u>ይግባኝ ማቅረብ</u>

1. በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄን በመቀበል ወይም ባለመቀበል ወይም በዋስትና ግዴታው ዐይነት ወይም መጠን ላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ ወይም ውሣኔ ላይ ይግባኝ ሊጠየቅበት ይችላል፡፡
2. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ሥልጣን ላለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የውሳኔውን ወይም የትዕዛዙን ግልባጭ በደረሰው በሃያ ቀን ውስጥ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡ በይግባኝ ማመልከቻው ላይ የይግባኙን ምክንያት መግለጽ አለበት፡፡
3. የይግባኝ ጥያቄውን የሚያቀርበው ዐቃቤ ሕግ እንደሆነ ይህንኑ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ እንደተሰጠ ወዲያውኑ በቃል ወይም በጽሑፍ ትዕዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ዐቃቤ ሕግ በይግባኝ ማመልከቻ ላይ የይግባኙን ምክንያት በመግለጽ የውሳኔው ግልባጭ በደረሰው ከአምስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 205** **ውሳኔን ወይም ትእዛዝን ማገድ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 206 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ከሚቀርበው የይግባኝ ማመልከቻ ጋር ወይም በተናጠል ዐቃቤ ሕግ ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የተያዘው ሰው በዋስትና እንዲለቀቅ የተሰጠ ትእዛዝ ታግዶ እንዲቆይ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት የተያዘው ሰው በዋስትና እንዲለቀቅ የተሰጠው ትእዛዝ ታግዶ እንዲቆይ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ፕሬዘዳንቱ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት ባሕርይዋስትናው ቢፈቀድ ወይም ቢታገድ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

3. በዚህ ሕግ አንቀጽ 182 ንዑስ አንቀጽ (1) እና አንቀጽ 201 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት የዋስትና መብቱ ተከልክሎ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ የተሰጠበት ተጠርጣሪ ይኸው ትእዛዝ እንዲታገድለት ለፍርድ ቤቱ ፕሬዘዳንት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ፕሬዘዳንቱም ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) በተደነገገው መሠረት በፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት የሚሰጥ የዕግድ ትእዛዝ ከአሥር ቀናት ላልበለጠ ጊዜ የሚቆይ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 206** **የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ**

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የይግባኝ ማመልከቻው በቀረበ ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## በምርመራ መዝገብ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ
## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**አንቀጽ 207** **የዐቃቤ ሕግ የመወሰን ሥልጣን**

1. በምርመራ መዝገብ ላይ የመወሰን ሥልጣን የዐቃቤ ሕግ ብቻ ነው፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ፡-

(ሀ) ምርመራ እንዲቋረጥ፣

(ለ) የተቋረጠ ምርመራ እንዲቀጥል፣

(ሐ) የምርመራ መዝገብ እንዲዘጋ፣

(መ) መሪ ትእዛዝ እንዲጠየቅበት፣

(ሠ) ክስ እንዳይመሠረት ወይም እንዲመሠረት ወይም እንዲቋረጥ፣ ወይም እንዲነሳ፣ ወይም

(ረ) በዚህ ሕግ መሠረት ጉዳዩ በዕርቅ፣ በድርድር ወይም በሌላ አማራጭ ዘዴዎች እንዲታይ፣

ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. ዐቃቤ ሕግ በምርመራ መዝገብ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ በቂ ማስረጃ እና የሕዝብ ጥቅም መኖሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

4. ክስ ለመመሠረት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ቢኖርም የሕዝብን ጥቅም የማያስከብር መሆኑ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከታመነ ክስ ላይመሠርት ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ወንጀልን ላይ ክስ ለመመሠረት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ሲኖር እና የግል ክስ እንዲቀርብ ዐቃቤ ሕግ ከፈቀደ የግል ተበዳዩ ወይም ወኪሉ ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

6. ዐቃቤ ሕግ ምርመራው በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ በዚህ አንቀጽ መሠረት ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 208 የዐቃቤ ሕግ ሥራ ሚዛናዊ መሆን**

ዐቃቤ ሕግ በምርመራ መዝገብ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ከማንኛውም ዐይነት ተፅዕኖ፣ ግፊት፣ ስጋት፣ ወይም ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን አለበት፡፡ ውሳኔውም በሕግና በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በሚሰጥ መመሪያ ብቻ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## በምርመራ መዝገብ ላይ ስለመወሰን

**አንቀጽ 209 የምርመራ መዝገብን መዝጋት**

1. ዐቃቤ ሕግ ተጠርጣሪው፡-

(ሀ) የሞተ እንደሆነ፣

(ለ) ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ዕድሜው ዘጠኝ ዓመት ያልሞላው እንደሆነ፣

(ሐ) የተጠረጠረበት ጉዳይ ወንጀል ካልሆነ፣

(መ) የፈጸመየፈጸመው ወንጀል በይርጋ የታገደ ወይም ምኅረት የተደረገለት እንደሆነ፣

(ሠ) ከዚህ ቀደም ተከሶ ነፃ የወጣ ወይም የጥፋተኛነት ውሳኔ የተሰጠበት ወይም በፍርድ ቤት ጉዳዩ እየታየ እንደሆነ ወይም ጉዳዩ በዕርቅ፣ በድርድር ወይም በሌላ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ውሳኔ ያገኘ እንደሆነ፣

እንደሆነእንደሆነየምርመራ መዝገብን መዝጋት አለበት፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ረ) መሠረት ውሳኔ ሲሰጥ ተጠርጣሪው በህክምና ተቋም ወይም በሌላ ቦታ ስለሚቆይበት ሁኔታ ተገቢውን ውሳኔ የመስጠትና ውሳኔው እንዲፈጸም ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 210** <u>መሪ ትእዛዝ መጠየቅ</u>

በምርመራ መዝገብ ላይ አግባብነት ያለው ውሣኔ ለመስጠት አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም ዐቃቤ ሕግ አጠራጣሪ ስለሆነው የሕግ ወይም የማስረጃ ጉዳይ ምክንያት በዝርዝር በመግለጽ መሪ ትእዛዝ እንዲሰጥበት የበላይ ዐቃቤ ሕግን መጠየቅ ይችላል፡፡ የበላይ ዐቃቤ ሕግ የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ተገቢ በሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 211** <u>የምርመራ መዝገብን ሥልጣን ላለው አካል መላክ</u>

1. ዐቃቤ ሕግ በምርመራ መዝገቡ ላይ ውሳኔ ለመሥጠት ሥልጣን የሌለው እንደሆነ መዝገቡን ሥልጣን ላለው የፍትሕ አካል መላክ አለበት፡፡

2. የምርመራ መዝገቡ ተደራራቢ ሥልጣን የሚመለከት እንደሆነእንደሆነ ከባዱን የወንጀል ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ያለው አካል በመዝገቡ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም ከባዱን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ያለው አካል ለክሱ ውጤታማነት፣ ቅልጥፍና እና ተደራሽነት ምርመራውን ያከናወነው ዐቃቤ ሕግ በመዝገቡ ላይ እንዲወስን ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) በተደነገገው መሠረት ለመወሰን አጠራጣሪ ሲሆን በመዝገቡ ላይ እንደ አግባብነቱ ፍትሕ ሚኒስቴር ወይም የክልል ፍትሕ ቢሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 212 ክስ አለመመሥረት**

ዐቃቤ ሕግ፡-

1. ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ የሌለ እንደሆነ፣
2. በቂ ማስረጃ ቢኖርም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በዚህ ሕግ አንቀጽ ---- (ቀጣዩ) መሠረት ክስ እንዳይቀርብ ከወሰነ፣
3. ተጠርጣሪው በሌለበት ክሱ የማይታይ እንደሆነ፣
4. ተጠርጣሪው ያለመከሰስ ልዩ መብት ያለው ሆኖ ይህ መብቱ ያልተነሳ እንደሆነ፣ ወይም
5. ተጠርጣሪው የተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት በግል አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ የሚያስቀጣ ሆኖ ተጠርጣሪውን ለማግኘት የማይቻል መሆኑን ሲያረጋግጥ
6. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 48 መሠረት ለተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት ፍፁም ኢ-ኃላፊ ስለመሆኑ በህክምና የተረጋገጠ እንደሆነ፣ ወይም
7. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 68 እና 70 መሠረት የተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት የተፈቀደ ወይም የማያስቀጣና ይቅርታ የሚያሰጥ እንደሆነ፤

ክስ ያለመመመሥረት ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 213 ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ አለመመሥረት**

1. ዐቃቤ ሕግ፡-

   (ሀ) ተጠርጣሪው በዕድሜ መጃጀት ወይም በማይድን በሽታ ወይም በአዕምሮ ልልነት ምክንያት ጉዳዩን በፍርድ ቤት መከታተል የማይችል እንደሆነ፣

   (ለ) ወንጀሉ ቀላል እሥራት ወይም በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ሆኖ በተበዳይና በተጠርጣሪ መካከል ዕርቅ ከተፈጸመ፣

(ሐ) ወንጀሉ ቀላልና ጉዳቱ አነስተኛ ሆኖ ተጠርጣሪው ጥፋቱን በማመን ተበዳዩን ወይም ስለተበዳዩ ባለመብት የሆነን ይቅርታ ከጠየቀ እና ከካሰ፣

(መ) ወንጀሉ ቀላል እና ጉዳቱ አነስተኛ ሆኖ ተጠርጣሪው ድርጊቱን የፈጸመየፈጸመው የወንጀል ባሕርይ እንዳለው ፍፁም እንደሆነ የግንዛቤ ማጣት የመነጨ እንደሆነ፣ ወይም

(ሠ) ወንጀል ቀላል ሆኖ ክሱ ቢመሠረት የሚወሰነው ቅጣት ተግሳጽ፣ ማስጠንቀቂያ ወይም ወቀሳ መሆኑ በግልጽ በሕግ ከተደነገገ እና ዐቃቤ ሕግ ካመነ፣

ለሕዝብ ጥቅም ሲል ክስ ያለመመሠረት ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደጉዳዩ ልዩ ሁኔታ ፍትሕ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት፡-

(ሀ) ተጠርጣሪው የፈጸመየፈጸመው የወንጀል ድርጊት በባህላዊ ሕጎችና ተቋማትበተሻለ መፍትሔ የሚያገኝ እንደሆነ፣

(ለ) ክሱ ቢመሠረት የዓለም አቀፍ ግንኙነትን ወይም ብሔራዊ ደኅንነትን የሚጎዳ እንደሆነ፤

(ሐ) ወንጀሉ በማንኛውም ምክንያት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በመቆየቱ ወቅታዊነቱን ወይም አስፈላጊነቱን ካጣ፤

(መ) የክሱ መመሥረት ተመጣጣኝና ሚዛናዊ ያልሆነ የጎንዮሽ ጉዳት የሚያስከትል እንደሆነ፣

(ሠ) ተጠርጣሪው በተፈጸመው የወንጀል ድርጊት ውስጥ ያለው ተሳትፎ አነስተኛ እንደሆነ፣ ወይም

(ረ) በሌላ ተመሣሣይ መስፈርት፣

መሠረት ዐቃቤ ሕግ ለሕዝብ ጥቅም ሲል ክስ ያለመመሠረት ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 214 <u>በምርመራ መዝገብ መዝጋት ወይም ክስ አለመመሠረት የሚኖር ሥነ ሥርዐት</u>**

1. ዐቃቤ ሕግ ፡-

   (ሀ) ክስ ለመመሠረት የሚያስችል በቂ ማስረጃ የለም ብሎ የምርመራ መዝገቡን ከዘጋ እና ወንጀሉ ስለመፈጸሙ እንደሆነዐቃቤ ሕጉ ሲያምን ምርመራው እንዲቀጥል ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

   (ለ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 216 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ተጠርጣሪው ያለመከሰስ መብቱ እንዲነሳ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የምርመራ መዝገቡ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ምክንያት የሆነውን የሚያስለውጥ ሁኔታ ወይም ተቃራኒ ማስረጃ የተገኘ እንደሆነ መዝገቡ እንደገና እንዲንቀሳቀስ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገቡን ከዘጋ ወይም ክስ ሳይመሠርት የቀረ እንደሆነ እና ተጠርጣሪው በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ እንዲለቀቅ ትእዛዝ ይሰጣል፤ የጊዜ ቀጠሮውን ለሚከታተለው ፍርድ ቤት እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

4. ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገብ መዝጋት ወይም የክስ አለመመሠረት ውሳኔ ሲሰጥ ከጉዳዩ ጋር የተያዘ ኤግዚቢት ወይም ሌላ ንብረት ላይ በሕግ መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

5. ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገብ መዝጋት ወይም የክስ አለመመሠረት የሰጠውን ውሳኔ ከነምክንያቱ በጽሑፍ ለበላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማሳወቅ አለበት፡፡ ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ መሠረት ውሳኔ ሲሰጥ ለመርማሪ፣ ለተጎጂ፣ ለአመልካች እና ለተከሳሽ በግልባጭ ያሳውቃል፡፡

6. የበላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የደረሰውን ውሳኔ ለማሻሻል ወይም ለመሻር በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን በአጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን ሊያሻሽል ወይም መሻር ይችላል፡፡

7. ዐቃቤ ሕግ የግል ተበዳይ የግል ክስ እንዲያቀርብ ከፈቀደ ውሳኔውን የግል ክስ ለማቅረብ መብት ላለው ሰው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለዕርቅ አፈጻጸም

**አንቀጽ 215 መርህ**

1. ዕርቅ በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስቀጣ ወይም እስከ ሦስት ዓመት በሚያስቀጣ ቀላል የወንጀል ዐይነት ላይ ሊደረግ ሆኖ ክስ ለመመሥረት የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡

2. ዕርቅ የሚደረገው ተጠርጣሪው ጥፋቱን አምኖ በመጸጸት ተጎጂን ይቅርታ የጠየቀ ወይም በዕርቅ ለመጨረስ የተስማማ እና የተጎጂን ፈቃድ ያገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**አንቀጽ 216 ዕርቅ የሚደረግበት ሥርዐት**

1. የዕርቅ ስምምነት የፍርድ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ተጠርጣሪ ወይም ተጎጂ ጥያቄ ሲያቀርብ፣ በመርማሪ ወይም በዐቃቤ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት አነሳሽነት አስተያየት ሲቀርብ ሊጀመር ይችላል፡፡

2. ዕርቅ በተጠርጣሪውና በተጎጂው በራሳቸው፣ በሌላ ሦስተኛ ወገን አደራዳሪነት ወይም በመርማሪ፣ በዐቃቤ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት አስማሚነት ሊካሄድ ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተጠርጣሪው ወይም በተጎጂው ጥያቄ ከቀረበ ጥያቄው የቀረበለት መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤትጉዳዩ በዕርቅ ስምምነት እንዲያልቅ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ ተጠርጣሪውና ተጎጂው በራሳቸው ወይም በሌላ ሶስተኛ ወገን አደራዳሪነት ዕርቁን ለመፈጸም ከተስማሙ ጉዳዩን በዕርቅ እንዲጨርሱ ከተፈቀደላቸው ቀን ጀምሮ ባሉ አሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ስምምነታቸውን ዕርቁ እንዲካሔድ ለፈቀደው አካል ማቅረብ አለባቸው፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የዕርቅ ስምምነት እንዲደረግ በመርማሪ ወይም በዐቃቤ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት ሐሳብ ከቀረበ እና ተጠርጣሪውና ተጎጂው ከተስማሙ ዕርቁ ወዲያውኑ ይካሔዳል፤ የዕርቅ ስምምነቱን ለማካሔድ ተጨማሪ ጊዜ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት ከአሥር ቀናት ያልበለጠ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

6. የዕርቅ ስምምነቱ እንደተፈጸመ ወይም እንደቀረበ፡-

(ሀ) መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ የስምምነት ሠነዱን በመመዝገብ ምርመራው እንዲቋረጥ ያደርጋል፡፡

(ለ) ዐቃቤ ሕግ የስምምነት ሠነዱን በመመዝገብ መዝገቡን ይዘጋል፤ ክስ ተመሥርቶ እንደሆነም ክሱን ያነሳል፡፡

(ሐ) ፍርድ ቤት ጉዳዩን እያየ እንደሆነ ሠነዱዕርቁን በመመዝገብ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ መሠረት በዕርቅ ስምምነት ያለቀ ጉዳይ ላይ በማንኛውም ጊዜ ክስ ሊቀርብበት አይችልም፤ ጉዳዩ በዕርቅ ስምምነት ያላለቀ እንደሆነ የምርመራ ወይም የክስ መስማት ሒደቱ ይቀጥላል፡፡

8. ዓለምመርማሪ ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ ሕግ አንቀጽ 222 የተደነገገውን ክልከላ ማረጋገጥ አለበት፡፡ ፍትሕ ሚኒስቴር ወይም ፍትሕ ቢሮ በምርመራና ክስ ሂደት የእርቅ አፈጻጸምን የሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 217 <u>ክልከላ</u>**

1. በዚህ ክፍል የተደነገገው ቢኖርም ደጋጋሚ ወንጀለኞች በተጠረጠሩበት ወይም በተከሰሱበት ወንጀል የዕርቅ ስምምነት ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

2. መርማሪ፣ ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት ጉዳዩ በዕርቅ እንዲያልቅ አስተያየት ሲያቀርብ ተጠርጣሪ እና ተጎጂ የዕርቅ ስምምነት እንዲፈጽሙ በማሰብ ማስገደድ ወይም የተጠርጣሪውን ወይም የተጎጂውን መብትና ጥቅም በሚጻረር አኳኋን ስምምነቱን ማስፈጸም የለባቸውም፡፡

3. በዚህ ክፍል መሠረት የሚደረግ ስምምነት ሕገ መንግሥቱን፣ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሠነዶች መርሆች እና ሌሎች ሕጎች የማይቃረን መሆኑን እንደነገሩ ሁኔታ መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## የጥፋተኝነት ድርድር

**አንቀጽ 218 ዓላማ**

የጥፋተኝነት ድርድር ዓላማ፡-

(1) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ለተፈጸመው የወንጀል ድርጊት በራሱ ነጻ ፈቃድ የእምነት ቃል እንዲሰጥ፣ እንዲጸጸት እና እንዲታረም፤

(2) የወንጀል ፍትሕ ሒደቱን ውጤታማነትማሳደግ፤

(3) በተከሳሽ፣ በተጎጂ እና በምስክር ሥነ ልቦና ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተጽእኖ ለመቀነስ፤

(4) የወንጀል ፍትሕ ሥርዐቱን እና በሒደቱ ተካፋይ የሆኑ አካላትን ጊዜና ወጪ መቀነስ፤

መሆን አለበት፡፡

**አንቀጽ 219 መርህ**

1. የጥፋተኝነት ድርድር ፍርድ ቤት ማስረጃ ከመስማቱ በፊት በማንኛውም የወንጀል ጉዳይ ላይ ሊካሔድ ይችላል፡፡

2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 229 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጥፋተኝነት ድርድር በተጠርጣሪው ወይም በተከሳሽ ነፃ ፈቃድ ሆኖ ጠበቃው ባለበት መካሔድ አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዐቃቤ ሕግ ከተጠርጣሪ ወይም ከተከሳሹ ጋር ድርድር ሲያደርግ ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማድረግ የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

4. የጥፋተኝነት ድርድር ስምምነት ለፍርድ ቤት በጽሑፍ ቀርቦ ካልጸደቀ በስተቀር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 220 የዐቃቤ ሕግ ሥልጣን**

የጥፋተኝነት ድርድር እንዲካሔድ የመወሰን፣ የድርድሩን ስምምነት በፍርድ ቤት አቅርቦ ማጸደቅና አፈጻጸሙን የመከታተል ሥልጣን የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡

**አንቀጽ 221 ቅድመ ሁኔታ**

የጥፋተኝነት ድርድር፡-

1. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ድርድሩን ለማካሔድ ፈቃደኝነቱን ሲገለጽ፣
2. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ድርድር የሚካሔድበትን ወንጀል መፈጸሙን ያመነ እና ኃላፊነት የሚወስድ እንደሆነ፣ እና
3. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ስለ ድርድሩ ሒደትና ውጤት በጠበቃ የሚወከልና የሕግ ምክር የሚያገኝ እንደሆነ፣
4. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ሕገ መንግሥታዊ መብቱን ለመተው የተስማማ ወይም የፈቀደ እንደሆነ

ሊካሔድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 222 ድርድር አጀማመር**

1. ዐቃቤ ሕግ ክስ ላለመመሥረት ከወሰነ በቂ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ እና በዚህ ሕግ አንቀጽ 223 የተመለከቱ ዓላማዎችን ያሳካል ብሎ ሲያምን ለድርድር ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ፈቃደኛ መሆኑን በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ድርድሩን ለማካሔድ ፈቃደኛ መሆኑን ጥያቄው በደረሰው በአምስት ቀን ውስጥ በጽሑፍ መግለጽ አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ፈቃደኝነቱን ካልገለጸ ድርድሩን ለማካሔድ እንዳልተስማማ ይቆጠራል፡፡

3. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ድርድር ለማካሔድ ለዐቃቤ ሕግ ሊያመለክት ይችላል፤ ዐቃቤ ሕግም በማመልከቻው ላይ ውሳኔውን ይወስናል፡፡

4. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር ዐቃቤ ሕግ የጥፋተኝነት ድርድር ለማካሔድ ከወሰነ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ፈቃደኛነቱን ከገለጸበት ወይም የተጠርጣሪን ወይም የተከሳሽን ማመልከቻ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ

በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ የድርድር ስምምነቱ ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 223 <u>ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ማወቅ የሚገባው ጉዳይ</u>**

ዐቃቤ ሕግ ወይም የተጠርጣሪ ወይም የተከሳሽ ጠበቃ ድርድር ሲካሔድ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ፡-

(1) ድርድሩን በነፃ ፈቃዱ ማካሔድ እንደሚችል፣

(2) የሚቀርብበትን ወይም የቀረበበትን የክስ ዐይነት፣ ይዘት፣ ብዛት እና ሊያስቀጣው የሚችለውን ቅጣት፤

(3) ድርድር ቢያካሔድ ሊያገኝ የሚችለውን መብትና ጥቅም፤

(4) በድርድሩ ሒደት መሳተፍ ያለበት መሆኑን፤

(5) በድርድሩ የሚገኝ ስምምነት በፍርድ ቤት ከፀደቀ ተፈጻሚ እንደሚሆን፣ እና

(6) የድርድሩን ሒደት፣ ውጤት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮችን፣

መረዳቱን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 224 <u>ጠበቃ በሌለበት የጥፋተኝነት ድርድር ማካሔድ</u>**

1. <u>በመካከለኛ እና በከባድ ወንጀሎች የጥፋተኝነት ድርድር ያለጠበቃ ሊካሔድ አይችልም፡፡</u>

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የተጠረጠረበት ወይም የተከሰሰበት ወንጀል ቀላል ሆኖ ድርድሩን ለማካሔድ ጠበቃ እንደማያስፈልገው በጽሑፍ ለዐቃቤ ሕግ ከገለጸ ድርድሩ ያለጠበቃ ሊካሔድ ይችላል፡፡

3. በዚህ ሕግ አንቀጽ 224 ንዑስ አንቀጽ (4) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የድርድሩን ስምምነት መቀበሉን በፈቃዱ ካላረጋገጠ የድርድሩ ውጤት ተቀባይነት የለውም፡፡

**አንቀጽ 225** <u>ጠበቃ ለማቆም አቅም አለመኖር</u>

1. ድርድር ለማካሔድ ጠበቃ ለማቆም የገንዘብ አቅም የሌለው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በመንግሥት ወጭ ጠበቃ ይመደብለታል፡፡
2. ፍትሕ ሚኒስቴር ወይም ፍትሕ ቢሮ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ነፃ የሕግ አገልግሎት ስለሚያገኝበት አግባብ ሥርዐት ይዘረጋል፡፡

**አንቀጽ 226** <u>የተጎጂ ተሳትፎ</u>

1. ዐቃቤ ሕግ ድርድር ሲካሔድ የተጎጂውን አስተያየት መጠየቅ አለበት፤ አስፈላጊ እንደሆነ በድርድሩ ሒደት እንዲገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ድርድር የሚካሔድበት የወንጀል ጉዳይ የፍትሐብሔር ኃላፊነትን የሚያስከትል እንደሆነ እና ዐቃቤ ሕግ ከተጎጂ ውክልና ካገኘ የፍትሐብሔር ኃላፊነትን በተመለከተ ድርድር ማካሔድ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚደረገው ድርድር ለተጎጂው ሊከፈል የሚገባውን የጉዳት ካሣና ሌላ ወጭ ማካተት አለበት፡፡ የጉዳት ካሣ መጠን እና ሌላ የወጭ ዝርዝር በዐቃቤ ሕግ መቅረብ አለበት፡፡
4. የወንጀል ጉዳዩ በመንግሥት ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ውክልና ሳያስፈልገው ድርድር ሊያካሒድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 227** <u>ማስረጃን ስለማስታወቅ ወይም ስለመግለጽ</u>

በዚህ ሕግ ወይም በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጥፋተኝነት ድርድር በሚካሔድበት ወቅት ዐቃቤ ሕግ በተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ላይ የሚያቀርበውን ማስረጃ ለተጠርጣሪው ወይም ለተከሳሹ ወይም ለጠበቃው መግለጽ አለበት፡፡

**አንቀጽ 228** <u>በጥፋተኝነት ድርድር ስለመገኘት</u>

1. የጥፋተኝነት ድርድር ሲካሔድ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በድርድር ሒደቱ ላይ በአካል መገኘት አለበት፡፡ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በሌለበት በተካሔደ ድርድር የተደረሰ ስምምነት ዋጋ አይኖረውም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መገኘት በማይችልበት ጊዜ ጠበቃው

እሱን ተክቶ እንዲደራደር በጽሑፍ ከፈቀደ ድርድሩ በዐቃቤ ሕግና በተጠርጣሪው ወይም በተከሳሹ ጠበቃ መካከል ሊካሔድ ይችላል፡፡

3. ድርድሩ የሚካሔደው ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በሚረዳው ቋንቋ ካልሆነ ወይም መስማት ወይም መናገር የተሳነው እንደሆነ በመንግሥት ወጪ አስተርጓሚ ይመደብለታል፤ አስተርጓሚ ካልተመደበለት ድርድሩና በድርድሩ የተደረሰበት ስምምነት ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 229** <u>**ኃላፊነትና የተከለከለ ድርጊት**</u>

1. የተጠርጣሪ ወይም የተከሳሽ ጠበቃ ከዐቃቤ ሕግ ጋር የጥፋተኝነት ድርድር ሲያካሔድ ሕግን፣ የጥፋተኝነት ድርድር ዓላማን፣ የጉዳዩን ሁኔታ፣ የደንበኛውን መብትና ጥቅም እና  የሙያ ሥነ ምግባርን ማክበር አለበት፡፡

2. ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ድርድር እንዲያካሔድ ወይም ከድርድሩ የሚገኝ ውጤት እንዲቀበል በማሰብ የመደለል፣ እንዲደለል የማድረግ፣ ከድርድሩ ሊገኝ የማይችል የተስፋ ቃል የመስጠት፣ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገርን አስመልክቶ በማስረጃ የተደገፈ ፍሬ ነገር እና ሌሎች ተመሳሳይ የሆኑ ማንኛውንም ድርጊት መፈጸም ወይም እንዲፈጸም ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

3. የጥፋተኛነትን ድርድር ሕግን፣ የጥፋተኝነት ድርድር ዓላማን፣ የሙያ ሥነ ምግባርን እንዲሁም የተጠርጣሪውን ወይም የተከሳሹን መብትና ጥቅም በሚጻረር አኳኋን ማካሔድ የተከለከለ ነው፡፡

4. የጥፋተኝነት ድርድር ሲካሔድ ተጠርጣሪው ወይም ተካሣሹ ሆን ብሎ የማታለል፣ የማሳሳት፣ የማጭበርበርና ሌላ ሕገ ወጥ ድርጊትን መፈጸም የለበትም፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)-(3) የተመለከቱ ክልከላዎችን በመተላለፍ የተገኘ ስምምነት ተቀባይነት የለውም፡፡

**አንቀጽ 230** <u>**የጥፋተኝነት ድርድር ይዘትና ፎርም**</u>

1. የጥፋተኛነት ድርድር በክስ ብዛት ወይም በፍሬ ነገር  ወይም በቅጣት መጠንና ዐይነት  ወይም በሦስቱም ላይ ሊካሔድ ይችላል፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ ድርድር ሲያካሔድ የጥፋተኝነት ድርድር መመሪያንና የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት ሆኖ የወንጀሉን ክብደት፣ የተጠርጣሪውን ወይም የተከሳሹን ባሕርይ፣ የቅጣቱን ወጥነት፣ ተገማችነትና አግባብነት ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

3. በክስ ብዛት ወይም በፍሬ ነገር ወይም በቅጣት መጠንና ዐይነት ወይም በሦስቱም ላይ የጥፋተኝነት ድርድር ስለሚካሔድበት ሁኔታና አፈጻጸም ፍትሕ ሚኒስቴር መመሪያ ያወጣል፡፡

4. የጥፋተኝነት ድርድር ስምምት በዚህ ሕግ በተመለከተው ቅጽ መሆን አለበት፡፡ ስምምነቱ በዐቃቤ ሕግ እና በተጠርጣሪ ወይም በተከሳሽ ወይም ጠበቃው መፈረም አለበት፡፡

**አንቀጽ 231 <u>ስምምነትን ማጽደቅ</u>**

1. በጥፋተኛነት ድርድር የተደረሰ ስምምነት የወንጀል ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ በድርድሩ ደረሰውን ስምምነት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቅርቦ የማጸደቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

3. በሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ ወይም በፍርድ ቤት የተለየ ትእዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር ስምምነቱ ፍርድ ቤት ቀርቦ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 232 <u>የፍርድ ቤት ሥልጣን</u>**

1. ፍርድ ቤት የድርድር ስምምነቱን ከማጽደቁ በፊት የድርድር ሒደቱና የተደረሰበት ስምምነት በዚህ ሕግ አንቀጽ 233 መሠረት የተካሔደ መሆኑን ተጠርጠሪውን ወይም ተከሳሹን ወይም ጠበቃውን በዝርዝር ጠይቆ አስተያየቱን መቀበል አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት የጥፋተኛነት ድርድር ሒደቱ እና የቀረበው ስምምነት ሕግን ወይም ሞራልን የሚቃረን ሆኖ ካላገኘው በስተቀር ማጽደቅ አለበት፡፡

ፍርድ ቤት የድርድሩን ሒደትና ስምምነት ካፀደቀ ተፈጻሚ እንዲሆን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 233 የስምምነት ያለማጽደቅ ውጤት**

በድርድሩ የተደረሰበት ስምምነት ፍርድ ቤት ቀርቦ ሳይጸድቅ የቀረ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ለስምምነቱ ያለመጽደቅ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ወይም ድርድሩን እንደገና እንዲካሔድ ወይም ክስ ለመመሠረት ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 234 ስለይግባኝ**

ፍርድ ቤት የድርድር ስምምነቱን በዚህ ሕግ አንቀጽ 238(2) መሠረት ያላጸደቀው እንደሆነ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ዐቃቤ ሕግ ይግባኙን የወንጀል ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት
## ከመደበኛ የፍርድ ሒደት ውጭ ስለሚኖር አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ

**አንቀጽ 235 ዓላማ**

ከመደበኛ የፍርድ ሒደት ውጭ የሚፈጸም አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ዓላማ፡-

(1) ተከሳሹ ለፈጸመው ወንጀል በራሱ ፍቃድ ኃላፊነት እንዲወስድ እና በድርጊቱ ተጸጽቶ እንዲታረም ማድረግ፣

(2) ከመደበኛ የፍርድ ሒደት ይልቅ በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ የሕዝብ ጥቅምን ማስከበር፣

(3) በወንጀል ድርጊቱ ምክንያት በተጎጂውና በተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኝ ማስቻልና ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን ከኅብረተሰቡ ጋር ማዋኃድ፤

(4) በወንጀል የፍትሕ ሒደት ውስጥ የኅብረተሰቡን ተሳትፎ ለማጎልበትና ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ፣

መሆን አለበት፡፡

**አንቀጽ 236 መርህ**

1. ዐቃቤ ሕግ በራሱ ወይም በተጠርጣሪ ወይም በተከሳሽ ጠያቂነት ወይም በፍርድ ቤት አነሳሽነትበማንኛውም የምርመራ፣ የክስና የፍርድ ሒደት ላይ ያለን የወንጀል ጉዳይ ከመደበኛው የፍርድ ሒደት ውጭ ባለ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ እንዲታይ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ የወንጀሉን ዐይነት፣ የተጠርጣሪውን ባሕርይ እና የወንጀሉን አፈጻጸም ከባቢያዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

3. ዐቃቤ ሕግ በዚህ ክፍል በተደነገገው መሠረት ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔው በሕዝብ ጥቅም ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ፣ የተጎጂውን ልዩ ሁኔታ፣ መብትና ጥቅም፣ የጉዳዩን ልዩ ሁኔታ እንዲሁም የተከሳሹን መብት፣ ፍላጎትና ፈቃድ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

4. ለዚህ ሕግ አፈጻጸም ሲባል አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ማለት በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው ከመደበኛው የፍርድ ሒደት ውጭ ባለ ሌላ አማራጭ ዘዴ ወይም ሒደት ወይም ፕሮግራም መሠረት የተፈጸመው ወንጀል መፍትሔ እንዲያገኝ የሚደረግበት ሥርዐት ነው፡፡

## አንቀጽ 237 ቅድመ ሁኔታ

1. ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ መፍትሔ እንዲያገኝ ሲወስን፡-

   (ሀ) ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖሩን፣

   (ለ) ጉዳዩ በአማራጭ መፍትሔ መታየቱ የሕዝብን ጥቅምና የተጎጂውን መብቶች የሚያስጠብቅ መሆኑን፣

   (ሐ) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን በፈቃዱ ማመኑን፣ ድርጊቱን በመፈጸሙ መጸጸቱን በጽሑፍ

   (መ)

   ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ እንዲታይ ውሳኔ ሲሰጥ እንደነገሩ ሁኔታ በጉዳዩ ላይ እውቀት ካለው ባለሙያ፣ ከተጎጂው ወይም ሌሎች ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 238 አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ተፈጻሚ የማይሆንበት ሁኔታ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 251 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ፡-

(1) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በፈጸመው ሌላ ወንጀል በአመክሮ ላይ እንደሆነ፤

(2) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በሌላ ወንጀል ተመሳሳይ ወይም ሌላ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ እየፈጸመ እንደሆነ፤

(3) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በሌላ ወይም በተመሳሳይ ወንጀል ተቀጥቶ እንደሆነ፤

(4) ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሹ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሌላ ወይም ተመሳሳይ ወንጀል ፈጽሞ አማራጭ መፍትሔ ርምጃን የፈጸመ እንደሆነ፤

(5) ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሹ አደገኛ እና ወንጀሉን የፈጸመበት ሁኔታ በወንጀል ሕግ መሠረት ቅጣትን ሊያከብድ በሚችል አኳኋን እንደሆነ፤

ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## አንቀጽ 239 አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ሰዎች

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 219 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩ ሁኔታዎች ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል፡፡

   (ሀ) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት፣ አካል ጉዳተኛ ወይም በዕድሜ የገፋ እንደሆነ፤

   ((ለ))ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ወንጀሉን በፈጸመበት ወይም በክስ መሰማት ጊዜ አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ህመምተኛ እንደሆነ፤

2. (ሐ)በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት ሰዎች በሕገ መንግሥትና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት፣ በሽብርተኝነት፣ በሙስና፣ በተደራጁ ቡድኖች በሚፈጸም ወንጀል፣ በዘር ማጥፋት፣ በከባድ የሰው ግድያ፣ በሰው ዘር ላይ በሚፈጸም ወንጀል፣ በአስገድዶ መድፈር፣ በሕፃናት ላይ በሚፈጸም ፆታዊ ጥቃት፣ በቦር መሣሪያ ወይም በኃይል በሚፈጸም ወንጀል የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ እንደሆነ የአማራጭ መፍትሔ ርምጃ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡እንደሆነ

## አንቀጽ 240 አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ዐይቶች

1. በዚህ ሕግ መሠረት የሚወሰድ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ፡-

   (ሀ) ባሕላዊ ሕጎች እና ተቋማት የሚወስዱት ርምጃ፣

(ለ) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በራሱ ወይም በመንግሥት ወጭ ህክምና እንዲከታተል፣ የሙያ ስልጠና እንዲያገኝ ወይም የቀለም፣ የሙያ ወይም የግብረ ገብ ትምህርት እንዲከታተል ማድረግ፣

ካማ (ሐ) ማኅበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣

(መ) ለተወሰነ ጊዜ በተወሰነ ቦታ እንዲቆይ ማድረግ፣

(ሠ) ምክርና ተግሳጽ መስጠት፣ ወይም

(ረ) ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በመመሪያ የሚወስነውን ሌላ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃን

ሊያካተት ይችላል፡፡

2. በዚህ ሕግ መሠረት ጉዳዩ በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ሲታይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ)-(ረ) ከተመለከቱ አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 241 በዕርቅ የሚወሰድ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ------------ ስለ ዕርቅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃን ተግባራዊ ለማድረግ፡-

(ሀ) የወንጀል ድርጊት ጥቆማ ወይም አቤቱታ ከቀረበ ተጠርጣሪውና የግል ተበዳዩ እንዲታረቁ፣

(ለ) የወንጀል ጉዳዩ በምርመራ ወይም በክስ ሒደት ላይ እንደሆነ በመርማሪ ወይም በዐቃቤ ሕግ አነሳሽነት ተከሳሹን እና ተጎጂውን በመጥራት እንዲታረቁ፣ ወይም

(ሐ) ጉዳዩ በፍርድ ሒደት ላይ እንደሆነ በተከሳሽ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጠያቂነት ወይም በፍርድ ቤቱ አነሳሽነት ወዲያውኑ እንዲታረቁ ወይም እንደአስፈላጊነቱ አሰታራቂ እንዲመደብ፣

ሊደረግ ይችላል፡፡

2. የወንጀል ጉዳዩ በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ሥርዐት በዕርቅ እንዲያልቅ ሲወሰን የማስታረቅ ሥራ የሚሠሩ የመንግሥት ወይም የግል ተቋማት የሚሰጡት ውሳኔ በዚህ ሕግ አንቀጽ 247 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ)፤ (ረ) ከተመለከቱ ውሳኔዎችን ውጭ መሆን የለበትም፡፡

**አንቀጽ 242** <u>በባህላዊ ተቋማትና ሕጎች የሚወሰድ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ</u>

1. ወንጀሉ መካከለኛ ወይም ከባድ እንደሆነ እና በተጠርጣሪውና በተጎጂው መካከል የተፈጠረው የወንጀል ምክንያት በባህላዊ ተቋማትና ሕጎች ዘላቂ መፍትሔ ያመጣል ተብሎ ሲታመን ጉዳዩ በባህላዊ ተቋማትና ሕጎች መፍትሔ እንዲሰጥ ተጠርጣሪው ፈቃደኛ የሆነ እንደሆነ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. ጉዳዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በባህላዊ ተቋማትና ሕጎች ታይቶ መፍትሔ ካገኘ መፍትሔው ከሕገ መንግሥቱ እና ከሌሎች ሕጎች ጋር የማይቃረን መሆኑን በማረጋገጥ ዐቃቤ ሕግ በአቅራቢያው በሚገኝ ፍርድ ቤት እንዲመዘገብ ያደርጋል፣ መዝገቡንም ይዘጋል፡፡

**አንቀጽ 243** <u>የፍርድ ቤት ሥልጣን</u>

1. ክስ የተመሠረተበት ጉዳይ በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ሥርዐት እንዲታይ በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ ጥያቄነት ወይም በፍርድ ቤት አነሳሽነት ጥያቄ ከቀረበ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአማራጭ የመፍሔ ርምጃ እንዲታይ ለዐቃቤ ሕግ ይመራል፡፡ ዐቃቤ ሕግም ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2. ጉዳዩ ወጣት ወንጀል አድርጊን የሚመለከተ እንደሆነ በፍርድ ቤት ወይም በዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ እንዲታይ ሊወሰን ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ወንጀሉ እስከ ስድስት ወር ቀላል እሥራት የሚያስቀጣ ወይም የደንብ መተላለፍ እንደሆነ መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩን በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ እንዲታይ ሊወስን ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ 244 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ)፣ (መ) እና (ሠ) የተመለከቱ አመራጭ የመፍትሔ ርምጃዎች በዐቃቤ ሕግ የተወሰነ እንደሆነ መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ ይህንኑ ለፍርድ ቤት ማሳወቅ አለበት፤ ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ይመዘግባል፡፡

**አንቀጽ 244 <u>የውሳኔው ይዘት</u>**

1. በዚህ ሕግ መሠረት ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ መፍትሔ እንዲያገኝ ውሳኔ ሲሰጥ የመፍትሔ ርምጃው፡-

   (ሀ) ተፈጻሚነት ስለሚጀምርበትና ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ፣ እና

   (ለ) የሚፈጸምበትን ተቋም እና አፈጻጸም ክትትል ስለሚደረግበት ሁኔታ መወሰን አለበት፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት የማስተካከያ ርምጃ ሲወስድ ስለ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ አፈጻጸም ለዚሁ ጉዳይ ከተቋቋሙ አግባብነት ካላቸው ተቋማት አስተያየት መጠየቅ አለበት፡፡

**አንቀጽ 245 <u>አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ የሚያስፈጽሙ አካላት</u>**

1. አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ የሚያስፈጽሙ አካላት በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዕውቅና ይሰጣቸዋል፣ እንዳስፈላጊነቱም እነዚህን አካላት የሚያስተባብር ተቋም ይቋቋማል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዕውቅና የተሰጣቸው አካላት፡-

   (ሀ) ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚዘረጋውን አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ሥርዐት ተግባራዊ የማድረግ፣

   (ለ) በዐቃቤ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት የሚሰጥ ማንኛውንም ትእዛዝ የመፈጸም ወይም የማስፈጸም፣

   (ሐ) የተጠርጣሪውን ወይም የተከሳሹን አሰፈላጊ መረጃ የመያዝና በዐቃቤ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት ሲጠየቁ የማቅረብ፣

   (መ) ለዐቃቤ ሕግ ወይም ለፍርድ ቤት ስለተጠርጣሪው ወይም ስለተከሳሹ ሁኔታ አስፈላጊውን ሪፖርት የማቅረብ፣

   (ሠ) ሌሎችም ተያያዥነትና አግባብነት ያላቸውን ተግባራት የማከናወን፣

   ግዴታ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 246 አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ መፈጸሙን ማረጋገጥ**

በዚህ ሕግ መሠረት የተሰጠው አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ መፈጸሙ የሚረጋገጠው እንደ አግባብነቱ በዐቃቤ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 247 የተፈጸመ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ የሚኖረው ውጤት**

1. በዚህ ሕግ መሠረት በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ መፍትሔ እንዲያገኝ የተወሰነ ጉዳይ በውሳኔው መሠረት የተፈጸመ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት መዝገቡን ይዘጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተዘጋ መዝገብ ላይ በማናቸውም ሁኔታ ክስ አይመሠረትም፤ ተከሳሹ በሌላ ወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ በተባለበት ወንጀል እንደቀድሞ ሪከርድ አይቀርብበትም፡፡

**አንቀጽ 248 ያልተፈጸመ ወይም ውጤታማ ያልሆነ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ውጤት**

1. በዐቃቤ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት የተወሰነ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ሳይፈጸም ወይም ውጤታማ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ ርምጃውን ለማስፈጸም ሥልጣን በተሰጠው ወይም አግባብነት ባለው ተቋም በሚቀርብ አስተያየት መሠረት እንደነገሩ ሁኔታ ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት ተገቢውን ይወስናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት
   (ሀ) ቀድሞ የተወሰነው አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ በድጋሚ ተፈጻሚ እንዲሆን፤ እንዳስፈላጊነቱም ርምጃውን የሚያስፈጽመው ተቋሙ እንዲቀየር፣
   (ለ) በሌላ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ እንዲፈጸም፣ ወይም
   (ሐ) ጉዳዩ በመደበኛ የክስ መሰማት ሒደት እንዲታይ
   ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የወንጀል ጉዳይ በማንኛውም ሁኔታ ከሁለት ጊዜ በላይ በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ እንዲታይ አይደረግም፤ ጉዳዩም በመደበኛ የክስ መስማት ሒደት ይታያል፡፡

**አንቀጽ 249 ስለክስና ይግባኝ**

ካማበአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ የተሰጠ ውሳኔ ወይም የተወሰደ ርምጃ የወንጀል ክስ አይቀርብበትም ይግባኝም አይባልበትም፡፡

**አንቀጽ 250 የአማራጭ መፍትሔ ርምጃ ተፈጻሚነት**

በዚህ ሕግ መሠረት የሚወሰድ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ  ውሳኔ ሲሰጥ ለተጠርጣሪው ወይም ለተከሳሹ፣ ለተፈጸመው ወንጀል አግባብነት ያለውና ለዚሁ የመፍትሔ ርምጃ አፈጻጸም የሚያስችል አደረጃጀትና አሠራር መኖሩን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማረጋገጥ አለበት፡፡

**አንቀጽ 251 የተከሳሹ የእምነት ቃል ወይም የጸጸት መግለጫ**

በዚህ ሕግ መሠረት ተከሳሹ የሚሰጠው የእምነት ቃል ወይም የጸጸት መግለጫ ወይም ይህንኑ በመግለጽ ሒደት ምክንያት የተገኘ ማስረጃ የሚኖረውን ተቀባይነት በተመለከተ እንደአግባብነቱ የዚህ ሕግ አንቀጽ 240 ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 252 ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚዘረጋው ሥርዐት**

1. በዚህ ሕግ መሠረት የወንጀል ጉዳይ በአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ መፍትሔ ስለሚያገኝበት ዝርዝር አሠራር ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መመሪያ ያወጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚያወጣው መመሪያ፡-
   (ሀ) የወንጀሉ ክብደት፣ ዐይነትና ባሕርይ፤
   (ለ) ወንጀሉ የተፈጸመበት ሁኔታና ዘዴ፤
   (ሐ) የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ ባሕርይና የወንጀል ሪከርድ፤
   (መ) የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ ዕድሜና ማኅበራዊ ሁኔታ፤
   (ሠ) በተጎጅው ላይ የደረሰው የጉዳት ዐይነትና መጠን፤
   (ረ) የተጎጅው ፆታ፣ ዕድሜ እና ሌሎች ማኅበራዊ ሁኔታዎች፤

(ሰ) ሌሎችም አግባብነት ያላቸው ተመሳሳይ ሁኔታዎች፣ መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## ስለክስ አመሠራረት
## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 253 መርህ

1. ዐቃቤ ሕግ ምርመራ መዝገቡን መርምሮ ተጠርጣሪን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ እና የሕዝብ ጥቅም መኖሩን ሲያረጋገጥ ክስ መመሠረት አለበት፡፡

2. በዚህ ሕግ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግሥት፣ ኢትዮጵያ በፈረመችውና ባጸደቀችው ዓለም አቀፍ ስምምነት እና በሌላ ሕግ በሰው ልጅ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀል ተብሎ የተወሰነ የሰው ዘር በማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት ርምጃ በመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን በመሰወር ወይም ኢ-ሰብዓዊ ድብደባ በመፈጸም ወንጀል የተጠረጠረን ሰው ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ካለ ዐቃቤ ሕግ ክስ መመሥረት አለበት፡፡

### አንቀጽ 254 ስለክስ ማመልከቻ

1. በሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ወይም በዚህ ክፍል በተደነገገው መሠረት በጽሑፍ ክስ ሳይቀርብበት ማንም ሰው ጉዳዩ በፍርድ ቤት እንዲሰማ አይደረግም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤት በያዘው መዝገብ ቅጣት መወሰን በሚችልባቸው ጉዳዮች ክስ በጽሑፍ ማቅረብ አያስፈልግም፡፡

3. ማንኛውም የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ በዚህ ክፍል በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 255** <u>የክስ ማመልከቻ ይዘት</u>

1. ማንኛውም የክስ ማመልከቻ፡-

   (ሀ) ቀን፣ ወርና ዓመተ ምኅረት የተጻፈበት፤
   
   (ለ) ክሱ የሚቀርብበት ፍርድ ቤት ስምና አድራሻ፤
   
   (ሐ) የዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ ስም፣ ማዕረግ፣ አድራሻና ፊርማ፣
   
   (መ) የተከሳሽ ስም፣ ፆታ፣ ዕድሜና አድራሻ፤
   
   (ሠ) ወንጀሉ የተፈጸመበት ጊዜና ሥፍራ፤ ተገቢ እንደሆነ የተበዳይ ስም ወይም ወንጀሉ የተፈጸመበት ንብረት፤
   
   (ረ) ወንጀሉ የተፈጸመበት ቀን በትክክል ያልታወቀ እንደሆነ ወንጀሉ ተፈጽሟል ተብሎ የሚገመትበት አግባብ ያለው ጊዜ፤
   
   (ሰ) ተከሳሹ ወንጀሉን በመፈጸም ተላልፏል የተባለበት ሕግ፣ የሕግ ቁጥር እና ወንጀሉን የሚመለከቱ የሕግና የፍሬ ነገር መሠረታዊ ነገሮች፤
   
   መያዝ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ማንኛውም የክስ ማመልከቻ ከዚህ ሕግ ጋር ተያይዞ በሚገኘው በሠንጠረዥ ………. ወይም በተቻለ መጠን ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ቅፅ መዘጋጀት አለበት፡፡

**አንቀጽ 256** <u>የወንጀል ክስ ዝርዝር ሁኔታ</u>

ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ እና አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል እያንዳንዱ ክስ ወንጀሉንና የወንጀል ድርጊቱን ሁኔታ በዝርዝር መግለጽ አለበት፡፡ ስለወንጀሉና ስለ ሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ተላለፈ የተባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ አነጋገር ጋር ተመሳሳይ ወይም በጣም የተቀራረበ መሆን አለበት፡፡

**አንቀጽ 257** <u>ተከሳሽ የተቀጣበትን ወንጀል በክስ ማመልከቻ መግለጽ የተከለከለ መሆን</u>

ለወንጀሉ መሠረታዊ ነገር ካልሆነ በስተቀር ተከሳሹ ከዚህ በፊት ተከሶ የተቀጣበት ወንጀልበክስ ማመልከቻ ውስጥ መገለጽ የለበትም፡፡

**አንቀጽ 258** <u>ክስን ማጣመር</u>

1. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 60፣ ከአንቀጽ 62-66 በተመለከተው መሠረት ከአንድ በላይ የሆኑ ወንጀሎች ፈጽመውተፈጽመው በተገኙ ጊዜ በአንድ ማመልከቻ ክሶችን አጣምሮ ማቅረብ ይቻላል፡፡

2. የቀረበውን የወንጀል ጉዳይ ተደራራቢ ወንጀል ሆኖ በወንጀል ጉዳዮቹ ላይ ክስ የማቅረብ ሥልጣን በተለያዩ የዐቃቤ ሕግ ተቋማት ሥልጣን እንደሆነ ከባዱን የወንጀል ጉዳይ ላይ ክስ የማቅረብ ሥልጣን ያለው ዐቃቤ ሕግ ክሱን በማጣመር ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

3. ተያያዥነት ያላቸው በተመሳሳይ የወንጀል ደረጃ ያሉ ተደራራቢ የወንጀል ጉዳዮች ከተፈፀሙና በጉዳዩ ላይ ክስ የማቅረብ ሥልጣን የተለያዩ የዐቃቤ ሕግ ተቋማት በመሆኑ ሥልጣኑን ለመወሰን ባልተቻለ ጊዜ ፍትሕ ሚኒስቴር ወይም ፍትሕ ቢሮ ሥልጣን ያለውን የዐቃቤ ሕግ ተቋምን በመወሰን ክሱ ተጣምሮ እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4. ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ክሶችን አጣምሮ ሲያቀርብ እያንዳንዱን የወንጀል ክስ ለየብቻው መግለጽ አለበት፡፡

**አንቀጽ 259** <u>ክሶችን መነጣጠል</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 263 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተጣምረው የቀረቡ ክሶች በአንድነት መታየት አለባቸው፡፡

2. ፍርድ ቤት የክሶቹ በአንድነት መሰማት የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ ወይም ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል ሆኖ ከታየው ወይም ጥያቄ ከቀረበለት ክሶቹ ተነጣጥለው ለየብቻቸው እንዲሰሙ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 260** <u>ተከሳሾችን አጣምሮ መክሰስ</u>

1. ከአንድ በላይ የሆኑ ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 እስከ 40 እና አንቀጽ 60-66 በተደነገገው መሠረት ወንጀል ፈጽመው በተገኙ ጊዜ በአንድ ማመልከቻ ክስ ሊመሠረትባቸው ይችላል፡፡

2. ከአንድ በላይ የሆኑ ተከሳሾች በአንድ የወንጀል ድርጊት የፈጸሙት ወንጀል የተለያየ ቢሆንም እንደነገሩ ሁኔታ በአንድ ክስ በጋራ ሊከሰሱ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 261 ቅጣትን ስለሚያከብዱ ወንጀሎች ክስ አቀራረብ**

ተከሳሹ ከዚህ በፊት በፈጸማቸው ወንጀሎች ምክንያት ቅጣትን በሚያከብድ ወንጀል የሚያስከስሰው ቢሆንም ክስ የሚቀርብበት ቅጣቱ በማይከብድበት ወንጀል ነው፡፡

**አንቀጽ 262 የተፈጸመ ወንጀል ዐይነት የሚያጠራጥር እንደሆነ የሚቀርብ ክስ**

1. የተፈጸመ ወንጀል ዐይነት የሚያጠራጥር እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ በሚያቀርበው የክስ ማመልከቻ አማራጭ ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. ለተፈጸመው ድርጊት ወይም ለተፈጸሙ ድርጊቶች የሚቀርበው ማስረጃ ከብዙ ወንጀሎች ውስጥ የትኛውን እንደሚያረጋግጥ ለማወቅ አጠራጣሪ እንደሆነ ተከሳሹ ለመፈጸሙ ይበልጥ የተረጋገጠ በሚመስለው ወንጀል እና በአማራጭ በማስረጃው ሊረጋገጡ ይችላሉ በሚባሉት ወንጀሎች ሁሉ ሊከሰስ ይችላል፡፡

3. የቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን በአማራጭ ሊያስከስሰው ይችል በነበረ ወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት በቂ እንደሆነና ይህም ወንጀል ክስ ከቀረበበት ወንጀል የሚያንስ እንደሆነ ክስ ያልቀረበበት ቢሆንም በዚሁ ወንጀል ተከሳሹ ሊቀጣ ይችላል፡፡

4. የቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን በአማራጭ ሊያስከስሰው ይችል በነበረ ወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት በቂ እንደሆነና ይህም ወንጀል ክስ ከቀረበበት ወንጀል የሚበልጥ ወይም የተለየ እንደሆነ ዐቃቤ ሕጉ ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃውን ከማቅረቡ በፊት ክሱን ትእዛዝሊያሻሽል ይችላል፡፡ ዐቃቤ ሕጉ ያሰማውን ማስረጃ በድጋሚ እንዲያቀርብ አይገደድም፡፡

**አንቀጽ 263 በሙከራ፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ጥፋተኛ ማድረግ**

1. ማንኛውም ሰው በወንጀል ተከሶ በሙከራ ወንጀል ክስ ባይቀርብበትም በሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል ይቻላል፡፡

2. ማንኛውም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከሶ፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ክስ ባይቀርብበትም በወንጀሉ አነሳሽነት ወይም በአባሪነት ጥፋተኛ ሊባል ይቻላል፡፡

**አንቀጽ 264** **ክስ ስለሚመሠረትበት የጊዜ ገደብ**

1. ዐቃቤ ሕግ በምርመራ መዝገብ ላይ ውሳኔ ከሰጠበት በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ተገቢ ነው ብሎ ያመነውን የክስ ማመልከቻ አዘጋጅቶ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ ክስ እስኪመሠርት ድረስ በጊዜ ቀጠሮ ያለ ተጠርጣሪ በማረፊያ ቤት ይቆያል፡፡

3. ዐቃቤ ሕግ እንደየወንጀሉ ዐይነት ክስ የሚመሰርትበትን የጊዜ ገደብ ዝርዝር አፈጻጸም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 265** **በጊዜ ገደብ ውስጥ ክስ አለመመሠረት**

1. ዐቃቤ ሕግ በዚህ ሕግ አንቀጽ 269 በተደነገገው የጊዜ ገደብ ክስ የማይመሰርት እንደሆነ እንደሆነ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ በመቅረብ ምክንያቱን ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት አለበት፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ በጊዜ ገደቡ ክስ ሊመሠርት ያልቻለበት ምክንያት በቂ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተገነዘበ ክሱን ለመመሥረት እስከ ሰባት ቀናት ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በተሰጠው ሰባት ቀናት ውስጥ ክሱን ካላቀረበ እና ተጠርጣሪው በማረፊያ ቤት ያለ እንደሆነ በዋስትና ይለቀዋል፡፡

3. ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ በቀጠሮው ቀን ቀርቦ ክስ ያልመሠረተበት ምክንያት ካላስረዳ ወይም ያቀረበው ምክንያት በቂ ያለመሆኑን ከተገነዘበና ወንጀል ዋስትና የማያስከለክል እንደሆነ ዋስትና በመፍቀድ ተጠርጣሪው እንዲለቀቅ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

4. በፍርድ ቤት የጊዜ ቀጠሮ በፈቀደበት የወንጀል ጉዳይ ላይ ዐቃቤ ሕግ ክስ የማይመሠርት እንደሆነ ይህንኑ የጊዜ ቀጠሮውን ለፈቀደው ፍርድ ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡

5. በጉዳዩ ላይ ክስ ያልተመሠረተ እንደሆነ እና ጉዳዩ ዋስትና የሚያስከለክል በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው ምክንያት በቂ መሆኑን ከተረዳ ክሱ እንዲቀርብ እስከ አሥራ አምስት ቀናት ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ዐቃቤ ሕጉ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ክሱን ያላቀረበ እንደሆነ

ተጠርጣሪ በዋስ እንዲለቀቅ ትእዛዝ ይሰጣል፣ የጊዜ ቀጠሮ መዝገቡንም ይዘጋል፡፡

**አንቀጽ 266** <u>ሥልጣን በሌለው ዐቃቤ ሕግ የሚቀርብ ክስ</u>

1. የወንጀል ክሱን የመሠረተው የዐቃቤ ሕግ ተቋም ሥልጣን በሌለው ጉዳይ ላይ ክስ መሥርቶ እየተከራከረ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በተረዳ ጊዜ የክስ ሒደቱ መካሔዱ እንደተጠበቀ ሆኖ ሥልጣን ያለው የዐቃቤ ሕግ ተቋም ስለክርክሩ እንዲያውቅ ያደርጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንዲያውቅ የተደረገው የዐቃቤ ሕግ ተቋም ካልቀረበ ክሱን ያቀረበው ዐቃቤ ሕግ ውክልና እንደተሰጠው ተቆጥሮ የጉዳዩ መታየት ይቀጥላል፡፡

**አንቀጽ 267** <u>ክስን ማንሳት</u>

1. ዐቃቤ ሕግ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ለፍርድ ቤቱ በማሳወቅ ማንሳት ይችላል፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ ያቀረበውን ክስ ካነሳ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን በመዝጋት ክሱ ለጊዜው እንዲቋረጥ እና ተከሳሹ ማረፊያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ እንዲለቀቅ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡ በክሱ ምክንያት የተያዘ ወይም የታገደ ንብረት ካለ እንዲለቀቅ ወይም ዕግዱ እንዲነሳ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. በወንጀል ሕጉ ስለይርጋ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ በማንኛውም ጊዜ ክሱን ሲያንቀሳቅስ ጉዳዩ ከተቋረጠበት ይቀጥላል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የግል ክስ የሚቀርብበት ሥነ ሥርዐት</u>

**አንቀጽ 268** <u>የግል ክስ አቀራረብ</u>

1. በግል አቤቱታ አቅራቢነት ወይም በቀላል እሥራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች ላይ በቂ ማስረጃ ቢኖርም የሕዝብ ጥቅም ላለባቸው ጉዳዮች ቅድሚያ በመስጠት ዐቃቤ ሕጉ ክስ ላለመመሠረት ከወሰነ የግል ክስ እንዲቀርብ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ክስ እንዲያቀርብ ፈቃድ ያገኘው የግል ተበዳይ የውሳኔ ግልባጩን ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ አለበት፤ ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡

3. የዚህ ሕግ አንቀጽ 259- 275 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በግል በሚቀርቡ የክስ ማመልከቻዎች ላይ እንደሁኔታው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 269** **የግል ከሳሽ ኃላፊነት**

በዚህ ሕግ ያለበት ሌላ ኃላፊነት እንደተጠበቁ ሆነው የግል ክስ እንዲያቀርብ የተፈቀደለት የግል ከሳሽ የሚከራከረው በራሱ ኃላፊነት ሆኖ የዳኝነት ክፍያና የክስ ወጭውን በተመለከተ የዚህ ሕግ አንቀጽ 528 እና 529 ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 270** **የግል ክስ ለማቅረብ መብት ያለው ሰው**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 241 መሠረት የግል ክስ ማቅረብ የሚችለው የግል ተበዳዩ ወይም ዐቃቤ ሕግ ሲፈቅድ የግል ተበዳዩ ወኪል የሆነ ሰው ብቻ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዐቃቤ ሕግ የግል ክስ እንዲመሠረት ሲፈቅድ በወንጀል ሕጉና በዚህ ሕግ ዓላማ መሠረት እየተከናወኑ መሆኑን መከታተል አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ዐቃቤ ሕግ ክትትል ሲያደርግ የወንጀል ሕጉንና የዚህ ሕግ ዓላማ በሚፃረር አኳኋን እየተፈጸመ መሆኑን ከተረዳ የግል ክሱ እንዲቋረጥ ለፍርድ ቤት ያሳውቃል፤ እንደነገሩ ሁኔታ ክሱን በራሱ ይከታተላል፡፡

**አንቀጽ 271** **የክስ ማመልከቻ እንዲሻሻል ስለማዘዝ**

የክስ ማመልከቻው የቀረበው ለግል ከሳሹ በዐቃቤ ሕግ በተሰጠው ፈቃድ መሠረት ካልሆነ በተሰጠው ፈቃድ መሠረት ክሱን እንዲያሻሽል ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 272 <u>ተከራካሪዎችን ስለመጥራት</u>**

የክስ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤት በዚህ ሕግ አንቀጽ 297 በተደነገገው መሠረት ለግል ከሳሹ መጥሪያ ይሰጣል፤ የግል ከሳሹም ለተከሳሹ መጥሪያውን ያደርሳል፡፡

**አንቀጽ 273 <u>ተከራካሪዎችን ስለማስታረቅ</u>**

1. በዚህ ሕግ መሠረት ክስ ከመመሥረቱ በፊት የሚደረጉ የዕርቅ ሙከራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፍርድ ቤቱ የክስ ማመልከቻውን ለተከሳሽ ከማንበቡ በፊት ተከራካሪዎቹን ለማስታረቅ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፡፡ ጉዳዩ በዕርቅ ከተቋጨ ፍርድ ቤቱ ዕርቁን በመዝገብ ይጽፋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በዕርቅ የተቋጨ የወንጀል ጉዳይ በፍርድ ቤት እንደተሰጠ ውሳኔ ተቆጥሮ ተፈጻሚነት አለው፡፡

**አንቀጽ 274 <u>ኪሣራ ላይ ስለሚደረግ መተማመኛ</u>**

በተከራካሪዎቹ መካከል ዕርቅ ለማድረግ ባልተቻለ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የግል ከሳሹ ስለ ኪሳራ ዋስትና እንዲሰጥ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን የዋስትናውን የገንዘብ ልክ ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 275 <u>ክርክሩን ስለመስማትና ፍርድ ስለመስጠት</u>**

የግል ከሳሽ በዚህ ሕግ አንቀጽ 277 መሠረት የግል ክስ እንዲያቀርብ ተፈቅዶለት ይህንኑ የፈጸመ እንደሆነ የጉዳዩ መሰማት ከአንቀጽ 279 እስከ 293 በተደነገገው መሠረት ይቀጥላል፡፡ የግል ከሳሽ እንዳግባብነቱ በዐቃቤ ሕግ በኩል እንደሚቀርበው ክስ ዐይነት መብትና ግዴታ አለው፡፡

**አንቀጽ 276 <u>ከፍ ያለ ወንጀል መሆኑ በታወቀ ጊዜ የሚኖር ሥነ ሥርዐት</u>**

1. በግል ክስ ከቀረበው ወንጀል ከፍ ያለ ወንጀል ለመሠራቱ በቀረበው ማስረጃ የተገለጸ ሲሆን ዐቃቤ ሕግ አዲስ ክስ እስኪያቀርብ ድረስ የግል ከሳሹ የግል ክስ እንዲቆም ፍረድ ቤትን መጠየቅ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም ክሱ እንዲቋረጥ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ሁኔታ መኖሩን ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ሕግ ወይም በግል ከሳሽ አመልካችነት የተረዳው እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ የግል ከሳሹን ተክቶ ጉዳዩን እንዲከታተል ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ማሻሻል፣ መጨመር ወይም አዲስ ክስ መመሠረት አስፈላጊ መሆኑን ካመነ የዚህ ሕግ አንቀጽ 273 እና አንቀጽ 274 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የግል ክሱ እንዲቋረጥ የተደረገ እንደሆነ ለግል ክሱ የኪሳራ ወጪ መንግሥት ኃላፊ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የፍትሐብሔር ክስ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ ስለሚቀርብበት ሥርዐት

### አንቀጽ 277 ዐቃቤ ሕግ ስለሚያቀርበው የፍትሐብሔር ክስ

1. ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ ሲያቀርብ ለወንጀል ክሱ ምክንያት የሆነው ድርጊት በሕዝብና በመንግሥት መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት ወይም በፍርድ ቤት ለመከራከር አቅም በሌላቸው ሰዎች ላይ ከባድ ጉዳት ባደረሰ ጊዜ የፍትሐብሔር ክሱን ከወንጀል ክስ ጋር አጣምሮ የወንጀል ክሱን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ጉዳቱ የደረሰው በሕፃን ወይም በሴት ላይ በተፈጸመ ጾታዊ ጥቃት እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ በተጎጂው ወይም በወኪሉ ሙሉ ፈቃድ የፍትሐብሔር ክሱን ከወንጀል ክሱ ጋር አጣምሮ ማቅረብ አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት በሚመሠረተው የፍትሐብሔር ክስ መንግሥት ተጣምሮ የሚከሰስ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ የፍትሐብሔር ክስ አያቀርብም፡፡

### አንቀጽ 278 ተጎጂ ስለሚያቀርበው የፍትሐብሔር ክስ

1. የዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ ማመልከቻ ለፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ በወንጀል ድርጊቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው የፍትሐብሔር ክስ ከወንጀል ክሱ ጋር ተጣምሮ እንዲታይለት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የቀረበው ክስ ከወንጀል ክሱ ጋር ተጣምሮ እንዲታይ የፈቀደ እንደሆነ፣ የፍትሐብሔር ክስ የሚያቀርበው ሰው የዐቃቤ ሕግንና የተከሳሹን የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር ማየት እና ተጨማሪ ማስረጃ ካለው እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት ፍርድ ቤቱን ለመጠየቅ ይችላል፡፡

3. የወንጀል ክሱ የቀረበው በግል ከሳሽነት እንደሆነ እና የግል ከሳሽ የፍትሐብሔር ክስ ተጣምሮ እንዲታይ ያቀረበ እንደሆነ የቀረበውን የወንጀል እና የፍትሐብሔር ክስ ለማስረዳት የሚያቀርባቸውን የማስረጃ ዝርዝር ለያይቶ ማቅረብ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ፍርድ ቤቱ የፍትሐብሔር ክሱን ለማስረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ማስረጃ የግል ከሳሹ እንዲያቀረብ ከፈቀደ የግል ከሳሹ ተጨማሪ ማስረጃ የሚቀርብበትን ወጪ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ይሸፍናል፡፡

**አንቀጽ 279 <u>የዳኝነትና ሌሎች ወጪዎች ክፍያ፣</u>**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 286 መሠረት የፍትሐብሔር ክስ ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያ አይከፈልበትም፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የፍትሐብሔር የግል ክስ አቅራቢው የዳኝነት ክፍያውን ጨምሮ ሌሎች ወጭዎችን ይሸፍናል፡፡

3. ፍርድ ቤት ተከሳሹ የክሱን ወጪና ኪሳራ እንዲከፍል ሲወሰን የዳኝነት ክፍያውንም ጨምሮ እንዲከፍል ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 280 <u>ክስ አቅራቢው ስለሚኖረው መብት</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 287 መሠረት የፍትሐብሔር ክስ ያቀረበ የግል ተበዳይ በወንጀል ክሱ የክስ መሰማት ሒደት እና በሚቀርበው ማስረጃ ሁሉ እንደ መደበኛ ተከራካሪ ወገን የመሳተፍ መብት አለው፡፡

**አንቀጽ 281 <u>የክስ ማቅረቢያ ጊዜ</u>**

ፍርድ ቤቱ በተለየ ሁኔታ ካልፈቀደ በስተቀር ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ባለው በማንኛውም ጊዜ የፍትሐብሔር ክስ ከቀረበው የወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ እንዲወሰን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 282** **ክሱ ለሌላ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ስለመጠየቅ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 286 እና 287 መሠረት የፍትሐብሔር ክስ ያቀረበ ሰው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ያቀረበው የፍትሐብሔር ክስ ከወንጀል ክሱ ተለይቶ በሌላ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንዲፈቀድለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ ክሱ በሌላ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሲወስን የጉዳዩ በሌላ ፍርድ ቤት መታየት ለከሳሽ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እና በተከሳሽ ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ በማመዛዘን መሆን አለበት፡፡ እንደአስፈላጊነቱም ተከሳሹ አስተያየቱን እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 283** **የተከሳሽ ጥፋተኛ አለመሆን ወይም የመለቀቅ ውጤት**

ተከሳሹ የወንጀል ክሱ በመቋረጡ የተለቀቀ ወይም ከተመሠረተበት የወንጀል ክስ በነፃ የተሰናበተ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን የፍትሐብሔር ክስ ሰምቶ ውሳኔ ሊሰጥ፣ ጉዳዩ በሌላ ችሎት ወይም ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲቀጥል ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 284** **አግባብነት ያለው ሕግ**

በዚህ ሕግ መሠረት ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ በሚቀርብ የፍትሐብሔር ክስ ላይ አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔርና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዐት ሕጎች ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

## ምዕራፍ ስድስት
## ስለክስ መሰማት፣ ማስረጃና ውሳኔ አሰጣጥ
## ክፍል አንድ
## ስለክስ መስማትና መወሰን
## ንዑስ ክፍል አንድ
## ስለመጥራት

**አንቀጽ 285** **መርህ**

1. መጥሪያ የሚወጣው የተከሳሽን የመሰማትና የመከላከል መብት በማክበርና በሕግ የሚኖርበትን ተጠያቂነት እንዲወጣ ለማስቻል፣ ተከራካሪ ወገኖች ቀርበው እንዲሰሙ፣ ለምስክርነት የተጠራ ሰው የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ፣ ሰነድ እንዲያቀርብ፣ የሠነዱን ይዘት እንዲያስረዳ ወይም የሙያ አስተያየት እንዲሰጥ

ወይም ማንኛውም የፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲፈጽም ለማድረግ እና ፍትሕ የማግኘት መብትን ለማረጋገጥ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጠራ ማንኛውም ሰው መጥሪያ ሊደርሰው ይገባል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤት እንደአስፈላጊነቱ፣

(ሀ) የመያዣ ትእዛዝ የተሰጠበት ሰው፣

(ለ) ችሎት የተገኘ ሰው፣ ወይም

(ሐ) ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በችሎት ላይ የታዘዘ ሰው፣

መጥሪያ መስጠት ሳያስፈልግ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 286** <u>**የመጥሪያ ይዘት**</u>

መጥሪያ፡-

1. የተጠሪን ሙሉ ስም፣
2. የተጠራበትን ምክንያት፣
3. የተጠራበት ፍርድ ቤት፣ ችሎት እና አድራሻ፣
4. የሚቀርብበት ሰዓት፣ ቀን፣ ወርና ዓመት ምኅረት፣ እና
5. በዚህ ሕግ መሠረት በሚዘጋጅ ቅጽ የተመለከቱት ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን፣

መያዝ አለበት ፡፡

**አንቀጽ 287** <u>**መጥሪያ የማዘጋጀትና የማድረስ ኃላፊነት**</u>

1. ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ለሚጠራ ሰው የሚሰጥ መጥሪያ የሚያዘጋጀው ፍርድ ቤት ነው፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ የክስ ማመልከቻውን ለፍርድ ቤቱ እንዳቀረበ መጥሪያ ወድያውኑ ይሰጠዋል፡፡ መጥሪያው ወድያው ካልተሰጠ ሬጅስትራር

ጉዳዩ ለሚመለከተው የዐቃቤ ሕግ ተቋም ወይም የግል ከሳሽ ማድረስ አለበት፡፡

3. በዚህ ሕግ አንቀጽ 295 ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት የሚወጣ መጥሪያ በጽሑፍ ሆኖ ቀጠሮ ከተያዘበት አሥር ቀናት አስቀድሞ ለተጠሪው በአካል መድረስ አለበት፡፡

4. መጥሪያው ለተጠሪ በአካል ማድረስ ያልተቻለ ወይም የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ የተጠሪው ቤተሰብ ወይም መጥሪያ ለመቀበል ውክልና ለተሰጠው ሰው መድረስ አለበት፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪው፡-

   (ሀ) ማቆያ፣ ማረፊያ ቤት ወይም ማረሚያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ የሚገኝበት ተቋም፣

   (ለ) ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች ወይም በፍርድ የተከለከለ እንደሆነ ሞግዚቱ ወይም አሳዳሪው፣

   (ሐ) የሕግ ሰውነት ያለው እንደሆነ የዋናው ወይም የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ወይም ወኪል፣

   (መ) ኤምባሲ ውስጥ የሚሰራ እንደሆነ እንደአመችነቱ ኤምባሲው መጥረያ ሊቀበል ይችላል፤ ለተጠሪም በአካል እንደደረሰው ይቆጠራል፡፡

6. ፖሊስ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችና የተከሳሽ መጥሪያ የማድረስ ኃላፊነት አለበት፡፡

7. የግል ከሳሽ የምስክሮቹና የተከሳሽ መጥሪያ የማድረስ ኃላፊነት አለበት፡፡

8. ተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮቹን መጥሪያ የማድረስ ኃላፊነት አለበት፡፡

**አንቀጽ 288** <u>ምትክ መጥሪያ</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 297 አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3-5) የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤት በቂና አሳማኝ ምክንያት መኖሩን ሲረዳ ተጠሪን፣

   (ሀ) በተመዘገበ የተጠሪ የፖስታ አድራሻ፣

(ለ) ተጠሪ በሚኖርበት ወይም የንግድ ሥራ በሚያከናውንበት ወይም ሕዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ በሚለጠፍ ማስታወቂያ፣

(ሐ) በጋዜጣ ወይም በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን በሚወጣ ወይም በሚነገር ማስታወቂያ፣

(መ) በተጠሪው ስልክ ወይም ፋክስ ቁጥር ወይም በኢ-ሜይል አድራሻ ወይም የስልክ አጭር መልዕክት፣

(ሠ) በፍርድ ቤት ድረ ገጽ ወይም እጥር ግቢ በሚለጠፍ ማስታወቂያ፣(ረ) ፍርድ ቤቱ በሚወስናቸው በመሳሰሉት የምትክ መጥሪያ ዓይነቶች፣

አመቺ በሆነው በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ እንዲጠራ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ የምትክ መጥሪያ ትእዛዝ ሲሰጥ ለተጠሪው ሊደርስ የሚችለውን የምትክ መጥሪያ  ዐይነት መምረጥ እና መድረሱን፣ በመገናኛ ብዙኃን መነገሩን ወይም ታትሞ መውጣቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ምትክ መጥሪያ ትእዛዝ በሰጠው ፍርድ ቤት፣ በፖሊስ፣    በዐቃቤ ሕግ ወይም በግል ከሳሽ ሊደርስ ወይም በመገናኛ ብዙኃን መነገሩ ወይም ታትሞ መውጣቱ ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 289** <u>የክልሎች ሥልጣን</u>

ክልል በዚህ ሕግ አንቀጽ 294 እና 295 የተደነገገውን መሠረት ማድረግ መጥሪያ የማድረስ ኃላፊነትን፣ የመጥሪያ አደራረስ ቅደም ተከተልን፣ የምትክ መጥሪያ ዐይነትን እና የሚደርስበት አግባብን በተለየ አኳኋን በሕግ ሊወን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 290** <u>መጥሪያ የመቀበል ግዴታ</u>

ማንኛውም የሚመለከተው ሰው በዚህ ሕግ መሠረት የወጣን መጥሪያ የመቀበልና የደረሰው መሆኑን ማረጋገጫ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ መጥሪያውን ለመቀበል ወይም ማረጋገጫ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ መጥሪያውን እንዲያደርስ የታዘዘው ሰው ይህንኑ ለፍርድ ቤት ማረጋገጥ አለበት፡፡

**አንቀጽ 291** **የመጥሪያ አለመድረስ**

1. ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ቀጠሮ በሰጠበት ቀን መጥሪያው ያልደረሰ ወይም በአግባቡ ያልደረሰ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ተጠሪ የሚቀርብበትን ቀን በመወሰን መጥሪያ በድጋሚ እንዲደርሰው ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

2. መጥሪያ የደረሰው ሰው በቀጠሮው ቀን ያልቀረበ ወይም መቅረብ የነበረበት ሰው ባለመቅረቡ ጉዳዩን ማየት የሚቻል ካልሆነ በስተቀር ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት ጉዳዩ የሚታይበትን የሚቀጥለው ቀነ ቀጠሮ ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 292** **የተከሳሽ አለመቅረብ**

ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ከአሥራ አምስት ቀናት ያልበለጠ ተለዋጭ ቀጠሮ በመስጠት በፖሊስ ተይዞ እንዲቀርብ ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 304 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 293** **ተከሳሽ በሌለበት የማይታይ ክስ**

1. በፍርድ ቤት የቀረበው ክስ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ጉዳይ ወይም በግል አቤቱታ የሚቀርቡ የወንጀል ክስ ጉዳይን የሚመለከት እንደሆነ ክሱ ተከሳሽ በሌለበት ሊታይ አይችልም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት በቀረበ ክስ ላይ ተከሳሽ ያልቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይዘጋል፡፡ የመዝገቡ መዘጋት መዝገቡን ማንቀሳቀስን ወይም ድጋሚ ክስ ማቅረብን አይከለክልም፡፡

**አንቀጽ 294** **ተከሳሽ በሌለበት የሚታይ ክስ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 304 ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ውጭ ባሉ የወንጀል ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ ማንኛውም የወንጀል ክስ ተከሳሽ በሌለበት ሊታይ ይችላል፡፡

2. ተከሳሽ በሌለበት በሚታይ ክስ ላይ ተከሳሽ ተይዞ ወይም በፍቃዱ ጉዳዩ በሚታይበት በማንኛውም ጊዜና ደረጃ ወደ ክርክሩ መግባት ይችላል፡፡

3. ተከሳሽ ወደ ክርክሩ የሚገባው በቀጠሮ ያልቀረበው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ ክርክሩ ከደረሰበት ደረጃ ይቀጥላል፡፡

4. ተከሳሽ በቀጠሮ ያልቀረበው መጥሪያ ሳይደረሰው ወይም ደርሶት ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ያረጋገጠ እንደሆነ የተሰጠ ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ተነስቶ ጉዳዩ እንደገና መታየት ይጀምራል፡፡ የቀረበው መዝገብ ከአንድ በላይ ተከሳሾች ያሉበት መዝገብ ሆኖ የጉዳዩ እንደገና መታየት የበሌሎች ተከሳሾች የመከላከል መብት የሚነካ ወይም የተቀላጠፈ ፍትሕ ለመስጠት የማያስችል እንደሆነ ለብቻው እንዲታይ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ወደ ክርክሩ ለመግባት የሚቀርብ ማመልከቻ ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት በቀረ ወይም በተወገደ በአንድ ወር ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

6. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት ማንኛውም ምክንያታዊ ሰው አስቀድሞ ሊገምተው እና በፍፁም ሊያስቀረው የማይችለው ምክንያት ነው፡፡

**አንቀጽ 295** <u>**የምስክር ወይም ሰነድ አቅራቢ አለመቅረብ**</u>

1. ምስክር ወይም ሰነድ አቅራቢ ወይም ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የታዘዘ ማንኛውም ሰው መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣል፤ እንደአስፈላጊነቱ ተይዞ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. ምስክር ማቅረብ ባልተቻለ ጊዜ ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ በቀረበው ማስረጃ፣ በቀዳሚ ምርመራ ወይም ፍርድ ቤት የተሰጠ የምስክርነት ወይም የተሳሽነት የእምነት ቃል ወይም በሌላ ማስረጃ መሠረት ውሳኔ እንዲሰጥ ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፤ ፍርድ ቤቱም ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

3. ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ተጠርቶ ያልቀረበው የተከሳሽ መከላከያ ምስክር፣ ሰነድ አቅራቢ ወይም የሙያ ምስክር እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በተከሳሽ አመልካችነት ወይም በራሱ አነሳሽነት በቀረበ ማስረጃ መሠረት ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት ውሳኔ መስጠት የማይቻል እንደሆነ መዝገቡ ለጊዜው ይቋረጣል፣ ተከሳሽ በማረፊያ ወይም ማቆያ ቤት እንደሆነ በዋስ ይለቀቃል፡፡

5. ኤግዚቢት ወይም የተያዘ ዕቃ ካለ ፍርድ ቤቱ ወሳኔ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 296** <u>የግል ከሳሽ አለመቅረብ</u>

1. የግል ከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከአምስት የሥራ ቀናት ያልበለጠ ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣል፡፡

2. የግል ከሳሽ በድጋሚ ቀጠሮ ያልቀረበ እንደሆነ መዝገቡ ለጊዜው ይቋረጣል፤ ተከሳሽ በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ በራስ ዋስትና ይለቀቃል፡፡

3. የግል ከሳሽ መዝገቡ በተቋረጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በቂ ምክንያት እንዳለው በማስረዳት መዝገቡን ካላንቀሳቀሰ የተቋረጠው ክስ እንደገና አይታይም፡፡

4. የግል ከሳሽ ባለመቅረቡ ለሁለት ጊዜ መዝገቡ ከተቋረጠ በማናቸውም ምክንያት መዝገቡን ማንቀሳቀስ አይቻልም፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ስለክርክር</u>
## <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
## <u>ከክስ መስማት በፊት ስለሚኖር ሥርዐት</u>

**አንቀጽ 297** <u>የክስ ማመልከቻ ማቅረብ</u>

ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ በዚህ ሕግ አንቀጽ 260 በተመለከተው መሠረት የክስ ማመልከቻ፣ የማስረጃዎች ዝርዝርና መግለጫ አዘጋጅቶ ክሱን የማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 298** <u>የክስ ብቃት ማረጋገጥ</u>

1. ሬጅስትራር በዚህ ሕግ አንቀጽ 307 መሠረት ክስ ሲቀርብለት፡-

(ሀ) ፍርድ ቤቱ ክሱን ለማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን፣

(ለ) የክስ ማመልከቻውና መግለጫው በዚህ ሕግ አንቀጽ 260 መሠረት መዘጋጀቱንና መሟላቱን፣

(ሐ) በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘሩ ምስክሮች ስምና አድራሻ በአግባቡ መገለፁንና ማስረጃዎች መሟላታቸውን፣እና

(መ) ክሱና ማስረጃው በበቂ ቅጂ መዘጋጀቱን

ያረጋግጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረውን የክስ ማመልከቻ ካረጋገጠ በኋላ ካልተሟላ ተሟልቶ እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፤ የክስ ማመልከቻው የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ፡-

   (ሀ) የክስ መዝገብ ይከፍታል፣

   (ለ) በቅደም ተከተል ቁጥር ይሰጣል፣

   (ሐ) በመዝገቡ ላይ የተሟላ መረጃ ይመዘግባል፣

   (መ) መዝገቡን በመረጃ ቋት (በዳታ ቤዝ) እንዲገባ ያደርጋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተከፈተውን መዝገብ የተከፈተውን መዝገብ ጉዳዩን ለሚመለከተው ዳኛ ይቀርባል፡፡

**አንቀጽ 299 ፍርድ ቤቱ ሥልጣን በሌለው ጊዜ የሚፈጸም ሥርዐት**

1. ሬጅስትራር በዚህ ሕግ አንቀጽ 307 መሠረት ክስ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ክሱን ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን ከተረዳ መዝገቡን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ያስተላልፋል፤ መዝገቡን ከማስተላለፉ በፊት ለዐቃቤ ሕግ ወይም ለግል ከሳሽ ያሳውቃል፡፡

2. ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ በሬጅስትራሩ ውሳኔ ካልተስማማ ቅሬታውን በጽሑፍ፣ በቃል ወይም አመቺ በሆነ ማንኛውም መንገድ ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት ሊያቀርብ ይችላል፤ ፕሬዚዳንቱም ወድያው ተገቢውን ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

3. ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ በፕሬዚዳንቱ ውሳኔ ካልተስማማ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተገቢው ውሳኔ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ መሠረት መዝገቡ ሥልጣን ወዳለው ፍርድ ቤት እስኪተላለፍ ወይም በቀረበው ቅሬታ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት ካለ ከሰባት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ባለበት ይቆያል፡፡

**አንቀጽ 300** <u>**የክስ ሕጋዊነት ማረጋገጥ**</u>

1. የክስ መዝገብ የቀረበለት ዳኛ፡-

    (ሀ) በዚህ ሕግ አንቀጽ ----- (ከ309 በላይ ያለው ነው) ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) በተደነገገው መሠረት ውሳኔ ካልተሰጠ በስተቀር ፍርድ ቤቱ ክሱን ለማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን፣

    (ለ) በክሱ የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊትና የተጠቀሰው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የሚጣጣም መሆኑን፣

    በማረጋገጥ ክሱን የሚሰማበትን ቀን ይወስናል፡፡

2. ዳኛው ፍርድ ቤቱ ክሱን ለማየት ሥልጣን የለውም ብሎ የወሰነ እንደሆነ ውሳኔውን እና መዝገቡን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዲተላለፍ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መዝገብ የተላለፈበት ፍርድ ቤት ክሱን ለማየት ሥልጣን የለኝም ብሎ የወሰነ እንደሆነ የዚሁ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ሥልጣን ያለውን ፍርድ ቤት በመለየት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

4. ክሱ የቀረበለት ዳኛ የተጠቀሰው የሕግ ቁጥርና የወንጀሉ ዝርዝር የማይጣጣም መሆኑን ሲያረጋግጥ እንደነገሩ ሁኔታ ወዲያውኑ ወይም በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክሱ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

5. ዳኛው በጊዜ ገደብ ውስጥ ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ ክሱን አስተካክሎ ካላቀረበ የፍሬ ነገር ማስተካከያ ሳያደርግ የሕጉን ቁጥር ከፍሬ ነገሩ ጋር ብቻ በማስተካከል ክሱን ማየት ሊቀጥል ይችላል፡፡

6. የክሱን ማሻሻል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ከተመለከተው በተለየ ሁኔታ ማስተካከልን የሚጠይቅ እንደሆነ ክሱ ተሻሽሎ የሚቀጥል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኛው መዝገቡን ይዘጋል፡፡

7. ዳኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (5) እና (6) የተመለከተውን ሲወስን የዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽን አስተያየት መቀበል አለበት፡፡

**አንቀጽ 301** <u>**ክሱ የሚሰማበትን ቀን ስለመወሰን**</u>

በአንቀጽ ..... መሠረት ክሱ ለፍርድ ቤት ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ ነገሩ የሚሰማበትን ቀን ወስኖ በተወሰነው ቀንና ሰዓት ተከሳሹና ዐቃቤ ሕጉ እንዲቀርቡ መጥሪያ ይሰጣል፤ ተከሳሹ በማረፊያ ቤት ያለ እንደሆነ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 302** <u>**ቅድመ ክስ መስማት**</u>

1. ዳኛው በዚህ ሕግ አንቀጽ 309 መሠረት የክሱን ሕጋዊነት ካረጋገጠ በኋላ ጉዳዩ፡-

   (ሀ) ቀላል ወንጀል እንደሆነ በቀጥታ ክስ እንዲታይ፤

   (ለ) መካከለኛ ወንጀል እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በቀጥታ ክስ ወይም በቅድመ ክስ እንዲታይ፤

   (ሐ) ከባድ ወንጀል እንደሆነ በቅድመ ክስ እንዲታይ፤

   መወሰን አለበት፡፡

2. በከባድ ወንጀል ጉዳዩ በጽሑፍ እንዲታይ ፍርድ ቤቱ ካልወሰነ በቀር የቅደመ ክስ ክርክር በቃል ሊካሔድ ይችላል፡፡

3. ዳኛው ቅድመ ክስ መስማት አስፈላጊ ነው ብሎ ሲወስን ተከራካሪ ወገኖች ይጠራል፣ የቅድመ ክሱ የሚሰማበትን ቀንና ዝርዝር ጉዳዮችን ከመጥሪያው ጋር ተያይዞ እንዲላክ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ሰነዶችና የማስረጃ ዝርዝር ከቀጠሮው ቀን ቢያንስ አሥር ቀን አስቀድሞ ለተከሳሹ መድረስ አለበት፡፡

4. ሬጅስትራር ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን የክስ ማመልከቻ፣ የማስረጃ ዝርዝርና መግለጫ ከመጥሪያው ጋር ለተከሳሹ እንዲደርስ ይልካል፡፡

5. በቅድመ ክስ በሚላክ መጥሪያ ተከሳሹ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ሰነድ ውስጥ የሚስማማባቸው ጉዳዮች፣ የመከላከያ ማስረጃዎች ዝርዝርና የማስረጃ መግለጫ እንዲያቀርብ ይገልጽለታል፡፡

## አንቀጽ 303 <u>የክልል ሥልጣን</u>

ክልሎች ስለቅድመ ክስ ሥርዐት በሚመለከት በሕግ በተለየ ሁኔታ ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 304 <u>በቅድመ ክስ መስማት የሚከናወኑ ተግባራት</u>

1. በቅድመ ክስ መስማት፡-

(ሀ) ክሱን በማሻሻል ተከራካሪዎች ካልተስማሙ ጭብጡን የመለየት፤

(ለ) በክስ መስማት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ጭብጥ መለየት፣ በመጀመሪያ ተቃውሞ የሚቀርብ ተቃውሞ ጭብጥ የመለየት፣

(ሐ) በተጨማሪ መቅረብ ያለበት ማስረጃን የመለየትና ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ የማድረግ፣

(መ) የታመነና የተካደ ጉዳይና ማስረጃን የመለየት፣

(ሠ) ተከሳሽ በክሱ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመሥራቱ በሙሉ ያመነ እንደሆነ ወዲያውኑ ውሳኔ እንዲሰጥ የማድረግ፣

(ረ) የምስክሮችና ሌሎች ማስረጃዎች አቀራረብ፣ ቅደም ተከተል የመለየት፣

(ሰ) ክርክሩ የሚመራበትን ሥነ ሥርዐት የመለየት፣

(ሸ) የፍርድ ሒደት ጊዜ ገደብን በዝርዝር የማስቀመጥ፣

(ቀ) ጉዳዩ በልዩ ሁኔታ በዝግ ችሎት መታየት ያለበት ስለመሆኑ የመለየት፣

(በ) የቃለ መኃላ አጠቃቀምን የመወሰን፣

(ተ) ፍርድ ቤት በዚህ ሕግ አንቀጽ 313 ንዑስ አንቀጽ (2) ቅድመ ክስ በጽሑፍ እንዲሆን ያዘዘ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ ማስረጃ እንዲያስታውቁ ወይም እንዲለዋወጡ የማድረግ፣

(ቸ) የመጥሪያ ዐይነትን የመለየት፣

(ኦ) ተከላካይ ጠበቃ፣ አስተርጓሚ፣ የትርጉም ሥራ እና ለፍትሕ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ባለሙያዎችን አስቀድሞ እንዲሟሉና እንዲታወቁ የማድረግ፣

(ከ) ክርክሩ የሚካሔድበት የችሎት አዳራሽና አስፈላጊ ቁሳቁሶች አሟልቶ ማዘጋጀትና ለባለጉዳዮችና ሊከታተሉ ለሚፈልጉ ሰዎች ችሎቱን የማሳወቅ፣ ተግባር ይከናወናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከ(ሀ) እስከ (ቀ) የተደነገገውን ተግባር የማከናወን የዳኛ ኃላፊነት ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከ(በ) እስከ (ከ) የተደነገገውን ተግባር የማከናወን የሬጅስትራር ኃላፊነት ነው፡፡

4. የቅድመ ክስ መሰማት በዳኛው ወይም በዳኛው ትእዛዝ በሬጅስትራር ሊከናወን ይችላል፡፡ ሒደትቱ የተከናወነው ሬጅስትራር እንደሆነ ሒደቱ እንደተጠናቀቀ ስለተከናወኑ ተግባራት ዝርዝርና የተሟላ መግለጫ ለዳኛው ያቀርባል፡፡

5. የቅድመ ክስ መሰማት ተግባር በዳኛው የሚከናወን እንደሆነ በተለዩት ጉዳዮች ላይ እንደነገሩ ሁኔታ ዳኛው ወድያውኑ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ተግባሩ በሬጅስትራር የሚከናወን እንደሆነ በፍርድ ቤቱ ሥልጣን ላይ በሚነሳ የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ላይ ሬጅስትራር ወዲያውኑ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 305** <u>**የዐቃቤ ሕግ የክስ መግለጫ**</u>

1. ዐቃቤ ሕግ ከክስ ማመልከቻ በተጨማሪ የሚያቀርበው የክስ መግለጫ፡-

(ሀ) ምስክሮች የሚመሰክሩበትን ጉዳይ እና ይህንኑ ለማስረዳት የሚጠሩ ምስክሮችን ስም፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ዜግነት ሥራና አድራሻ፣

((ለ) ክሱን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለማስረዳት የቀረበ የኤግዚቢት ዝርዝር፣ ማስረጃና ስለሚያስረዳው ጉዳይ አጭር መግለጫ፣ እና

(ሐ) ተከሳሽ ጥፋተኛ ቢባል በዐቃቤ ሕግ ሊቀርብ የሚችል የቅጣት ማክበጀና ማቅለያን ያገናዘበ የቅጣት አስተያየትን፣

መያዝ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1(ሐ) መሠረት የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤት ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት አያስችልም ብሎ ካመነ የቅጣት አስተያየት ከፍርድ በፊት እንዳይቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. የምስክሮች ማንነት ወይም ሌላ ማስረጃ በቅድመ ክስ ወይም በክስ መስማት ደረጃ ቢታወቅ የምስክሮች ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወይም መገለፁ እውነቱን ለማግኘት እንቅፋት የሚፈጥር ወይም በሕዝብ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ ዐቃቤ ሕግ ካመነ ይህንኑ ከማስረጃው ዝርዝር መግለጫ ጋር መግለጽ አለበት፡፡

4. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የቀረበውን ማመልከቻ ከተቀበለ የምስክሮችን ማንነትና ሌሎች ማስረጃዎች በሚስጢር እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡ ፍርድ ቤት የተከሳሹን ጥፋተኝነት ለማስረዳት የሚቀርቡ ማስረጃዎች መኖራቸውና በክስ መግለጫው የማይገለጹ መሆናቸውን በመጥሪያው ላይ ማመልከት አለበት፡፡

## አንቀጽ 306 <u>የተከሳሽ የመከላከያ መግለጫ</u>

1. የዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ እንደደረሰ የተከሳሽየመከላከያ መግለጫ፡-

   (ሀ) ክስና ማስረጃ ላይ የሚስማማባቸውና የማይስማማባቸው ጉዳዮች፣

   (ለ) የመከላከያውን ሐሳብና የማስረጃውን ዝርዝር፣ እና

   (ሐ) ተከሳሽ ጥፋተኛ ቢባል ሊጣልበት ስለሚችለው የቅጣት አስተያየትና ይህንኑ ለማስረዳት የሚጠቅምን ማስረጃ፣

   ሊይዝ ይችላል፡፡

2. የወንጀል ክሱ የሙስና ወይም የሽብርተኝነት እንደሆነ የተከሳሽ መከላከያ መግለጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱ ዝርዝሮችን መያዝ አለበት፡፡

3. ፍርድ ቤት በተከሳሹ የቀረበው የመከላከያ መግለጫ ቅድመ ክስ ከሚሰማበት ቀጠሮ ቢዘገይ ከአምስት ቀናት በፊት ለዐቃቤ ሕግ እንዲደርስ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

## አንቀጽ 307 ያልተገለጸ ተጨማሪ ማስረጃ

1. ፍርድ ቤት ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ጠቃሚ የሆነ ያልተገለጸ ማስረጃ አለ ብሎ ካመነ ማስረጃውን ያልገለፀው ተከራካሪ ወገን ማስረጃውንና መግለጫውን እንዲያቀርብ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበ ማስረጃና መግለጫ ወይም ከክስ መሰማት ቀጠሮ ሰባት ቀናት በፊት ወይም በቅድመ ክስ መስማት ቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤቱ ለሌላኛው ተከራካሪ ወገን እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 308 የክስ መስማት ቀንን መወሰን

1. የቅድመ ክስ መግለጫን መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤት እንደአግባብነቱ ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ፣ የዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ ማስረጃ ክስ እንዲሰማ በተወሰነው ቀንና ሰዓት እንዲቀርቡ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

2. ተከሳሽ፣ በተወሰነው ቀን እንደማይቀርብ ከወዲሁ በእርግጠኝነት ከታመነ በዐቃቤ ሕግ አመልካችነት ክሱ በሚሰማበት ቀን ተይዞ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

3. ፍርድ ቤቱ መቅረብ ያለበት ሌላ ማስረጃ በቀጠሮ ቀን ማቅረብ እንደማይቻል ከወዲሁ እርግጠኛ እንደሆነ በዐቃቤ ሕግ ወይም በግለ ከሳሽ ወይም በተከሳሽ አመልካችነት ክርክሩ የሚመራበት፣ ማስረጃ የሚቀርብበትና የሚቀበልበት ሌላ አግባብ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 309 የክርክር ዝግጅት

1. ፍርድ ቤቱ የክስ መስማት ከመጀመሩ በፊት በግልጽ ችሎት ክርክሩን ለማካሄድ በቂ ዝግጅት መደረጉንና የችሎት ክፍሉን ተከራካሪዎች ማወቃቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. ፍርድ ቤት ክርክሩን የሚያካሔድበትን ቦታና ክርክሩ የሚጀምርበት ሰዓት ክርክሩ መከታተል ለሚፈልግ ሰው አመቺ በሆነ ማንኛውም መንገድ ማሳወቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 310 <u>የክርክር ሥነ ሥርዐት</u>**

በሌላ ሕግ በተለየ መንገድ ክርክር እንዲካሔድ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም የወንጀል ክርክር፡-

(1) በመደበኛ ሥርዐት፣

(2) በተፋጠነ ሥርዐት፣

(3) በክለሳ ሥርዐት፣

(4) በደንብ መተላለፍ ሥርዐት፣

(5) በወጣት ጥፋተኞች ሥርዐት፣

(6) የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ሥርዐት፣

(7) በይግባኝ፣ ሰበር፣ ፍርድ ክለሳ እና መሰየም ሥርዐት

ብቻ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 311 <u>የክስ መስማት ሒደትን በሕመም ምክንያት መከታተል አለመቻል</u>**

1. ማንኛውም ተከሰሰ ሰው የክስ መስማት ሒደቱና ክርክሩን ለመከታተል ብቁ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በተከሳሹ በአካል ወይም በአዕምሮ የህመም ምክንያት፡-

(ሀ) የእምነት ክህደት ቃል መስጠት ካልቻለ፣

(ለ) የቀረበበትን ክስና ውጤት መረዳት ካልቻለ ወይም በዚህ ረገድ ጠበቃውን ማዘዝና ማገዝ ካልቻለ፣

(ሐ) የቀረበበትን ክስ መከላከል፣ ወይም

(መ) በሌላ መሰል ምክንያት የመስማት ሒደቱን መከታተል ከተሳነው፣

በራሱ ወይም በጠበቃው ጠያቂነት የክስ መስማት ሒደቱ እንዲተላለፍ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

3. ፍርድ ቤቱም እንደነገሩ ሁኔታ ጥያቄውን ከተቀበለ ተከሳሹ በጤና ባለሙያ እንዲመረመርና የምርመራ ውጤት እንዲቀርብለት ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በቀረበ የባለሙያ ሪፖርት የተከሳሽ የጤና መታወክ ጊዜያዊ እንደሆነና ክሱን ለመከታተል ብቁ እንደሆነ አጭር ቀጠሮ በመስጠት ፍርድ ቤቱ ክሱን መስማት ይቀጥላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በቀረበ የባለሙያ ሪፖርት:-

   (ሀ) ተከሳሽ ጉዳዩን ለመከታተል ብቁ አለመሆኑን ካመላከተና ዐቃቤ ሕግ ከተስማማ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲተላለፍ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

   (ለ) ዐቃቤ ሕግ ስለተከሳሹ ብቁ አለመሆን ካልተስማማ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ለመስማት ሒደቱ ብቁ መሆን አለመሆን በማከራከር ይወስናል፡፡

6. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ተከሳሽ ለክርክሩ ብቁ አይደለም ብሎ የወሰነ እንደሆነ፡

   (ሀ) ተከሳሹ በራሱ ወይም በኅብረተሰቡ ላይ አደጋ የሚፈጥር እንደሆነ ለዚህ ዓላማ ተብሎ በተቋቋመ ተቋም ሥር እንዲቆይ፣

   (ለ) እንደነገሩ ሁኔታ በማረሚያ ቤት እንዲቆይ፣ ወይም

   (ሐ) በዋስ እንዲለቀቅና በየጊዜው ሪፖርት እንዲቀርብለት፣

   ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

7. ተከሳሹ ፍርድ ቤቱ ከወሰነው ጊዜ ገደብ ወይም ከአንድ ዓመት በኋላ መሻሻል ካላሳየ ፍርድ ቤቱ የተከሳሽ ጠበቃ ባለበት ጉዳዩን በማየት የመሰለው ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 312 <u>የተቀላጠፈ የክርክር ሥርዐት</u>

1. በዚህ ወይም ሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም የወንጀል ክርክር በተቀላጠፈ ሥነ- ሥርዐት መመራት አለበት፡፡

2. ማንኛውም ጉዳይ ከዓቅም በላይ በሆነ ወይም በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት ብቻ ካልሆነ በስተቀር በቀጠሮ ቀን ውሳኔ ማግኘት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

(ሀ) ሬጅስትራር ለሚያከናውነው ተግባር፤

(ለ) ማስረጃ ማስታወቅ ወይም ማለዋወጥ፤

(ሐ) ፍሬነገርና የሕግ ቁጥርን ለማስማማት፤

(መ) በሕግ ነገር ላይ የተነሳ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ፤

ቀጠሮ መሰጠት የለበትም፡፡

4. ማንኛውም የወንጀል ክርክር ክስ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ አለበት፡፡

5. ክልሎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተውን ጊዜ ባጠረ መልኩ ክርክሩን ለማጠናቀቅ በሕግ ሊወሰን ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 313 <u>የተፋጠነ የክርክር ሥርዐት</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 328 የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ፣

   (ሀ) በእጅ ከፍንጅ ወንጀል፣ ወይም

   (ለ) ተከሳሽ ጥፋተኝነቱን ባመነበት ጉዳይ፣ ወይም

   (ሐ) የተከሳሽ ጥፋተኝነት ሊያረጋግጥ የሚችል ግልጽና የተሟላ ማስረጃ ሲቀርብ፣ እና

   (መ) ዐቃቤ ሕግ በተፋጠነ ሥነ ሥርዐት እንዲታይለት ሲጠይቅ፣

   ጉዳዩን በቀጥታ ሰምቶ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ወድያውኑ መሰጠት አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚሰጥ ውሳኔ ክሱ በቀረበበት በአሥራ አምስት ቀናት ውስስጥ መጠናቀቅ አለበት፡፡

3. በተፋጠነ ሥነ ሥርዐት የሚቀርብ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ክስ በቃል ሊቀርብ ይችላል፤ በቃል የቀረበው ክስ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ለፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ክስ በተቀላጠፈ ሥርዐት እንዲታይ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ የለበትም፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ክስ ስለመስማት
## ዝቅተኛ ንዑስ ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 314 ግልጽ ችሎት

1. የተከሰሰ ሰው ክስ ከቀረበበት በኋላ ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመስማት መብት አለው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ የተከራካሪ ወገኖችን የግል ህይወት፣ የሕዝቡን ሞራል ሁኔታና የሃገሪቱን ደኅንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት እንዲሰማ ሊያዝ ይችላል፡፡ ጉዳዩ በዝግ ችሎት መታየቱ አከራካሪ እንደሆነ ይኸው በዝግ ችሎት ታይቶ ይወሰናል፡፡

3. ፍርድ ቤቱ በዝግ ችሎት በልዩ ሁኔታ እንዲከታተሉ የተፈቀደላቸው ሰዎች በችሎት ከተደረገ ክርክር ያገኙትን መረጃ በምስጢር የመጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸውና ይህን ቢጥሱ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ማስጠንቀቅ አለበት፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ጠቅላይ ፍርድ ቤት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 315 የመገናኛ ብዙኃን ዘገባ

በሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኛው ካልከለከለ በስተቀር ለሕዝብ ግልጽ የሆነ ችሎት ለመገናኛ ብዙኃንም መሆን አለበት፡፡

### አንቀጽ 316 የችሎት ሥርዐት ማስጠበቅ

1. የፍርድ ሒደቱ ሁሉም ተከራካሪ ወገን በእኩልነት የሚስተናገድበት፣ የሕግ የበላይነት የሚረጋገጥበት፣ ለተከራካራዎች ነፃና ምቹ በሆነ መልኩ እየተካሔደ መሆኑን ዳኛው ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. የየፍርድ ሒደቱን የሚመራው ዳኛ የችሎት ሥርዐትን የማስከበር ኃላፊነት አለበት፡፡ ሥርዐቱን በሚተላለፉት ላይ በሕግ መሠረት ተገቢውን ርምጃ ይወስዳል፡፡

## ዝቅተኛ ንዑስ ክፍል ሁለት
## የዳኞች መሰየም

### አንቀጽ 317 በአምስትና በላይ በሆኑ ዳኞች የሚታዩ ጉዳዮች

በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ፡-

1. በሰበር የሚታዩ ጉዳዮች፣
2. ይግባኝ ቢቀርብበትም ባይቀርብበትም በጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚታይ የሞት ፍርድ ቅጣት ይግባኝ ጉዳዮች
3. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች የተለያየ ውሳኔ የሰጡባቸው ጉዳዮች፣
4. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ጉባዔ በአምስት ወይም ከአምስት በላይ ዳኞች እንዲታዩ የወሰነባቸው ጉዳዮች፣

ከአምስት እና በላይ በሆኑ ዳኞች መታየት አለባቸው፡፡

### አንቀጽ 318 በሦስት ዳኞች የሚታዩ ጉዳዮች

1. በማንኛውም ደረጃ፡-

 (ሀ) አሥራ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ በጽኑ እስራት የሚያስቀጡ ጉዳዮች፣

 (ለ) ከአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት በታች የሚያስቀጡ የወንጀል ጉዳዮች ሆነው የጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኞች ጉባዔ በሦስት ዳኞች እንዲታዩ በመመሪያ የወሰናቸው ጉዳዮች፣

 (ሐ) በጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚታዩ ጉዳዮች፣ እና

 (መ) የሰበር የማጣራት ጉዳዮች፣

 በሦስት ዳኛ መታየት አለባቸው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፡-

 (ሀ) በዕርቅ፣ በጥፋተኝነት ድርድርና በአማራጭ የመፍትሔ ሥርዐት ታይቶ ለፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ፣

 (ለ) የክስን ሕጋዊ ብቃት ለማረጋገጥ፣

(ሐ) ከሳሽ ወይም ምስክር መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ ቢቀር ተይዞ እንዲቀርብ ወይም ያልቀረበው መጥሪያ ሳይደርሰው እንደሆነ ተገቢውን ትእዛዝ ለመስጠት፣

(መ) የተከራካሪዎች ማስረጃ በበቂ ምክንያት ባልቀረበ ጊዜ ተለዋጭ ቀጠሮ ለመስጠት፣

(ሠ) ጉዳዩ በተቀጠረበት ቀን አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ያልተሠራ እንደሆነ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠትን የሚመለከቱ ትእዛዝ የመስጠት፣ ወይም

(ረ) የክስ ማዛወርን የሚመለከቱ አቤቱታዎች

ጉዳይ በአንድ ዳኛ ሊታዩ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 319 <u>በአንድ ዳኛ የሚታዩ ጉዳዮች</u>

በማንኛውም ደረጃ፡-

(ሀ) ከአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት በታች የሚያስቀጡ ጉዳዮች፣

(ለ) ከአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት በላይ የሚያስቀጡ የወንጀል ጉዳዮች ሆነው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ጉባዔ በአንድ ዳኛ እንዲታዩ በመመሪያ የወሰናቸው ጉዳዮች፣

(ሐ) የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል ጉዳይ ተጠያቂ የሚሆንባቸው ጉዳዮች፣

(መ) በገንዘብ ብቻ ወይም በእስራት  የሚያስቀጡ ወንጀሎች፣

(ሠ) የመያዣ፣ የብርበራ እና መሰል የትእዛዝ ጉዳዮች፣ ወይም

(ረ) በሦስት እና ከሦስት በላይ በሆኑ ዳኞች የተሰጠን ፍርድ ወይም ውሳኔ ለተከራካሪዎች ለመግለጽ፣

በአንድ ዳኛ ሊታዩ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 320 <u>ልዩ ሁኔታዎች</u>

1. በማንኛውም ደረጃ፡-

(ሀ) የዋስትናን ጥያቄ ተመልክቶ ተገቢውን ትእዛዝ መስጠት፣

(ለ) በዕግድ መጠየቂያ አቤቱታ ላይ ትእዛዝ መስጠት እና የይግባኝ ቅሬታን ለመስማት፣

(ሐ) በክስ ላይ የቀረበውን መቃወሚያ ሰምቶ ተገቢውን ትእዛዝ ለመስጠት፣

(መ) ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠውን ፍርድ ውድቅ እንዲደረግለት የሚያቀርበውን አቤቱታ ተመልክቶ ተገቢውንትእዛዝ ለመስጠት፣ወይም

ጉዳዩ በሁለት ዳኛ ሊታይ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዕስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ለቀረቡ ጉዳዮች በዳኞች ውሳኔ ሲሰጥ የልዩነት ሐሳብ ከተፈጠረ ጉዳዩ በተሟላ ችሎት ታይቶ ውሳኔ መሰጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 321 <u>ተደራራቢ ወንጀሎች</u>**

ለፍርድ ቤት የቀረበው ክስ በተደራረቡ ወንጀሎች እንደሆነ ጉዳዩ የሚታየው ከባዱን ወንጀል ለማየት በሚሰየመው ችሎት መሆን አለበት፡፡

**አንቀጽ 322 <u>የውሳኔ አሰጣጥ</u>**

ማንኛውም ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 323 <u>የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ</u>**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ የዚህ ሕግ አንቀጽ 254 እና አንቀጽ 255 ድንጋጌዎችን በመመሪያ ወይም በውሳኔ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 324 <u>የክልሎች ሥልጣን</u>**

ክልሎች በዚህ ሕግ አንቀጽ 389 እና 390 በተመለከቱ ጉዳዮች በሕግ በተለየ ሁኔታ ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡

## <u>ምዕራፍ ሰባት</u>
## <u>ክስ ስለመስማት</u>

**<u>አንቀጽ 324 የክሱ መስማት ስለመጀመር</u>**

1. ፍርድ ቤቱ ክስ መስማት ከመጀመሩ በፊት፡-

(ሀ) ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ እና ተከሳሽ መቅረባቸውን ያረጋግጣል፡፡

(ለ) ተከሳሽ የፍርድ ቤቱን የሥራ ቋንቋ ይረዳ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ ተከሳሹ የፍርድ ቤቱን የሥራ ቋንቋ የማይረዳ እንደሆነአስተርጓሚ ይመድብለታል፡፡ ያለአስተርጓሚ የተካሔደ የፍርድ ሒደት እንዳልተካሔደ ይቆጠራል፡፡

(ሐ) ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ አቅም በማጣት ምክንያት በጠበቃ ያልተወከለ መሆኑንና ያለጠበቃ ቢከራከር ፍትሕ ይዛባል ብሎ ሲያምን በመንግሥት ወጪ ጠበቃ እንዲመደብለት ያዛዝል፡፡

2. ተከሳሹ አደገኛ ወይም የኃይል ድርጊት የሚፈጽም ለመሆኑ ወይም ለማምለጥ የሚሞክር መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ምክንያት ቀርቦ ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደ በስተቀር ፍርድ ቤት በሰንሰለት ታስሮ ችሎት አይቀርብም፡፡
3. ፍርድ ቤት ለክርክር የቀረበውን ማንኛውም ተከሳሽ ለክርክሩ በተለየ ቦታ ሆኖ ክርክሩን እንዲያካሔድ ያደርጋል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ የተከሳሹን ማንነት ለማረጋገጥ ስሙን፣ ዕድሜውን፣ ፆታውን፣ የመኖሪያ አድራሻውን፣ ሥራውን፣ የትምህርት ደረጃውን፣ የቤተሰቡን ሁኔታ እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን መረጃዎች ጠይቆ ወይም የተረዳውን ይመዘግባል፡፡
5. ፍርድ ቤቱ የተከሳሹን ማንነት ከመዘገበ በኋላ የቀረበውን እያንዳንዱን ክስ በንባብ በማሰማት ተከሳሹ እንዲረዳው ያደርጋል፡፡
6. ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 310 እና 311 መሠረት የቅድመ ክስ መስማት መካሔዱን ያረጋግጣል፣ ውጤቱን ለተከራካሪዎች ይገልፃል፡፡ ሌሎች በቅድመ ክስ መስማት የተለዩ ጉዳዮች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የክስ መስማት ይቀጥላል፡፡ዐቃቤፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ ... እና ... መሠረት የቅድመ ክስ መስማት ወይም የቀዳሚ ምርመራ መካሔዱን ያረጋግጣል፣ የመዝገቡ ግልባጭ ወይም እንዳግባብነቱ ውጤቱን ለተከራካሪዎች ይገልፃል፡፡

**<u>አንቀጽ 325 የአስተርጓሚ ቃለ መኃላ ወይም ማረጋገጫ</u>**

በፍርድ ቤት የትርጉም አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው አገልግሎቱን ከመስጠቱ በፊት የፍርድ ሒደቱን በትክክል የሚተረጉም ስለመሆኑ በዚህ ሕግ አንቀጽ 370 ለምስክር በተመለከተው ዓይነት ቃለ መኃላ መፈጸም ወይም ማረጋገጫ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል አንድ
## ቀጠሮና የቀጠሮ ውጤት

**አንቀጽ 326 ቀጠሮና የቀጠሮ ምክንያቶች**

1. ዐቃቤ ሕጉ ወይም ተከሳሹ ሲያመለክት ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚረዳ መሆኑን ሲገነዘብ ክሱ በሚሰማበት በማንኛውም ጊዜ ቀጠሮ ለመስጠት ይችላል፡፡
2. ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች፡-
   (ሀ) ዐቃቤ ሕጉ፣ የግል ከሳሽ ወይም ተከሳሹ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ፣
   (ለ) ከዚህ በታች በአንቀጽ ... በተነገረው ምክንያት ተከሳሹ ጉዳዩን መከታተል ያልቻለ እንደሆነ፣
   (ሐ) በአንቀጽ ... መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የተነሳ እንደሆነና ወዲያውኑ መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ፣
   (መ) ዐቃቤ ሕጉ ወይም ተከሳሹ ክሱ የደረሰው ወይም ጠበቃ ያገኘው ከነገሩ መሰማት ጥቂት ቀናት በፊት በመሆኑ ለመዘጋጀት በቂ ያልሆነ እንደሆነ፣
   (ሠ) የዐቃቤ ሕግ፣ የግል ከሳሽ ወይም የተከሳሽ ምስክሮች ተሟልተው ያለመቅረብ ክርክሩን ለማስቀጠል የማይቻል እንደሆነ፣
   (ረ) በዚህ ሕግ አንቀጽ... መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ እንደሆነ፣
   (ሰ) የክሱ ማመልከቻ በተለወጠ፣ በተጨመረ ወይም አዲስ ክስ በቀረበ ጊዜ ተከሳሽ ማስተካከያውን ወይም አዲሱን ክስ በተመለከተ አስተያየት እንዲሰጥበት ወይም ጉዳዩን መስማት ለመቀጠል ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልገው እንደሆነ፣
   (ሸ) ዐቃቤ ሕጉ ወይም ተከሳሹ እንደሚቀርብ ቀደም ብሎ ሊገምት የማይችለው ወይም እንደሚቀርብ ያላሰበው አዲስ ማሰረጃ በድንገት የቀረብ እንደሆነ፣
   (ቀ) በሌላ ፍርድ ቤት የተያዘ ጉዳይ መጀመሪያ ውሳኔ ካላገኘ በቀር በቀረበው ክስ ላይ ውሳኔ የማይሰጥ እንደሆነ፣
   (በ) የተከሳሹን አእምሮ ትክክለኛነት በልዩ አዋቂ ለመወሰን የሚያስፈልግ እንደሆነ፣ ወይም

(ተ) የክሱን መስማት ለመቀጠል የማያስችል ሌላ አስገዳጅ ምክንያት ሲኖር፣

ፍርድ ቤት አግባብነት ያለው ቀጠሮ ለመስጠት ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ረ)፣ (ሰ)፣ እና (ሸ) መሠረት የሚሰጥ ቀጠሮ ፍርድ ቤቱ በበቂ ምክንያት ካላራዘመ በስተቀር ከሰባት ሥራየሥራ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

## አንቀጽ 327 አዲስ ቀጠሮና መጥሪያ

1. ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ... ንዑስ አንቀጽ (3) ከተደነገገው ውጭ ባሉ ፍሬ ነገሮች ላይ የነገሩን መሰማት ሲቀጥር ለቀጠሮ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ለመፈጸም በቂ ለሆነ ጊዜ ብቻ ነው፡፡
2. በዐቃቤ ሕጉ ወይም በተከሳሹ ጥፋት ሳይሆን ቀጠሮ የተሰጠበት ምክንያት ሳይፈጸም የቀረ እንደሆነ ያንኑ ያህል ወይም አጭር ቀጠሮ ይሰጣል፡፡
3. ከዚህ በላይ በአንቀጽ ... ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ)፣ (ቀ) እና (በ) መሠረት የነገሩ መሰማት የተቀጠረ እንደሆነ ቀጠሮ የተሰጠበት ምክንያት ሲፈጸም ባለጉዳዮቹና ምስክሮቹ እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዲስ መጥሪያ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 328 የቀጠሮ ውጤት

1. የነገሩ መሰማት በተቀጠረ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ የተሰጠበት ምክንያት እንዲፈጸም አስፈላጊውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ ይኸውም በአንቀጽ ... በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት የሚሰጠውን የመያዝ ትእዛዝ ይጨምራል፡፡
2. በአንቀጽ ... መሠረት ቀጠሮ ሲሰጥ ተከሳሹ አእመሮውን ልዩ አዋቂ ሊመረምረው በሚቻልበት ሥፍራ ተይዞ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 329 የክስ መሰማት ተከታታይ ስለመሆኑ

ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግን ወይም የተከሳሽን ማስረጃ በሚሰማበት ጊዜ በተከታታይ መስማት አለበት፡፡ ሆኖም ለዳኞች፣ ለተከራካሪ ወገኖች እና ለምስክሮች እረፍት ወይም ጉዳዩን በአዳሪ በቀጣዩ የሥራ ቀን ለመስማት ወይም ሌላ አስገዳጅ ነገር ሲከሰት ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ ለመስጠት ይችላል፡፡

## አንቀጽ 330 የክስ መስማት ሂደትን በሕመም ምክንያት መከታተል አለመቻል

1. ማንኛውም የተከሰሰ ሰው የክስ መስማት ሂደቱና ክርክሩን ለመከታተል ብቁ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በተከሳሹ በአካል ወይም በአዕምሮ የህመም ምክንያት፡-

   (ሀ) የእምነት ክህደት ቃል መስጠት ካልቻለ፣

   (ለ) የቀረበበትን ክስና ውጤት መረዳት ካልቻለ ወይም በዚህ ረገድ ጠበቃውን ማዘዝና ማገዝ ካልቻለ፣

   (ሐ) የቀረበበትን ክስ መከላከል፣ ወይም

   (መ) በሌላ መሰል ምክንያት የመስማት ሂደቱን መከታተል ከተሳነው፣

   በራሱ ወይም በጠበቃው አማካኝነት የክስ መስማት ሂደቱ እንዲተላለፍ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
3. ፍርድ ቤቱም እንደነገሩ ሁኔታ ጥያቄውን ከተቀበለ ተከሳሹ በጤና ባለሙያ እንዲመረመርና የምርመራ ውጤት እንዲቀርብለት ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በቀረበ የባለሙያ ሪፖርት የተከሳሽ የጤና መታወክ ጊዜያዊ እንደሆነና ክሱን ለመከታተል ብቁ እንደሆነ አግባብ ያለው ቀጠሮ በመስጠት ፍርድ ቤቱ ክሱን መስማት ይቀጥላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በቀረበ የባለሙያ ሪፖርት፡-

   (ሀ) ተከሳሽ ጉዳዩን ለመከታተል ብቁ አለመሆኑን ካመላከተ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲተላለፍ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

   (ለ) ፍርድ ቤቱ ስለተከሳሹ ጉዳዩን የመከታተል ብቃት ዐቃቤ ሕግ አስተያየት እንዲሰጥበትና በማከራከር ሊወስን ይችላል፡፡
6. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ተከሳሽ ለክርክሩ ብቁ አይደለም ብሎ ከወሰነ፣

   (ሀ) ተከሳሹ በራሱ ወይም በሕብረተሰቡ ላይ አደጋ የሚፈጥር እንደሆነ ለዚህ ዓላማ ተብሎ በተቋቋመ ተቋም ስር እንዲቆይ፣

   (ለ) እንደነገሩ ሁኔታ በማረሚያ ቤት እንዲቆይ፣ ወይም

   (ሐ) በዋስ እንዲለቀቅና በየጊዜው ሪፖርት እንዲቀርብለት፣

   ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
7. ተከሳሹ ፍርድ ቤቱ ከወሰነው ጊዜ ገደብ ወይም ከአንድ ዓመት በኋላ መሻሻል ካላሳየ ፍርድ ቤቱ የተከሳሽ ጠበቃ ባለበት ጉዳዩን በማየት የዐቃቤ ሕጉን የመክሰስ መብት ጠብቆ ፋይሉን ይዘጋል ወይም ክሱን ይሰርዛል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የመጀመሪያ ደረጃ መቃዎሚያ

**አንቀጽ 331 ክሱን ስለመቃወም**

1. ፍርድ ቤቱ ክሱን ለተከሳሹ ካነበበለትና እንዲረዳው ካደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ክሱን ይቃወም እንደሆነ ይጠይቀዋል፡፡

(ሀ) ፍርድ ቤቱ ክሱን ለመስማት ሥልጣን የሌለው እንደሆነ፣

(ለ) በቀረበበት ክስ ከዚህ ቀደም ተከሶ ነፃ የወጣ ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ከሆን፣

(ሐ) ጉዳዩ በእርቅ፣ በድርድር፣ በአማራጭ መፍትሔ ሥርዐት ወይም በሌላ የሕግ አግባብ ውሳኔ ያገኘ እንደሆነ፣

(መ) ክስ የቀረበበት ወንጀል በይርጋ የታገደ ወይም ምኀረት የተደረገበት እንደሆነ፣

(ሠ) ተከሳሹ ያለመከሰስ ልዩ መብት ያለው ሲሆንና ይኸው መብት ያልተነሳ እንደሆነ፣

(ረ) ክሱ መታየት ያለበት በልዩ ሥነ ሥርዐት ሆኖ ክሱ በመደበኛ ክስ የተመሠረተ ሰሆን፤

(ሰ)ተከሳሹ የቀረበበት ክስ በሌላ ፍርድ ቤት ወይም ችሎት እየታየ እንደሆነ፣

(ሸ) በሌላ ፍርድ ቤት ወይም በሌላ ችሎት የቀረበ ክስ ሳይጠናቀቅ በዚህ የወንጀል ክስ ውሳኔ ለመስጠት የማይቻል እንደሆነ፣

(ቀ) የክስ ማመልከቻው በዚህ ሕግ መሠረት ያልተዘጋጀ እንደሆነ፣

(በ) በክስ ማመልከቻው የተጠቀሰው የሕግ ቁጥር ከወንጀሉ ዝርዝር ጋር የማይጣጣም እንደሆነ፣

(ተ)ተከሳሹ ከሌሎች ጋር በመሆን በተከሰሰበት ወንጀል ክሱ ለብቻው ተነጥሎ ባይታይለት የሚጎዳው እንደሆነ፣ ወይም

(ቸ) የቀረበበት ክስ ሁለትና ከዚያ በላይ ሆኖ የተወሰኑት ክሶች በአንድ ክስ የሚጠቃለሉ እንደሆነ፣

ይህንኑ በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም፣ ፍርድ ቤቱ ወደሥረ ነገሩ እንዳይገባ የሚከለክለው ፍሬ ነገር መኖሩን ከተረዳ በራሱ አስተያየት አግባብነት ያለው ትእዛዝ ለመስጠት ይችላል፡፡

3. ተከሳሹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (1) መሠረት የተጠቀሱት የመጀመሪያ ደረጃ መቃዎሚያዎች ወዲያውኑ ያላቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱን የሚጸና ፍርድ ለመስጠት የሚያግደው ካለሆነ በቀር እነዚህን መቃወሚያዎች በሌላ ጊዜ ሊያቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 332 በመቃወሚያ ላይ ስለመወሰን**

ፍርድ ቤቱ፣

(1) ተከሳሽ በዚህ ሕግ አንቀጽ … መሠረት የሚያቀርበው መቃወሚያ ከመዘገብ በኋላ፣

(ሀ) የዐቃቤ ሕጉን መልስ ወይም አስተያየት እንዳለው ይጠይቀዋል፤

(ለ) በቀረበው መቃወሚያ ወድያውኑ መወሰን የሚቻል እንደሆነ ወይም ዐቃቤ ሕጉ መልስ ወይም አስተያየት የሌለው ወይም ተቃውሞው ተቀባይነት ካላገኘ ቀጠሮ መስጠት ሳያስፈልግ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

(2) ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ማጣራት ወይም በተጨማሪ ማስረጃ ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን ካመነ አጭር ቀጠሮ በመስጠት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የተከሳሹ እምነት ክህደት

**አንቀጽ 333 ተከሳሹን የእምነት ወይም ክህደት ቃል ስለመጠየቅ**

1. ፍርድ ቤቱ፣ ተከሳሹ ተቃውሞ ያላቀረበ ወይም ውድቅ የተደረገበት ያለ እንደሆነ በተከሳሹ የክስ ተቃውሞ ላይ ትእዛዝ ከሰጠና ክሱን ለተከሳሹ አንብቦለት እንዲረዳው ካደረገ በኋላ የተከሳሹን እምነት ክህደት ይጠይቀዋል፡፡
2. ክሱ ከአንድ በላይ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እያንዳንዱን ክስ በተለይ ለተከሳሹ አንብቦለት ካስረዳው በኋላ ለድያንዳንዱ ክስ እምነት ክህደቱን ተቀብሎ ይመዘግባል፡፡
3. የተከሳሹ የእምነት ክህደት ቃል ተከሳሹ በሚሰጠው ቃል አነጋገር ዓይነት መመዝገብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 334 የተከሳሹ የእምነት ቃል**

1. ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረው ወንጀል ለመሥሥራቱ በሙሉ ያመነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል ሲል ከመዘገበ በኋላ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡ ፍርድ ቤቱ የተከሳሹን

ጥፋተኝነት ሲመዘግብ ተከሳሹ የሠጠውን ቃል በተከሳሹ አነጋገር ዓይነት መመዝብ ይኖርበታል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል መፈፀሙን ያመነ ቢሆንም ዐቃቤ ሕግ ማስረጃውን እንዲያቀርብ ለማዘዝና ተከሳሹም የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያሰማ ለመፍቀድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 335 የተከሳሹ የክህደት ቃል

ተከሳሹ የእምነት ክህደት ጥያቄውን በግልፅ የካደ፣ ለጥያቄው መልስ ያልሰጠ፣ ወይም ወንጀሉን መፈጸሙን አምኖ መብቱን ጠብቆ የተከራከረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ አይደሁም ብሏል በማለት ይመዘግባል፡፡

## አንቀጽ 336 የተከሳሹን እምነት ክህደት ስለማሻሻል

1. በተከሳሽ የተሰጠው ቃል የእምነት እንደሆነ እና ፍርድ ቤቱ ክሱን መስማት በሚቀጥልበት ጊዜ ጥፋተኛ አይደለሁም የሚል ቃል መመዝገብ የሚገባው ሆኖ ያገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ አይደሁም ብሏል የሚለውን ቃል ይመዘግባል፡፡
2. በተከሳሹ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔም ውድቅ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 337 ክስ ተነጥሎ እንዲሰማ ስለማዘዝ

ፍርድ ቤት ተከሳሾቹን በአንድነት አጣምሮ ጉዳያቸውን መስማት የመከላከል መብታቸውን የሚያጣብብ ወይም ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል ሆኖ ካገኘው ተከሳሾቹ ጉዳያቸው ተነጣጥሎ ለየብቻ እንዲሰማ ማዘዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 338 ክስን መለወጥና በክስ ላይ መጨመር ወይም ማሻሻል

1. በተከሳሹ ላይ የቀረበው ክስ፡-
   (ሀ) መሠረታዊ ስህተት ያለበት እንደሆነ፣
   (ለ) በክሱ ላይ ያልተጠቀሰ ነገር ሲገኝ፣
   (ሐ) ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ያሳሳተ፣
   (መ) የመከላከል መብቱን ያጣበበ በመሰለ ጊዜ፣ ወይም
   (ሠ) ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል እንደሆነ፣

ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ ማመልከቻ ከቀረበለት እንደነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ ወይም እንዲሻሻል ወይም አዲስ ክስ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

2. ክሱ በተለወጠ፣ በተጨመረ፣ በተሻሻለ ወይም አዲስ ክስ በቀረበ ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ ለተከሳሹ እንዲነበብለትና እንዲረዳው ወይም ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ እንዲቀጥል ሊደረግ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 339 ክስ መለወጥ ወይም መጨመር ስለሚኖረው ውጤት

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 274 መሠረት በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ የክስ መሻሻል ጥያቄ ሲቀርብክሱ ተሻሽሎ ወይም ተለውጦ ወይም አዲስ ክስ የሚቀርብበትን በቂ ጊዜ በመወሰን ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

2. ክሱ በተለወጠ፣ በተጨመረ ወይም አዲስ ክስ በቀረበ ጊዜ ተከሳሹ በዚሁ ክስ ነገሩ እንዲሰማ ዝግጁ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ይጠይቀዋል፡፡ ተከሳሹ ዝግጁ አይደለሁም ካለ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ የሰጠውን ምክንያት ይመረምራል፡፡

3. ፍርድ ቤቱ የክሱ ወዲያውኑ መሰማት የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚነካ ወይም የዐቃቤ ሕግን ክስ ሁኔታ የሚለውጥ ወይም ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ተለዋጭ ቀጠሮ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ክሱ ወዲያውኑ ቢቀጥል የተከሳሹን የመከላከል መብት የማይነካ መስሎ ከታየው ክሱ መሰማት ይቀጥላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጠ የጊዜ ውስጥ ዐቃቤ ሕግ ክሱ አሻሽሎ ወይም ለውጦ ወይም አዲስ ክስ ካላቀረበ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይዘጋል፡፡ ተጠርጣሪው በማረፊያ ቤት ያለ እንደሆነ በዋስትና ይለቀቃል፡፡ በዚህ ክስ ምክንያት የተያዘ ወይም የታገደ ንብረት ካለ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ ክሱን አሻሽሎ ወይም ለውጦ ወይም አዲስ ክስ ለማቅረብ ያልቻለበትን በቂ ምክንያት አቅርቦ ተቀባይነት ካገኘ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከሰጠው ጊዜ ያልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

6. ጉዳዩ መሰማት ከተጀመረ በኋላ ክሱ የተለወጠ ወይም የተጨመረ ወይም አዲስ ክስ የቀረበ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ የዚህ ሕግ አንቀጽ 392 ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት
## ማስረጃና ፍርድ

### አንቀጽ 340 የክርክር መክፈቻ ንግግር

1. ተከሳሽ ወንጀሉን ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ ማስረጃውን ከማሰማቱ በፊት የክርክር መክፈቻ ንግግር ያደረጋል፡፡
2. የክርክር መክፈቻ ንግግር ዓላማም ዐቃቤ ሕግ ክርክሩን ስለሚያቀርብበት አግባብ፣ የማስረጃ ዓይነት፣ ቅደም ተከተልና ስለሚያስረዱበት ጉዳይ የመግለጽ ነው፡፡ ይህንንም በትክክልና ያለ አድልዎ ማመልከት አለበት፡፡
3. ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ የክርክር መክፈቻውን ካበቃ በኋላ መንግሥት የፍትሐብሔር ጉዳዮችን በመወከል ያቀረበውን የፍትሐብሔር ክሱን የክርክር መክፈቻ ንግግር ያደርጋል፡፡
4. ዐቃቤ ሕግ የክስ መክፈቻ ንግግሩን ካበቃ በኋላ በፍትሐብሔር የግል ከሳሽ አጣምሮ ያቀረበውን የፍትሐብሔር ክስ የክርክር መክፈቻ ንግግር ያደርጋል፡፡

## ክፍል አምስት
## በማስረጃ መረጋገጥ የሚያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች

### አንቀጽ 341 መረጋገጥ የሚያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች

ዐቃቤ ሕግ በፍርድ ቤቱ በጭብጥ የተያዘን ፍሬ ነገር እና በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለውን ፍሬ ነገር አግባብነትና ተቀባይነት ባለው ማስረጃ ማረጋገጥ አለበት፡፡

### አንቀጽ 342 በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገር

1. በዚህ ሕግ ውስጥ በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገር ማለት ተከራካሪ ወገኖች ያልተሰማሙበትና የፍሬ ነገሩ መረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለው እንደሆነ ነው፡፡
2. በአንድ የወንጀል ክስ ጉዳይ እንደነገሩ ሁኔታ አንድና ከዚያ በላይ የሆኑ ጭብጦች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 343 አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር**

1. አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር ማለት በጭብጥ ከተያዘው ፍሬ ነገር ጋር ግንኙነት ያለው ሆኖ፣ የዚህ ፍሬ ነገር መረጋገጥ በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር መከሰተ አለመከሰተ የማሳየት ዝንባሌ ያለው ማለት ነው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም፣
   (ሀ) ፍሬ ነገሩ በጭብጥ ከተያዘው ፍሬ ነገር ጋር የተፈጥሮ (የሁነት)፣ የጊዜና ቦታ ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ በጭብጥ የተያዘው ፍሬ ነገር አካል እንደሆነ፣
   (ለ) ፍሬ ነገሩ በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር ለመፈጸም ምክንያት ወይም የታቀደ ዓላማ እንደሆነ፣
   (ሐ) ፍሬ ነገሩ በጭብጥ ለተያዘውን ፍሬ ነገር ለመፈጸም ወይም መከሰት አጋጣሚን የፈጠረ እንደሆነ፣
   (መ) በጭብጥ ለተያዘውን ፍሬ ነገር ለመፈጸም የተደረገ ዝግጅት ወይም በተከታይ የተከናወነ ተግባር እንደሆነ፣
   (ሠ) በጭብጥ የተያዘው ፍሬ ነገር ከመከሰቱ በፊትና ከተከሰተ በኋላ የተከሳሹ፣ የተበዳዩ ወይም በአካባቢው የነበሩ የሌሎች ሰዎች ተግባር፣
   (ረ) ፍሬ ነገሩ በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር ሁነት ውጤት እንደሆነ፣
   (ሰ) በጭብጥ የተያዘው ፍሬ ነገር ከመከሰቱ በፊትና ከተከሰተ በኋላ የነበረው የአካባቢው ሁኔታ፣
   (ሸ) የፍሬ ነገሩ ሁነት በጭብጥ ከተያዘው ፍሬ ነገር ጋር ተመሳሳይነት ሲኖረው፣ ወይም
   (ቀ) በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር በተመለከተ የተከሳሽን ወይም የተበዳይን መልካም ወይም መልካም ያልሆነ ጠባይ፣
   (በ) በሌላ በማናቸውም መልኩ በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር መከሰተ አለመከሰት የማሳየት ዝንባሌ ሲኖረው፣

   ይህ ፍሬ ነገር በጭበጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር አግባብነት አለው፡፡

**አንቀጽ 344 የተረጋገጠ፣ የተስተባበለ ወይም ያልተረጋገጠ ፍሬ ነገር**

1. አንድ በጭብጥ የተያዘ ወይም አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር ተረጋግጧል የሚባለው ፍርድ ቤቱ የነገሩን ሁነት፣ መከሰት አለመከሰት በተገቢው የማስረዳት መጠን መረጋገጡን ሲያምን ነው፡፡
2. አንድ በጭብጥ የተያዘ ወይም አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር ተስተባብሏል የሚባለው ፍርድ ቤቱ የነገሩን አለመሆን ወይም አለመፈጸም በተገቢው የማስረዳት መጠን መረጋገጡን ሲያምን ነው፡፡
3. አንድ በጭብጥ የተያዘ ወይም አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር አልተረጋገጠም የሚባለው ከዚህ በላይ በተነገረው መልኩ ካልተረጋገጠ ወይም ካልተስተባበለ ነው፡፡

## ክፍል ስድስት
## በማስረጃ መረጋገጥ የማያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች

**አንቀጽ 345 የታመነ ፍሬ ነገር**

1. በዚህ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በቀር በተከራካሪ ወገኖች በግልጽ የታመነ ፍሬ ነገር ወይም የእምነት ቃል በማስረጃ መረጋገጥ አያስፈልገውም።
2. ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበበት በስተቀር ጉዳዩን ከሚያየው ፍርድ ቤት ውጪ የታመነ ፍሬ ነገር ወይም የተሰጠ የእምነት ቃል ማስረጃ ማቅረብ ሳይስፈልግ እንደተረጋገጠ ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 346 ፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወስድበት ፍሬ ነገር**

1. የፌደራሉ ፍርድ ቤቶች በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ የታተሙትን የፌደራል ሕጎች በተመለከተ ግንዛቤ ይወስዳሉ፡፡ የክልል ፍርድ ቤቶችም በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣና በራሳቸው ክልል የሕግ ጋዜጣ ታትመው የወጡ ሕጎችን በተመለከተ ግንዛቤ ይወስዳሉ።
2. በጠቅላላ እውቀት እውነትነቱ በታወቀ ፍሬ ነገር እና በቀላሉ በሚገኝ አስተማማኝ ሰነድ ሊረጋገጥ በሚችል ፍሬ ነገር ላይ ፍርድ ቤት ግንዛቤ ይወስዳል፡፡
3. ፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወስድበት ማንኛውም ፍሬ ነገር ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ እንደተረጋገጠ ፍሬ ነገር ይቆጠራል፡፡

4. ሆኖም ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች ላይ ፍርድ ቤቱ ግንዛቤ ሊወስድ አይችልም።
5. ተከራካሪ ወገኖች በጭብጥ የተያዘ ወይም አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር ግንዛቤ እንዲወሰድበት ጥያቄ ወይም በቀረበው ጥያቄ ላይ መቃወሚያ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 347 የህሊና ግምት**

1. የተወሰኑ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች መረጋገጥ የሌላውን ተያያዥ ፍሬ ነገር ሁነት ወይም መከሰት በተመለከተ የህሊና ግምት ለመውሰድ እንደሚቻል በፍሬ ሕጉ የተደነገገ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሌላኛው ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ ሊቆጥረው ወይም ማስረጃ እንዲቀርብበት ሊያዝ ይችላል፡፡
2. የተወሰኑ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች መረጋገጥ የሌላውን ፍሬ ነገር ሁነት ወይም መከሰት የህሊና ግምት መወሰድ እንዳለበት በፍሬ ሕጉ የተደነገገ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮቹ ከተረጋገጡ ሌላው ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ መቁጠር አለበት፡፡ የህሊና ግምት የሚወሰድበት ፍሬ ነገር በመሰረታዊው ፍሬ ነገርና የህሊና ግምት በሚወሰድበት ፍሬ ነገር መካከል ያለው ግንኙነት መረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት
## የማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት

**አንቀጽ 348 አግባብነት ተቀባይነት ስላለው ማስረጃ**

1. አግባብነት ያለው ማስረጃ ማለት በጭብጥ የተያዘውን ጉዳይ ለመወሰን የሚረዱ ፍሬ ነገሮችን መከሰት ወይም አለመከሰት፣ መኖር ወይም አለመኖር፣ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚያስረዳ ወይም የማስረዳት ዝንባሌ ያለው ማለት ነው።
2. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት፣ በዚህ ሕግ ወይም በሌሎች ሕጎች በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር አግባብነት ያለው ማስረጃ ሁሉ ተቀባይነት አለው፡፡

**አንቀጽ 349 ተቀባይነት ስለሌላቸው ማስረጃዎች**

4. ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ተገዶ የሰጠው የእምነት ቃል ወይም በምርመራ ወቅት የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴን በተመለከተ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ

ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ወይም በዚህ ሕግ የተደነገገውን በመተላለፍ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡

5. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-
   (ሀ) ከተበዳይ ጋር በተደረገ የእርቅ ስምምነት፣ በጥፋተኝነት ድርድር ወይም በአማራጭ መፍትሔ ድርድር ወቅት የተገኘ ማስረጃ ወይም የተሰጠ የእምነት ቃል፣
   (ለ) ተከሳሽ ተጎጂን ለመርዳት ወይም አንድን ነገር ለማሻሻል የወሰደው የርምት እርምጃ የወንጀል ድርጊቱን የፈጸመ መሆኑን ያስረዳል በሚል የሚቀርብ ማስረጃ፣
   (ሐ) ተከሳሽ ክዶ በሚከራከርበተ ጉዳይ በአንድ ዓይነት ወንጀል በተከሰሰ ሌላ ተከሳሽ የተሰጠ የእምነት ቃል ክዶ በሚከራከረው ተከሳሽ ላይ፣
   (መ) አንድ ተከራካሪ ወገን ያቀረበውን ማስረጃ ትክክለኛነት እንዲያረጋግጥ ፍርድ ቤቱ ካዘዘ የዚህ ማስረጃ ትክክለኛነት እስከሚረጋገጥ ድረስ፣ ተቀባይነት የለውም፡፡

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሁኖ ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ አንድ ምስክር በሚመሰክርበት ጊዜ የምስክሩን ቃል ለማስተባበል መጠቀም ይቻላል፡፡

<u>**አንቀጽ 350 ጠባይን ስለማስረዳት**</u>

1. የአንድ ሰው መልካም የሆነን ወይም ያልሆነን ጠባይ በማስረዳት የወንጀል ተግባሩን ለማስረዳት የሚቀርብ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖሩም፡-
   (ሀ) ተከሳሹ የወንጀል ተግባሩን ለማስረዳት መልካም ጠባይ እንዳለው የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረበ እንደሆነ ተቃራኒ ማስረጃ ሊቀርብ ይቻላል።
   (ለ) የተበዳዩን ጠባይ መልካም አለመሆን ለማሳየት በተከሳሹ የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ማስተባበል ይቻላል።
3. የምስክሩን እውነተኛነት በማናቸውም ማስረጃ ማስረዳት ይቻላል።

<u>**አንቀጽ 351 የቀድሞ ጥፋቶችና መሰል ተግባራት**</u>

የተከሳሹ የቀድሞ ጥፋቶችና ሌሎች ተግባራት አሁን የተከሰሰበትን የወንጀል ተግባር ለማስረዳት ተቀባይነት የላቸውም። ሆኖም የተከሳሹን የቀድሞ እቅድ፣

ማንነት፣ አጋጣሚ፣ ዝግጅት፣ ሀሳብ፣ ወይም የነገሩ ሁነት ድነገተኛ አለመሆን ለማስረዳት ተቀባይነት አለው፡፡

**አንቀጽ 352 አግባብነት ወይም ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ ውጤት**

1. አግባብነት ወይም ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ ፍርድ ቤት እንዳልቀረበ ይቆጠራል፡፡
2. ጉዳዩ በመታየት ላይ እያለ ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም በማንኛውም ተከራካሪ ወገን አመልካችነት ማስረጃ ተቀባይነት እንደሌለው ከተረዳ ማስረጃው ውጤት እንደሌለው በመቁጠር ሌሎች ተቀባይነት ያላቸውን ማስረጃዎች ብቻ ይመዝናል፡፡

## ክፍል ስምንት
## የሰው ማስረጃ

**አንቀጽ 353 የምስክር የመመስከር ብቃትና ግዴታ**

1. ማንኛውም የሕግ ወይም በወንጀል ምክንያት በፍርድ ቤት ገደብ ያልተጣለበት ሰው ለመመስከር ብቃት እንዳለው ይገመታል።
2. ማንኛውም በምስክረነት የተጠራ ሰው ፍርድ ቤት ቀርቦ የመመስከር ወይም የማይመሰክርበትን ምክንያት የማስረዳት ግዴታ አለበት።
3. ምስክሩ ልዩ አዋቂ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የምስክሩን የትምህርት ደረጃና ሥራየሥራ ልምድ እንዲሁም ሌሎች የብቃት ማረጋገጫዎችን ከመረመረ በኋላ በጭብጥ በተያዘው ወይም አግባብ ባለው ፍሬ ነገር ላይ ለመመስከር ብቃት ያለው እንደሆነ ይወስናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤት በዕድሜ ለጋነት ወይም መጃጃት፣ በአካል ወይም በአእምሮ በሽታ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት የሚመሰክረውን ፍሬ ነገር ወይም የሚቀርብለትን ጥያቄ ሊረዳው የማይችል መሆኑን ሲረዳ የምስክርት ቃሉን እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 354 ለምስክርነት የተከላከለ ልዩ አዋቂ**

ፍርድ ቤት ምስክር እንዳይሆን ክልከላ ያደረገበት ልዩ አዋቂ በምሰክርነት ሊቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 355 ለመመስከር ያለመገደድ ልዩ መብት**

1. የተከሳሹ ኃይማኖት አባት፣ ጠበቃ ወይም ሐኪም በሚሰጠው የኃይማኖት ወይም የሙያ አገልግሎት አጋጣሚ ባገኘው መረጃ ላይ በተከሳሹ ላይ እንዲመሰክሩ አይገደዱም።
2. አንድ ሰው በትዳር ዘመኑ በመካከላቸው ባለው እምነት ምክንያት ከትዳር ጓደኛው ባገኘው መረጃ በወንጀል በተከሰሰ የትዳር ጓኛው ላይ እንዲመሰክር አይገደድም። ሆኖም ወንጀሉ የተፈጸመው በሌላው የትዳር ጓደኛ ላይ እንደሆነ ይህ ልዩ መብት ተፈጻሚ አይሆንም።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ምስክርነት የሚሰጥበት የወንጀል ጉዳይ የሙስና፣ ሽብርተኝነት፣ አደገኛ እጽ ዝውውር፣ የጦር መሣሪያ ዝውውር፣ ኮንትሮባንድ፣ ታክስ፣ ሕገወጥ ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና መሰል ከባድ ወንጀሎች ሆኖ ምስክሩ ብቸኛ ማስረጃ እንደሆነ የመመስከር ግዴታ ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ተከሳሹ እነዚህ ሰዎች ከሱ ጋር ባላቸው ልዩ ግንኙነት ምክንያት በሱ ላይ ላለመመስከር የተሰጠውን ልዩ መብት የተወ እንደሆነ ወይም በመከላከያ ምስክርነት የጠራቸው እንደሆን የመመስከር ግዴታ አለባቸው።
5. በዚህ ሕግ በልዩ ምርመራ የተሳተፈ ሰው በተሳተፈበት ጉዳይ ላይ በምስክርነት ሊቀርብ አይችልም፡፡
6. ዳኛ ወይም ዐቃቤ ሕግ ውሳኔ በሰጠበት ጉዳይ ላይ በምስክርነት ሊቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 356 የመንግሥትን ምስጢርን ስለመጠበቅ**

1. የመረጃው ምስጢርነት በሕግ በተደነገገ ጉዳይ ላይ አንድ የመንግሥት ተቀጣሪ ቀርቦ እንዲመሰክር ወይም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማናቸውንም ሰነድ እንዲሰጥ አይገደድም።
2. የመረጃው ምስጢርነት በሕግ ያልተደነገገ እንደሆነና ከአገር ደኅንነት ጋር የተያያዘ እንደሆነ፣ የሚመለከተው የመንግሥት ተቋም የበላይ ኃላፊ ውሳኔ እንዲሰጥበት ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል።
3. ሆኖም መረጃው የአገርን ደኅንነት የማይመለከት ነው ብሎ ሲያምን ፍርድ ቤቱ የመረጃው መገለጥ የአገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን አለመሆኑን በዝግ ችሎት ያያል። ዋናውም ጉዳይ በዝግ ችሎት ማየት አለበት፡፡

**አንቀጽ 357 የምስክሮች ብዛትና አቀራረብ ቅደም ተከተል ስለመወሰን**

1. አንድን ፍሬ ነገር በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ብዛት ምስክር ማስረዳት ይቻላል።
2. በዚህ ሕግ አንቀጽ (የቅድመ ክስ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽበጭብጥ የተያዘውን ወይም አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት ይጠቅመኛል ብሎ ባመነበት ቅደም ተከተል ምስክሮቹን ያቀርባል።
3. አንድ ፍሬ ነገር በጭብጥ ለተያዘው ጉዳይ ተቀባይነት የሚኖረው በመጀመሪያ ሌላ ፍሬ ነገር ሲረጋገጥ በሚሆንበት ጊዜ በቀዳሚው ፍሬ ነገር ላይ ምስክሮች ከመመስከራቸው በፊት በኋለኛው ፍሬ ነገር ላይ እንዲመሰክሩ ፍርድ ቤቱ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 358 ቃለ-መኃላ ስለመፈጸም ወይም ማረጋገጫ ስለመስጠት**

1. ማንኛውም ምስክር ሆኖ የቀረበ ሰው የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት እንደኃይማኖቱ ወይም ልማድ መሠረት ቃለ-መኃላ መፈጸምመፈጸም ወይም እውነቱን ለመናገር ማረጋገጫ መስጠት አለበት።
2. በዕድሜ ማነስ ወይም በሌላ ምክንያት የመኃላውን ወይም የማረጋገጫውን ውጤት ለመገንዘብ የማይችሉ በምስክርነት የተጠሩ ሰዎች በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ቃለ-መኃላ ለመፈጸም ወይም እውነቱን ለመመስከር ማረጋገጫ ለመስጠት አይገደዱም፡፡

**አንቀጽ 359 ለምስክር የሚቀርብ ጥያቄ አግባብነት**

1. በዚህ ክፍል በተደነገገው መሠረት ለምስክር የሚቀርበው ጥያቄ አግባብ አለመሆኑ ተከራካሪው በተቃውሞ ያነሳ ወይም በፍርድ ቤቱ አስተያየት ጥያቄው ተገቢ ያልሆነ መስሎ የታየ እንደሆነ ወድያውኑ ይወስናል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ዳኛው ተከራካሪን እና አስፈላጊ ሲሆን ተጐጂን አመቺ በሆነ መንገድ አነጋግሮ በተነሳው ጥያቄ ላይ ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 360 የምስክሩን የምስክርነት ቃል ስለመቀበል**

ምስክሩ የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ፍርድ ቤቱ፡-

1. የምስክሩን ማንነት ያረጋግጣል፤ ስለሆነም የምስክሩን ሙሉ ስም፣ የመኖሪያ አድራሻ፣ ዕድሜና ሥራ፣ አስፈላጊ ሲሆን ዜግነት ይጠይቀዋል፡፡

2. ምስክሩ ከተከሳሽ፣ ከተበዳይ ወይም ጉዳዩ ከሚመለከተው ሌላ ሰው ጋር ያለው ፀብ፣ ዝምድና፣ ጓደኝነት፣ የተለየ ቅርበት ወይም በምስክርነት ቃሉ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ነገሮችን ጠይቆ ይረዳል፡፡
3. ምስክሩ ለፍርድ ቤት የሚሰጠው የምሰክርነት ቃል ሐሰተኛ እንደሆነ በወንጀል እንደሚያስጠይቀውና የሚያስከትለውንም ቅጣት ይነግረዋል፡፡

**አንቀጽ 361 ለምስክር የሚቀርብ ዋና ጥያቄ**

1. ዐቃቤ ሕጉ ወይም የግል ከሳሹ ለጠራው ምስክር ዋና ጥያቄ ያቀርባል፡፡ ምስክሩንም በጭብጥ ስለተያዘው ወይም አግባብነት ስላለው ፍሬ ነገር የሚያውቀውን እንዲመሰክር ይጠየቃል፡፡
2. በዋና ጥያቄ ጊዜ ምስክሩ ስለሚመሰክርበት ፍሬ ነገር መሪ ጥያቄ አይጠየቅም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ምስክሩ፡-

   (ሀ) አስጠቂ ምስክር እንደሆነ፤

   (ለ) ስለሚመሰክረው ነገር የዘነጋ እንደሆነና የፍሬ ነገሩን ጫፍ ለማስያዝ፤ ወይም

   (ሐ) ምስክሩ ሕፃን ከመሆኑ የተነሳ ርዳታ የሚያስፈልገው እንደሆነ፤

   ዐቃቤ ሕጉ ፍርድ ቤቱን አስፈቅዶ መሪ ጥያቄ ሊጠይቀው ይችላል፡፡
4. መሪ ጥያቄ ማለት ጠያቂው እንዲመለስለት የሚፈልገውን መልስ የሚያመላክት ጥያቄ ማለት ነው፡፡
5. ፍርድ ቤቱ በክርክር ሒደት ለምስክሩ የቀረበው ጥያቄ በጭብጥ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም ብሎ ካመነ በተቃራኒው ወገን ተቃውሞ ባይቀርብም ምስክሩ መልስ ከመስጠቱ በፊት ጥያቄው አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እንዲስተካከል ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
6. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም '**አስጠቂ ምስክር**' ማለት ምስክሩ ከዐቃቤ ሕጉ ወይም ከግል ከሳሹ የቀረበለትን ጥያቄ ሲመልስ በበቂ ፍላጎት የማይመሰክር እንደሆነ ወይም የጸብና የጠላትነት መንፈስ ያሳዬ እንደሆነ በተለይም በቅንነት ማነስ ምስክሩ የሚሰጠው የምስክርነት ቃል አስቀድሞ በመርማሪ ወይም በሌላ ውሳኔ ሰጪ አካል ፊት ከሰጠው የምስክርነት ቃል ጋር የማይጣጣም ምስክርነት የሚሰጥ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 362 ምስክርን ማዘጋጀት</u>**

የምስክርነት ቃል የሚቀበል ዳኛ፣

1. ምስክርነት የሰጠ ካልሰጡት ጋር እንዳይገናኝ፣
2. የተከሳሽ ምስክር የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሲመሰክር፣ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የተከሳሽ ምስክር ሲመሰክሩ በችሎት አዳራሽ እንዳይገኙ፣
3. ምስክርነት እንደ ቪዲዮ ኮንፈረንስና በመሰሉት መገናኛ ዘዴዎች የሚሰጥ እንደሆነ እውነተኛ ምስክርነት እንዲሰጥ፣
4. እውነተኛ ምስክርነት ለመሰጠት የሚያስችል የችሎት ድባብ እንዲኖር ፣

አስፈላጊውን ዝግጅት መደረጉን በማረጋገጥ የጥንቃቄ ርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 363 ማስታወሻን ሰነድን ወይም መሣሪያን ስለመጠቀም</u>**

1. ምስክሩ የሚመሰክረው ስለሚያስታውሰው ፍሬ ነገር ነው፡፡ ምስክሩ የምስክርነት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ በማስታወሻነት የሚያገለግል ሰነድ ወይም መሣሪያ እንዲጠቀም አይፈቀድም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ምስክሩ፡-
   (ሀ) በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ያገኘን አንድን ሰነድ ወይም ኤግዚቢት እየተመለከተ ወይም
   (ለ) ሰነድ ሳይዝ ወይም በመሣሪያ ሳይታገዝ የተሟላ ምስክርነት ለመስጠት የማይችል ወይም የሚቸገር ወይም የሚመሰክርበት ጉዳይ ባሕርይ የሚያስገድድ መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተገነዘበ እንደሆነ ማንኛውም ማስታወሻ ሰነድ ወይም መሣሪያ በመጠቀም

   እንዲመሰክር ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ለ) ምስክሩ ማስታወሻ ሰነድ ወይም መሣሪያ እንዲጠቀም የፈቀደ እንደሆነ አስፈላጊ የሆነውን የሰነዱን ክፍል ወይም መሣሪያ ግልባጭ ለተቃራኒ ወገን መስጠት ወይም ማሳየት ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ 364 ምስክሩ የሚመሰክርበት አኳኋን</u>**

ምስክሩ የሚመሰክረው በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆን መንገድ ወይም በስሚ ስሚ ስለሚያውቀው ፍሬ ነገር ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 365 ስለመስቀልኛ ጥያቄ

1. የዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ ዋና ጥያቄ እንዳበቃ ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ምስክሩን መስቀልኛ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል፡፡ የመስቀልኛ ጥያቄ ዓላማም በዋና ጥያቄ በተሰጠው ምስክርነት ውስጥ ያለውን ስህተት የሆነውን፣ የሚቃረነውን፣ የሚያጠራጥር ወይም እውነት ያልሆነውን ምስክርነት ለፍርድ ቤቱ ለመግለጽና ለማስተባበል ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳካት እስከቻለ ድረስ ምስክሩ በዋና ጥያቄ ባልተነሳ ፍሬ ነገርም ላይ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ምስክሩ ልዩ አዋቂ እንደሆነ በጭብጥ ለተያዘው ወይም አግባብነት ስላለው ፍሬ ነገር ለመመስከር ያለውን ብቃትም በተመለከተ ጥያቄ ሊቀርብለት ይችላል፡፡
3. በመስቀልኛ ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ ለመጠየቅ ይቻላል፡፡
4. መስቀልያ ጥያቄ አለመጠየቅ በዋና ጥያቄ ተቃዋሚው ወገን የተመሰከረባቸውን ፍሬ ነገሮች እውነተኛነት እንዳመነ አይቆጠርም፡፡

## አንቀጽ 366 የማስተባበያ ጥያቄ የተከለከለ መሆን

1. በምስክሩ ተዓማኒነት ወይም ባሕርይ አስመልክቶ በራሱ በምስክር የተሰጠን መልስ ለማስተባበል ሌላ ጥያቄ ማቅረብ አይፈቀድም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ በምስክሩ የተሰጠው መልስ ግልጽ የሆነን ፍሬ ነገርን በመካድ የተፈጸመ ሐሰተኛ መሆኑን ከተረዳ የተሰጠው መልስ ስህተት መሆኑን ለማስረዳት ተጨማሪ ጥያቄ እንዲቀርብ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 367 ስለድጋሚ ጥያቄ

1. የተከሳሹ ወይም የጠበቃው መስቀልኛ ጥያቄ እንዳበቃ ዐቃቤ ሕጉ ወይም የግል ከሳሹ ምስክሩን ድጋሚ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል፡፡ ተከሳሹ መስቀልኛ ጥያቄ ካልጠየቀ ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ የድጋሚ ጥያቄ መጠየቅ አይችልም፡፡
2. የድጋሚ ጥያቄ ዓላማም በመስቀልኛ ጥያቄ ስህተት የመሰለውን፣ የሚቃረን፣ የሚያጠራጥር ወይም እውነት ያልሆነ የሚመስለውን ምስክርነት በርግጥም ስህተት፣ የሚቃረን፣ የሚያጠራጥር አለመሆኑን ወይም እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡

3. ስለሆነም በድጋሚ ጥያቄ ጊዜ ጥያቄ ሊቀርብባቸው የሚችለው ፍሬ ነገሮች በመስቀልኛ ጥያቄ የተነሱ ፍሬ ነገሮች ብቻ ናቸው፡፡ በድጋሚ ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ ለመጠየቅ ይቻላል፡፡

**አንቀጽ 368 በፍርድ ቤቱ ስለሚቀርብ ጥያቄ**

ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ይረዳል ብሎ ያመነውን ጥያቄ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 369 በፍርድ ቤቱ ስለሚጠራ ምስክር**

1. ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ይረዳል በሎ ሲያምን ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በተከራካሪ ወገኖች ያልተቆጠረ ምስክር ቀርቦ እንዲሰማለማዘዝ ይችላል፡፡
2. የተጠራው ምስክር የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ አግባብ የመሰለውን ጥያቄ በጭብጥ በተያዘው ወይም አግባብነት ባለው ፍሬ ነገር ላይ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3. የፍርድ ቤቱ ጥያቄ እንዳበቃ ለተከራካሪ ወገኖች መስቀልኛ ጥያቄ እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣል፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜም ሌላኛውም ወገን ድጋሚ ጥያቄ ለማቅረብ ይችላል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ ግልጽ ያልሆነነ ነገር ለማጥራት ወይም ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑን ሲረዳ አስቀድሞ የምስክርነት ቃሉን የሰጠ ሰው እንደገና እንዲመሰክር ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## የሰነድ ማስረጃ

**አንቀጽ 370 ፍሬ ነገሮችን በሰነድ ስለማስረዳት**

1. የማንኛውም ሰነድ ይዘት የሚረጋገጠው በዋናው ሰነድ ነው፡፡ ዋናውን ሰነድ ማቅረብ ባልተቻለ ጊዜ ሰነዱን ለማረጋገጥ ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ቅጂማቅረብ ይቻላል፡፡
2. በዚህ ሕግ መሠረት ሰነድ ማለት የጽሑፍ፣ የድምጽ፣ የምስል፣ የተንቀሳቃሽ ምስል፣ የኤሌክትሮኒክ የመረጃ ስብስብ፣ መሰልመረጃ የያዘ ሆኖ በሰው ወይም በመሣሪያ መነበብ የሚችል ማለት ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ዋናው ሰነድ ወይም የተረጋገጠው ቅጂ  የጠፋ፣ የተቀደደ፣ የተቃጠለ፣ ወይም ከተከራካሪው ወገን

አቅም በላይ በሆነ በሌላ በማናቸውም ምክንያት ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ የሰነዱን ይዘት፡-

(ሀ) ከዋናው ሰነድ ጋር በተመሳከረ ቀጂ፤ ወይም

(ለ) በምስክር ማስረዳት ይቻላል፡፡ ከሰነዱ ይዘት ብዛት ወይም በሌላ ቴክኒካዊ ምክንያት የሰነዱን ይዘት መመርመር ለፍርድ ቤቱ አስቸጋሪ እንደሆነ ወይም በሰነዱ ከባድነት ምክንያት ፍርድ ቤት ሊቀርብ የማይችል እንደሆነ የሰነዱን ይዘት በምስክር ወይም በፎቶግራፍ ማስረዳት ይቻላል፡፡

4. አንድን ሰነድ ዋጋ ለማሳጣት ወይም በሕግ ፊት የጸና አለመሆኑን ለማሳየት ማንኛውንም ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል፡፡

## አንቀጽ 371 የአንድን ፍሬ ነገር አለመከሰት ስለማስረዳት

1. አንድን በሕዝብ መዛግብት ወይም በንግድ መዛግብት መመዝገብ የነበረበትን ፍሬ ነገር በዚሁ መዝገብ ውስጥ አለመኖር የፍሬ ነገሩን አለመከሰት ማስረዳት ይቻላል፡፡
2. ሆኖም ፍርድ ቤቱ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አንድን ፍሬ ነገር ተረጋግጧል ወይም ተስተባብሏል ከማለቱ በፊት የተጠቀሰው ምዝገባ በትክክል እንደሚከናወን ወይም መዝገቡ የተሟላ መሆኑ እንዲረጋገጠለት ለመጠየቅ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 372 የሰነዱን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

ሌላኛው ወገን ስለሰነዱ ትክክለኛነት አግባብነት ያለው መቃወሚያ ያነሳ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ ያቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በማስረጃነት ከማቅረቡ በፊት የሰነዱን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለበት፡፡

## አንቀጽ 373 የሕዝብ መዛግብትን ይዘት ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

1. የሕዝብ መዛግብት ማለት ዋና ዋና ሁነቶችንና መሰል ፍሬ ነገር ለመመዝገብ ሥልጣን ባለው የመንግሥት ተቋም የተመዘገበ ሆኖ የዚህ መዝገብ ይዘት ትክክለኛ ነው የሚባለው፡-

   (ሀ) ሁነቱ የተመዘገበው የፍሬ ነገሩ በተከሰተ ጊዜ ወይም ወዲያውኑ እንደተከሰተ እንደሆነ፣ እና

   (ለ) ሁነቱ በመዝገብ የሰፈረው ይህንኑ ፍሬ ነገር ለመመዝገብ ሥልጣን በተሰጠው ሰው ሆኖ፣

(ሐ) መዝገቡ ሲመለከቱት የተሰረዘ፣ የተደለዘ ወይም ሌላ የሚያጠራጥር ነገር የሌለበት መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

2. ሌሎች የመንግሥት ሰነዶችን ማስረጃነት በተመለከተ ትክክለኛነታቸው አጠራጣሪ እንደሆነ፣ በተከራካሪ ወገኖች ተቃውሞ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ ሥልጣን ውድቅ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

## አንቀጽ 374 የንግድ መዛግብትን ይዘት ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

የንግድ መዛግብት ማለት የንግድ ድርጅቱ ስለሚያከናውነው የንግድ ተግባር ሕግ በሚያዘው ዓይነት ወይም በድርጅቱ ልማድ መሠረት አዘውትሮ የሚመዘግበው ፍሬ ነገር ሆኖ የዚህ መዝገብ ይዘት ትክክለኛ መሆኑ የሚረጋገጠው፡-

(1) የፍሬ ነገሩ በተከሰተ ጊዜ ወይም ወዲያውኑ ከዚያ በኋላ የተመዘገበ እንደሆነ፣ እና

(2) ፍሬ ነገሩ በመዝገብ የሰፈረው ይህንኑ ፍሬ ነገር አዘውትሮ መመዘግብ መደበኛ ሥራው በሆነ ሰራተኛ ሆኖ፣

(3) ሰነዱ ሲመለከቱት የተሰረገ፣ የተደለዘ ወይም ሌላ የሚያጠራጥር ነገር የሌለበት መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

## አንቀጽ 375 የኤሌክትሮኒክ መረጃ ስብስብን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

1. አንድን የኰምፒዩተር መረጃ ስብስብ ይዘት ትክክለኛነት ማረጋገጥ የሚቻለው፡-

(ሀ) ኰምፒዩተሩ አግባብ ባለው ጊዜ ሁሉ ኰምፒዩተሩን ለመያዝና መረጃዎቹን ለመመዝገብ ሃላፊነት ባለበት ሰው ቁጥጥር እንደነበረ፣

(ለ) መረጃው በተመዘገበበት ጊዜ ኰምፒዩተሩ በትክክል ይሰራ እንደነበረ፣ እና

(ሐ) መረጃው የተመዝገውና አሁንም መረጃው የተገኘው በአግባቡና በተለመደው አሰራር፣

መሆኑን በማሳየት ነው፡፡

2. ይህንንም በፍሬ ነገር ምስክር ወይም በልዩ አዋቂ ማስረዳት ይቻላል፡፡

## አንቀጽ 376 የፊርማን ወይም ጽሑፍን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

1. የአንድ ሰው የእጅ ጽሑፍ ወይም ፊርማ ትክክለኛነት እንደነገሩ ሁኔታ ከዚሁ ሰው ናሙና የእጅ ጽሑፍ ወይም ፊርማ ጋር በማነጻጸር፣ በፍርድ ቤቱ፣ በምስክር ወይም በልዩ አዋቂ ምርመራ ማረጋገጥ ይችላል፡፡

2. ይህንንም ለማድረግ የተባለው ሰው ቀድሞ የጻፈው ወይም የፈረመው ሰነድ ካለ እንዲያቀርብ ወይም የተወሰኑ ቃላትን ወይም አኃዞችን እንዲጽፍ ፍርድ ቤቱ ሊያዘው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 377 በማኅተም ወይም ፊርማ ላይ የሚወሰድ የሕሊና ግምት**

1. ፍርድ ቤቱ በቀረበለት ሰነድ ላይ ያለ ፊርማ ወይም ማኅተም ትክክል ስለመሆኑና ማህተሙን ያተመው ወይም ፊርማውን የፈረመው ሰው ማህተሙን ባተመበት ወይም ፊርማውን በፈረመበት ጊዜ ሥልጣኑ በሚፈቅድለት ልክ እንዳከናወነው የሕሊና ግምት ሊወሰድ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ተቃራኒ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡

**አንቀጽ 378 የህሊና ግምት የሚወሰድበት ሰነድ**

1. ፍርድ ቤት፡-
   (ሀ) በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል የተሠራና ለሕዝብ ይፋ የሆነ የቦታ ካርታ ወይም ፕላን ትክክለኛ መሆኑ፤
   (ለ) በማንኛውም የውጭ መንግሥት የታተመ የፍርድ ውሳኔ ትክክለኛ መሆኑ፤
   (ሐ) የሕዝብ ጉዳዮችን የሚመለከት ማንኛውም መጽሐፍ፣ ታትሞ የወጣ የቦታ ካርታ ወይም ቻርት ጽፎ ወይም አትሞ አወጣ የተባለው ሰው ተጻፈ ወይም ታተመ በተባለበት ጊዜና ቦታ የጻፈውና አትሞ ያወጣው ሰው መሆኑን የሕሊና ግምት ይወስዳል፡፡
2. ሥልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ ሰነድ በውስጡ ስለሚገኘው ይዘት ሙሉ ዕምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው፡፡

**አንቀጽ 379 በሰነድ ላይ የተካተተ ቃልን በሌላ ማስረጃ ማስረዳት አለመቻሉ**

ሰነዱ ግልጽነት የጎደለው ወይም በይዘቱ ርስ በርሱ የሚጋጭ ካልሆነ በስተቀር ስለይዘቱ በምስክር ማስረዳት አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 380 በተከራካሪ ወገን እጅ ሰለሚገኝ ሰነድ**

1. በየትኛውም ወገን የተቆጠረ ሰነድ ይሁን ከተከራካሪ ወገኖች መካከል ሰነዱ በይዞታው ያለ ተከራካሪ ወገን ሰነዱን የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

2. አንድ ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤት እንዲያቀርብ የታዘዘውን ሰነድ ከእርሱ አቅም በላይ ባልሆን ምክንያት ሳያቀርብ የቀረ እንደሆን ይኸው ሲረጋገጥ ፍርድ ቤቱ በፍሬ ነገሩ ላይ የራሱን ግምት መውሰድ ይችላል፡፡ ሆኖም ወንጀሉን ከሚያቋቁሙት ፍሬ ነገሮች ላይ ፍርድ ቤቱ በማስረጃ ከሚረጋገጥለት ውጭ ማናቸውንም ግምት መውሰድ አይችልም፡፡

3. እንዲሁም የተጠየቀውን ሰነድ ያላቀረበ ተከራካሪ ወገን ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደ በቀር ሠነዱን በማስረጃነት ማቅረብ ወይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ መስቀለኛ ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 381 በሦስተኛ ወገን ይዞታ ስለሚገኝ ሰነድ

ፍርድ ቤት በተከራካሪ ወገኖች ጠያቂነት ወይም በራሱ ተነሳሽነት ለተያዘው ጭብጥ አግባብነት ያለው ማስረጃ በሦስተኛ ወገን ይዞታ ሥር ያለ ሰነድ እንዲቀርብ ለባለይዞታው ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

# ክፍል አሥር
# ስለ ኤሌክትሮኒክ ማስረጃ

## አንቀጽ 382 ትርጉም

1. አንድን ፍሬ ነገር በኤሌክትሮኒክ ማስረጃ ማስረዳት ይቻላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ ሥርዐት ላይ ሥልጣን ባለው አካል የሚወጡ ሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡
3. በሌሎች ሕጎች የተደነነገው እንደተጠበቀ ሆኖ “**የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ**” ማለት ዳታን፣ የኤሌክሮኒክ መዝገብንና ሥርዐትን ጨምሮ በማንኛውም መሣሪያ የተመዘገበ፣ የተከማቸ በሰው ወይም በኮምፒውተር ወይም በሌላ መሣሪያ ሊነበብ ወይም ሊታወቅ የሚችል ማስረጃን ያካትታል፡፡

## አንቀጽ 383 የማስዳት ደረጃ

1. ደህንነቱ የተጠበቀ የኤሌክትሮኒክ ማስረጃን የሚመለከት ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበበት ድረስ ትክክለኛ ማስረጃ እንደሆነ ይገመታል።
2. አንድን የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ ዋጋ ለማሳጣት ወይም በሕግ ፊት የጻና አለመሆኑን ለማሳየት ማንኛውንም ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል፡፡
3. የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ሥርዐትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ባልተቻለ ጊዜ፡-

(ሀ) የኤሌክትሮኒክ መዝገቡ ወይም መሣሪያው በተግባር ሲሠራ መቆየቱን፣ ብልሽት ያጋጠመው ቢሆንም የመዝገቡን አስተማማኝነት የማያጓድለው መሆኑን፤

(ለ) የኤሌክትሮኒክ መዝገቡ እንዲመዘገብ የተደረገው ማስረጃውን ለማቅረብ በሚፈልግ ተከራካሪ ወገን መሆኑን፤

(ሐ) የኤሌክትሮኒክ መዝገቡ እንዲመዘገብ ወይም እንዲከማች ያደረገው ሰው ማስረጃውን ለማቅረብ በሚፈልገው ሰው ቁጥጥር ሥር ያለመሆኑና ምዝገባው ወይም ክምችቱ የተለመደውን ሥራ ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን፣

የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ
## ኤግዚቢት

**አንቀጽ 384 ስለኤግዚቢት**

1. አንድ ግዙፋዊነት ያለው ወይም የሌለው ነገር ለፍርድ ቤት እይታ በእግዚቢትነት ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. ኤግዚቢት ማለት ከወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል የሚያስችል በወንጀል የተያዘ ህገ-ወጥ ነገር፣ ወንጀል ለመሥራት በመሣሪያነት ያገለገለ ነገር፣ የወንጀል ፍሬ፣ወንጀል የተፈጸመበት የሰውነት አካል ወይም ንብረት፣ ወይም የወንጀል ምልክት ሆኖአሻራን፣ የጫማ ኮቴን እና ሌሎች መሰልነገሮችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ ነው፡፡
3. ዐቃቤ ሕግ የሚያቀርበውን ኤግዚቢት ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለበት፡፡

**አንቀጽ 385 የኤግዚቢትን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ**

ዐቃቤ ሕጉ ያቀረበውን ኤግዚቢት ትክክለኛነት፡-

(1) ኤግዚቢቱን የሚለዩና በኤግዚቢቱ ላይ የሚገኙ እንደ ልዩ ምልክትና መለያ ቁጥር የመሳሰሉ ነገሮች በማሳየት፣

(2) የኤግዚቢቱን አሰባሰብ፣ አጠባበቅና አቀራረብ በማስረዳት፣ ወይም

(3) አግባብ ባለው ምስክር ፣

ማስረዳት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 386 የዐቃቤ ሕግ የማስረዳት ኃላፊነትና የማስረዳት ደረጃ**

1. ዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽ ባቀረበው ክስ መሠረት ወንጀሉን የሚያቋቁሙትን ሞራላዊና ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮችን፣ ሌሎች በጭብጥ የተያዙ ወይም አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች በበቂ ሁኔታ ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ ተከሳሹ የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸሙን ያሳያል ብሎ ባቀረበው ማስረጃ ላይ የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች መኖራቸውን በበቂ ሁኔታ ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. የቅጣት ማክበጃ ፍሬ ነገሮችን በፍትሐ ብሔር የማስረዳት መጠን ማረጋገጥ አለበት፡፡

**አንቀጽ 387 የፍርድ ቤት ውሳኔ**

1. የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተሰምቶ ካበቃ በኋላ ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ፍሬ ነገሮች በሙሉ ሳይረጋገጡ በመቅረታቸው ማፍረሻ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በነጻ እንዲለቀቅ ያዛዝል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽማስረጃ ተቃራኒ ማስረጃ ባይቀርብበት ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማለት የሚያስችል እንደሆነ ተከሳሹ መካላከያ ማስረጃውን እንዲያሰማ ያዛል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተከሳሹ በነፃ ሲያሰናብት በኤግዚቢት በተያዘ ዕቃ እንዲሁም በዋስትናው ላይ ተገቢውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## ክፍል አሥራ ሁለት
## የተከሳሹን የመከላከያ ማስረጃ ስለመስማት

**አንቀጽ 388 ስለተከሳሹ የክርክር መክፈቻ ንግግር**

1. ተከሳሹ ወይም ጠበቃው የክርክር መክፈቻ ንግግር ያደርጋል፡፡ ስልሆነም መከላከያውን ሲከፍት በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ላይ ተረጋግጧል ወይም አልተረጋገጠም ብሎ የሚያምንበትን ነገር ካመላከተ በኋላ በዚያ ረገድ ሊያስረዳ ያቀረበውን መከላከያና የሚያቀርበውን የማስረጃ ዓይነት ባጭሩ ይገልፃል፡፡

2. ተከሳሹ በራሱ ጉዳይ በምስክርነት ለመቀረብ ወይም የተከሳሽነት ቃሉን ብቻ ለመስጠት የመወሰን መብት አለው፡፡ ይህንኑም የተከሳሹን ውሳኔ ተከሳሹ ወይም ጠበቃው በክርክር መክፈቻ ንግግሩ ለፍርድ ቤቱ ያስመዘግባል፡፡
3. ሆኖም በራሴ ጉዳይ የምስክርነት ቃሌን እሰጣለሁ ብሎ ያስመዘገበ ተከሳሽ ያለመመስከር መብት አለው፡፡ እንደዚህ ቃሉን የለወጠ ተከሳሽ በተለዋጭ የተከሳሽነት ቃሉን ለመስጠት አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 389 የተከሳሹን የመከላከያ ማስረጃ ስለመስማት</u>**

1. ከዚህ በላይ ስለዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በአጠቃላይ የተነገረው አግባብ ያለው ማሻሻያ ተደርጎበት ለተከሳሽ መከላከያ ማስረጃም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. ሆኖም ተከሳሹ የምስክርነት ቃሉን ወይም የተከሳሽነት ቃሉን ሌሎች ምስክሮች ከመቅረባቸው በፊት ይሰጣል፡፡
3. ተከሳሹ በራሱ ጉዳይ ላይ ምስክር ሆኖ ለመቅረብ የመረጠ እንደሆን ቃለ-መኃላ ፈጽሞ ወይም እውነቱን ለመመስከር ማረጋገጫ ሰጥቶ ይመሰክራል፡፡ ዐቃቤ ሕጉም መስቀልኛ ጥያቄ ሊጠይቀው ይችላል፡፡ የሚሰጠውም ምስክርነት እንደማንኛውም የምስክር ቃል ይመዘናል፡፡
4. ተከሳሹ ለቀረበበት ጥያቄ መልስ ያልሰጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ለቀረበው ጥያቄ የራሱን ግምት ሊወስድ ይችላል፡፡

1. ተከሳሹ የተከሳሽነት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ ቃለ-መኃላ እንዲፈጽም ወይም እውነቱን ለመመስከር ማረጋገጫ እነዲሰጥ አይደረግም፤ በዐቃቤ ሕግም መስቀልኛ ጥያቄ አይጠይቅም፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ አንዳንድ ግልጽ ባልሆኑ ነገሮች ላይ የማብራሪያ ጥያቄ ብቻ ሊጠይቀው ይችላል፡፡
2. ተሰካሹ የሚሰጠውን የተከሳሽነት ቃል ፍርድ ቤቱ በማስረጃነት አግባብ ነው ያለውን ዋጋ ይሰጠዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 390 የተከሳሹ የማስረዳት ኃላፊነት</u>**

1. ተከሳሹ ከተከሰሰበት ወንጀል ነፃ ለመባል ዐቃቤ ሕጉ ባስረዳው ወንጀሉን በሚያቋቁሙት ፍሬ ነገሮች ወይም ማስረጃ ላይ በቂ ጥርጣሬ መፍጠር አለበት፡፡
2. ተከሳሹ ወንጀሉን መፈጸሙን አምኖ ስለአፈጻጸሙ መብቱን ጠብቆ የተከራከረ እንደሆነ ወይም በወንጀል የማያስጠይቅ በሕግ የተደነገገ መከላከያ መኖሩን

የጠቀሰ እንደሆነ ለዚሁ መሠረት የሆኑትን ፍሬ ነገሮች በፍትሐብሔር የማስረዳት መጠን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል አሥራ ሦስት
## የወል ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 391 ተጨማሪ ማስረጃ

1. ክስ በሚሰማት ጊዜ በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ ያልታወቀ ወይም በወቅቱ ያልተገኘ ተጨማሪ ወይም ድንገተኛ ማስረጃ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. ሆኖም የተጨማሪ ወይም ድንገተኛ ማስረጃ ይቅረብልኝ ጥያቄ የቀረበው በማስረጃው አግባብነት ላይ የተመረኮዘ ሳይሆን የነገሩን መሰማት ለማዘግየት የሆነ እንደሆን ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን አይቀበለውም፡፡
3. ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ ይረዳል ብሎ ሲያምን በተከራካሪ ወገኖች ያልተጠቀሰ ማስረጃ እንዲቀርብለት ለማዘዝ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 392 በሌላ ፍርድ ቤት የተሰጠ የምስክርነት ቃል ስለሚቀርብበት ሁኔታ

1. ምስክሩ የሞተ እንደሆነ፣ ወይም የአእምሮ ጉድለት ያገኘው እንደሆነ፣ ምስክሩን ማግኘት ያልተቻል እንደሆነ፣ በህመም ምክንያት ወይም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ባለመኖሩ በፍርድ ቤት ለመቅረብ ያልቻለ እንደሆነ በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት የሰጠው ቃል ተነቦ በማስረጃነት ጉዳዩን በሚሰማው ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡
2. ምስክርነት የተሰጠው ተከሳሹ ተከራካሪ ወገን በነበረበት በሌላ ፍርድ ቤት ሆኖ ተከሳሹ መስቀልኛ ጥያቄ የማቅረብ እድል የነበረው እንደሆነ የምስክርነቱ ቃል ተነቦ ጉዳዩን በሚሰማው ፍርድ ቤት በማስረጃነት መቅረብ አለበት፡፡

### አንቀጽ 393 ለፖሊስ የተሰጠ ቃል በማስረጃነት ስለመቅረቡ

1. ምስክር በፍርድ ቤት ቀርቦ የሚሰጠው የምስክርነት ቃል በፖሊስ ምርመራ ጊዜ ከተሰጠ የምስክርነት ቃል ጋር የሚጣረስ እንደሆነ፣ የምስክሩን ቃል ለማስተባበል ዐቃቤ ሕጉ ወይም ተሰካሹ ሲያመለክት ፍርድ ቤቱ የፖሊስን የምርመራ መዝገብ ሊመለከተው ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱም የዚህ ቃል ግልባጭ ለተከሳሹ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 394 በማስረጃ ላይ ስለሚቀርብ መቃወሚያ**

1. አንደኛው ተከራካሪ ወገን በሚያቀርበው ማስረጃ ላይ ሌላኛው ወገን ማስረጃው አግባብነት ወይም ተቀባይነት የለውም ሲል መቃወም ይችላል፡፡ ይህ መቃወሚያ በቃል ወይም በጽሑፍ ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. እንዲሁም በመሰማት ላይ ላለ ምስክር የሚቀርብ ጥያቄ አግባብነት ላይ ሌላኛው ወገን ተቃውሞ ሊያነሳ ይችላል፡፡ ምስክሩ የቀረበለትን ጥያቄ ከመመለሱ በፊት ፍርድ ቤቱ ብይን ይሰጣል፡፡ ሆኖም ምስክሩ ጥያቄውን መልሶ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ ተቃውሞውን ከተቀበለው ጥያቄውና መልሱ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ያዛል፡፡

**አንቀጽ 395 ስለክርክር ማቆሚያ ንግግር**

1. የዐቃቤ ሕግና የተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ ተሰምቶ እንዳበቃ ተከራካሪ የክርክር ማቆሚያ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
2. ዐቃቤ ሕጉ ወይም የግል ከሳሽ በክርክር ማቆሚያ ንግግሩ ክሱን፣ ሕጉን፣ ፍሬ ነገሩንና ያቀረበውን ማስረጃ በመጥቀስ ጥፋተኛ ሊያስብሉ የሚችሉ ምክንያቶችን ይናገራል፡፡
3. ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ክሱንና የዐቃቤ ሕጉን ክስና ማስረጃ እንዲሁም በመከላከያነት ያቀረበውን ማስረጃ በመጥቀስ ጥፋተኛ የማይባልበትን ምክንያት ያስረዳል፡፡ ተከሳሹም ሁልጊዜ የመጨረሻ ንግግር ያደርጋል፡፡
4. ተከሳሾቹ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በተለየ ካላዘዘ በቀር በክሱ ላይ ስማቸው በተጠቀሰበት ቅደም ተከተል ይናገራሉ፡፡
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ የክርክር ማቆሚያ ንግግር በግልጽ ሆኖ በቃል ወይም በጽሑፍ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 396 ክንዋኔዎችን መመዝገብ**

1. ፍርድ ቤቱ በፍርድ ሂደቱ፡-
   (ሀ) የዳኛው ስም፣ የችሎቱን ስያሜ፣ ቀንና መዝገብ ቁጥሩን፣
   (ለ) የከሳሽና የተከሳሽ ስምና አድራሻ፣
   (ሐ) እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችና ሁኔታዎች፣

   በመዝገብ ወይም በኤሌክትሮኒክ መዛሪያ ውስጥ ማስፈር አለበት፡፡
2. ዳኛው የእያንዳንዱ የምስክር ቃል አመቺ በሆነ መንገድ መመዝገቡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. ማስረጃው ሲመዘገብ ዋና፣ መስቀለኛ እና ድጋሚ ጥያቄ ተብሎ መለየት አለበት፡፡ ዋና ጥያቄ፣ መስቀልኛ ጥያቄ ወይም ድጋሚ ጥያቄ የሚጀምርበትና የሚያበቃበት በግልጽ መለየት አለበት፡፡
4. ሌሎች ማስረጃዎቹም ምልክት እየተደረገባቸው ይመዘገባሉ፡፡
5. ዳኛው አንድን ጥያቄ ወይም መልስ በተለየ ለመፃፍ፣ ለመቅረጽ ወይም ለመቅዳት ካልፈቀደ በስተቀር የሚሰጠው የምስክርነት ቃል ምንጊዜም ቢሆን በተነገረበት አግባብ በሐተታ ዓይነት መመዝገብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 397 ስለቅጣት አስተያየት

1. ተከሳሹ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ ተከራካሪ ወገኖች በወንጀል ሕግና ሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎችና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት ማኑዋል መሠረት የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
2. የግል ተበዳይ ካለ ስለደረሰበት ጉዳት ማጠቃለያ ሀሳብ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. በዚህ ሕግ አንቀጽ (<u>በችሎት የተገኙ ሰዎች የሚሰጡት አስተያየት</u>) የተመለከቱ ሰዎች አስተያየት መስጠት ይችላሉ፡፡
4. ዐቃቤ ሕግ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶቹን በማስረጃ አስደግፎ ሊጣል ስለሚገባው ቅጣት አስተያየት ያቀርባል፡፡
5. ተከሳሹም የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶቹን በማስረጃ አስደግፎና ቅጣቱ ሊቀልለት የሚገባበትን አግባብ ያቀርባል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተከራካሪ ወገኖች ባቀረቧቸው የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች እንዲሁም በቅጣቱ ላይ ክርክር ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 398 በችሎት የተገኙ ሰዎች የሚሰጡት አስተያየት

1. ፍርድ ቤቱ የክርክር ማጠቃለያ ሐሳብ ከሰማ በኋላ በችሎት የተገኙ ሰዎች አስተያየት ወይም አጭር ንግግር እንዲያደርጉ ይፈቅዳል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አስተያየታቸውን የሚሰጡ ሰዎች፡-
   (ሀ) ስለ ጉዳዩ የተሟላ ግንዛቤ ያላቸው፣
   (ለ) እውነተኛና ያልወገነ አስተያየት የሚሰጡ መሆኑን፣
   (ሐ) ተዋፅኦና ብዛታቸው አሳታፊ መሆኑን፣

   ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. የዚህ አንቀጽ አፈጻጸም በዝርዝር መመሪያ ይወሰናል፡፡
4. ክልሎች በችሎት የተገኙ ሰዎች ስለሚኖራቸው ተሳትፎን በተመለከተ በሕግ ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 399 ቅጣት መወሰን**

ፍርድ ቤቱ፡-

1. የቅጣት አስተያየቱን መሠረት በማድረግ ማስረጃ ለመስማት ወይም ለመመርመር የግድ ተጨማሪ ተጨማሪ ጊዜ ካላስፈለገው በስተቀር የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት ዕለት የቅጣት ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2. ማስረጃ ለመስማት ወይም ለመመርመር የግድ ጊዜ የሚያስፈልገው እንደሆነ አጭር ቀጠሮ ይሰጣል፡፡ ማስረጃ ሰምቶ ቅጣት ለመወሰን  የሚሰጥ ቀጠሮ እጅግ ቢበዛ ከአሥራ አምስት ቀን መብለጥ የለበትም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ቅጣቱን ለመወሰን ቀጠሮ የሰጠ እንደሆነ ተከሳሽ የሚቆይበትን ሁኔታ የዐቃቤ ሕግን አስተያየት ከሰማ በኋላ አግባብነት ያለውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 400 ፍርድ**

1. የዐቃቤ ሕግንና የተከሳሹ የክርክር ማቆሚያ ንግግር ከሰማ በኋላ ፍርድ ቤቱ ፍርድ ይሰጣል፡፡ ፍርዱም በጽሑፍ ሆኖ ፍርዱን በፈረደው ዳኛ ወይም ዳኞች ተፈርሞበት ፍርድ ቤቱ በሌላ ሁኔታ ካልወሰነ በቀር በግልጽ ችሎት በይፋ ይነበባል፡፡
2. ፍርዱም የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች መያዝ አለበት፡፡
   (ሀ) የከሳሹንና የተከሳሹ ስም፣ የተከሰሰበትን ሕግና የሕጉ አንቀጽ፣ የተከሳሹን እምነት ክህደት፣
   (ለ) ክሱን ለማስረዳት ዐቃቤ ሕጉ ያቀረበውን ማስረጃ፣ ከነዚህም መካከል ፍርድ ቤቱ ያልተቀበለውን ማስረጃ ለይቶ ያልተቀበለበትን ምክንያት፣
   (ሐ) ፍርድ ቤቱ የተቀበላቸው ማስረጃዎች ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል የሚያቋቁሙትን ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ሌሎች በጭብጥ የተያዙትን ወይም አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች በበቂ ሁኔታ መረጋገጣቸውን ወይም አለማስረዳታቸውን፣
   (መ) ተከሳሹ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ ጥፋተኛ የተባለበትን ሕግና የሕጉን አንቀጽ፣

(ሠ) ተከሳሽ ጥፋተኛ አይደለም በተባለ ጊዜ ተከሳሽ ነፃ እንዲሆንና በእስር ላይ ካለም ከማረሚያ ቤት እንዲለቀቅ የሚል ትእዛዝ፤

(ረ) ተከሳሽ ነፃ ወይም ጥፋተኛ በተባለ ጊዜ ፍርዱን የሚያስፈፅመውን አካል ለይቶ ውሳኔው እንዲፈጽም ትእዛዝ ያስተላልፋል፡፡

3. ፍርድ ቤቱ በፍርድ ውሳኔው ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ሌሎች ጉዳዮች በዋስትና የተያዘ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም በማስረጃነት የተያዙ እግዚቢቶችን በተመለከተ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

4. ፍርድ ቤት ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ዐቃቤ ሕጉ ወይም ተካሣሹ የይግባኝ መብት ያለው መሆኑን ይነገረዋል፡፡

## አንቀጽ 401 የፍትሐብሔር ክስ መወሰን

1. ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ በታየው የፍትሐብሔር ክስ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2. ኪሳራ፣ ወጪ እና የዳኝነት አከፋፈል በተመለከተ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ መሠረት ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 402 ፍርድ አፃፃፍ

1. ፍርዱ በቅደም ተከተል፡-

(ሀ) የመዝገብ ቁጥር፤

(ለ) ፍርዱ የተሰጠበትን ቀን፣ ወር፣ እና ዓመተ ምህረት፤

(ሐ) የፍርድ ቤቱን ስም፤

(መ) የዳኛ ስም፤

(ሠ) ክሱ በአጭሩ፣ እንዳስፈላጊነቱ ክሱ በቀረበበት ዐይነት፤

(ረ) ቀድመው ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች በአጭሩ፤

(ሰ) የክርክሩ ጭብጥ፣ ጭብጡን ያስረዱ ማስረጃዎች አጭር መግለጫ፤

(ሸ) ፍርድ ቤቱ የተቀበላቸው ማስረጃዎች ከነምክንያቱ፤

(ቀ) ጭብጡን ያላስረዱ ማስረጃዎች፤

(በ) ፍርድ ቤቱ ያልተቀበላቸው ማስረጃዎች ምክንያት፤

(ተ) ለድምዳሜ መሠረት የሆነው ዝርዝር የፍሬ ነገር፣የማስረጃና የሕግ ምክንያቶች፤

(ቸ) ድምዳሜ፤

(ነ) ውሳኔው፤

(ኘ) ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ የቅጣቱ አፈጻጸም፤

(አ) ልዩ ልዩ ትእዛዞች፤

(ከ) የዳኛ ፊርማ፤

መያዝ አለበት፡፡

2. በማስረጃነት የቀረበ ምስል ወይም ሌላ በጽሑፍ ሊገለጽ የማይችል ማስረጃ በማጣቀሻ ሊገለጽ ይችላል፡፡
3. ፍርዱን የሰጠው ዳኛ በበቂ ምክንያት በፍርዱ ላይ ሳይፈርምበት ከቀረ ምክንያቱ ተገልፆ በሹመት ቀደምት በሆነው ዳኛ ወይም ፕሬዚዳንቱ ሊፈረም ይችላል፡፡ የፍርድ ኮፒ በሬጅስትራሩ ይፈረማል፡፡
4. በፍርድ ውሳኔ ውስጥ የሚካተተው ከፍርድ ድምዳሜ በመነሳት ተፈጻሚ ሊሆን የሚገባው ለፍርድ አካል ብቻ ነው፡፡
5. በተለያዩ አካላት የሚገለጹ ጉዳዮች፣ የመዝገቡን አስተዳደር የሚመለከቱ ጉዳዮች፣ የይግባኝ መብት የሚመለከቱ ጉዳዮች በውሳኔ ሥር ይገለጻሉ፡፡

<u>አንቀጽ 403 ስለማገድ</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 433 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ ተከሳሹ እንዳይለቀቅ፣ የተያዘው ንብረት ወይም ገንዘብ ወይም ኤግዚቢት እንዳይመለስ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆን በይግባኝ ጥያቄው ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በተከሳሹ፣ በተያዘው ንብረት ወይም በገንዘብ ወይም ኤግዚቢት ላይ በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሳይፈጸም ይቆያል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይግባኙ እንደቀረበለት ወዲያውኑ ይወስናል፡፡
2. ጥፋተኛ ሆኖ የተፈረደበት ይግባኝ ባይ የይግባኝ ማስታወቂያ የሰጠ እንደሆነ ይግባኙ ሳይሰማ ወይም ይግባኙን ይግባኝ ባዩ ካልተወ በቀር የግርፋቱ ቅጣት አይፈጸምም፡፡
3. ተከሳሹ ይግባኙ እስኪወሰን ድረስ በዋስትና ወረቀት የተለቀቀ እንደሆነ የእስራቱ ቅጣት የይግባኙ ፍርድ ቤት ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ አይጀመርም፡፡
4. ይግባኝ የተባለበት ፍርድ ቤት እንዲፈጸሙ ለጥንቃቄ የሰጣቸወው ትእዛዞች ይግባኝ የተባለባቸው ቢሆኑም መፈጸም አለባቸው፡፡
5. ስለ ካሣ ወይም ስለ ኪሣራ ወጪ የተሰጠ ፍርድ ከመፈጸም አይታገድም፡፡
6. ይግባኙ ከመሰማቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ወይም ይግባኙ በሚሰማበት በማንኛውም ጊዜ ፍርዱ እንዲታገድ ለይግባኝ ፍርድ ቤት ማመልከት ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት
## ስለቅጣት አወሳሰን
## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 404 መርህ**

1. ቅጣት ትክክለኛነትን፣ ወጥነትን፣ ተመጣጣኝነትን፣ አግባብነትን፣ ፍትሓዊነትን እና ሕጋዊነትን መርህን በመከተል እና ጥፋት የፈፀሙ ሰዎችን ለማረምና ለማስተማር፣ ወንጀል የመፈጸም ችሎታን ማሳጣት መወሰን አለበት፡፡

2. ዳኛ ማንኛውም ቅጣት ሲወስን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተመለከቱት መርሆዎች መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

**አንቀጽ 405 የቅጣት አፈጻጸም ትእዛዝ**

ፍርድ ቤቱ የወሰነው ቅጣት፡-

1. የሞት ቅጣት እንደሆነ ቅጣቱ ፀድቆ እስኪፈፀም ፍርደኛው በማረሚያ ቤት እንዲቆይ፣

2. የገንዘብ መቀጮ እንደሆነ ወይም የእሥራት ቅጣቱ ገንዘብ የሚጨምር እንደሆነ ተከሳሽ ገንዘቡን እንዲከፍል የአከፋፈሉን ሁኔታ በመለየት፣ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
3. ሌሎች የቅጣት ርምጃዎችን በተመለከተ ስለ አፈጻጸሙ

ተገቢውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## ስለ ቅጣት፣ የጥንቃቄ ርምጃ አፈጻጸም እና መሰየም

**አንቀጽ 406 መርህ**

1. ቅጣትና የጥንቃቄ ርምጃ አፈጻጸም የወንጀል እና ይህ ሕግ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ መፈጸም አለበት፡፡
2. በዚህ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር ቅጣት እንደተወሰነ ወድያውኑ መፈጸም አለበት፡፡

## ክፍል አንድ
## ስለሞት ቅጣትና ተጨማሪ ቅጣት አፈጻጸም
## ንዑስ ክፍል አንድ
## ስለሞት ቅጣት አፈጻጸም

**አንቀጽ 407 የሞት ቅጣት ውሳኔ የሚፈጸምበት ሁኔታ**

1. የሞት ቅጣት ፍርድ የሰጠ ፍርድ ቤት ውሳኔውንና የመዝገቡን ግልባጭ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስተላለፍ አለበት፡፡ ውሳኔውን የሰጠው ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሆነ ውሳኔው በአምስት ዳኞች መታየት አለበት፡፡
2. የሞት ፍርድ በፍርደኛው ይግባኝ ካልተባለበት አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መታየት አለበት፡፡ ፍርዱን ያስተላለፈው ፍርድ ቤት የፍርዱን መዝገብ ወይም ትክክለኛ ግልባጩን ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስተላለፍ አለበት፡፡ የሞት ፍርዱን ያጸደቀው ወይም ያጸናው እንደሆነ ለአፈጻጸም ወደ ፍትሕ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡
3. የፍትሕ ሚኒስቴር የሞት ፍርዱ በጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ፣ በይቅርታ ወይም ምኅረት ያልተሻረ ወይም ያልተለወጠ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲጸድቅ ለርዕሰ ብሔሩ ያቀርባል፡፡
4. የሞት ቅጣት ፍርዱ በጸደቀበት በስድስት ወር ውስጥ ሰብዓዊበሰብዓዊ ሁኔታ በማረሚያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ መፈጸም አለበት፡፡
5. የሞት ቅጣት ፍርዱ በስድስት ወር ውስጥ ካልተፈጸመ አስፈጻሚው ያልፈጸመበት ምክንያት እንዲያስረዳ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ ፍርድ ቤቱ ፍርዱ ያልተፈጸመበት ምክንያት በቂና አሳማኝ ሆኖ ካገኘው ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ጊዜ ገደብ ፍርዱ ይፈጸማል፡፡
6. ፍርዱ ያልተፈጸመበት ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ካገኘው ፍርድ ቤቱ ላለመፈጸሙ ምክንያት የሆነ ሁኔታ በተወገደበት በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ እንዲፈጸም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
7. በማንኛውም ምክንያት የሞት ፍርድ ሳይፈጸም ከአምስት ዓመት በላይ የቆየ እንደሆነ ወደ ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ይቀየራል፡፡
8. የሞት ፍርድ አፈጻጸምን በተመለከተ ፍትሕ ሚኒስቴር መመሪያ ያወጣል፡፡

**አንቀጽ 408 <u>የሞት ቅጣት አፈጻጸም ማገድ</u>**

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 119 በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት የሞት ቅጣት አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ ፍርዱን ለፈረደው ፍርድ ቤት ሲቀርብ ማስረጃውን ሰምቶ ሊያግደው ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የግል ነፃነት የሚያሰጡ ቅጣቶች አፈጻጸም

**አንቀጽ 409 <u>የሚሰጥ ትእዛዝ</u>**

ማንኛውም ሰው በቅጣት ምክንያት እንዲያዝ፣ እንዲታሰር ወይም በአንድ ቦታ እንዲወሰን ፍርድ ቤት ሲወስን ቅጣቱ እንዲፈጸም በዚህ ሕግ ሠንጠረዥበተመለከተው ቅጽ መሠረት ዳኛው ፈርሞ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 410 <u>የእስራት ቅጣት ማስተላለፍ</u>**

1. ፍርድ ቤት፡-

   (ሀ) የቀላል እስራት ቅጣት የወሰነ ወይም በጥፋተኝነት ድርድር ያጸደቀ እንደሆነ፣

   (ለ) ፍርደኛው ለኅብረተሰቡ ደኅንነት አደጋ እንደማይሆን ሲያረጋግጥ፣ እና

   (ሐ) ፍርደኛው በቂ ዋስትና የሚያቀርብ እንደሆነ፣

   በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተዘረዘሩት ምክንያቶች የቀላል እስራት አፈጻጸሙን እንዲተላለፍ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. ፍርድ ቤት በፍርደኛው ወይም በጠበቃው አመልካችነት ፍርዱ እንደተሰጠ ወድያውኑ ከሚከተሉት ምክንያቶች ቢያንስ አንዱ መኖሩን ሲያረጋግጥ ቅጣቱ የሚፈጸምበትን ጊዜ ማስተላለፍ ይችላል፡፡

   (ሀ) በጠና ከመታመሙ የተነሳ በማረሚያ ቤት ቅጣቱን ለመፈጸም የማይችል መሆኑን በሐኪም ሲረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ከሕመሙ እስኪድን አስፈላጊነው ብሎ ለሚወስነው ጊዜ፣

   (ለ) አንድ ዓመት ያልሞላው ሕፃን ያላት እናት ስትሆን ሕፃኑ አንድ ዓመት እስኪሞላው፣

(ሐ) ሦስት ወርና ከዚያ በላይ ነፍሰ ጡር እንደሆነች ይኸው የእርግዝና ጊዜ እስከሚያበቃና ከወለደች በኋላ አንድ ዓመት እስኪሞላው፣

(መ) ፍርዱ ከተሰጠበት ቀን በፊት ባለው አንድ ሳምንት ውስጥ ወላጁ፣ ልጅ ወይም የትዳር ጓደኛው የሞት ወይም በጠና የታመመ እንደሆነ ከሰባት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ፣

(ሠ) ፍርዱ ከተሰጠበት ቀን ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የትዳር ጓደኛው የወለደች እንደሆነ ወይም ፍርድ ከተሰጠ በሚቀጥለው አንድ ወር ውስጥ የምትወልድ እንደሆነ እና ከተፈረደበት ሰው ሌላ ረዳት የሌላት እንደሆነ ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ፣

(ረ) ቤተሰቡን የሚንከባከብ ሌላ ሰው ከሌለና  ባልና ሚስት አንድ ላይ የተፈረደባቸው እንደሆነ ሚስት፣ ወይም ከሁለቱም አንዱ ቀደም ብሎ የታሰረ እንደሆነ አሁን የተፈረደበት ሰው ለሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ፣

(ሰ) የቅጣቱ አፈጻጸም እንዲተላለፍለት የተጠየቀለት ምክንያት አጣዳፊ (ወቅታዊ) ለሆነ የግብርና ሥራ ወይም ባልታሰበ ምክንያት የተፈጠረ በአስቸኳይ ሊከናወን የሚገባው ሥራ እንደሆነ ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ፣

(ሸ) የተፈረደበት ሰው ቀደም ብሎ የጀመረው ሆኖ በሌላ ሰው ሊጠናቀቅ የማይችል አጣዳፊ ሥራ ሲሆንና ሥራው ባለመጠናቀቁ ምክንያት ጉዳት የሚደርስ እንደሆነ ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ፣

(ቀ) የተፈረደበት ሰው የጀመረውን ትምህርት ወይም የተማረበትን ፈተና ለማጠናቀቅ እንደሆነና በሌላ ሁኔታ ማጠናቀቅ የማይቻል እንደሆነ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ወይም ለፈተናው የሚያስፈልገው ጊዜ፣

**አንቀጽ 411** <u>የአቤቱታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ</u>

1. ፍርደኛው የቅጣት አፈጻጸም ጊዜው እንዲተላለፍለት የሚያቀርበው  አቤቱታ፡-
   (ሀ) አቤቱታው የቀረበበትን ምክንያት፣
   (ለ) ምክንያቱን ለማስረዳት የሚቀርብን የማስረጃ ዝርዝር፣ እና
   (ሐ) የቅጣቱ አፈጻጸም ለምን ያህል ጊዜ ሊተላለፍለት እንደሚገባ፣

   ከቅጣት አስተያየት ጋር አብሮ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ፍርድ ቤቱ በቀረበው አቤቱታ ዐቃቤ ሕግ አስተያየቱን እንዲሰጥበትና አስፈላጊ ሲሆን ማስረጃውን ወይም የባለሙያ አስተያየት ከሰማ በኋላ ከቅጣት ውሳኔው ጋር አብሮ ውሳኔውን መስጠት አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ የቅጣት አፈጻጸም ለጊዜው እንዲተላለፍ ከፈቀደ የተፈቀደለት ሰው የእስራት ቅጣቱን መፈጸም በሚገባው ጊዜ እንዲጀምር ለማረጋገጥ የሚያስችለው በቂ ዋስትና እንዲያቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 412 <u>የተላለፈን ቅጣት ማቋረጥ</u>**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 473 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም፡-

   (ሀ) ፍርደኛው የተላለፈበት የእስራት ጊዜን ለሌላ ዓላማ ካዋለው ወይም ምክንያቱ ቀሪ እንደሆነ፣

   (ለ) ቅጣቱ እንዲፈጸም በተወሰነበት ጊዜ መፈጸም ያልጀመረ እንደሆነ፣

   (ሐ) ፍርደኛው በማንኛውም መንገድ ለሕዝብ ደኅንነት አደጋ መሆኑን ከተረጋገጠ፣

   (መ) ያመልጣል ተብሎ የሚጠረጠር ሆነ፣

   (ሠ) ቅጣቱ እንዲተላለፍለት ያቀረበው ምክንያት የሌለ ወይም የተቋረጠ እንደሆነ፣

   የተላለፈለት ቅጣት ተቋርጦ መፈጸም አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተላላፈለት ቅጣት ተቋርጦ እንዲፈጽም ትእዛዝ የተሰጠበት ፍርደኛ የተላለፈበት የእስራት ጊዜ ከዋናው ቅጣት አይታሰብለትም፡፡ ፍርድ ቤቱም ፍርደኛው አመክሮ እንዳይሰጠውና የዋስትና መብት እንዲከለከል ወይም የዋስትና ገንዘብ ወይም ንብረት ገቢ እንዲደረግ ሊወስን ይችላል፡፡
3. በዚህ ሕግ አንቀጽ 428 የተላለፈው የእስራት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ የተፈላለፈውን የእስራት ቅጣቱ እንዲፈጸም በተወሰነበት ጊዜ መፈጸም ያልጀመረ እንደሆነ በዋስትና ያስያዘው ገንዘብ ወይም ንብረት ገቢ ይሆናል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ስለ ገንዘብ ቅጣት አፈጻጸም

**አንቀጽ 413 የዋስትና ገንዘብ ወይም መያዣ ገቢ ማድረግ**

1. በወንጀል ሕጉ መሠረት ፍርድ ቤቱ የገንዘብ መቀጮ የወሰነ እንደሆነ ተቀጪው ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ወድያውኑ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡
2. የገንዘብ መቀጮውን ወድያውኑ ገቢ ማድረግ ካልቻለ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ ……………… የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ ተቀጪው በዋስትና ያስያዘው ገንዘብ ካለ ወይም ከሌለው በዋስትና ያስያዘውን ንብረት ተሸጦ በቅጣቱ ልክ ገቢ እንዲሆን ትአዛዝ ይሰጣል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ በዋስትና ያስያዘው ንብረት ከመሸጡ በፊት ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ የእፎይታ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ተቀጪው በዋስትና ያስያዘው ንብረት ከሌለ ሌላ ንብረት ተፈልጎ ተሸጦ ገቢ እንዲደረግ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
4. ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ ተከታትሎ ማስፈጸም አለበት፡፡
5. ከንብረቱ ተሸጦ ገቢ የሚደረገው ለቅጣቱ ተመጣጣኝ በሆነ ልክ ሆኖ ንብረቱ ከመሸጡ በፊት የቅጣት ገንዘቡን ገቢ ካደረገ የሽያጭ ሒደቱ ሊቋረጥ ይችላል፡፡
6. ተቀጪው መቀጮውን በሙሉ ወይም በከፊል ገቢ ለማድረግ ያልቻለ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤቱ ያሳውቃል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተገቢ የመሰለውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 414 ካሣና ኪሳራ መክፈል ወይም ንብረት መተካት**

ፍርድ ቤት የጉዳት ካሣና ኪሳራ እንዲከፈል እንዲሁም ንብረት እንዲተካ ያዘዘ እንደሆነ ውሳኔው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ ስለ ውሳኔ አፈጻጸም በተደነገገው መሠረት ይፈጸማል፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት
## ስለተጨማሪ ቅጣት አፈጻጸም

**አንቀጽ 415 የተጨማሪ ቅጣት ትእዛዝ**

1. ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ቅጣት የወሰነ እንደሆነ ለዚህ ቅጣት አፈጻጸም ግልጽ ትእዛዝ ወድያውኑ መስጠት አለበት፡፡

2. ተጨማሪ ቅጣቱ ወድያውኑ የሚፈጸም ቅጣት ዐይነት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ወድያውኑ ማስፈጸም አለበት፡፡

## አንቀጽ 416 <u>ንብረትን መውረስ</u>

1. ፍርድ ቤት ንብረት እንዲወረስ የወሰነ እንደሆነ ስለአወራረሱና ስለ አስተዳደሩ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡
2. በዚህ ሕግ ስለንብረት ዕግድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም ሰው እንዲወርስ ትእዛዝ የተሰጠበት ንብረት እንዲለቀቅለት ለፍርድ ቤቱ ማመልከት ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚቀርበው ማመልከቻ በጹሑፍ ሆኖ አመልካቹ በንብረቱ ላይ ያለውን መብት ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
3. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለቀረበው አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የመውረስ ትእዛዝ ማገድ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከመፈጸም ታግዶ እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) አመልካቹ ላቀረበው ጥያቄ ዐቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ አግባብነት ያለውን ሕግና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
5. የንብረት መወረስ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ፡-
   - (ሀ) በወንጀሉ ምክንያት የተገኘ ሌላ ንብረት የተገኘ እንደሆነ፣
   - (ለ) ንብረቱ በተገኘበት እንዲወረስ ትእዛዝ የተሰጠበት ካልሆነ፣
   - (ሐ) ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ የንብረቱ መኖር ከዐቃቤ ሕግ ዕውቅና ውጭ መሆኑና ንብረቱን ለማግኘት ጥረት ማድረጉን ዐቃቤ ሕግ ካስረዳ፣
   - (መ) የንብረቱ ዝርዝር ያልቀረበው ከዐቃቤ ሕጉ ዕውቅና ውጭ በሆነ ስሕተት ወይም በተከሳሽ ማታለልወይም ማጭበርበር ምክንያት እንደሆነ፣

   ንብረቱ እንዲወረስ አቤቱታ ሊቀርብበት ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የሚቀርበው የንብረት ይወረስ ጥያቄ ውሳኔ ከተሰጠበት ወይም ንብረቱ ከተገኘበት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
7. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 101 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በተወረሰ ንብረት ላይ የወንጀል ተጎጅው ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ይቀድማል፤ መንግሥት

ከወንጀል ተጎጅው ቀጥሎ ቀደምትነት አለው፤ ሌሎች ንብረቱ የሚገባቸው ካሉ በሕግ መሠረት የሚከፋፈል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 417 ይቅርታ

1. ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ጥፋቱን አምኖ ተበዳዩን ወይም ስለ እሱ ባለመብቶች የሆኑትን በግልጽ ይቅርታ እንዲጠይቅ የወሰነ እንደሆነ የአካባቢውን ልማድ ግምት ውስጥ በማስገባት፡-

   (ሀ) ጥፋተኛው በእነማን ፊት ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት፣

   (ለ) ይቅርታ የሚፈጸምበት ቦታና ጊዜ፣

   (ሐ) አስፈላጊ እንደሆነ ይቅርታ በሚፈጸምበት ቦታ መገኘት ያለበት የመንግሥት አካል፣

   በመለየት ይቅርታ እንዲጠይቅ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

2. ፍርድ ቤት ፍርደኛው በእሥር ላይ ያለ ከሆነ ማረሚያ ቤት የይቅርታ ሥርዐቱን እንዲያስፈጽመው እና ይህንኑ ሥርዐት ሳይፈጸም በአመክሮ ሊለቀቅ እንደማይገባ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

3. ፍርድ ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይቅርታው እንደአግባብነቱ በመገናኛ ብዙኃን ወይም ሌሎች አመች መንገድ እንዲገለጽ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 418 ተጨማሪ ቅጣትን ስለማሳወቅ

ፍርድ ቤቱ በአጥፊው ላይ መብትን የመሻር ቅጣት፣ ከደረጃ ዝቅ ወይም ከመከላከያ ሠራዊት አባልነት እንዲሰናበት፣ መዓረግ ካለው እንዳይገለገልበት የማድረግ ወሳኔ የሰጠ እንደሆነ ይኸው እንዲፈጸም አግባብ ላለው አካል ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

# ክፍል ሁለት
# ቅጣትን ትእዛዝ ስለመለወጥ

## አንቀጽ 419 የቅጣት አፈጻጸም ትእዛዝን መለወጥ

1. ቅጣቱ ወይም የጥንቃቄ ርምጃውን የወሰነው ፍርድ ቤት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ ................መሠረት ቅጣቱን ሊለውጥ ይችላል፡፡
2. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶች የሚሰጥ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ ርምጃ በዚህ ሕግ አንቀጽ .................... መሠረት ሊለወጥ ይችላል፡፡

**ትእዛዝአንቀጽ 420** ***<u>የማመልከቻ አቀራረብና ውሳኔ</u>***

1. ዐቃቤ ሕግ፣ ፍርደኛ ወይም ወኪሉ ቅጣቱን ወይም የጥንቃቄ ርምጃው እንዲያስፈጽም ወይም አፈጻጸሙን እንዲቆጣጠር የተፈቀደለት ሰው ወይም ተቋም የበላይ ኃላፊ ለፍርድ ቤት በጽሑፍ ወይም በሌላ ዘዴ ቅጣቱ እንዲለወጥ ማመልከት ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለቀረበው ማመልከቻ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
3. ፍርደኛው ቅጣቱን ከወሰነበት ፍርድ ቤት የግዛት ክልል ሥልጣን ውጭ በሆነ ማረሚያ ወይም ማረፍያ ቤት እንደሆነ የተቀጣበትን ወንጀል ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ያለው ፍርደኛው በሚገኝበት ቦታ የሚገኝ ፍርድ ቤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 202 እስከ 207 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ፍርደኛው እንዲለቀቅ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
## <u>ስለአማራጭ ቅጣት</u>

**አንቀጽ 421** ***<u>መርህ</u>***

1. ፍርድ ቤት በራሱ አስተያየት ወይም በፍርደኛው ጥያቄ በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት በዋና ቅጣት ምትክ አማራጭ ቅጣትን መወሰን ይችላል፡፡ በሕግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የሚወሰነው አማራጭ ቅጣት በጉልበት ሥራ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
2. ፍርድ ቤት አማራጭ ቅጣት የሚወሰነው የቅጣት ዓላማን ይበልጥ ያሳካል ብሎ ሲያምን እና ተቀጭው፡-

   (ሀ) ጥፋተኛ የተባለበት ወንጀል ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በገንዘብ ብቻ የሚያስቀጣ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ በቀላል እስራትና በገንዘብ የሚያስቀጣ ወንጀል ሲሆን፣

   (ለ) ጤንነቱ ተመርምሮ የጉልበት ሥራ መሥራት መቻሉ ሲረጋገጥ፣ እና

   (ሐ) ከእስራት ይልቅ በጉልበት ሥራ ቢቀጣ ለኅብረተሰቡ አደገኛ አለመሆኑ በማረጋገጥ መሆን አለበት፡፡
3. አማራጭ ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው በተፈጥሮ ሰው ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 422 በውሳኔ የሚገለጹ ጉዳዮች**

ፍርድ ቤት የአማራጭ ቅጣት ውሳኔ ሲሰጥ እንደነገሩ ሁኔታ፡-

(1) የቅጣቱ ዐይነትና የሚከናወንበት ቦታ፣ የሚቆይበት ጊዜ በግልጽ የተለየ መሆኑ፣

(2) ከተወሰነ ቦታ ውጭ መሥራት ስለመቻሉ፣

(3) የግል ነፃነቱ የሚደገብ እንደሆነ የገደቡ አግባብና ግዜ፣

(4) ፍርደኛው ቁጥጥር ሊደረግበት የሚገባ ስለመሆኑ፣ እና

(5) ከሥራው ፍሬ ፍርደኛው ስለሚያገኘው ገቢ እና ለመንግሥት ገቢ ስለሚሆነው የገንዘብ መጠን

በውሳኔው ላይ በግልጽ ማስፈር አለበት፡፡

**አንቀጽ 423 የባለሙያ ድጋፍ**

ተቀጭ ቅጣቱን በሚፈጽምበት ጊዜ እንደነገሩ የማኅበራዊ ሳይንስ፣ የሥነ-ልቦና ወይም ሌላ የሙያ ድጋፍና ክትትል እንዲደረግለት ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 424 አማራጭ ቅጣትን ማቋረጥ**

1. ፍርድ ቤቱ፡-

(ሀ) ፍርደኛው ግዴታውን ጥሶ የተገኘ እንደሆነ፣

(ለ) ፍርደኛው ያለበት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ወይም የቤተሰብ አስተዳዳሪ ኃላፊነት የቅጣቱን መፈጸም እንድያቋርጥ ያስገደደው እንደሆነ፣ ወይም

(ሐ) አሳማኝ ነው ባለው ሌላ ምክንያት፣

በራሱ ተነሳሽነት ወይም በማንኛውም ሰው አመልካችት የአመራጭ ቅጣቱ እንዲቋረጥ ሊወሰን ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቅጣቱ መፈጸም ሲቋረጥ ፍርድ ቤቱ እንደ ነገሩ ሁኔታ ቀሪ ቅጣቱ እንዲፈጸም፣ እንዲሻሻል ወይም ለሌላ ጊዜ ተላልፎ እንዲፈጸም ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 425 የአስፈፃሚ አካላት**

የአማራጭ ቅጣት አመራር፣ አፈጻጸምና የአስፈፃሚ አካላት ዝርዝር ሁኔታ በተመለከተ በሕግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 426** ***<u>የክልል ሥልጣን</u>***

የግዴታ ቅጣት ሥራን በተመለከተ በዚህ ክፍል አንቀጽ 423 የተመለከተውን መርህ በጠበቀ መልኩ ክልሎች በሕግ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

## ***<u>ክፍል ሦስት</u>***
## ***<u>ስለመሰየም</u>***

**አንቀጽ 427** ***<u>መርህ</u>***

1. መሰየም የፍርደኛው መልካም ስም እንዲመለስ ለማድረግ ነው፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የመሰየም ውሳኔ ሲሰጥ ፍርደኛው የሠራቸው መልካም ሥራዎች በተለይ የበደለውን ኅብረተሰብና ተጎጂውን በተመለከተ የፈጸማቸው ተግባራት መሠረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡

**አንቀጽ 428** ***<u>የመሰየም ውሳኔ የሚሰጥበት ሥርዐት</u>***

በወንጀል ሕጉ መሠረት የመሰየም ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት፡-

(1) አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የመሰየም ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩ እንዲጣራ ወይም ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

(2) ጥያቄውን የተቀበለው እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 233 እና 234 በተደነገገው መሠረት እንዲፈጸምና የተሰረዘው ቅጣት፣ የተሰያሚው ስም በጥፋት ተመዝግቦበት ከነበረው የወንጀለኞች መዝገብ ላይ እንዲፋቅ አግባብ ላላቸው አካላት ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

(3) ፍርደኛው እንዲሰየም የወሰነ እንደሆነ ስለአፈጻጸሙና ከወንጀለኞች መዝገብ ስለመፋቁ ለሚመለከታቸው አካላት ትእዛዝ ማስተላለፍ አለበት፤ እንዳአስፈላጊነቱ በግልጽ ችሎት፣ በአደባባይ መነበብ ወይም በጋዜጣ ሊወጣ ይችላል፡፡

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ ምክንያቱ መገለጽ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አሥር
## ስለ ፍርድን እንደገና ማየት፣ ሰበር እና ይግባኝ
## ክፍል አንድ
## ተከሳሽ በሌለበት የተካሔድን የፍርድ ሒደት እንደገና ስለማየት

**አንቀጽ 429** **የማመልከቻው ይዘትና አቀራረብ**

1. በወንጀል ተከሶ በሌለበት የተፈረደበት ሰው ፍርዱ ውድቅ እንዲሆንለት ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

2. አመልካች የሚያቀርበው ማመልከቻ በዚህ ሕግ አንቀጽ 297 መሠረት መጥሪያ ያልደረሰው በመጥሪያ አድራሹ ምክንያት መሆኑ ወይም መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን በዝርዝር የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረብ መሆን አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ማመልከቻ ሊቀርብ የሚችለው አመልካቹ ውሳኔው መሰጠቱን ካወቀበት ወይም ከዓቅም በላይ የሆነው ምክንያት ከተወገደበት ቀን አንስቶ ባሉት ሰላሳ ቀናት ውስጥ ነው፡፡

**አንቀጽ 430** **በማመልከቻው ላይ የሚሰጥ ትእዛዝ**

1. ፍርድ ቤቱ ማመልከቻው በዚህ ሕግ አንቀጽ 447 መሠረት መቅረቡን ካረጋገጠ በኋላ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀን በመወሰን ዐቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥ የማመልከቻውን ግልባጭ ከመጥሪያ ጋር እንዲሰርሰው ያደርጋል፡፡

2. አመልካች በሌለበት የእሥራት ቅጣት የተወሰነበት እንደሆነ የቀረበው ማመልከቻ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ በማረሚያ ቤቱ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ያዛል፡፡

3. ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ በሰጠበት ቀን አመልካቹ የቀረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርጋል፤ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

4. ዐቃቤ ሕጉ እና አመልካቹ የቀረቡ እንደሆነ አመልካቹ ማመልከቻውን መሠረት በማድረግ በቃል ያስረዳል፤ ዐቃቤ ሕግም መልስ ይሰጣል፡፡ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ተከሳሹ የመልስ መልስ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

5. ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግንና የአመልካቹን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካቹ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ይወሰናል፡፡ የአመልካቹ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ከተረዳ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶ የተሰጠ ፍርድ ካላ እንዲፈጸም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

6. አመልካቹ ቀርቦ ሊከራከር ያልቻለው በዚህ ሕግ አንቀጽ 297 በተደነገገው መሠረት መጥሪያ ያልደረሰው ወይም መጥሪያ ደርሶት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ ፍርድ ቤት እንዳአግባብነቱ የተሰጠ ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ተነስቶ ጉዳዩ በሌላ ዳኛ ወይም ፍርድ ቤት እንደገና እንዲታይ ይመራዋል፡፡ ጉዳዩ የተመራለት ዳኛ ወይም ፍርድ ቤት ክርክሩን ሰምቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ይግባኝ

### አንቀጽ 431 መርህ

1. ይግባኝ፡-
   (ሀ) በሥር ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ የተከሳሽን ይግባኝ የማቅረብ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ለማረጋገጥ፤
   (ለ) በሥር ፍርድ ቤት የተፈጸመ የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ስሕተትን ለማረም፤
   (ሐ) ወጥ ወይም ተቀራራቢ የሆነ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር ለማድረግ፤
   የሚፈጸም መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ይግባኝ ጠያቂ ይግባኝ ከመጠየቁ በፊት በሥር ፍርድ ቤት መፍትሔ ማግኘት የሚገባው እንደሆነ ይህንን ሥርዐት ሳይፈጽም ይግባኝ ማቅረብ አይችልም፡፡
3. የቅድመ ክስ ሥነ ሥርዐት እንደአግባብነቱ በይግባኝ በሚታዩ ጉዳዮችም ሊከናወን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 432 ይግባኝ ስለሚያቀርቡ ሰዎች**

1. በዚህ ሕግ መሠረት መሠረት በወንጀል ጉዳይ ላይ በተሰጠ ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችሉት ዐቃቤ ሕግ፣ የግል ከሳሽ፣ ፍርደኛ ወይም ጠበቃው ብቻ ናቸው፡፡
2. ከወንጀል ጉዳዩ ጋር በተያያዘ የፍትሐብሔር ጉዳይ ላይ በተሰጠ ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ እንደነገሩ ሁኔታ ዐቃቤ ሕግ፣ የግል ከሳሽ፣ ተጎጂ፣ ፍርደኛ፣ ጠበቃው ወይም ሌሎች በፍትሐብሔር ሕግ ይግባኝ እንዲያቀርቡ መብት የተሰጣቸው ሰዎች ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 433 ይግባኝ የሚባልባቸው ጉዳዮች**

1. ማንኛውም ተከራካሪ ወገን፡-

   (ሀ) የጥፋተኝነት ወይም ነፃ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ሁኔታ መዝገቡ የተዘጋ፣

   (ለ) የተከሳሽ የዋስትና መብትን በመፍቀድ ወይም በመከልከል ውሳኔ፣

   (ሐ) በተከሳሹ የጥፋተኝነት ወይም ነፃ የማለት ውሳኔ፣ እና

   (መ) የተወሰነው የቅጣት መጠን፣

   ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡
2. ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጥፋተኝነት ውሳኔን አጽንቶ ቅጣቱን የለወጠ ወይም ቅጣቱን አጽንቶ ጥፋተኛ ነው የተባለበትን ውሳኔ የለወጠ እንደሆነ ጥፋተኛ ነው በተባለበት ወይም ቅጣቱ እንዲለውጥ በተወሰነው ላይ ብቻ ሁለተኛ ጊዜ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡
3. ተከሳሽ በሌለበት በተወሰነ ጉዳይ ወደ ክርክር እንዲገባ በቀረበ አቤቱታ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት የለም በተባለ ጊዜ በተሰጠ በጥፋተኝነት ፍርድ ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለሥር ፍርድ ቤት የቀረቡ ማስረጃዎችን እና ፍርደኛው ጥፋተኛ የተባለበትን የሕግ አንቀጽ ብቻ በመመርመር ይግባኙን ሊመረምር ይችላል፡፡

**አንቀጽ 434 ይግባኝ የማይባልባቸው ጉዳዮች**

1. ይግባኝ፡-

   (ሀ) በዚህ ሕግ በተቃራኒው ካልተደነገገ በስተቀር በዕርቅ ወይም በድርድር ወይም በሌላ አማራጭ የመፍትሔ ሥርዐት ባለቀ ጉዳይ፣

   (ለ) ማስረጃ በመቀበል ወይም ባለመቀበል በሚሰጥ ትእዛዝ፣

(ሐ) ጉዳዩን የሚሰማው ፍርድ ቤት በክርክሩ ሒደት መዝገቡ ሳይዘጋ በሚሰጠው ትእዛዝ ወይም መዝገቡን በዘላቂነት በማያዘጋ ትእዛዝ፣

(መ) ተከሳሹ ጥፋተቱን ያመነ እንደሆነ በእምነት ቃሉ መሠረት የተሰጠ የጥፋተኝነት ውሳኔ፣

(ሠ) ተከሳሽ በሌለበት በተወሰነ ጉዳይ ወደ ክርክር እንዲገባ በቀረበ ጥያቄ በሚሰጥ ትእዛዝ፤

(ረ) የይግባኝ ማስፈቀጃ ተቀባይነት የለውም በማለት በሚሰጥ ውሳኔ፣

(ሰ) ፍርድን እንደገና የማየት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት በሚሰጥ ትእዛዝ ወይም ውሳኔ፣

(ሸ) በዚህ ሕግ መሠረት በቀረበ የመሰየም ጥያቄ ላይ የተሰጠ ውሳኔ፣

(ቀ) በደንብ መተላለፍ ጉዳዮች፣

ላይ ሊቀርብ አይችልም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶ መዝገብ የተዘጋ እንደሆነ ይግባኝ በሚባልባቸው ጉዳዮች ላይ ለይግባኝ ምክንያቶች ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 435 <u>በይግባኝ ጉዳይ የክልሎች ሥልጣን</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 428 የተደነገገውን መሠረት በማድረግ ክልሎች የተከሳሹን ወይም ፍርደኛውን ይግባኝ የማቅረብ መብት በሚያስፉ መልኩ ይግባኝ በሚባልባቸውና በማይባልባቸው ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ በሕግ ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 436 <u>በካሣ ጥያቄ ላይ የሚቀርብ ይግባኝ</u>**

1. ከወንጀል ክስ ጋር ተያይዞ በቀረበው የፍትሐብሔር ክስ ላይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይግባኝ የሚቀርበው በይግባኝ የወንጀል ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው፡፡
2. የይግባኝ አቀራረቡ፣ የሚቀርብበት ጊዜና የመስማት ሒደቱ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 437 <u>ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ማገድ</u>**

1. ይግባኝ ከመሰማቱ በፊት ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ እንዲታገድ ፍርዱን ለሰጠው ችሎት ወይም ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

ፍርዱ፣ውሳኔው ወይም ትእዛዙ ከተሰጠ ከሦስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ማመልከት ይችላል፡፡

2. ፍርዱን የሰጠው ችሎት ወይም የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት ፍርዱን፣ ውሳኔው ወይም ትእዛዙን እንዳይፈጸም ከሰባት ተከታትይ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያግደው ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የዕግድ ትእዛዝ የሚሰጠው የዕግድ ጥያቄው ሳይዘገይ መቅረቡ እና ፍርዱ፣ ውሳኔው ወይም ትእዛዙ ቢፈጸም የማይተካ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ የታመነ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡
4. ይግባኝ በሚሰማበት በማናቸውም ጊዜ ፍርዱ፣ ውሳኔ ወይም ትእዛዙ እንዲታገድ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የቀረበው አቤቱታ ተመልክቶ ተገቢ የመሰለውን ትእዛዝ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡
5. ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት
   (ሀ) ጉዳዩን መርምሮ ወደ ነገሩ ለመግባት በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን፣ እና
   (ለ) የሥር ፍርድ ቤት ፍርድ ፣ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ቢፈጽም የማይተካ ጉዳት ይደርሳል ብሎ ሲያምን፣

   የዕግድ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 438 <u>ግልባጭ ወይም መረጃ ማግኘት</u>

1. በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ወይም የወንጀል ተጎጂ መዝገቡ ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውም ሰነድ በማንኛውም ጊዜ ግልባጭ ማግኘት ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ተከራካሪ ወገን ወይም የወንጀል ተጎጂ የሚጠይቀውን ግልባጭ ወይም ሌላ መረጃ ወድያውኑ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 439 <u>የይግባኝ ማመልከቻ ይዘት</u>

1. ማንኛውም የይግባኝ ማመልከቻ፣
   (ሀ) የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ስምና አድራሻ፣
   (ለ) የይግባኝ ባይ ስምና አድራሻ፣
   (ሐ) የመልስ ሰጪ ስምና አድራሻ፣

(መ) ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት ስምና አድራሻ እንዲሁም የመዝገቡ ቁጥር፣

(ሠ) ቀንና ዓመተ ምኅረት፣ የይግባኝ ባይ ወይም የጠበቃው ፊርማ፣

(ረ) ይግባኝ የተባለበት የወንጀል ጉዳይ፣

(ሰ) ይግባኝ ባይ ቅር የተሰኘበትና ስሕተት ነው ብሎ ያመነበት የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ጉዳይ፣

(ሸ) የሚጠይቀውን ዳኝነት፣

ባካተተ እና አጭርና ግልጽ በሆነ መልክ መቅረብ አለበት፡፡

2. ይግባኝ ማመልከቻ ከዚህ ሕግ ጋር በተያያዘ ቅጽ መሠረት መቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 440 የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ

1. ማንኛውም በፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ይግባኝ ማለት ሲፈልግ የይግባኝ መጠየቂ ማመልከቻ ፍርዱን፣ ውሳኔን ወይም ትዕዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት በጽሑፍ ወይም በቃል ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም የፍርዱን፣ ውሳኔውን ወይም ትዕዛዙን ግልባጭ ወዲያውኑ መስጠት አለበት፡፡
2. ይግባኝ ማመልከቻ ፍርዱ፣ ውሳኔው ወይም ትእዛዝ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰላሳ ተከታታይ ቀናት ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ጊዜ የፍርድ፣ የውሳኔ ወይም የትእዛዝ ግልባጭ ለመስጠት የወሰደውን ጊዜ አይጨምርም፡፡

## አንቀጽ 441 የይግባኝ አላላክ

ይግባኝ ባይ ይግባኙን በአካል ወይም በድረ-ገጽ አድራሻ፣ ማረሚያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ በጠበቃው ወይም በማረሚያ ቤቱ በኩል ወይም በሌላ አመቺ መንገድ ማቅረብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 442 ሬጅስትራር የሚያከናውነው ተግባር

1. በዚህ ሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ሬጅስትራር፡-

(ሀ) የይግባኝ ማመልከቻው ወይም ማስፈቀጃው በዚህ ሕግ አንቀጽ 435 የተዘረዘሩ ነጥቦችን ማሟላቱን፣

(ለ) የሥር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ መያያዙን ወይም ከዳታ ቤዝ መቅረቡን፣

በማረጋገጥ መዝገብ ከፍቶ ለችሎት ያቀርባል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ ይግባኙን የማየት ሥልጣን የሌለው እንደሆነ የይግባኝ ማመልከቻውን የማይቀበል መሆኑን ሬጅስትራሩ ለይግባኝ ባዩ በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡
3. ይግባኝ ባይ ሬጅስትራሩ በሰጠው ውሳኔ የማይስማማ እንደሆነ ቅሬታውን ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንቱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ፕሬዘዳንቱም ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ ይግባኙን ለማየት ሥልጣን ያለው እንደሆነ ሬጅስትራር፣
   (ሀ) መዝገቡን ለችሎት ያቀርባል፣
   (ለ) መዝገቡ የቀረበበት ችሎት፣ በችሎቱ የተሰጠውን ቀጠሮ እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ለይግባኝ ባይ ይነግራል፡፡

## አንቀጽ 443 <u>ጊዜ ያለፈበት የይግባኝ ጥያቄ</u>

1. ይግባኝ ባይ በዚህ ሕግ አንቀጽ 436 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ጊዜ ያለፈበት እንደሆነ ይግባኝ እንዲፈቀድለት ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጥያቄውን ከይግባኝ ማመልከቻው ጋር አያይዞ በጽሑፍ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. የይግባኝ ማስፈቀጃ በዚህ ሕግ አንቀጽ 435 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተ ዝርዝርን የያዘ ሆኖ ይግባኙ የዘገየበትንና ነገሩ በይግባኝ የሚሰማበትን ምክንያት በግልጽ የሚያስረዳ መሆን አለበት፡፡
3. ሬጅስትራር በዚህ አንቀጽ 435 በተደነገገው መሠረት የይግባኝ ጥያቄው ተሞልቶ መቅረቡን በማረጋገጥ መዝገብ በመክፈት ለችሎት ያቀርባል፤ ይህንኑ ለይግባኝ ባይ ይነግራል፡፡
4. ችሎቱ መዝገቡን በዚህ ሕግ አንቀጽ 438 በተደነገገው መሠረት መርምሮ ወድያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 444 <u>በማስፈቀጃ ጥያቄ የሚሰጥ ውሳኔ</u>

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት፡-

1. ይግባኝ ባይ ወይም ወኪሉ መቅረቡን ካረጋገጠ በኋላ ማመልከቻውን በመመርመር አመልካቹ ይግባኙን በጊዜው ያላቀረበበት በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን ያቀረበው ማስረጃ የሚያረጋግጥ እንደሆነ ሌላውን ወገን መጥራት ሳያስፈልግ ይግባኝ እንዲቀርብ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይግባኝ ከመፍቀዱ በፊት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የመልስ ሰጪውን አስተያየት ሊቀበል ይችላል፡፡

3. ይግባኝ ጊዜው ሊያልፍ የቻለው በበቂ ምክንያት አለመሆኑን ከተረዳ የማስፈቀጃ ጥያቄውን ውድቅ ያደርገዋል፡፡ ሆኖም ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ ከበድ ያለ የፍትሕ መዛባት የሚፈጥር እንደሆነ ይግባኙን እንዲሰማ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (4) የተደነገገው ቢኖርም ከአንድ ዓመት በላይ ጊዜ ያለፈበት የይግባኝ ጥያቄ በማንኛውም ምክንያት እንዲሰማ መፍቀድ የለበትም፡፡

**አንቀጽ 445** <u>**የይግባኝ ቅሬታ መመርመር**</u>

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት፡-

(1) የቀረበው ይግባኝ በዚህ ሕግ መሠረት የተሟላ መሆኑን፣ ይግባኙን ለማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤ ሥልጣን ከሌላው ውሳኔውንና መዝገቡን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ያስተላልፋል፣ይህንኑ ይግባኝ ባይ ያሳውቃል፡፡

(2) ይግባኙን ለማየት ሥልጣን ካለው ይግባኝ ባዩ መቅረቡን ያረጋግጣል፣ ይግባኝ ባዩ ያልቀረበ እንደሆነ ውሳኔውና የይግባኝ ማመልከቻውን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ ይግባኝ ባዩ ሳይቀርብና ሳይሰማ ውሳኔ መስጠት የማይቻል እንደሆነ ይግባኙን ሰርዞ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

(3) መዝገቡ እንደቀረበ ወይም በቀጠሮ ቀን ይግባኝ ባይ ወይም ወኪሉ ከቀረበ ይግባኙን ይሰማል፣ መዝገቡን መርምሮ በነገሩ ውስጥ የሚያስገባ በቂ ምክንያት ከሌለ መልስ ሰጪን መጥራት ሳያስፈልግ ይግባኙን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ይዘጋል፣ ይግባኝ ባዩን ያሰናብታል፡፡

(4) በነገሩ ውስጥ የሚያስገባ በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያረጋግጥ፣

(ሀ) በነገሩ የሚያስገቡ ነጥቦች በመለየት መልስ ሰጪ በሙሉ ወይም በከፊል መልስ እንዲሰጥበት፣ እና

(ለ) የቀጠሮ ቀንና ሰዓት በመወሰን መልስ ሰጪ መልሱን እንዲያቀርብ፣ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 446** <u>**መጥሪያ**</u>

1. በዚህ ሕግ ስለ መጥሪያ በአንቀጽ ………… የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይግባኝ ባይ ወይም መልስ ሰጪ በማረሚያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ መጥሪያው በፍርድ ቤት፣ በዐቃቤ ሕግ ወይም በፖሊስ አማካኝነት በማረሚያ ቤቱ በኩል ሊደርሰው ይችላል፡፡

2. ይግባኝ ባዩ ለመልስ ሰጪው መጥሪያ የማድረስ ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 447** ***ይግባኙን መስማት***

1. ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይና መልስ ሰጪ በቀጠሮ ቀን መቅረባቸውን በማረጋገጥ፡-
   (ሀ) ሁለቱም ከቀረቡ ይግባኙን ይሰማል፣ እንደነገሩ ሁኔታ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
   (ለ) ይግባኝ ባይ ቀርቦ መልስ ሰጪ ካልቀረበ ያልቀረበው መጥሪያ ሳይደርሰው ቀርቶ እንደሆነ በድጋሚ መጥሪያ እንዲደርሰው ያደርጋል፣ መጥሪያ ደርሶት ካልቀረበ እንደሆነ ጉዳዩን በሌለበት ይሰማል፡፡
   (ሐ) መልስ ሰጪ ቀርቦ ይግባኝ ባይ ካልቀረበ መዝገቡን መርምሮ የመልስ ሰጪን መልስ ይሰማል፣ መልስ ሰጪ ይግባኙን ያልተቃወመው እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
   (መ) መልስ ሰጪ ቀርቦ ይግባኝ ባይ ካልቀረበ፣ መልስ ሰጪ ይግባኙን ከተቃወመው እና የይግባኝ የቃል ክርክር አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው መዝገቡን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የይግባኝ ባይ የቃል ክርክር ሳይሰማ ውሳኔ መስጠት የማይቻል እንደሆነ መዝገቡን ይዘጋል፡፡
   (ሠ) ይግባኝ ባይና መልስ ሰጪ ካልቀረቡ መዝገቡን ይዘጋል፡፡
2. ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይና መልስ ሰጪ በቀጠሮ ቀን መቅረባቸውን ካረጋገጠ ይግባኝ ባይ በቅድሚያ ይግባኙን እንዲያስረዳ እና መልስ ሰጭም ለቀረበው ይግባኝ መልስ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ይግባኝ ባይ የመልስ መልስ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 448** ***የተዘጋ መዝገብ መክፈት***

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ ..............ንዑስ አንቀጽ.........በተደነገገው መሠረት መዝገቡ የተዘጋበት ይግባኝ ባይ መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ውስጥ ይግባኝ ክርክሩ እንዲሰማለት ፍርድ ቤቱን ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ባይ በቀጠሮው ቀን ያልቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑን ካረጋገጠ መዝገቡ ተከፍቶ ይግባኙ እንዲሰማ እና ይግባኝ የሚሰማበትን ቀን በመወሰን መልስ ሰጪ እንዲጠራ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 449 <u>ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል</u>**

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ አስፈላጊ መሆኑን ካመነ ማስረጃው የሚቀርብበትን ምክንያቱን በመግለጽ ማስረጃው እንዲሰማ ወይም ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 450 <u>ውሳኔ መስጠት</u>**

1. ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ክርክሩን ከሰማ በኋላ

(ሀ) አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ በመሻር፣ በማጽናት ወይም በማሻሻል፣

(ለ) ይግባኙ የቀረበው በፍርደኛው ቢሆንም ቅጣቱን ከፍ በማድረግ ወይም በመለወጥ፣

(ሐ) ይግባኝ የቀረበው በዐቃቤ ሕግ ወይም በግል ከሳሽ ቢሆንም ቅጣቱን ዝቅ በማድረግ ወይም በማሻሻል ወይም በመለወጥ

ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ፣

(ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በመመሥረት እንደሆነ፣

(ለ) ተከሳሽ መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት እንደሆነ ፣ወይም

(ሐ) ወደ ሥር ፍርድ ቤት ሊያስመልስ የሚችል ሌላ ምክንያት ላይ ተመሥርቶ እንደሆነ፣

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ቀድሞ ጉዳዩን ወዳየው ፍርድ ቤት ወይም ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ሥር ፍርድ ቤቱ ሌላ ችሎት ተመልሶ እንዲታይ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመቺ ነው ብሎ ካመነ ጉዳዩን መመለስ ሳያስፈልገው እራሱ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4. ይግባኝ በሚሰማበት ጊዜ ፍርደኛው የሞተ እንደሆነ መዝገቡ ይቋረጣል፤ ሆኖም ከመዝገቡ ጋር በተያያዙ የንብረት መወረስ ወይም የካሣ ወይም ፍርደኛው በመሞቱ ሊቋረጡ የማይችሉ ተጨማሪ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤት መዝገቡን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ ይግባኝ ባልጠየቁ በሥር ፍርድ ቤት በአንድነት በተፈረደባቸው ሰዎችም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለሰበር

**አንቀጽ 451 ዓላማ**

የሰበር ዓላማ  መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተትን በማረም፡-

1. በፍርድ ቤቶች ወጥ ወይም ተቀራራቢ የሕግ አተረጓጐምን፣ ርግጠኝነትን ወይም ተገማችነትን፣
2. የሕግ አውጪውን ፍላጐት (ዓላማ) የሕዝብ ጥቅምና ስለጠቅላላው ሥርዐት መጠበቁን፣ እና
3. የሕጋዊነት መርህ መጠበቁን፣

ማረጋገጥ መሆን አለበት፡፡

**አንቀጽ 452 መርህ**

1. ሰበር መሠረታዊ የሕግ ስሕተት በመፈጸም የተሰጠን ውሳኔ ለማረም በጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚኖር ክርክር ሥርዐት ነው፡፡
2. የሰበር  ሥልጣን የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሥልጣን ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ ክፍል በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ለይግባኝ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ለሰበር ጉዳዩችም ተፈጻሚ ይሆናሉ ፡፡

**አንቀጽ 453 የሰበር ማመልከቻ ማቅረብ**

1. የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ወይም ጉዳይ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ተከራካሪ ወገን አቤቱታውን ለሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የሰበር ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት የይግባኝ፣ ፍርድን እንደገና የማየት ሥርዐት ወይም ሌላ ሕጋዊ ሥርዐት መጠናቀቅ ይገባዋል፡፡
3. የሰበር ማመልከቻ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በስልሳ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
4. ጊዜው ካለፈ በኋላ የሚቀርብ የሰበር አቤቱታን ጊዜው ካለፈ በኋላ የሚቀርብ ይግባኝ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 454 <u>በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የሚመራ የሰበር ጉዳይ</u>**

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መሠረታዊ የሕግ ስሕተት መፈጸሙን የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠበት ስድስት ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ በማንኛውም መንገድ ሲረዳ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ያለውን ነጥብ በመለየት ጉዳዩ በሰበር እንዲታይ ሊመራ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 455 <u>መሠረታዊ የሕግ ስሕተት መኖር</u>**

መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚባለው ውሳኔው ወይም ፍርዱ በተለመደው መልኩ ያልተሰጠና በሕግ ሥርዐቱ ላይ መናጋት የሚፈጥር ሆኖ፡-

1. ግልጽ የሆነ የሕገ መንግሥት ወይም የሕግ ድንጋጌን ወይም የሰበር ውሳኔን በመጣስ ፣
2. ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌን በመጣስ የተገኘ ማስረጃን መሠረት በማድረግ፣
3. ግልጽ የሆነ የሥነ ሥርዐት ወይም የማስረጃ ሕግን፣
4. የሕግ መሠረት ሳይኖረው፣
5. በተሻረ፣ በተሳሳተ ወይም አግባብነት በሌለው ሕግን መሠረት በማድረግ፣
6. የተዛባ የሕግ ትርጉምን መሠረት በማድረግ፣
7. ጉዳዩን ዐይቶ ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን ሳይኖረው፣
8. በሕግ ከተሰጠ ሥልጣን ውጭ፣

የተሰጠ እንደሆነ ነው፡፡

**አንቀጽ 456 <u>ሰበር የማይቀርብበት ጉዳይ</u>**

1. የሰበር ማመልከቻ፣

(ሀ) መሠረታዊ ያልሆነ የሕግ ስህተት ባለው ጉዳይ፣

(ለ) የፍሬነገር ስህተት ባለበት ውሳኔ፣

(ሐ) አግባብነት ባለው ሕግ የሚወሰድ ርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በነፃ በተለቀቀበት ጉዳይ ሰብዓዊ መብቴ ተጥሷል በማለት ብቻ በሚቀርብ አቤቱታ፣

(መ) በሰበር ጉዳዮች አጣሪ ችሎት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ለሰበር አያስቀርብም ተብለው ውድቅ በተደረገ ጉዳይ፣

ላይ ሊቀርብ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 457 ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ማገድ

1. ዕግድን በተመለከተ ለይግባኝ በዚህ ሕግ አንቀጽ 433 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር ጥያቄው መነሻ የሆነውን ውሳኔ የሰጠው ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሆነ እግዱ፣

   (ሀ) ጉዳዩ ወደ አጣሪ ችሎት ያልቀረበ እንደሆነ በፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት፣

   (ለ) ጉዳዩ ወደ አጣሪ ችሎት የቀረበ እንደሆነ በአጣሪ ችሎቱ፣ ወይም

   (ሐ) ጉዳዩ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ እንደሆነ ሰበር ችሎቱ፣

   የዕግድ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ የዕግድ ትእዛዝ በፕሬዚዳንቱ ሲሆን ከሰባት ቀን መብለጥ የለበትም፡፡
3. በሰበር አጣሪ ችሎት የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ሰበር ሰሚ ችሎት የተለየ ትእዛዝ ካልሰጠ በስተቀር የጸና ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት በተሰጠ ዕግድ ላይ የዕግድ ይነሳልኝ ጥያቄ የእግዱ ትዕዛዙን ለሰጠው አካል መቅረብ ይችላል፤ ጥያቄውም እንደቀረበ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

## አንቀጽ 458 የሰበር ማመልከቻ ይዘት

1. የሰበር ማመልከቻ የክሱን ይዘትና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎችን፣ ቅር የተሰኘበትን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት እና የሚጠይቀውን ዳኝነት አጭርና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያካተተ መሆን አለበት፡፡ ከማመልከቻው ጋር በየደረጃው የተሰጡ ፍርዶች በአመልካቹ ወይም ከዳታ ቤዝ ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡
2. ማንኛውም የሰበር ማመልከቻ ከዚህ ሕግ ጋር አባሪ ሆኖ በቀረበው ቅጽ መሠረት ይቀርባል፡፡

**አንቀጽ 459** **<u>የሰበር ማመልከቻ መቀበል</u>**

የሰበር ማመልከቻ አቀባበልን በተመለከተ በዚህ ሕግ አንቀጽ 439 የተደነገገው እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 460** **<u>የሰበር ማመልከቻ መመርመር</u>**

1. በዚህ ሕግ መሠረት የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖር የሚያጣራው ሦስት ዳኞች በሚሰየሙበት የሰበር ጉዳዮች አጣሪ ችሎት ይሆናል፡፡

2. የሰበር ጉዳዮች አጣሪ ችሎት አመልካቹን አቅርቦ ማነጋገር አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር ጉዳዩን መርምሮ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የለም ብሎ ካመነ ምክንያቱን በማብራራት አቤቱታውን ውድቅ ያደርጋል፤ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ችሎቱ ይህንኑ ለአመልካቹ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

3. የሰበር ጉዳዮች አጣሪ ችሎት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ይህንኑ በግልጽ ለይቶ በማመልከት ተጠሪው መልስ እንዲሰጥበት ቀጠሮ በመስጠት የሰበር ማመልከቻውን ከመጥሪያው ጋር እንዲደርሰው ያደርጋል፤ መዝገቡም ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ለሚሰየሙበት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀርባል፡፡

4. ፍርድ ቤቱ ስለመጥሪያ አደራረስ እንዳግባብነቱ ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 461** **<u>የሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን</u>**

የሰበር ሰሚ ችሎት፡-

1. የሰበር አጣሪ ችሎት የመራለትን ጉዳይ የተጠሪውን መልስ በቃል ወይም በጽሑፍ ይቀበላል፡፡
2. የአመልካችና የተጠሪን የቃል ክርክር ይሰማል፡፡
3. የሰበር ጉዳዮች አጣሪ ችሎት የለየውን አከራካሪ ነጥብ መሠረት በማድረግ ወይም በመለወጥ ፍርድ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 462 <u>የሰበር ውሳኔ መስጠት</u>**

የሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩን ከሰማ በኋላ ማመልከቻ የቀረበበትን ውሳኔ በመሻር፣ በማጽናት ወይም በማሻሻል ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ችሎቱ አስፈላጊ መሆኑን ካመነ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለሥር ፍርድ ቤቱ ሌላ ችሎት ወይም በሌላ ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን ሊመልሰው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 463 <u>የተከራካሪ አለመቅረብ</u>**

የሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩ በሚሰማበት ቀን ተከራካሪዎች ባይቀርቡም መዝገቡን መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 464 <u>የሰበር ውሳኔ ውጤት</u>**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል በማለት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በራሱ ውሳኔ ወይም በሌላ ሕግ ካልተለወጠ በስተቀር በየትኛውም ደረጃ ለሚገኝ ፍርድ ቤት አስገዳጅነት አለው፡፡

2. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ ስለሚኖረው ውጤት ክልሎች በሚያወጡት ሕግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 465 <u>የክልሎች ሥልጣን</u>**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 428፣ 429፣ 430 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሠ) እና ንዑስ አንቀጽ (2)፣ 431፣ 433 ስለ ይግባኝ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሎች በሰበር ጉዳዮች አጣሪ ችሎት መኖር አለመኖር፣ በሰበር የሚታዩ ጉዳዮች ዐይነት እና የዳኞች ብዛትን በተመለከተ ስለሚመራበት ሥርዐት ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>የመጨረሻ ፍርድን እንደገና ስለማየት</u>

**አንቀጽ 466 <u>ዓላማ</u>**

የመጨረሻ ፍርድን እንደገና የማየት ሒደት ዓላማ በተዛባ ፍርድ ንፁኃን እንዳይቀጡ ፍርድን ማረም ነው፡፡

## አንቀጽ 467 የወንጀል ፍርድ እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ ማመልከቻ

1. ማንኛውም የጥፋተኛነት ፍርድ የተሰጠበት ፍርደኛ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ወንጀል አለመፈጸሙን የሚያሳምን በቂ ማስረጃ በተገኘ ጊዜ ፍርደኛው፣ ወኪሉ፣ ቤተሰቡ ወይም ዐቃቤ ሕግ ፍርዱ እንደገና እንዲታይ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም በቂ ማስረጃ ማለት ማስረጃው ቀደም ብሎ ቢገኝ ኖሮ ፍርዱ በማያጠራጥር ሁኔታ አይሰጥም ነበር የሚያስብል ሆኖ፣
   (ሀ) ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ጥፋተኛውን ነፃ ሊያደርግ የሚችል ጠቃሚ ማስረጃ ከተገኘ፣
   (ለ) ከፍርድ በኋላ በሳይንሳዊ ዘዴ የተገኘ እውነት እንደሆነ፣
   (ሐ) ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ዳኛው ኃላፊነቱን አጓድሏል ተብሎ በወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ፣
   (መ) በጉዳዩ ላይ ሌላ በነፃ የተለቀቀ ሰው ከፍርድ ቤት ውጭ በሚታመን ሁኔታ ወንጀሉን መፈጸሙ ጥፋተኛነቱን በማመን ቃል የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም
   (ሠ) እውነተኛ መስሎ የቀረበ ማስረጃ በሐሰት ወይም በማጭበርበር መዘጋጀቱ ሲረጋገጥ፣

   ፍርዱ እንደገና እንዲታይለት ሊያመለክት ይችላል፡፡
3. ማመልከቻው የሚቀርበው በጉዳዩ ላይ የጥፋተኝነት ፍርድ ለመጨረሻ ጊዜ ለሰጠው ፍርድ ቤት ነው፡፡

## አንቀጽ 468 የማመልከቻው ይዘትና የሚቀርብበት ጊዜ

1. በዚህ ሕግ የመጨረሻ ፍርድ እንዲታይ የሚቀርብ ማመልከቻ የይግባኝ ማመልከቻ በሚቀርበው ዐይነት መሆን አለበት፡፡
2. ፍርዱን እንደገና እንዲታይለት የሚቀርብ ማመልከቻ በማንኛውም ጊዜ ማቅረብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 469** <u>ማልከቻውን መስማት እና መወሰን</u>

1. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን አቤቱታና ማስረጃዎች መርምሮ ፍርዱን እንደገና ለማየት በቂ ካልሆነ አቤቱታውን ውድቅ ያደርጋል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የቀረበው አቤቱታ እንደገና ለማየት በቂ መስሎ ከታየው ተከራካሪዎች መልስ ወይም አስተያየት እንዲሰጡበት ቀጠሮ በመስጠት ያሳውቃል፡፡
3. የተከራካሪዎች መልስና ማስረጃዎች መርምሮ የመሰለውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን እንደገና ለማየት ከወሰነ እንደአግባብነቱ የተሰጠ ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በማንሳት ጉዳዩ እንደገና እንዲሰማ ቀድሞ ጉዳዩን ወዳየው ፍርድ ቤት፣ ወደ ሌላ ፍርድ ቤት፣ ወደ ሥር ፍርድ ቤቱ ሌላ ችሎት ተመልሶ እንዲታይ ወይም በራሱ ለመወሰን ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 470** <u>ካሣ</u>

1. ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ የተሰጠውን ውሳኔ የሻረ ወይም ያሻሻለ እንደሆነ ቅጣቱን ባስከተለው ውሳኔ ምክንያት አመልካቹ ለደረሰባቸው የሞራልና የንብረት ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ ከመንግሥት እንዲከፈል ያዛል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ የሞት ቅጣት በመሆኑ ተጎጂው በሕይወት የሌለ እንደሆነ ለተጎጂ ሊከፈል ከሚገባው ካሣ በተጨማሪ ቅጣቱን ባስከተለው ውሳኔ ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት የትዳር ጓደኛ ወይም ወራሽ የሞራል እና የንብረት ጉዳት ካሣ ከመንግሥት እንዲከፈል ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ተጎጂ፣ የትዳር ጓደኛው ወይም ወራሾቹ ለደረሰባቸው ጉዳት ይቅርታ ይጠይቃል፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ዝርዝር በደንብ ይወሰናል፡፡ ደንቡ እስኪወጣ ድረስ ሌላ አግባብ ያለው ሕግ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ሦስተኛ መጽሐፍ
# ልዩ ሥነ ሥርዐት
# ምዕራፍ አንድ
# በወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶች የክስ ሥነ ሥርዐት

**አንቀጽ 471 ተፈፃሚነት**

1. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ዕድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ አሥራ አምስት ዓመት የሞላቸው ወንጀል ያደረጉ ወጣቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፡-

   (ሀ) በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘን ወጣት ምርመራ በሚጀምርበት ጊዜ ከአሥራ አምስት እስከ አሥራ ስምንት ዓመት የሆነው እንደሆነ፤

   (ለ) በምርመራው ወይም ክስ መስማት ሒደት ጊዜ ከአሥራ አምስት እስከ አሥራ ስምንት ዓመት የሆነው እንደሆነ፣

   እንደነገሩ ሁኔታ አካለ መጠን እንደደረሰ ተቆጥሮ የምርመራ፣ የክስና የክርክር ሒደቱ በዚህ ሕግ በተመለከቱ መደበኛ ድንጋጌዎች ሊቀጥል ይችላል፡፡
3. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ እንደሆነ የምርመራ፣ የክስና የክርክር ሒደቱ በዚህ ሕግ በተመለከቱ መደበኛ ድንጋጌዎች እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡
4. በዚህ ክፍል የተመለከቱ ድንጋጌዎችን እስካልተቃረኑና በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን ጥቅምና ደኅንነት እስከጠበቁ ድረስ የዚህ ሕግ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው በተገኙ ወጣቶች በሚቀርብ የወንጀል ክስ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
5. የጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ነገር ገብተው የተገኙ ወጣቶች የወንጀል ክስ አመራርን የሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 472 መርህ**

1. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ምርመራ፣ ክስ መስማት፣ የፍርድ ሒደትና ውሳኔ በተፋጠነና መደበኛ ባልሆነ ሥነ ሥርዐት መመራት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከናወን ሥነ ሥርዐት፡-

   (ሀ) በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ጥቅምና ደኅንነት ማስከበርና ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡

   (ለ) ወጣቱን የማያገል፣ የሚያሳትፍ፣ ምቹና የማያስፈራ መሆን አለበት፡፡

(ሐ) የወጣቱን ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ሁኔታውን ግምት ውስጥ ያስገባና በማኅበራዊ፣ በሥነ-ልቦናና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ባለሙያዎች መታገዝ አለበት፡፡

## አንቀጽ 473 የምርመራ አጀማመርና የክስ አመሠራረት

1. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ በተገኘ ጊዜ መርማሪው፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ወላጁ፣ ሞግዚቱ፣ ወይም አሳዳሪው በቅርብ ወደሚገኘው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይዞት መቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ ሲቀርብለት ወይም በራሱ ሲያውቅ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘው ወጣት፡-
   (ሀ) የተጠረጠረበት ጉዳይ ወንጀል ካልሆነ፤
   (ለ) ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ዕድሜው ዘጠኝ ዓመት ያልሞላው እንደሆነ፤
   (ሐ) በወንጀሉ ከዚህ ቀደም ተከሶ ነፃ የወጣ ወይም የጥፋተኛነት ውሳኔ የተሰጠበት ወይም በፍርድ ቤት ጉዳዩ እየታየ ከሆነ ወይም በሌላ አማራጭ መፍትሔ ርምጃ ያገኘ እንደሆነ
   (መ) የፈጸመው ወንጀል በይርጋ የታገደ እንደሆነ
   ጉዳዩን ይዘጋዋል፡፡
3. ፍርድ ቤት በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን ያመጣ ሰው የወንጀሉንና የማስረጃውን ዝርዝር እንዲገልጽ ያደርጋል፤ የቀረበውን አቤቱታ እና የሚሰጠውን ቃል በመዝገብ ይጽፋል፡፡
4. ፍርድ ቤቱም የቀረበውን አቤቱታና ቃል መርምሮ በወጣቱ ላይ ምርመራ እንዲደረግ ወይም የተጀመረ ምርመራ እንዲቀጥል ከወሰነ ምርመራው የሚፈጸምበትን ዝርዝር ሁኔታ ላይ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚፈፀመው እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ለምርመራ ወይም ምርመራውን ጨርሶ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ለማቅረብ የወሰነ እንደሆነ ወላጁ፣ ሞግዚቱ፣ ወይም አሳዳሪው እና አቤት ባዩአብረው እንዲቀርቡ ተገቢውን ይፈጽማል፡፡
6. ትእዛዝጉዳዩ መቀጠር ወይም ሥልጣኑ ለሚፈቅድለት ሌላ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚያስፈልገው እንደሆነ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ነገሩ በሚሰማበት ቀን ለማቅረብ ለሚችሉ ለወላጆቹ፣ ለአሳዳጊው፣ ለዘመዶቹ፣ ለመንግሥታዊ ተቋም ወይም ሌላ ድርጅት ወይም እራሱን ለቻለ እምነት

ለሚጣልበት ሰው እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ምስክሮች ነገሩ በሚሰማበት ቀን ሊቀርቡ ግዴታ መግባት አለባቸው፡፡

7. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ትእዛዝ ሲሰጥ፣

(ሀ) ተመልሶ ከሌሎች ወንጀል ፈፃሚዎች ጋር ሊቀላቀል አለመቻሉን፣

(ለ) ለሞራላዊ፣ አካላዊ ወይም ሥነ-ልቦናዊ አደጋ የማያጋልጥ መሆኑ፣ እና

(ሐ) ፈጸመ የተባለውን ወንጀል ክብደት እና ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የማያደናቅፍ

መሆኑ ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 474 ምርመራው የሚያካትታቸው ተጨማሪ ሁኔታዎች

1. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን በተመለከተ የሚካሔድ ምርመራ

(ሀ) የወጣቱን ባሕርይ፣

(ለ) የግል ኑሮውን፣ ያደገበትንና የኖረበትን አካባቢ ሁኔታ፣

(ሐ) የተከሰሰበትን ወንጀል ፈፀመ ከተባለበት ጊዜ በፊትና በኋላ የነበረውን ጠባይ፣እና

(መ) ሌሎች ለእርምትና ለትምህርታዊ ርምጃዎች አወሳሰድ መሠረት

የሚሆኑ ሁኔታዎች ለማጣራት የሚረዳ መሆን አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመከቱትን ሁኔታዎች በትክክል ለማረጋገጥ እንደነገሩ ሁኔታ መርማሪው፣ ዐቃቤ ሕጉወይም ፍርድ ቤቱ የወጣቱን ወላጆች፣ አሳዳሪ፣ ቤተዘመድና እንዲሁም በቂ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች ሰዎችን ወይም ተቋማትን ጠርቶ መጠየቅ፣ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች መመልከትና እንደአስፈላጊነቱ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 475 ቤተዘመድ ወይም አሳዳጊ መጥራት

በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ወደ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ወላጆቹ፣ አሳዳጊው፣ ወይም ከቤተ ዘመዶቹ አንዱን ሰው እንዲሁም ዕጓለ ማውታን ወይም

የተቋም ተወካይ ባልቀረቡ ጊዜ ፍርድ ቤቱ እነዚህ ሰዎች እንዳሉ ጠይቆ እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 476** __በጠበቃ መወከል__

በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት በየትኛውም ደረጃ በመረጠው ጠበቃ የመወከል መብት አለው፡፡ ወጣቱ እራሱ ጠበቃ ለመወከል አቅም የሌለው እንደሆነ በመንግሥት ወጪ ጠበቃ ይመድብለታል፡፡

**አንቀጽ 477** __በማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት ማቆየት__

1. ፍርድ ቤቱ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት በማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት የለበትም፡፡
2. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት በዚህ ሕግ አንቀጽ 503 (__ጊዜያዊ ትእዛዝ)__ ንዑስ አንቀጽ (3)_ሰዎች ማቆየት ካልተቻለ እና፡-

   (ሀ) ወጣቱ በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ስለመሆኑ ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው እና በማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት መቆየቱ ሊደርስበት ከሚችል አደጋ የሚጠብቀው እንደሆነ፣

   (ለ) ወጣቱ ከወላጅ፣ ከሞግዚቱ ወይም ከሌሎች ቤተ ዘመዶቹ እንደሚያመልጥ ለማመን በቂ ምክንያት ያለ እንደሆነ፣ ወይም

   (ሐ) ክሱ በመሰማት ላይ እያለ ወጣቱ ከሃገር የሚወጣ ስለመሆኑና ተመልሶ እንደማይቀርብ ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖር

   በማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት ሊቆይ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ ለተገኘ ወጣት በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት ሊቆይ የሚችለው በተለየ ቦታ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 478** __የተቋም ክትትል__

ፍርድ ቤቱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የአቤቱታውን ወይም የክስ ማመልከቻውን እና ሌሎች ተገቢ ሰነዶችን በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን ደኅንነት መጠበቅ ለሚችል ተቋም በመላክ ጉዳዩን እንዲከታተል ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 479** <u>ክስ መመሥረት</u>

1. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ በተገኘ ወጣት ላይ የቀረበ ክስ አሥር ዓመት ወይም በዕድሜ ልክ ወይም በሞት የሚያስቀጣ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ክሱን በጽሑፍ ማቅረብ አለበት፡፡

2. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ በተገኘ ወጣት ላይ የሚቀርብ የወንጀል ክስ አካለ መጠን ከደረሰ ሰው ክስ ጋር አብሮ መታየት የለበትም፡፡ ክሱ በአንድ ላይ የቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ክሱ ተለይቶ እንዲቀርብ እና ተነጥሎ እንዲሰማ ማዘዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 480** <u>ጊዜያዊ ትእዛዝ</u>

1. ክሱ በሒደት እያለ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ወላጁ፣ ሞግዚቱ፣ አሳዳሪው ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ከወጣቱ ጋር ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ፍርድ ቤቱ ጊዜያዊ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. የወንጀል ድርጊቱን ሪፖርት ያደረገው ሰው በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘውን ወጣት በተመለከተ ፍርድ ቤት፡-
   (ሀ) በተወሰነ ሰው ወይም ተቋም ጊዜያዊ ጥበቃ ሥር እንዲሆን፣
   (ለ) ለመንብኙት መብት ባላቸው ሰዎች ላይ ገደብ እንዲጣል፣
   (ሐ) ለጤናው፣ ለምግቡና ለመልካም አያያዙ አስፈላጊ የሆነ ወጪ እንዲመደብ፣
   (መ) በሚኖርበት ቤት ወይም ቦታ ያለ ሰው ለቆ እንዲሔድ፣
   (ሠ) ወላጁ፣ አሳዳሪው፣ ጠባቂ ወይም ሌላ ግንኙነት ያለው ሰው አስፈላጊውን ምክር እንዲያገኝ፣ ወይም
   (ረ) ማንኛውም ከጥቅሙ ጋር ተቃራኒ የሆነ ድርጊት እንዲቆም

   ፍርድ ቤት ጊዜያዊ ትእዛዝ እንዲሰጥለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ጥቅም አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የወጣቱን አስተያየት በመቀበል የከሳሽና የተነጂ መገኘት ሳይጠብቅ ጊዜያዊ ትእዛዙን ወዲያውኑ መስጠት አለበት፡፡
4. ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ጊዜያዊ ትእዛዝ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በሌላ ሰው አመልካችነት እንደገና መርምሮ ሊያሻሽለው ወይም ሊለውጠው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 481** **ክስን ወደ ሌላ ሥፍራ ማዛወር**

በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ ለተገኘ ወጣት የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ወዳለው ሌላ ፍርድ ቤት ክሱን ሊያዛውረው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 482** **መጥራት**

1. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የሚጠራው በወላጆቹ፣ በአሳዳሪው፣ በሞግዚቱ ወይም አደራ በተቀበለው ሌላ ሰው ወይም ተቋም መሆን አለበት፡፡
2. በጥበቃ ሥር ያለ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት የሚጠራው በጥበቃው አስተዳደር በኩል ይሆናል፡፡
3. ዐቃቤ ሕግ ክስ በመሠረተ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ክስ በሚሰማበት ቀን እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 483** **ክሱ የሚሰማበት ሁኔታ**

1. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ክሱ የሚሰማው በዝግ ችሎት ነው፤ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ከምስክር፣ ከልዩ አዋቂ፣ ከወላጅ፣ ከሞግዚት ወይም ከሚመለከተው ተቋም ባልደረባ በስተቀር ማንም ሰው መገኘት የለበትም፤ በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመሠረተ እንደሆነ ዐቃቤ ሕጉ መገኘት አለበት፡፡
2. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት የተከሰሰበትን ነገር የሚሰማው ችሎት በሌላ ነገር ተሰይሞ ከሚያነጋግረው አኳኋንና ሁኔታ የተለየ ይሆናል፡፡
3. በዚህ ሕግ አንቀጽ 495 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረበ ክስ ወይም አቤቱታ ወይም በአንቀጽ 495 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የቀረበው ክስ ወይም አቤቱታ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ ለተገኘው ወጣት ከተነበበለት በኋላ ለክሱ ወይም ለአቤቱታው የሚሰጠው መልስ እንዳለው ይጠየቃል፡፡
4. ተከሳሹ በሚሰጠው መልስ የቀረበበትን ክስ ወይም አቤቱታ በሙሉ ዐውቆ ያመነ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ለፍርድ ቤቱ በታየው ጊዜ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት የሰጠውን መልስ በመዝገብ ጽፎ ወዲያውኑ የጥፋተኛነት ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡
5. ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል በሙሉ ከተረዳው በኋላ ክሱን ወይም አቤቱታውን ያላመነ እንደሆነ ለቀረበው ክስ ወይም አቤቱታ ለመመስከር

የሚጠሩትን ምስክሮች ፍርድ ቤቱ ይጠይቃል፡፡ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ወይም እንደራሴው ወይም ጠበቃው ማንኛውም ምስክር እንዲጠራለት ማድረግ ይችላል፡፡

6. ምስክሮቹን ሁሉ ፍርድ ቤቱ በጥያቄ ከመረመረ በኋላ የተከሳሹ ወገን መስቀልያ ጥያቄ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የሚሰጠው ቃል ሁሉ በመዝገብ ይጻፋል፡፡
7. ማንኛውም የመገናኛ ብዙኃን በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘውን ወጣት የምርመራ ወይም የክስ ሒደትም ሆነ ፍርድ ሊዘግብ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘውን ወጣት ስም፣ አድራሻ፣ ትምህርት ቤት ወይም ማንነት የሚያመለክት ሆኖ ሊቀርብ ወይም ፎቶ ግራፉን ወይም ምስሉን ይዞ መውጣት የለበትም፡፡
8. ማስረጃ ተሰምቶ ካለቀና የተከሳሹ ወገን ስለነገሩ ጠቅላላ ንግግር ካደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ፍርድ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 484** <u>ፍርዱ</u>

1. ፍርዱ በየትኛው ሕግ መሠረት እንደተሰጠ በፍርዱ ውስጥ ይጠቀሳል፡፡ ፍርዱ በዚህ ሕግ የተመለከቱ ዝርዝሮችን የሚይዝ ሆኖ የወጣቱን ዕድሜ፣ ስብእናው፣ የወደፊቱን እና አጠቃላይ ሁኔታውን በማይጎዳ መልኩ መዘርዘር አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ 500 ንዑስ አንቀጽ (2)(ሐ) መሠረት በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘው ወጣት ግልጽና በቂ በሆነ መልኩ ወንጀል መፈፀሙን በማስረጃ ማረጋገጥ ካልተቻለ በነፃ የመልቀቅ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ ሕግ አንቀጽ 500 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) መሠረት ፍርድ ቤቱ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በወንጀል ሕግ ከአንቀጽ 157 ጀምሮ የተመለከቱ የጥንቃቄ ርምጃዎችን ወይም ቅጣትን ይወስናል፡፡
4. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘው ወጣት የሚጠቅም ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችለው ስለወጣቱ ጠባይና ስለቀድሞ ጥፋቱ ለመጠየቅ ከማንኛውም ድርጅት ማንኛውም ሰው ወይም እንደራሴ ፍርድ ቤቱ መጥራት ይችላል፡፡
5. እነዚህ ሰዎች የሚሰጡት ቃል ከተሰማ በኋላ የተከሳሹ ወገን መልስ መስጠትና ስለ ጠባዩ ምስክሮች መጥራት ይችላል፡፡ እነዚህንም ምስክሮች ፍርድ ቤቱ ከጠየቀ በኋላ የተከሳሹ ወገን ስለ ቅጣቱ በቃል ሊያመለክት ይችላል፡፡

6. ፍርድ የሚሰጠው እንደ ማንኛውም ደንበኛ ክስ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘው ወጣት ካስረዳው በኋላ ለወደፊቱ ጠባዩን እንዲያርም ያስጠነቅቀዋል፡፡

## አንቀጽ 485 <u>ሌሎች ሰዎች ላይ የሚሰጥ ትእዛዝ</u>

1. ፍርድ ቤቱ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ወላጅ፣ ሞግዚት፣ አሳዳሪ ወይም ኃላፊነት የተሰጠው ሌላ ሰው ተግባሩን በሚገባ ያልፈፀመ መሆኑን ካመነ በሌሎች ሕጎች የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማስጠንቀቂያ እና እርምት መስጠት ወይም መውቀስ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤት በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘውን ወጣት በሚገባ ባለመጠበቁና ባለመያዙ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ወጣቱን በሌላ ሰው እጅ እንዲያድግ ወይም ወደሚታረምበት ወይም ወደሚሻሻልበት ተቋም የሚልከው እንደሆነ ለእድገቱና ለኑሮው የሚደረገውን ወጪ በሙሉ ወይም በከፊል ወላጅ፣ ሞግዚት፣ አሳዳሪ ወይም ኃላፊነት የተሰጠው ሌላ ሰው እንዲከፍል ማዘዝ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚጣለውን ግዴታ ልክና የሚቆይበትን ጊዜ በውሳኔው ውስጥ መመልከት አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) በተመለከተው መሠረት በተሰጠ ትእዛዝ እና ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 486 <u>ትእዛዝ ወይም ውሳኔ መለወጥ ወይም ማሻሻል</u>

1. ስለ ይግባኝ፣ ሰበርና ፍርድን እንደገና ስለማየት በዚህ ሕግ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ በተገኘ ወጣት ላይ ትእዛዝ የሰጠ ማንኛውም ፍርድ ቤት በራሱ አስተያየት ወይም ወጣቱ፣ በጠበቃው፣ በዐቃቤ ሕጉ፣ በወላጅ፣ በሞግዚቱ፣ በአሳዳሪው፣ ኃላፊ በሆነለት ሌላ ወይም አደራ በተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት አመልካችነት ቀደም ሲል የሰጠውን ትእዛዝ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፍርድ ቤቱ ትእዛዙን ሲሰጥ ለወጣቱ ጥቅም አስፈላጊ መሆኑን ማረጋገጥ እና ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው፣ ባለሙያ ወይም ድርጅት የሚያቀርበውን አስተያየት መቀበል አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## ደንብ መተላለፍ ስለ ሚመራበት ሥነ ሥርዐት

**አንቀጽ 487 የደንብ መተላለፍ ሥነ ሥርዐት**

1. ደንብ መተላለፍን የሚመለከቱ ጉዳዮች በዚህ ክፍል ወይም ክልሎች በሚወስኑት ሕግ መሠረት ይመራል፡፡
2. በዚህ ክፍል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ክፍል ባልተሸፈ ጉዳይ ላይ የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት አላቸው፡፡
3. የደንብ መተላለፍን የሚመለከቱ በልዩ ሕጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

**አንቀጽ 488 ደንብ የተላለፈው እንዲጠራ የሚቀርብ ማመልከቻ**

1. የደንብ መተላለፍ በተፈጸመ ጊዜ ደንብ የተላለፈው እንዲጣራ ፍርድ ቤቱ መጥሪያ እንዲሰጥ ከሳሹ ያመለክታል፡፡
2. በማመልከቻው የደንብ ተላላፊውን ስም፣ የደንብ መተላለፍ የተፈጸመበትን ሁኔታ፣ ክስ የቀረበበት ሕግና የሕጉን አንቀጽ እንዲሁም ሌሎች ለክሱ አስፈላጊ ጉዳዮችን መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 489 መጥሪያ መላክ**

1. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ በዚህ ክፍል በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት መመራት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ካረጋገጠ ለተከሳሹ መጥሪያ ይልካል፡፡
2. መጥሪያው፡-
   (ሀ) ተከሳሹ ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ቦታ፣ ቀን፣ሰዓት፣ እራሱ መቅረብ ወይም ወኪሉን መላክ እንደሚችል፣
   (ለ) ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ ካመነ ፍርድ ቤት መቅረብ ሳያስፈልገው ማመኑን በጽሑፍ ለፍርድ ቤቱ ከቀጠሮ በፊት መግለጽ ወይም፣በወኪሉ መላክ የሚችል መሆኑንና የደንብ መተላለፍ ሊያስከትልበት የሚችለውን ከፍተኛ ቅጣት መጠን፣
   (ሐ) መጥሪያው የደረሰው መሆኑን ለማረጋገጥ በተላከለት መጥሪያ ላይ መፈረም ያለበት መሆኑን ሊያመለክት ይገባል፤

መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 490** <u>ፍርድ ቤት ሳይቀረብ ክስን ማመን</u>

1. ደንብ ተላላፊው የቀረበበትን ክስ ካመነ ፍርድ ቤት መቅረብ ሳያስፈልገው ማመኑን በጽሑፍ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡
2. ጥፋተኝነቱን የሚገለፀው ጽሑፍ የደንብ ተላላፊውን ስም እና ፊርማ መያዝ አለበት፤ በመጥሪያው የተመለከውን መቀጮ በፖስታ፣ በመልእክተኛ ወይም በሌላ ተገቢ መንገድ መላክ ይቻላል፡፡
3. በዚህ ሕግ አንቀጽ 508 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ደንብ ተላላፊው ፍርድ ቤት መቅረቡ አስፈላጊነቱ ሊቀር ይችላል፡፡

**አንቀጽ 491** <u>ሥነ ሥርዐትና ውሳኔ</u>

1. ተከሳሹ ጥፋቱን ያመነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ፣

    (ሀ) የገንዘብ መቀጮ ቅጣት ብቻ የሚፈርድ እንደሆነ ውሳኔው ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡ የውሳኔውንም ግልባጭ ለደንብ ተላላፊው ይልካል፡፡

    (ለ) ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በማረፊያ ቤት እንዲታሰር፣የግዴታ ሥራ እንዲሠራ ወይም ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ወይም እንዲወቀስ ሲፈልግ ተከሳሹ እንዲቀርብ በማድረግ ስለቅጣቱ ፣አስተያየቱን ይጠይቀዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) በተደነገገው መሠረት ደንብ ተላላፊው የገንዘብ መቀጮ የተወሰነበት ሆኖ የመቀጮውን ገንዘብ አስቀድሞ የላከ እንደሆነ እና ፍርድ ቤቱ የወሰነው መቀጮ በመጥሪያ ላይ ከተገለጸው የገንዘብ መጠን የበዛ ወይም ያነሰ እንደሆነ ልዩነቱን ለደንብ ተላላፊው ተመላሽ እንዲሆን ወይም ተጨማሪ ልዩነቱ እንዲከፍል ያዛል፡፡

**አንቀጽ 492** <u>ክሱ በተካሔደ ጊዜ የሚኖር ሥነ ሥርዐት</u>

1. ተከሳሹ መጥሪያው ላይ ጥፋተኝነቱን በማመን ያልፃፈ እንደሆነ ነገሩ እንዲሰማ በተቀጠረው ቀንና ሰዓት ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡
2. ዐቃቤ ሕግ፣ የግል ከሳሽ ወይም ተከሳሹ ምስክር ወይም ሌላ ማስረጃ እንዳላቸው በቀጠሮው ቀን እንዲቀርቡ አስፈላጊውን ይፈጽማሉ፡፡
3. ክርክሩና የማስረጃ መስማት ሒደቱ በቃል ይፈፀማል፡፡ ፍርድ ቤቱም ምስክሩ ከሚሰጠው ቃል ውስጥ ዋናውን ነገር ብቻ በመዝገብ ይጽፋል፡፡

4. የክሱ መሰማት ሒደት ማመልከቻ ከቀረበበት ቢበዛ በሁለት ሳምንት ውስጥ መጠናቀቅ አለበት፡፡

5. ፍርድ ቤቱ ውሳኔው የተመሠረተበትን ሕግና ምክንያት በአጭሩ በመግለጽ ውሳኔውን በቃል ያሳውቃል፤ ይመዘግባል፡፡

## አንቀጽ 493 ተከሳሹ ባልቀረበ ጊዜ የሚኖር ሥነ ሥርዐት

ተከሳሹ በቀጠሮ ቀን ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 494 ልዩ ሁኔታ

1. በዚህ ክፍል ለደንብ መተላለፍ የተደነገገው ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ የምርመራ ውጤቱን ተመልክቶ ሲያመለክትና በተከሳሽ ላይ የሚሰጠው፡

   (ሀ) የገንዘብ ቅጣት ብቻ እንደሆነ፣

   (ለ) የመንገድና የማሽከርከር ገደብ ማለፍ ላይ የሚሰጥ ቅጣት እንደሆነ፣

   (ሐ) ለሕዝብ ጥቅም ንብረትን በመልቀቅን በተመለከተ ክስ ላይ የሚወሰድ ቅጣት፣

   (መ) ቅጣቱ ማስጠንቀቂያ ብቻ እንደሆነ፣

   (ሠ) በአንድ የተለየ ነገር እንዳይገለገል ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውል ሲወሰን፣

   (ረ) መንጃ ፍቃድ መመለስ የተመለከተ ቅጣት፣

   (ሰ) እስከ አንድ ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት ሆኖ የሚገደብለት እንደሆነ፣

   ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ተቀብሎ በመወሰን ውሳኔውን ከመጥሪያ ጋር ለተከሳሽ ሊልክለት ይችላል፡፡

2. ተከሳሽ አምኖ ውሳኔውን በጽሑፍ የተቀበለና ውሳኔውን ከፈፀመ ወይም ሊፈጽም ከተስማማ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ እንዲፈጽም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

3. ተከሳሹ መጥሪያ ደርሶት በሁለት ሳምንት ውስጥ መልስ ያልሰጠበት እንደሆነ እንዳመነና ውሳኔውን እንደተቀበለ ተቆጥሮ ውሳኔውን እንዲፈጽም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

4. ተከሳሹ ያልተስማማ እንደሆነ ክሱ በመደበኛ የክስ ሥነ ሥርዐት ይታያል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ይግባኝ አይባልበትም፡፡

# አራተኛ መጽሐፍ
# በወንጀል ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብር
## ምዕራፍ አንድ
## በወንጀል ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብር
### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌ

**አንቀጽ 495 ዓላማ**

በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ የዓለም አቀፍ ትብብር ዓላማ ሀገሪቱ ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖሩ መብትና ጥቅሞችን ለማስከበር እና ግዴታዎችን በአግባቡ ለመወጣት ሥራለማስቻል ነው፡፡

**አንቀጽ 496 መርህ**

(1) ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክመንግሥትበወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ዓለም አቀፍ ትብብር ሕግኢትዮጵያ በፈረማቸው ስምምነት መሠረት ይፈጸማል፡፡

(2) ዓለም አቀፍግልጽ የሆነ ስምምነት የሌለ እንደሆነ ትብብሩ በዚህ ክፍል በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት ይፈጸማል፡፡ ሕግመሠረት

**አንቀጽ 497 ትብብር ማድረግ የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች**

1. የትብብር ጥያቄው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትንና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ እና በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የትብብር ጥያቄው፡-

(ሀ) የማንኛውንም ሰው መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ሊጥስ ይችላል ተብሎ የሚታመን እንደሆነ በተለይም ለግርፋት፣ ጭካኔ፣ ኢ-ሰብዓዊ ለሆነ አያያዝ ወይም ቅጣት ይጋለጣል ተብሎ ሲታመን፣ ወይም

(ለ) አንድን ሰው በዘር፣ በብሔር ማንነት፣ በኃይማኖት፣ በፆታ፣ በቀለም፣ በዜግነት ወይም ባለው የፖለቲካ አቋም ሊያስከስሰው ወይም ሊያስቀጣው ይችላል ተብሎ ሲታመን

ትብብር መፈጸም የለበትም፡፡

3. ለትብብር የሚላከው ሰው ኢትዮጵያዊ እንደሆነ በሕገ መንግሥቱ የተመለከቱ መብቶችና ነፃነቶች እንደሚከበሩለት መረጋገጥ አለበት፡፡

4. ለተጠየቀው ትብብር መነሻ የሆነውን የወንጀል ድርጊት እና ለወንጀሉ የተቀመጠውን ቅጣት የመወሰን ሥልጣን የተሰጠው ለልዩ ፍርድ ቤት ወይም የአስተዳደር ፍርድ ቤት እንደሆነ፣

**አንቀጽ 498** <u>**የትብብር ዓይነቶች**</u>

1. በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ትብብር፡-
   (ሀ) የወንጀል ምርመራና ከምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን፣
   (ለ) መረጃና ማስረጃ ልውውጥን፣
   (ሐ) የወንጀል ተጎጅዎች፣ ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃን፣
   (መ) አሳልፎ መስጠትን፣
   (ሠ) የማስተላለፍ ጥያቄ መፈጸምን፣
   (ረ) የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረትን ወይም ገንዘብን ማገድና መውረስ፣
   (ሰ) የተያዘ ሰው ልውውጥ ወይም ፍርደኛንና የፍርድ ሂደትን ማስተላለፍን፣
   (ሸ) የፍርድ ቤት ውሳኔ ዕውቅና መስጠትና መፈፀምን፣
   (ቀ) ሌሎች በፍትሕ ሚኒስቴር የሚፈቀዱ መሰል የትብብር ዓይነቶችን፣

   ያጠቃልላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ቀ) በተደነገገው መሠረት ፍትሕ ሚኒስቴር መሰል የትብብር ዓይነቶችን ሲፈቅድ በዚህ ሕግ አንቀጽ 519 የተደነገገውን መርህ መሠረት ማድረግ አለበት፡፡

**አንቀጽ 499** **የትብብር መስመርና የማስፈጸም ሥልጣን**

1. በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ የዓለም አቀፍ ትብብር ጥያቄ በዲፕሎማሳዊ የግንኙነት መስመር መቅረብና መፈጸም አለበት፡፡
2. ፍትሕበዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ የሆነ ጉዳይ የገጠመ እንደሆነ ፍትሕ ሚኒስቴር ከዲፕሎማዋዊ የግንኙነት መስመር ውጪ የትብብር ጥያቄ ሊያቀርብ ወይም ሊፈጸም ይችላል፡፡
3. ፍትሕ ሚኒስቴር በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ዓለም አቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የማስፈጸም፣ የመምራት፣ የመከታተል ኃላፊነት አለበት፡፡
4. ፍትሕ ሚኒስቴር በዚህ ሕግ መሠረት የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ትብብር የትብብሩ ዓላማ እና አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እየተፈጸመ መሆኑን መከታተል አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጉዳዩ ዓይነትና ለግንኙነቱ መሠረት በሆነ ስምምነት ወይም ሕግ መሠረት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፍትሕ ሚኒስቴርን ማስታወቅ አለበት፡፡

**አንቀጽ 500** **የትብብር ወጪ**

(1) በስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር የትብብር ወጭ በትብብር ጠያቂ ሀገር የሚሸፈን ይሆናል፡፡

(2) በኢትዮጵያ የሚጠየቅ ትብብር ወጪው በፌዴራል መንግሥት ይሸፈናል፡፡

(3) በኢትዮጵያ የሚሸፈን የትብብር ወጪ ክፍያ በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ሥርዐት እና የፋይናንስ ሕግ መሠረት ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 501** **የትብብር ጥያቄ ማቅረብ ስለሚችሉ አካላት**

1. በወንጀል ጉዳይ ሥልጣን ያለው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል በዚህ ሕግ መሠረት የትብብር ጥያቄውን በቀጥታ ለፍትሕ ሚኒስቴር ሊያቀርብ ይችላልፍትሕ፡፡
2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 521 ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል መንግሥት አካል በቀጥታ የትብብር ጥያቄ እንዲያቀርብ ፍትሕ ሚኒስቴር ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 502 <u>የጥያቄው አቀራረብ</u>

1. ማንኛውም የትብብር ጥያቄ በጽሑፍ መቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም የትብብር ጥያቄ በቃል ሊቀርብ ይችላል፤ ጥያቄውም በሰባ ሁለት ሰዓት ውስጥ በጽሑፍ ካልተረጋገጠ ጥያቄው እንዳልቀረበ ይቆጠራል፡፡
3. ጥርጣሬ በመኖሩ ምክንያት ማረጋገጥ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ከጥያቄው ጋር የተያያዙ አባሪ ሰነዶች ወይም በጽሁፍ የተሰጡ ምላሾችን ሰነድ ለማረጋገጥ ሥልጣን ባለው አካል ማረጋገጥ አያስፈልግም፡፡

## አንቀጽ 503 <u>የትብብር ጥያቄ ይዘት</u>

ማንኛውም የትብብር ጥያቄ እንደነገሩ ሁኔታ፡-

1. የትብብሩን ዓላማ እና ዓይነት፣
2. የቀረበውን ጥያቄ የሚከታተል ተቋም ስምና አድራሻ፣ ጥያቄውን ለማቅረብ ያለው ሕጋዊመሠረት፣ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ያለው ኃላፊነት እና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች፣
3. ጥያቄው ከግለሰብ ጋር የሚያያዝ እንደሆነ ግለሰቡ የሚጠራበትና የሚታወቅበት ስም፣ ወቅታዊ አድራሻ፣ ዜግነት እና እንደነገሩ ሁኔታ የግለሰቡ መለያና ዝርዝር ሁኔታ፣
4. ጥያቄው ከንብረት ጋር የተያያዘ እንደሆነ የተወረሰ ወይም የታገደ የንብረት ዓይነትን እና ንብረቱ የሚገኝበት ቦታ የሚያብራራ አጭር መግለጫ፣ ጥፋተኝነቱን የሚያሳይ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ፣
5. የወንጀል ጉዳይ እንደሆነ ወንጀሉን የሚደነግገውን ሕግ፣ መግለጫ፣ ተፈጸመ የተባለውን ድርጊት፣ ድርጊቱ የተፈጸመበት ጊዜና ቦታ፣ የሚያስከትለውን ወይም የተወሰነበትን ቅጣት፣ ወሳኔ የሰጠው አካል እንደጉዳዩ ሁኔታ የወንጀሉን ፍሬ ነገርና ጉዳዩ በምርመራ ላይ እንደሆነ ወንጀሉ ስለመፈጸሙ የሚያስረዳ የምርመራ ውጤት መግለጫ እና
6. በሚመለከተው አካል የሚጠየቁ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን

መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 504 <u>የጥያቄውን ተቀባነይት፣ አግባብነት ማረጋገጥ እና ውሳኔ መስጠት</u>**

1. ፍትሕ ሚኒስቴር የትብብር ጥያቄው፡-

(ሀ) በዚህ ሕግ አንቀጽ የተመለከቱትን የሚያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ይወስናል፡፡

(ለ) ተቀባይነት የሌለው ወይም ያልተሟላ እንደሆነ ለጠያቂው አካል ውሳኔውን ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡

(ሐ) ያልተሟላ እንደሆነ በጥያቄው ላይ የታዩ ጉድለቶችን ለይቶ በማመልከት ማስተካከያ ተደርጎበት ወይም ጥያቄውን አሟልቶ እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡

(መ) ተቀባይነት ያለው እንደሆነ እና

(1) ጥያቄው የቀረበው በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት አካል እንደሆነ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ትብብር ለሚጠይቀው አካል ይልካል፡፡

(2) ጥያቄው የቀረበው ለኢትዮጵያ እንደሆነ እንደአግባብነቱ ቀጥሎ ባለው ክፍል መሠረት እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 505 <u>ማረጋገጫ መስጠት</u>**

1. በዚህ ሕግ መሠረት የተያዘ ሰው የተላለፈለት ትብብር ጠያቂ ሀገር፡-

(ሀ) የተላለፈው ሰው ከግዛቱ ከመውጣቱ በፊት በፈጸመው ተግባር እንደማይያዝ፣ እንደማይከሰስ፣ እንደማይቀጣ ወይም የትኛውም የግል ነጻነቱ እንደማይገደብ፣ ወይም በማንኛውም የፍትሐብሔር ኃላፊነት ተጠያቂ እንደማይሆን፣

(ለ) በራሱ እና አሳልፎ በሰጠው ሀገር ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ትብብር ከተጠየቀበት ጉዳይ ውጪ ድጋፍ እንዲሰጥ እንደማይገደድ፣

(ሐ) በስምምነት በተገለጸው የጊዜ ገደብ ቀደም ሲል ወደነበረበት ሀገር እንደሚመለስ፣

(መ) የተያዙ ሰዎችን መሠረታዊ መብቶች ሊያስጠብቅ በሚችል ማቆያ ወይም ማረፊያ እንደሚጠብቀው፣

ማረጋገጫ መስጠት አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የትብብር ጥያቄው የቀረበለት ሀገር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተጨማሪ ማረጋገጫ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 506** <u>**የወንጀል ተጎጂ መብት**</u>

ማንኛውም የትብብር ጥያቄ የወንጀል ተጎጂን ወይም የወራሽን የካሣ ወይም ሌላ የመብት ጥያቄ በሚያጓድል መልክ መፈጸም የለበትም፡፡

**አንቀጽ 507** <u>**ይርጋ**</u>

የትብብር ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ የክስ ማቅረቢያ ወይም የቅጣት ውሳኔ ማስፈጸሚያ የይርጋ ጊዜ በወንጀል ሕግ መሠረት ይቆጠራል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የትብብር ጥያቄ አፈጻጸም</u>

**አንቀጽ 508** <u>**ጠቅላላ**</u>

(1) የቀረበው የትብብር ጥያቄ በዚህ ሕግ መሠረት ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ በዚህ ሕግና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

(2) የቀረበው የትብብር ጥያቄ በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ የማይታወቅ እንደሆነ በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ በሆነ ሕግ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 509** <u>**የወንጀል ምርመራና ከምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ትብብር**</u>

1. ትብብር ጠያቂው ሀገር አንድ የወንጀል ድርጊት እንዲመረመር በጠየቀ ጊዜ ፍትሕ ሚኒስቴር ምርመራው በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 84 እስከ አንቀጽ 211 በተደነገገው ሥነ ሥርዐት በሕግ የመመርመር ሥልጣን በተሰጠው አካል እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ የምርመራውንም ውጤት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካይነት ለጠያቂው ሀገር ይልካል፡፡

2. በጋራ የምርመራ ቡድን ወንጀልን ለመመርመር ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ፍትሕ ሚኒስቴር ምርመራው በዚህ ሕግ ምርመራ እንዲያከናውኑ ሥልጣን የተሰጣቸው

አካላት እና የጥያቄ አቅራቢው አገር የምርመራ አካላት ወንጀሉን በጋራ የሚመረምሩበትን አግባብ ይወስናል፡፡

3. የትብብር ጠያቂው ሀገር ምርመራ አካላት በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ ወንጀልን እንዲመረምሩ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ከተደነገገው ሥርዐት ጋር የሚመሳሰል ምርመራ እንዲካሔድ ጥያቄ ከቀረበ ፍትሕ ሚኒስቴር አግባብነቱን ዐይቶ ይወስናል፤ የምርመራውን ሂደትና አፈጻጸም ይከታተላል፡፡

## አንቀጽ 510 በኢትዮጵያ ውስጥ ያለን ሰው በጊዜያዊነት የማስተላለፍ ትብብር

1. በማረፊያ ወይም በማቆያ ቤት ያለ ሰው ምስክርነት ለመስጠት ወይም ለሌላ ምርመራን የማገዝ ሥራ በተጠየቀ ጊዜ ትብብር ጠያቂው ሀገር በዚህ ሕግ አንቀጽ 532 የተመለከተውን ማረጋገጫ ሲያሟላ ፍትሕ ሚኒስቴር ትብብሩ እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ተፈላጊው ሰው በማረፊያ ወይም በማቆያ ቤት የማይገኝ እንደሆነ እና ለተፈለገው ዓላማ በጊዜያዊነት ሊተላለፍ ፈቃደኛ እንደሆነ ፍትሕ ሚኒስቴር ይኸውን ያስፈጽማል፤ ተፈላጊው ፈቃደኛ ካልሆነ በጉዳዩ ላይ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የሚተላለፈው ሰው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው እንደሆነ በጊዜያዊነት ሊተላለፍ የሚችለው ፈቃደኛ ሲሆን ብቻ ነው፡፡
4. የፌዴራል ፖሊስ ከፍርድ ቤት ትእዛዝ በማውጣት ለትብብር የተጠየቀውን ሰው ከሚገኝበት ማረፊያ ወይም ማቆያ ቤት በመረከብ ለጠያቂው ሀገር እንዲያስረክብ፣ ትብብሩን አጠናቅቆ ሲመለስም ወደ ነበረበት ማረፊያ ወይም በማቆያ ቤት እንዲያስረክብ ይደረጋል፡፡
5. በትብብር ጠያቂው አገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት የትብብሩን አፈጻጸም እንዲከታተል መደረግ አለበት፡፡

## አንቀጽ 511 በውጭ ሀገር በቁጥጥር ሥር ያለን ሰው ለትብብር መጠየቅ

1. በውጭ ሀገር በቁጥጥር ሥር ያለ ሰው ለትብብር በተፈለገ ጊዜ እና ተጠያቂው ሀገር ወይም ተቋም ሲፈቅድ ፍትሕ ሚኒስቴር የተጠየቀውን ሰው ተረክቦ ትብብሩን ለጠየቀው አካል እንዲያስረክብ እና ትብብሩም ከተጠናቀቀ በኋላ ከትብብር ጠያቂው ተረክቦ ትብብሩን ላደረገው ሀገር እንዲያስተላልፍ ለፌዴራል ፖሊስ ያሳውቃል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለኢትዮጵያ የተላለፈ ሰው ወደ ኢትዮጵያ መግቢያ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
3. የተላለፈ ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ይደረጋል፤ ማረፊያ ቤት በሚቆይበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ ማረፊያ ቤት በሚገኙ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ሕግ ይሆናል፡፡
4. በሕግ ጥበቃ ሥር ያለ የተላለፈው ሰው ቢያመልጥ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ተይዞ በሕግ ጥበቃ ሥር እንዲውል ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 512 <u>ለትብብር ወደ ኢትዮጵያ የገባ ሌላ ሰው</u>

በዚህ ሕግ አንቀጽ 533 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሕግ አንቀጽ 532 ከተመለከተው ውጭ በትብብር ጥያቄ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ሌላ ሰው ለትብብሩ አስፈላጊ እንዳልሆነ እና የኢትዮጵያን ግዛት እንዲለቅ ከታዘዘበት ጊዜ ጀምሮ ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ በሚፈጽማቸው ወንጀሎች ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 513 <u>በጠያቂ አገር ማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤት መቆየት ያለው ውጤት</u>

በዚህ ሕግ መሠረት የተላለፈ ሰው በክርክር ሂደት ወይም የፍርድ ቅጣቱን በመፈጸም ላይ የነበረ እንደሆነ ተላልፎ በተሰጠበት ጊዜ በማረፊያ ወይም በማረሚያ ቤት የቆየው ጊዜ መፈጸም ካለበት ግዴታ ገብቶ ይታሰብለታል፡፡

## አንቀጽ 514 <u>መረጃና ማስረጃ ልውውጥ ትብብር</u>

1. ለጠያቂ አካል የተሰጠ ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ፣ መረጃ፣ ሰነድ ወይም ሪከርዶችን እና ሌላ የማስረጃ ዋጋነት ያለው ነገር በአግባቡ የሚያዝ ስለመሆኑ ማረጋገጫ መሰጠት እና ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ መመለስ አለበት፡፡
2. በትብብር ጥያቄ የተገኘው ማንኛውም መረጃ ወይም ማስረጃ ትብብር ከተጠየቀበት ዓላማ ወጭ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም፡፡

## አንቀጽ 515 <u>መጥሪያና ሌሎች ሰነዶች የማድረስ ትብብር</u>

1. ለኢትዮጵያ የቀረበው የትብብር ጥያቄ የመጥሪያ ወይም ሌላ ሰነድ የማድረስ እንደሆነ ይኸው ወዲያውኑ መፈጸም አለበት፡፡

2. ጥያቄው መጥሪያ የማድረስ የሆነ እንደሆነ ይኸው ተፈላጊው እንዲቀርብ ከተፈለገበት ቀን ቀደም ብሎ የሃያ ስምንት ቀናት ባለነሰ ጊዜ ውስጥ መጥሪያና የመጥሪያ የማድረስ ጥያቄው መቅረብ አለበት፤ የሚመለከተው አካል መጥሪያው እንደደረሰው ከአሥራ አምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለተፈላጊው ማድረስ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም እና ይኸው በፍትሕ ሚኒስትሩ ከታመነ ጥያቄው ከተደነገገው ጊዜ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ቢቀርብም ጥያቄው ተቀባይነት አለው፡፡

**አንቀጽ 516** <u>የፍርድ ሂደትን ማስተላለፍ</u>

1. የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ በምትክነት ተፈፃሚ በሚሆንባቸው ወንጀሎች ላይ የፍርድ ሒደት እንዲተላለፍ የትብብር ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ሂደቱ በዚህ ሕግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ሊታይ ይችላል፡፡
2. ለተላለፈው የፍርድ ሂደት ውጤታማነት ለማገዝ የሚያስችል አስፈላጊ ምርመራ ማካሔድ ተገቢ ካልሆነ በስተቀር የፍርድ ሂደት ማስተላለፍ በተጠየቀው ሀገር ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ በዚህ ሕግ መሠረት የተመለከቱ የእርቅ፣ የጥፋተኝነት ድርድር፣ የአማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ወይም የክስ ሂደት መቋረጥ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተላለፈ የፍርድ ሂደት ውሳኔ ካገኘ ይኸውን ለጠያቂው ሀገር መገለጽ አለበት፡፡

**አንቀጽ 517** <u>ፍርደኛን ማስተላለፍ</u>

1. በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት በመጨረሻ ውሳኔ ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ ሰውን ቅጣት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈጸም የትብብር ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፤ አፈጻጸሙም በዚህና እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ፍርደኛን የማስተላለፍ የትብብር ጥያቄ፡-

   (ሀ) ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ቅጣት የተጣለበት ፍርደኛ ሙሉ ወይም ቀሪ ቅጣቱን እንዲፈጽም፣

(ለ) ቅጣት የተገደበለት ፍርደኛ የገደቡን ቅድመ ሁኔታዎች መፈጸሙን ለመከታተል፣ ወይም

(ሐ) በአመክሮ የተለቀቀ ወይም ቅጣት የተላለፈለት ፍርደኛ ለአመክሮው ወይም ለቅጣት መተላለፉ ምክንያት የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን መፈጸሙን ለመከታተል፣

ሊሆን ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም፡-

(ሀ) ፍርደኛው ቋሚ ኗሪ ካልሆነ፣ ወይም

(ለ) በዚህ ወይም ሌላ ሕግ ቅጣቱ የሚፈጸምበት የይርጋ ጊዜ ካለፈ፣

ፍርደኛን የማስተላለፍ የትብብር ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

4. የተላለፈ ፍርደኛን ቅጣት በማስፈጸም ሂደት ፍርዱ እንዲከለስ ወይም የመጨረሻን ፍርድን እንደገና የማየት ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የትብብር ጠያቂው ሀገር ይሆናል፡፡

5. በስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ፍርደኛን በማስተላለፍ የትብብር ሂደት የፍርደኛውን ባሕርይ፣ የቅጣት አፈጻጸም፣ የክትትል አግባብና አተገባበር ሪፖርት የሚቀርብበትን ሁኔታ ፍትሕ ሚኒስቴር ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 518** <u>የፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ ዕውቅና መስጠትና ማስፈጸምን፣</u>

1. በውጪ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጠ ትእዛዝ፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ ዕውቅና የመስጠትና የማስፈጸም የትብብር ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በዚህ ሕግ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ይፈጸማል፡፡

2. ንብረቱ እንዲታገድ ወይም እንዲወረስ በጠያቂው መንግሥት የተሰጠ ትእዛዝ፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

3. ፍትሕ ሚኒስቴር በተቃራኒው ካልወሰነ በስተቀር በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የተወረሰ ማንኛውም ንብረት ለመንግሥት ገቢ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 519** <u>በኢትዮጵያ ግዛት እስረኛን ማስተላለፍ</u>

1. ትብብር ጠያቂ ሀገር እስረኛን በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ወደ ሦስተኛ ሀገር ለማስተላለፍ ጥያቄ ሲያቀርብ ፍትሕ ሚኒስቴር የተላላፊውን ማንነት፣ የሚተላለፍበትን ምክንያት በቀረበው ማስረጃ መሠረት መርምሮ ፈቃድ

ይሰጣል፡፡ የእስረኛውን መተላለፍ ያልፈቀደ እንደሆነ ትብብር ጠያቂው ሀገር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካይነት ምክንያቱን እንዲያውቅ ያደርጋል፡፡

2. ፍትሕ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፈቃድ በሰጠ ጊዜ የተላላፊውንና የአስተላላፊውን ማንነት እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ማስረጃዎችን በመላክ አግባብ ያለው ባለሥልጣን እንዲያስፈጽም ሊያደርግ ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑም ትብብሩን እንዳስፈጸመ ወዲያውኑ ለፍትሕ ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. ያልተጠበቀ የእስረኛ ማስተላለፍ ባጋጠመ ጊዜ፣ ፍትሕ ሚኒስቴር መረጃ እንደደረሰው ወይም በአስተላላፊው ሀገር ባለሥልጣን አመልካችነት ተላላፊው ሰው በኢትዮጵያ ግዛት ክልል እንዲተላለፍ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ማስተላለፉ ባልተፈቀደ ጊዜ ተላላፊው ሰው በመጣበት አግባብ ወደመጣበት ሀገር እንዲመለስ ይደረጋል፡፡
4. ፍትሕ ሚኒስቴር ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) አፈጻጸም ተላላፊው ሰው ከአራባ ስምንት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ በፌዴራል ፖሊስ ቁጥጥር ሥር እንዲውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 520** ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት

ለዚህ ምዕራፍ አፈጻጸም ፍርድ ቤት ማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡

## ክፍል ሦስት
## በወንጀል ተፈላጊን ሰው አሳልፎ ስለመስጠት
### ንዑስ ክፍል አንድ
### አሳልፎ ለመስጠት በቀረበ ጥያቄ ላይ ስለሚፈጸም ስነሥርዐት

**አንቀጽ 521** ትርጓሜ

አሳልፎ መስጠት ማለት አንድን የሚፈለግ ተጠርጣሪ፣ ተከሳሽ ወይም ፍርደኛ ለወንጀል የክስ ሂደት፣ ቅጣት ለመወሰን ወይም ለማስፈጸም የሚቀርብ የትብብር ጥያቄ ነው፡፡

**አንቀጽ 522** አሳልፎ የሚያሰጥ የወንጀል ድርጊት ወይም ቅጣት

1. በስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፣

(ሀ) ሁለት ዓመትና በላይ በእሥራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል የወንጀል ተግባር ለወንጀል የክስ ሂደት ወይም ቅጣትን ለመሰወን፣ ወይም

(ለ) ስድስት ወር እና በላይ ያልተፈጸመ ወይም ሳይፈጸም የቀረ የእሥራት ቅጣትን ለማስፈጸም

አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ሊቀርብበት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተላልፎ እንዲሰጥ የተወሰነበት ሰው የተከሰሰበት ወይም ጥፋተኛ የተባለበት ሌላ ተደራቢ ወንጀል ከሁለት ዓመት በታች በእሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ወይም ፍርደኛው ሳይፈጽመው የቀረ ከስድስት ወር በታች የእሥራት ቅጣት እንደሆነ ተላልፎ ሊያሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 523 <u>ስለጣምራ የወንጀል ድርጊት</u>

1. ድርጊቱ ወይም በድርጊቱ ምክንያት ተወስኖ ሳይፈጸም የቀረ ቅጣት በውጭ ሀገር እና በኢትዮጵያ ሕግ ወንጀል ወይም ቅጣት መሆኑ የተደነገገ ካልሆነ በቀር አሳልፎ አያሰጥም፡፡
2. ወንጀሉ ወይም ቅጣቱ በውጭ ሀገርና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በአንድ ዓይነት ስያሜ አለመጠራቱ ወይም በተመሳሳይ የወንጀል ድንጋጌ ሥር አለመጠቀሱ ወይም በአንድ ዓይነት አገላለጽ አለመቀመጡ አሳልፎ የሚያሰጥ ወንጀል ወይም ቅጣት መሆኑን አያስቀረውም፡፡

## አንቀጽ 524 <u>አሳልፎ መስጠት የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች</u>

በዚህ ሕግ አንቀጽ 519 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አሳልፎ ይሰጠኝ ጥያቄ የቀረበበት ሰው፡-

(1) የኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው፣

(2) በተከሰሰበት ወይም ጥፋተኛ በተባለበት አሳልፎ በሚያሰጥ የወንጀል ተግባር አስቀድሞ በኢትዮጵያ ወይም በሌላ ሀገር ፍርድ ቤት በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ቅጣት ተወስኖበት የፈጸመ፣ ወይም

(3) በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ወይም በጠያቂው ሀገር ሕግ መሠረት ጥያቄው በቀረበበት ወቅት በይቅርታ፣

በምኅረት፣ በይርጋ የታገደ ወይም ከመከሰስ ወይም ከቅጣት ነፃ የሚያደርግ ማንኛውም ምክንያት ያለ እንደሆነ፣

ተላልፎ አይሰጥም፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ለአሳልፎ መስጠት የክስ ሂደት ሰነዶች ስለሚጠይቁበት ሁኔታ

### አንቀጽ 525 የአሳልፎ መስጠት ጥያቄ ይዘትና ስለሚቀርብ ሰነድ

1. ሥልጣን ባለው የጠያቂ መንግሥት አካል በጽሑፍ የሚቀርብ አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ተቀባይነት አለው፡፡
2. አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ እንደነገሩ ሁኔታ፡-

(ሀ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 525 የተመለከቱ ሁኔታዎችን፣

(ለ) በተፈላጊው ሰው ላይ ሊቀርብበት የሚችለውን ክስ፣ ወንጀሉን የሚያቋቁም የሕግ ድንጋጌና ይዘት፣ ወንጀሉ የሚያስከትለው ቅጣት፣

(ሐ) ተፈላጊው ሰው ክስ የተመሰረተበት እንደሆነ ወንጀሉ የተፈጸመበት ጊዜ፣ ቦታና የወንጀሉ አፈጻጸም ዝርዝር ሁኔታ፣ ተፈላጊው ሰው ያለው ተሳትፎ፣ ወንጀሉ የሚያስከትለው ቅጣት፣ ማስረጃና የሚያስረዱት ጭብጥ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠ የመያዣ ትእዛዝ፣

(መ) ተፈላጊው ሰው ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ እንደሆነ የፈጸመው ወንጀል አጭር መግለጫ፣ ጥፋተኝነቱን የሚያሳይ የፍርድ ቤት ውሳኔ፣ የተጣለበትና ያልፈጸመው የቅጣት ዓይነት ወይም መጠን፣

(ሠ) ጉዳዩ በሌለበት የተወሰነበት እንደሆነ ተፈላጊው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (መ) ከተመለከቱ መረጃዎች በተጨማሪ በቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የተሰጠ መጥሪያ፣ መከላከያውን ለማቅረብ የሚያስችለውን የሕግ መነሻ ስለመኖሩ ወይም ጉዳዩን እንደገና ለማየት ስለሚፈቅድ ሕግ ድጋፍ አጭር መግለጫ፣

(ረ) ተፈላጊው ሰው ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ እንደሆነ የፈጸመው ወንጀል አጭር መግለጫ፣ ጥፋተኝነቱን የሚያሳይ የፍርድ ቤት ውሳኔና ቅጣቱን ለመወሰን የሚያስችል ማረጋገጫ፣

(ሰ) ሌሎች በፍትሕ ሚኒስቴር የሚጠየቁ መረጃዎችን ወይም አባሪ ሰነዶችን መያዝ አለበት፣

**አንቀጽ 526 <u>ተደራራቢ ጥያቄዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታ</u>**

1. ፍትሕ ሚኒስቴር ተፈላጊ ሰው ለአንድ ዓይነት ወይም ለተለያየ አሳልፎ ለሚያሰጥ የወንጀል ድርጊት ወይም ቅጣት ከተለያዩ መንግሥታት የተላልፎ ይሰጠኝ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ፡-
   (ሀ) በዚህ ሕግ አንቀጽ 518 የተቀመጡትን መርሆዎች በተሻለ ሁኔታ የሚያስከበር መሆኑን፣
   (ለ) ከጠያቂው መንግሥት ጋር የተፈጸመ አሳልፎ የመስጠት ስምምነት እና በስምምነቱ የተደነገገ ግዴታ፣
   (ሐ) ጥያቄው የቀረበበትን ቅደም ተከተልና ይዘት፣ የወንጀሉና የቅጣቱ ዓይነት፣
   (መ) ተፈጸመ የተባለውን የወንጀል ድርጊት ዓይነት ወይም ሳይፈጸም የቀረ ቅጣት መጠን፣
   (ሠ) የተከሳሹን መብት በተሻለ ሁኔታ የሚያስጠብቅ መሆኑን፣
   (ረ) የተጎጂውንና የተፈላጊውን ሰው ዜግነት እና የተጎጂውን መኖሪያ ሀገር፣ እና
   (ሰ) መሰል ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት

   ተፈላጊውን ሰው ለመዳኘት ወይም የተጣለበትን ቅጣት ለማስፈጸም ቅድሚያ የሚኖረውን ጠያቂ መንግሥት ይወስናል፡፡
2. ተፈላጊው ሰው ቅድሚያ ለተሰጠው መንግሥት አሳልፎ ያልተሰጠ እንደሆነ የሌሎች ጠያቂ መንግሥታት ጥያቄ በዚህ ሕግ መሠረት ታይቶ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 527 <u>ጊዜያዊ እሥር</u>**

1. በጉዳዩ አስቸኳይነት ምክንያት ተላልፎ እንዲሰጥ ጥያቄ የሚቀርብበትን ሰው በእሥር ማቆየት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በዚህ ሕግ መሠረት የአሳልፎ መስጠት ጥያቄው እስኪቀርብ ድረስ ወይም የማስተካከያ ምላሽ እስኪያገኝ ድረስ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ተፈላጊው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የጊዜያዊ እሥር ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ፍትሕ ሚኒስቴር የአሳልፎ መስጠት የትብብር ጥያቄን ወስኖ በፍርድ ቤት እስኪያቀርብ ድረስ ተፈላጊውን በጊዜያዊ እስር ማቆየት አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ እንደአግባብነቱ በዚህ ሕግ የተመለከቱ የመያዝና የዋስትና ግዴታ ድንጋጌዎች (ከፍል-----አንቀጽ ---- እና አንቀጽ -----) ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
3. የጊዜያዊ እሥር ጥያቄ፡-

ሀ. ተፈላጊው መደበኛ መኖሪያው በኢትዮጵያ የሆነ ወይም በተደጋጋሚ ወደ ኢትዮጵያ የሚመላለስ እንደሆነ፣

ለ. ጥያቄው ተፈጸመ ከተባለው ወንጀል ጋር ግንኙነት ያለው እንደሆነ፣

ሐ. ለእሥር ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ ትእዛዝ የተሰጠበት ወይም በውጪ ሀገር ክስ የተመሠረተ እንደሆነ፣ እና

መ. ለማምለጥ ወይም ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም ሲባል

ሊቀርብ እና ሊፈጸም ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱ የትብብር ጥያቄዎች ለሚመለከተው አካል በሃያ ስምንት ቀን ውስጥ ካልቀረበ ተፈላጊው ሰው ከእሥር ይለቀቃል፡፡ የተፈላጊው ሰው ከእሥር መለቀቅ የድጋሜ እሥር ወይም የተላልፎ ይሰጥ ጥያቄ ሂደትን ደግሞ ከማቅረብ የሚከለክል አይሆንም፡፡
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ የጊዜያዊ እሥር ጥያቄ ወይም ማመልከቻ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ ሕግ አንቀጽ 549 የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 528** <u>የአሳልፎ ይሰጥ ጥያቄን ለፍርድ ቤት ማቅረብ</u>

1. ፍትሕ ሚኒስቴር በዚህ ሕግ አንቀጽ 526 በተደነገገው መሠረት የጥያቄውን አግባብነት መርምሮ ከተቀበለ የተላልፎ ይሰጥ ማመለከቻ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ያቀረበውን መንግሥት፣ በተፈላጊው ሰው ላይ የቀረበበት ክስ፣ ወይም የተሰጠ ውሳኔ አጭር መግለጫ እና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች መያዝ አለበት፡፡
3. ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ እንዲታይ ከተወሰነበት ቀን በፊት የተላለፎ ይሰጥ ማመልከቻውን ቅጅ ለተፈላጊው ሰው እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡
4. ተፈላጊው ሰው በቀረበው ተላልፎ ይሰጥ ጥያቄ ላይ ያለውን መልስና አስተያየት ከቀጠሮ ቀን በፊት በጽሑፍ ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 529** <u>ተፈላጊውን ሰው መያዝ</u>

1. ፍትሕ ሚኒስቴር የአሳልፎ ይሰጥ ጥያቄውን ፍርድ ቤት ሲያቀርብ ተፈላጊው ያልተያዘ እንደሆነ የመያዝ ትእዛዝ እንዲሰጠው ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ የተፈላጊው ሰው መያዝ አስፈላጊ መሆኑን ካመነ በዚህ ሕግ መሠረት የመያዣ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ ተፈላጊው ተይዞ እንዲቀርብ ትእዛዝ ከሰጠ የፌዴራል ፖሊስ ተፈላጊውን ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሕግ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ስለመያዝ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 530 <u>ተፈላጊውን ሰው ፍርድ ቤት ማቅረብ</u>**

1. ፌዴራል ፖሊስ ወይም ውክልና የተሰጠው የክልል ፖሊስ በዚህ ሕግ አንቀጽ 553 መሠረት የተያዘውን ተፈላጊ ሰው በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ፡-
   ሀ. ተፈላጊው ተላልፎ እንዲሰጥ ፈቃደኝነቱን ካልገለጸ ወይም ተቃውሞ ካቀረበ ጉደዩን ሰምቶ ከአሥራ አምሰት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሰምቶ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
   ለ. በዋስትና መልቀቅ አስፈላጊ መሆኑን ካላመነ በስተቀር ጉዳዩን ሰምቶ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ተፈላጊው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 531 <u>መሰማትና ውሳኔ መስጠት</u>**

1. ፍርድ ቤቱ፡-
   (ሀ) ጉዳዩ በሚሰማበት ዕለት አግባብ ሆኖ ባገኘው ማንኛውም መንገድ የተፈላጊውን ሰው ማንነት ማረጋገጥ አለበት፡፡
   (ለ) ተፈላጊው ሰው በቀረበው አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ላይ ያለውን መልስ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ መጠየቅ አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በአመልካች የቀረበውን ጥያቄ እና በተፈላጊው ሰው የተሰጠውን መልስ ወይም አስተያየት ከመረመረ በኋላ እንደነገሩ ሁኔታ፡-
   (ሀ) ተፈላጊው ተልፎ እንዲሰጥ ፈቃደኝነቱን ከሰጠ፤ ማንነቱን በማረጋገጥ ተላልፎ እንዲሰጥ፣

(ለ) ፈቃደኝነቱን ካልገለጸ ወይም ተቃውሞ ካቀረበ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄ የቀረበበት ሰው መሆኑን እና አሳልፎ ለመስጠት የተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ተፈላጊው ሰው ተላልፎ እንዲሰጥ፣ ወይም

ሐ. የቀረበው ሰው ተፈላጊው አለመሆኑን ወይም ተፈላጊው አሳልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀበትን የወንጀል ተግባር ስለመፈጸሙ በቂ ጥርጣሬ የሚያሳድር ማስረጃ አለመቅረቡን ሲረዳ ዋስ መጥራት ሳያስፈልገው እንዲለቀቅ፣ እንደነገሩ ሁኔታ የተያዘ ንብረት እንዲመለስለት፣

ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 532 <u>በቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤት አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት</u>**

1. ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በሚሰማበት እለት ተፈላጊው ሰው ያልቀረበ እንደሆነ ታስሮ እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
2. በተለዋጭ የቀጠሮ ቀን ተፈላጊው ሰው ፍርድ ቤት ያልቀረበ እንደሆነ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

**አንቀጽ 533 <u>ይግባኝ ወይም እንደገና እንዲታይ መጠየቅ</u>**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበውን የይግባኝ ክርክር ከመረመረ በኋላ የይግባኝ አቤቱታው በቀረበ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
2. በዚህ ሕግ መሠረት በፍርድ ቤት በተሰጠ የአሳልፎ መስጠት ውሳኔ ላይ የሚቀርብ የይግባኝ ቅሬታ ውሳኔው በተሰጠ በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ካልቀረበ በማናቸውም ምክንያት በይግባኝ አይታይም፡፡
3. በዚህ ሕግ መሠረት ጉዳዩ በመታየት ላይ ያለ ወይም ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ፣ በሌላ ወንጀል ወይም በሌላ ጠያቂ ሀገር ጥያቄ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በዚህ አንቀጽ መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት የአሳልፎ መስጠት ጉዳይ እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡
4. በዚህ ሕግ ስለ ይግባኝ አቀራረብ የተደነገገው እንደአግባብነቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት በቀረበ ይግባኝ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 534 <u>ውሳኔን ስለማሳወቅ</u>**

ፍትሕ ሚኒስቴር

1. በዚህ ሕግ መሠረት የተሰጠ የአሳልፎ መስጠት የመጨረሻ ውሳኔን ለጠያቂው ሀገር ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤት በመጨረሻ ውሳኔ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄውን ውድቅ ካደረገ የውሳኔውን ምክንያት ለጠያቂው ሀገር ያሳውቃል፡፡

**አንቀጽ 535 <u>ተፈላጊውን ማስረከብ</u>**

1. ፍትሕ ሚኒስቴር
   (ሀ) በመጨረሻ ውሳኔ ተላልፎ እንዲሰጥ የተወሰነበትን ተፈላጊ ለጠያቂው መንግሥት ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ማስረከብ አለበት፤ ርክክቡ እንደአስፈላጊነቱ ተያያዥ ሰነዶችንም ሊያካትት ይችላል፡፡
   (ለ) ተፈላጊው ተላፎ እስኪሰጥ ድረስ ተይዞ በእሥር የቆየ እንደሆነ ይኸው የጊዜ መጠን ማስረጃን ለጠያቂው መንግሥት መግለፅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጠያቂው መንግሥት የተረከበውን ተፈላጊ ወይም ሰነድ መመለስ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተላልፎ ይሰጠኝ ጥያቄው የቀረበበት ዓላማ እንደተፈጸመ የሚመልስ ስለመሆኑ መተማመኛ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 536 <u>የውሳኔ ተፈጻሚነትን ማራዘም ወይም ማገድ</u>**

1. ፍትሕ ሚኒስቴር
   (ሀ) ተፈላጊው ሰው ተላልፎ ቢሰጥ ከባድ የጤና መታወክ ወይም ህይወቱ ለአደጋ ይጋለጣል ብሎ ሲያምን፣ በተፈላጊው ሰው ላይ የወንጀል ምርመራ እየተጣራ፣ በወንጀል ክስ የቀረበበትና ጉዳዩ በፍርድ ሂደት ላይ ካለ ወይም ሌላ ቅጣት እየፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ ተፈላጊው ተላልፎ የሚሰጥበትን ጊዜ ለፍርድ ቤት በማሳወቅ ሊያራዝም ይችላል ፡፡
   (ለ) ተፈላጊው ተላልፎ እንዲሰጥ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔን ሊያስቀይር ወይም እንዲራዘም እንዲቆይ የሚያስገድድ ምክንያት ባጋጠመ ጊዜ ምክንያቱ ቀሪ እስኪሆን ድረስ ውሳኔው ታግዶ እንዲቆይ ወይም እንዲሻር ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ የተለየ ውሳኔ ካልሰጠ በስተቀር የአሳልፎ መስጠት ውሳኔው እንዲራዘም ትእዛዝ ከተሰጠ እና ተፈላጊው በእሥር ላይ ያለ እንደሆነ በዋስትና እንዲለቀቅ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 537** __ውድቅ በተደረገ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄ ላይ ስለሚፈፀም ስነ -ሰርዓት__

ወንጀል ሕግ ከአንቀጽ 17 እሰከ 20 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄው፡-

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 526 መሠረት ፍትሕ ሚኒስቴር አግባብነቱን መርምሮ ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ወይም
2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 557 መሠረት የመጨረሻ ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት የተላልፎ ይሰጥልኝ ማመልከቻውን ውድቅ ያረገው ወይም ውሳኔውን የሻረው እንደሆነ፣

በዚህ ሕግ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሠረት ክስ እንዲመሠረት፣ ቅጣት እንዲወሰንበት ወይም የተጣለበትን ቅጣት እንዲፈፅም ትእዛዝ መሰጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ 538** __በጊዚያዊነት ተላልፎ የተሰጠ ሰው__

1. በውጪ ሀገር በእሥር ላይ ያለ ተፈላጊ በጊዚያዊነት ለኢትዮጵያ ተላልፎ የተሰጠ እንደሆነ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ግለሰቡ በእሥር ላይ እንዲቆይ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
2. ተላልፎ የተሰጠው ሰው በእሥር እንዲቆይ የሚሰጠው ትእዛዝ ተላልፎ የተሰጠበት ምክንያት እስኪጠናቀቅ ድረስ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መሠረት ተላፎ የተሰጠው ሰው የተላለፈበት ምክንያት ከተጠናቀቀ አሳልፎ ለሰጠው ሀገር መመለስ አለበት፡፡
4. በጊዚያዊነት ተላልፎ በተሰጠ እና ክስ በተመሰረተበት የወንጀል ድርጊት ፈፃሚ ላይ የመጨረሻው የአሳልፎ መስጠት ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ የተላለፈበት ፍርድ አይፈጸምም፡፡

**አንቀጽ 539** __ተፈላጊውን መረከብ ወይም ማስረከብ__

1. ለኢትዮጵያ መንግሥት ተላልፎ እንዲሰጥ የተወሰነበትን ተፈላጊ ሰው የፌዴራል ፖሊስ ይረከባል፣ ተገቢውን ይፈጽማል፡፡

2. ፍትሕ ሚኒስቴር፡-

(ሀ) ለኢትዮጵያ መንግሥት ተላልፎ የተሰጠው ሰው የፍርድ ሂደቱን ወይም ቅጣቱን ሲያጠናቅቅ ተመልሶ ከሀገር መውጣቱን ወይም መቅረብ ያለበት ሌላ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄ መኖሩን አጣርቶ ይወስናል፣

(ለ) በማስረጃነት የቀረበ ዕቃ በተገቢው መንገድ መያዙን ወይም የቀረበለት ዓላማ ሲጠናቀቅ በሕግ መሠረት መመለሱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## በኢትዮያጵያ ማስተላለፍ የሚፈጸምበት ሥነ ሥርዐት

**አንቀጽ 540** ማስተላለፍን ስለመፍቀድ

1. ከሌላ ሀገር ተላልፎ የተሰጠን ተፈላጊ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንዲተላለፍ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄ ያቀረበው ሀገር የትብብር ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበ የማስተላለፍ የትብብር ጥያቄን ፍትሕ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ በማለፉ የሀገሪቱን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን በማረጋገጥ ተፈላጊው እንዲያልፍ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 541** በመተላለፍ ያለ ተፈላጊን ስለማሰር

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 565 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ማስተላለፍ የተፈቀደ እንደሆነ ማስተላለፉ እስኪፈፀም ድረስ ወይም በማስተላለፉ ሂደት ተፈላጊው ከአርባ ስምንት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ በማረፊያ ቤት ሊቆይ ይችላል፤ የፌዴራል ፖሊስ ተፈላጊውን በመረከብ ትዕዛዙን ያስፈጽማል፡፡

2. ፍትሕ ሚኒስቴር ተፈላጊውን ማስተላለፍ እስኪፈጸም ደረስ ወይም የማስተላለፉ ሂደት ባለመጠናቀቁ ምክንያት ተፈላጊውን ሰው ከአርባ ስምንት ሰዓት በላይ በእስር ማቆየት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ጉዳዩን ፍርድ ቤት እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 542** ልዩ ሁኔታ

1. ተላላፊው ሰው በአየር ትራንስፖርት የሚጓጓዝ ወይም በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ እንዲያርፍ የታሰበ ካልነበረ፣ በዚህ ሕግ አንቀጽ 565 ፈቃድን የተመለከተ ቅድመ ሁኔታ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

2. ባልታሰበ ሁኔታ ተላፊው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ያረፈ እንደሆነ እና አጃቢው ተላላፊው በእሥር እንዲቆይ ጥያቄ ካቀረበ ከአርባ ስምንት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ በእሥር እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡

3. ተቀባዩ ሀገር በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ መደበኛ የማስተላለፍ የትብብር ጥያቄ ካላቀረበ ተፈላጊው ወደመጣበት ሀገር እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም ከተቀባዩ ሀገር መደበኛ የማስተላለፍ ጥያቄ ከቀረበና ፍትሕ ሚኒስቴር በማስተላለፍ ጥያቄው ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ከአርባ ስምንት ሰዓት በላይ ተላላፊውን በእስር ማቆየት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ጉዳዩን ፍርድ ቤት እንዲያውቀው በማድረግ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

## አምስተኛ መጽሐፍ
## ልዩ ልዩ ጉዳዮች
## ምዕራፍ አንድ
## ስለኪሳራና ወጪ

### አንቀጽ 543 የዐቃቤ ሕግ የክስ ወጪ

1. በዐቃቤ ሕግ ስለሚቀርበው የክስ፣ ይግባኝና የሰበር ክርክር ወጪ በሙሉ በመንግሥት ይሸፈናል፡፡
2. በተፈረደበት ሰው ክርክር ምክንያት ዐቃቤ ሕግ የተለየ ወጪ ያወጣና የተፈረደበት ሰው የመክፈል አቅም ያለው እንደሆነ ከተወሰነበት ቅጣት በተጨማሪ ዐቃቤ ሕግ የሚያቀርበውን የወጪ ዝርዝር ተመልክቶ የተፈረደበት ሰው በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ኃላፊ የሆኑ የተፈረደባቸው ሰዎች ከአንድ በላይ የሆኑ እንደሆነ ወጪው በተለየ ኃላፊ የሚሆን ሰው የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ሁሉም በአንድነት ወይም በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡
4. የወንጀል ተጎጂው ውሳኔ ባገኘው ወንጀል ምክንያት ያወጣው ወጪ ካለ በፍርደኞቹ እንዲከፈል ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
5. ፍርድ ቤቱ ወጪው እንዲከፈል ከማዘዙ በፊት የተፈረደበት ሰው በቀረበው የወጪ ዝርዝር ላይ አስተያየቱን እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፡፡

**አንቀጽ 544** <u>በግል አቤቱታ የሚቀርብ የወንጀል ክስ ወጪ</u>

1. በግል አቤቱታ ለሚቀርብ የወንጀል ጉዳይ የዳኝነት ክፍያ የግል ከሳሽ ይከፍላል፡፡ የክፍያውን መጠን በተመለከተ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
2. በግል ከሳሽ በሚቀርብ ክስ በሚያስከትለው የኪሳራ ወጪ የግል ከሳሽ ኃላፊ ይሆናል፤ ከአንድ በላይ የሆኑ ከሳሾች ሲኖሩ በአንድነት ወይም በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡
3. በግል ክስ ቀርቦ ተከሳሽ ነፃ የተለቀቀ እንደሆነና ክሱ የቀረበው በቅን ልቦና አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ የተገነዘበ እንደሆነ ተከሳሹ ያወጣው ወጪ በሙሉ ወይም በከፊል የግል ከሳሹ እንዲከፍል ለማዘዝ ይችላል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ በቀረበ ክስ ላይ በከፊል ከወሰነ የተከሳሽ ከሳሽ ክስ ከተቀበለ ወጪው በጋራ እንዲሸፈን ሊወሰን ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም በግል አቤቱታ በሚቀርብ ክስ በዐቃቤ ሕግ በኩል ክሱ ከቀረበ በኋላ አቤት ባዩ አቤቱታውን የተወ እንደሆነ ለክሱ ለተደረገው ወጪ ሁሉ ኃላፊ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 545** <u>የፍትሐብሔር ክስ፣ የዳኝነትና ሌሎች ወጪዎች ክፍያ</u>

1. በዚህ ሕግ መሠረት የፍትሐብሔር ክስ ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያን ጨምሮ ወጪና ኪሳራ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ መሠረት ይሸፈናል፡፡
2. የፍትሐብሔር ክሱን ያቀረበው ዐቃቤ ሕግ እንደሆነ የዳኝነት ክፍያ አይከፍልም፡፡ ይሁንና ተከሳሽ የክሱን ወጪና ኪሳራ እንዲከፍል ሲወስን የዳኝነት ክፍያውንም ጨምሮ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 546** <u>የምስክሮች ወጪ</u>

1. ለምስክሮች ወይም ሰነድ አቅራቢዎች የሚከፈለው አበል ወይም ወጪ በደንብ ይወሰናል፡፡
2. የግል ከሳሽ ወይም ተከሳሽ የሚጠራቸው ምስክሮች ወይም ሰነድ አቅራቢዎች ወጪ በግል ከሳሽ ወይም በተከሳሽ ይሸፈናል፡፡
3. ምስክሩን ወይም ሰነድ አቅራቢውን ለመጥራት የገንዘብ አቅም የሌለውና መክፈል የማይችል ተከሳሽ ወጪ በመንግሥት ይሸፈናል፡፡

## አንቀጽ 547 ልዩ ልዩ ወጪዎች

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 484(2) የተደነገገው ቢኖርም በማንኛውም ምክንያት የተከላካይ ጠበቃ፣ የአስተርጓሚ፣ ውሳኔ ለማስፈጸም የሚወጣን እና ለእስራት ለሚወጣ ወጪን ተከሳሽ ሊከፍል አይችልም፡፡
2. ተከሳሽ በሐሰት ወይም በውሸት ክስ ቀርበት በነፃ ከወጣ የሐሰት ክስ ያቀረበ ሰው ተከሳሽ ሊከፍል የሚገባቸውን ወጭዎች እንዲከፍል ፍርድ ቤት ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

## አንቀጽ 548 ደንብ የማውጣት ሥልጣን

በዚህ ሕግ የተደነገገው ደንብ የማውጣት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም የክልል መስተዳድር ምክር ቤት፡-

(1) የአማራጭ መፍትሔ አፈጻጸምና አስፈፃሚ አካላት ዕውቅና አሰጣጥ፤
(2) ነፃ የሕግ ድጋፍና አገልግሎት አሰጣጥ፤
(3) የዐቃቤ ሕግ የመተዳደሪያና የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ፤
(4) የምስክሮች አቀራረብና የወጪ ማካካሻ፣ እና
(5) ፍርድን እንደገና በማየት ውሳኔ የተሻረላቸው ሰዎች ለደረሰባቸው ጉዳት ተመጣጣኝ የካሣ ክፍያ አፈጻጸምን፣

የተመለከቱ ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 549 መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. በዚህ ሕግ የተደነገገው መመሪያ የማውጣት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፡-
   (1) ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-
      (ሀ) የችሎት ሥነ ሥርዐት ክትትልና የጉዳዮች አመራር፣
      (ለ) የቅሬታ ማስተናገጃና አወሳሰን መማሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
   (2) ፍትሕ ሚኒስቴር የጠቋሚዎች፣ የምስክሮችና የወንጀል ተጎጂዎች አያያዝ፣ ድጋፍና ጥበቃ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
   (3) ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፡-
      (ሀ) የምርመራ፣ የክስ ዝግጅትና የክርክር አካሔድ፤

(ለ) በምርመራና ክስ የሚቀርቡ ቅሬታ ማስተናገጃና ውሳኔ አሰጣጥ፤

(ሐ) የግል ክስ አመራር፤

(መ) የቅጣት አፈጻጸም ክትትል እና

(ሠ) በምርመራና ክስ ሂደት የመረጃ አሰጣጥ

መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2. በዚህ ሕግ መሠረት የሚወጣ መመሪያ መታተምና ለሚመለከተው አካል መሰራጨት አለበት፡፡

**አንቀጽ 550** <u>ቅጽ የማውጣት ሥልጣን</u>

የፍትሕ አካላት በዚህ ሕግ ተለይተው የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ለማስፈጸም ልዩ ልዩ ቅፆችን ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የሥነ ሥርዐት ሕጉን ስለማሻሻል

**አንቀጽ 551** <u>ሕጉን ስለማሻሻል</u>

ይህንን ሕግ ለማሻሻል የሚቀርብ ማንኛውም የማሻሻያ ሀሳብ በፍትሕ አካላት ውይይት በፍትሕ ሚኒስቴር በኩል መቅረብ አለበት፡፡